# መሠረተ ሕይወት

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
## የልጆች መማሪያ መጽሐፍ

### ሁለተኛ ክፍል

አዘጋጅ - ቀሲስ ሰሎሞን መሉጌታ

www.zeorthodox.org

መስከረም
፳፻፯ ዓ.ም

© ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ ፳፻፭ ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነት ሥርዓት እና ትውፊት መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት

አድራሽ፡-
ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ
ፖ.ሳ.ቁ 43200
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

Email:- kesisolomon@gmail.com
Website፡- www.zeorthodox.org

የኮምፒውተር ሌይ አውት ዲዛይን
ልደት አስፋው

www.zeorthodox.org

## ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ ተሰራጭቶ የሚገኘው ገቢ በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም፣ በቦሌ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል፣ በቦሌ ሰሚት መካነ ሰላም መድኃኔዓለም እና ወደ ፊትም በተለያዩ አጥቢያዎች ለሚከናወኑ የሕፃናት፣ አዳጊዎች፣ ወጣቶችና ወላጆች ኦርቶዶክሳዊ ትምህርትና ተመሳሳይ አገልግሎቶች የሚውል ይሆናል፡፡

# መታሰቢያነቱ



ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ይሁንልኝ፡፡

# ምስጋና

www.zeorthodox.org

ይህ የመማሪያ መጽሐፍ ሲዘጋጅ በቀጥተኛ ተሳታፊነት የተሰለፉትን ዲ. ዘላለም ረድኤትና ዲ. ዮናታን ኢያሱን፣ መጽሐፉን በማረም የተባበሩትን መጋቤ ብሉይ አእመረ አሸብርን፣ መምህር ካሕሳይ ገብረ እግዚአብሔርን እና አቶ አስራት ከበደን እንዲሁም በኮምፒዩተር የለቀማ ሥራ ያገለገሉትን ልደት አስፋውን፤ መጻሕፍቱን ለማጠናቀቅ ሳደርግ በነበረው ጥረት ውድ ባለቤቴና ልጆቼ የእንቅልፍና የእረፍት ሰዓታቸውን ሳይቀር መሥዋዕት በማድረግ ስላሳለፉ ስለ ከፈሉት መሥዋዕትነት እግዚአብሔር ዋጋ ከፋይ ነውና ዋጋቸውን ይክፈላቸው እላለሁ፡፡ በመጨረሻም የሚያስፈልገውን ሁሉ የሚያከናውኑ የመርሐ ግብራችን አስተባባሪ የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሰንበቴ የሥራ አስፈጻሚ አባላትን እግዚአብሔር በቸርነቱ ይጠብቅልኝ ሳልል አላልፍም፡፡

# ማውጫ


| ተ.ቁ | አርእስተ ትምህርት | ገጽ | ትምህርቱ የሚሠጥበት ወቅት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
| 1. | ዓውደ ዓመት | 1 | | 1ኛ ሳምንት | ዘመን |
| 2. | ካህኑ ዘካርያስ | 4 | መስከረም | 2ኛ ሳምንት | መለወጫ |
| 3. | መስቀል | 6 | | 3ኛ ሳምንት | በዓለ መስቀል |
| 4. | ሥነ ፍጥረት ፩ | 9 | | 4ኛ ሳምንት | |
| 5. | ሥነ ፍጥረት ፪ | 12 | | 5ኛ ሳምንት | |
| 6. | የአዳም እና ሔዋን አፈጣጠር | 15 | ጥቅምት | 6ኛ ሳምንት | |
| 7. | የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ትእዛዝ | 18 | | 7ኛ ሳምንት | |
| 8. | እግዚአብሔር ኖኅን በመርከብ አዳነ | 21 | | 8ኛ ሳምንት | |
| 9. | ተወዳጁ የኖኅ መሥዋዕት | 23 | | 9ኛ ሳምንት | |
| 10. | በባሕር የተጣለው ሙሴ ባሕር አሻገረ | 26 | ኅዳር | 10ኛ ሳምንት | |
| 11. | አብርሃም በጌራራ | 28 | | 11ኛ ሳምንት | |
| 12. | እጆቼን ወደ እግዚአብሔር አንሥቼአለሁ | 30 | | 12ኛ ሳምንት | |
| 13 | ሎጥ | 33 | | 13ኛ ሳምንት | |
| 14 | ይስሐቅ | 36 | ታኅሣሥ | 14ኛ ሳምንት | |
| 15 | ብስራት/የምሥራች መላእክት/ | 39 | | 15ኛ ሳምንት | |
| 16 | ልደት | 42 | | 16ኛ ሳምንት | |
| 17 | ጥምቀት | 44 | | 17ኛ ሳምንት | |
| 18 | ቅዱስ እስጢፋኖስ | 46 | ጥር | 18ኛ ሳምንት | |
| 19 | የሳዉል መጠራት | 49 | | 19ኛ ሳምንት | |
| 20 | ተተኪው ኢያሱ - ባሕር አሻገረ | 52 | | 20ኛ ሳምንት | |
| 21 | ብኩርና | 55 | | 21ኛ ሳምንት | |
| 22 | በወላጆቻችሁ ትባረኩ ዘንድ ታዘዙ | 57 | የካቲት | 22ኛ ሳምንት | |
| 23 | ታማኙ ያዕቆብን እግዚአብሔር ባረከለት | 60 | | 23ኛ ሳምንት | |
| 24 | ዮሴፍ - ክፉን በበጎ አሸነፈ | 63 | | 24ኛ ሳምንት | |
| 25 | ጌታችን በሰይጣን ተፈተነ | 66 | | 25ኛ ሳምንት | |
| 26 | መጻጉዕ ተፈወሰ | 68 | መጋቢት | 26ኛ ሳምንት | |
| 27 | ሕፃናት ጌታችንን ተቀበሉ | 71 | | 27ኛ ሳምንት | |
| 28 | የኤማሁስ መንገደኞች | 73 | | 28ኛ ሳምንት | |
| 29 | ጴጥሮስ እና ዮሐንስ በቤተ መቅደስ | 76 | | 29ኛ ሳምንት | |
| 30 | መልአኩ ቅዱስ ጴጥሮስን ከእስር አወጣው | 78 | ሚያዝያ | 30ኛ ሳምንት | |
| 31 | ከዓሣ አጥማጅነት የተጠሩት ሐዋርያት | 81 | | 31ኛ ሳምንት | |
| 32 | የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ (እግዚአብሔርን መፍራት) | 84 | | 32ኛ ሳምንት | |


www.zeorthodox.org

| ተ.ቁ | አርእስተ ትምህርት | ገጽ | ትምህርቱ የሚሠጥበት ወቅት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
| 33 | ልደታ ለማርያም…………………………………… | 87 | | 33ኛ ሳምንት | |
| 34 | ዘመን ጸራቅሊጦስና የማትያስ መመረጥ… | 92 | ግንቦት | 34ኛ ሳምንት | |
| 35 | ትጋት……………………………………………… | 93 | | 35ኛ ሳምንት | |
| 36 | የቤተ ክርስትያን ግቢ አቀማማጥ………….. | 95 | | 36ኛ ሳምንት | |
| 37 | ለሌሎች ያለን ፍቅር…………………………… | 98 | | 37ኛ ሳምንት | |
| 38 | ጸሎት…………………………………………… | 101 | ሰኔ | 38ኛ ሳምንት | |
| 39 | አባታችን ሆይ እና እመቤታችን…………………… | 104 | | 39ኛ ሳምንት | |
| 40 | ቅዱስ ዮሐንስ ሐፂር ………………… | 107 | | 40ኛ ሳምንት | |
| 41 | ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ ማድረግ ያለብን | 110 | | 41ኛ ሳምንት | |
| 42 | የእግዚአብሔር ስሞች………………………… | 113 | ሐምሌ | 42ኛ ሳምንት | |
| 43 | መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል፤ ቂርቆስና ኢየሉጣን አዳነ…….. | 116 | | 43ኛ ሳምንት | |
| 44 | ነቢይት ዲቦራ……………………………………… | 119 | | 44ኛ ሳምንት | |
| 45 | ጌታችን ሕፃናትን ይወዳል…………………………… | 122 | | 45ኛ ሳምንት | |
| 46 | ዕርገታ ለማርያም………………………………… | 125 | ነሐሴ | 46ኛ ሳምንት | |
| 47 | አቡነ ተክለ ሃይማኖት………………………………… | 127 | | 47ኛ ሳምንት | |
| 48 | ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ……………………… | 130 | | 48ኛ ሳምንት | |
| 49 | መታዘዝ……………………………………………………… | 133 | ጳጉሜን | 49ኛ ሳምንት | |
| 50 | ኤልሳዕ ውኃውን አጣፈጠ ……………………… | 136 | | 50ኛ ሳምንት | |
| | | | | | |
| | | | | | |


www.zeorthodox.org

# መቅድም

በአሁኑ ወቅት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች ቤተ ክርስቲያናቸውን እያወቁ በመልካም ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚያደርግ፣ ጥያቄዎቻቸውን የሚመልስ ብሎም ችግሮቻቸውን የሚፈታ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት የመኖሩ አስፈላጊነት በብዙዎቻችን ዘንድ ይታመንበታል፡፡ ቤተ ክርስቲያናችንም በዚሁ ዙሪያ በርካታ ተግባራትን እንደምታከናውን እምነቴ ነው፡፡

ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመላክ ለተስተካከለ ዕድገታቸው አስተዋጽዖ በማድረግ የወላጅነት ሓላፊነታቸውን ለመወጣት ፍላጐቱ አላቸው፡፡ ሆኖም በአንዳንድ ሁኔታዎች አለመመቻቸት የተነሣም ይሁን በሌላ ምክንያት ከሕፃንነታቸው ጀምሮ እንዲማሩላቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያቀርቡ ምእመናን እጅግ ጥቂቶች መሆናቸውን የተለያዩ አጋጣሚዎች ማሳያዎች ሆነውኛል፡፡

ከዛሬ ሰባት ዓመት በፊት በእግዚአብሔር ፈቃድ በምሠራበት መሥሪያ ቤት በኩል ለተዘጋጀ ሙያዊ ሥልጠና ከአገር ውጪ ባደረግሁት ጉዞ ዘወትር አብረውኝ የሚቆሙ ቤተሰቦቼ ምክንያት ሆነው ግብጽንና ገዳማቱን የመጐብኘት ዕድል አገኘሁ፡፡ ይህም የተቀደሰ አጋጣሚ ስለ ልጆች፣ በቅድመ ጋብቻ ስላሉ ወጣቶችና በትዳር ስለሚኖሩ ኦርቶዶክሳዊያን የተናጠል መርሐ ግብር እንዳስብ አደረገኝ፡፡ በእግዚአብሔር ፈቃድም በኅዳር ወር ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም መጥምቀ ዮሐንስና አቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን የልጆች መርሐ ግብር በሃያ አራት ልጆች ተጀመረ፡፡ አሁን ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል የሆኑ ከሦስት ሺህ በላይ የሚሆኑ ልጆች፤ በየሳምንቱ ቅዳሜና እሑድ ቀን ከአራት እስከ ስድስት ሰዓት በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰጠውን መንፈሳዊ ትምህርት ይከታተላሉ፡፡ በርካታ ምእመናንም በየሳምንቱ ረቡዕ ከምሽቱ አሥራ ሁለት እስከ ሁለት ሰዓት ለአዋቂዎች በተዘጋጀው የትምህርት መርሐ ግብር ተሳታፊዎች ናቸው፡፡

www.zeorthodox.org

ይሁን እንጂ ሁሉንም ልጆች በየትምህርት ደረጃቸው በመመደብ ማስተማር የሚያስችል መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ነበር፡፡ በመሆኑም ቀድመው የተዘጋጁትን ትምህርቶች ተካተውበት ለዚሁ ሥራ እገዛ የሚያደርጉ ወንድሞች ጋር በመመካከር ዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ዲያቆን ዘላለም ረድኤት ተገኝተውበት ለትምህርቱ አጋዥ የሆኑ መጻሕፍትን ለማዘጋጀት ጥረት ተጀመረ፡፡ እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ከአራት ዓመታት ጥረት በኋላ፤ ለሥርዓተ ትምህርቱ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ በኋላ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ የሆኑ አሥራ ሦስት ጥራዝ የማስተማርያ መጻሕፍት ዝግጅት ተጠናቅቆ ለኅትመት እንዲበቁ ለማድረግ ወደ ማተሚያ ቤት ገብተዋል፡፡

በማስተማርያ መጻሕፍቱ ዝግጅት፤ ለመረጃ የምንገለገልባቸው ምንጮች፣ የምእመናን የኑሮና የትምህርት ደረጃ፣ የመኖሪያ ሥፍራዎችና የባህል ልዩነቶች፣ እንዲሁም በአገር ውስጥ እና ከሀገር ዉጪ በሚገኙ ኢትዮጵያዊያን መካከል ያሉ የአኗኗርና የሥራ ሁኔታዎችና አካባቢያዊ ልዩነቶችን ታሳቢ በማድረግ ከግንዛቤ ውስጥ እንዲገቡ ተሞክሮአል፡፡ በዚህ ሥራ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላደረጉት ለዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ለዲያቆን ዘላለም ረድኤት፤ እግዚአብሔር በቸርነቱ ጠብቆ ረጅም ዕድሜ ይስጥልን እላለሁ፡፡

ይኸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ ላሉ ወጣቶች ለሚሰጠዉ ‹‹መሠረተ ሕይወት›› መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ የሚሆኑ መጻሕፍት ለንትመት በቅተዉ ለአገልግሎት የተዘጋጁ መሆናቸውን በታላቅ ደስታ እገልጻለሁ፡፡

***“እስከ አሁን ድረስ እግዚአብሔር ረድቶናል፡፡” ፩ኛ ሳሙኤል ፯ ፥ ፲፪***

www.zeorthodox.org

# መግቢያ

የዚህ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትና ትውፊተ ቤተክርስቲያን ናቸው። በዚህም መሠረት ጥርት ያለውን የቅድስት ቤተ ክርስቲንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ታሪክ ከመልካም ሥነ ምግባር ጋር፤ በዓለማዊ ትምህርት ቤት ለሚማሩ ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች እንዲደርስ ለማድረግ፤ በየትምህርት ደረጃቸው እና ዕድሜአቸው እንዲመጥን ሆኖ የሥርዓተ ትምህርት አዘገጃጀትን ስልት በመከተል ለማዘጋጀት ተሞክሮአል። አንዳንዶቹ ትምህርቶች ልጆች ትምህርቱን በሚገባ ተረድተዉ ማስታወስ እንዲችሉ በየደረጃዉ በሚገኙ የተለያዩ ክፍሎች ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ በድጋሚ ተካትተዋል።

ትምህርቶቹ በየወሩ ተከፋፍለው በቤተ ክርስቲያን ከሚከበሩ በዓላትም ጋር እየተቀራረቡ እንዲዘጋጁ ጥረት ተደርጎአል። በየመካከሉ ለሚኖሩ ክፍተቶች በሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በቅደም ተከተል አገልግሎት ላይ እንዲውል ሆኖ የማሟያ ትምህርቶቹ ተወስደው ተካትተዋል። ያም ሆኖ እንደየ ጊዜው ሁኔታ ዘመኑን እንዲዋጅ መሻሻልና መዳበር ያለበት መሆኑ ግን የማይዘነጋ ነው።

በሙዓለ ሕፃናት የሚገኙ ልጆች በጣም አጫጭር ታሪኮችን ብቻ ሰምተው ጥቂቶቹን ብቻ ማስታወስ የሚችሉ ናቸው። ረጅም ጽሑፍና ሐሳብ በትኩረት አንብበዉ በቀላሉ ለመረዳትም ሆነ ለማስታወስ ስለማይችሉ ወይም ስለሚቸገሩ በመምህራን እንዲሁም በወላጆች መታገዝ ያስፈልጋቸዋል። በተረት፣ በታሪክ፣ በሕልምና በእውነታ መካከል ያለውን ልዩነት አገናዝቦ ለመረዳት ይቸገራሉ። በጣም ፈጠራ የታከለባቸው የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች የሚያስፈልጓቸው ቢሆኑም መምህራ ኖቻቸው የሚዘምሩላቸዉን መዝሙሮች ማስታወስና በአእምሮአቸው መያዝ፣ በትምህርታዊ ጨዋታዎቻቸውም ሆነ በማንኛውም ሁኔታ መምሰልና ማስመሰል ይችላሉ። በዚህ ደረጃ የሚገኙ ልጆች የሚንቀሳቀሱና የተለያዩ ድምፆች ያሉባቸውን ነገሮች እንዲሁም ከሌሎች ጋር መጫወትንና ያዩትን በተግባር ማሳየትን ይወዳሉ።

www.zeorthodox.org

ልጆች ቤተ ክርስቲያን መምጣታቸው ደስታን እንዲፈጥርላቸውና ፈጽመውም የሚወደዱ መሆናቸውን እንዲሰማቸው ማድረግ እንጂ ቶሎ ሊያስደነግጣቸው ወደ ሚችል አቀራረብና ቅጣት ማዘንበል አይገባም። በየደረጃው የሚገኙ ልጆችን የሚያስተምሩ መምህራን በተፈጥሮ ለልጆች ፍቅር ያላቸውና ፍቅራቸውንም መግለጽ የሚችሉ መሆን ይገባቸዋል። በዚህ ትምህርት የሚጠበቁ መልካም ውጤቶችም በሚቀርቡላቸው መርጃዎችና በመምህራኑ ጥረት ላይ የተመረኮዙ ናቸው። መምህራኑ ልጆችን ለመሳብ ብሩህ ፈገግታና ፍቅር ያለው አቀራረብ እንዲሁም፤ ደመቅ ያሉ ቀለማትን፣

ድምፅና ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ቢጠቀሙ መዝሙራትንም ቢያዘምሩላቸው ለትምህርቱ ታላቅ ኃይል ይሆናል፡፡ ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር መምህራን ልጆቹን በየዕለቱ የትምህርት መርሐ ግብሮች መዝሙራትን ሊዘምሩላቸውና ሊያስጠኑአቸው ያስፈልጋል፡፡ አንዳንድ ጊዜም ከትምህርቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሥዕላትን ቢያሳዩአቸዉ፣ ቢሰጡአቸው የተማሩትን ትምህርት በቀላሉ ለማስታወስና ለሌሎችም ለማስረዳት የበለጠ ዕድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ቤተሰቡ ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጣ ልጆች ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉና፡፡ ይህንኑ ለማገዝም በቀለም የሚቀቡ ሥዕሎችና የመዝሙር ጥራዞችን ዝግጅት አጠናቀናል፡፡ በሙዓለ ሕፃናት ደረጃ የሚገኙ ልጆች ከትምህርታቸዉ ጋር ተያያዥነት ያለውን ርእሰ ጉዳይ ሥዕሉን ቀለም በመቀባት የሚቀስሙት ትምህርት የበለጠ ስለሚሆን የተዘጋጁትን ሥዕሎች በአግባቡ ቀለም እንዲቀቡአቸው የወላጆች እገዛ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

በዓመቱ ውስጥ ባልተካተቱት ሁለት ሳምንታትም ገዳማትንና አብያተ ክርስቲያናትን መጐብኘታቸውና ክትትል ባለበት ሁኔታ በማኅበራዊ ነገሮች ተሳታፊ መሆናቸውም እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን መምህራን ለዚህ አገልግሎት በትጋት መጸለይና በየመካከሉ የሚቀሩ ወይም ጨርሰው ያልመጡ ልጆችንም መጐብኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡ መምህራንን ማግኘት በማይቻልባቸው ሥፍራዎች ወላጆች በሥርዓተ ትምህርቱ በመመራት ልጆችን ማስተማር ይችላሉ፡፡ ልጆች በመንፈሳዊው ትምህርት እስከአሁን ድረስ ያደጉበት ሁኔታ ያልተመጣጠነ ስለሆነ የክፍል ደረጃቸው ከፍ ቢልም ከሙዓለ ሕፃናት መጽሐፍ ደረጃ ጀምረው መማራቸው ለመንፈሳዊዉ ዕዉቀታቸዉ መሠረት ስለሆነ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በዚህ አጋጣሚም በየአብያተ ክርስቲያናቱ የተከፈቱ ትምህርት ቤቶችም ይህንን ሥርዓተ ትምህርት መጠቀማቸው ልጆች በየደረጃው ቤተ ክርስቲያናችንን እያወቁ፣ ሃይማኖታቸውን ተረድተውና በበጐ ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚረዳቸው ይሆናል ብዬ አምናለሁ፡፡

በመጨረሻም ይኸን ዝግጅት የበለጠ ለማሻሻል የሁሉም አስተያየትና ምክር በጣም አስፈላጊ ስለሆነ እገዛችሁ እንዳይለየኝ እያልኩ አስቀድሞ በተጠቀሱት አድራሻዎች አስተያየቶቻችሁን እንድትልኩልኝ ስል በታላቅ ትሕትና እጠይቃለሁ፡፡

www.zeorthodox.org

# ዓውደ ዓመት

# አንደኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** አዲስ ዓመት በቤተ ክርስቲያን እንዴት እና ለምን እንደሚከበር ልጆች ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *“ አምላክህ እግዚአብሔር የሚኀበኛት አገር ናት ፤ ከዓመቱ መጀመሪያ እስከ ዓመቱ መጨረሻ ድረስ የአምላክህ የእግዚአብሔር ዓይን ሁልጊዜ በእርስዋ ላይ ነው ፡፡ ”* ዘዳ. ፲፩÷፲፪

**መግቢያ፡-** ልጆች እንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሳችሁ፡፡ ዛሬ ስለ አዲሱ ዓመት የመጀመሪያ ቀን እንማራለን፡፡

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ**

1. በየዓመቱ መስከረም ፩ ቀን የምናከብረዉ በዓል ምን ይባላል? የምታውቁትን ስያሜ ለመምህሩ ንገሩ፡፡
2. ለምን እናከብረዋለን ?
3. እናንተስ እንዴት ታከብሩታላችሁ ?
4. በቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደሚከበርስ አይታችኋል ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

**ስያሜዎቹ፡-** ልጆች የአዲሱ ዓመት መጀመሪያ ቀን በተለያዩ ስያሜዎችም ይጠራል፡፡ መስከረም ፩ ቀን የምናከብረው በዓል ፡- ዘመን መለወጫ ፣ አዲስ ዓመት ፣ እንቁጣጣሽ ፣ ዐውደ ዓመት … ይባላል፡፡ በዚህ ቀን አሮጌው ዘመን አልፎ አዲሱ ዘመን መተካቱን በማብሰር ይከበራል፡፡

www.zeorthodox.org

**ዘመን መለወጫ ፡-** አሮጌው ዓመት በአዲሱ ስለሚለወጥ የተሰጠው ስያሜ ነው፡፡

**ዓውደ ዓመት ፡-** የዓመታት መመላለሻ ማለት ነው፡፡

**እንቁጣጣሽ ፡-** ምድር በአበቦች ማጌጥዋን ለማመልከት የሚሠጥ ስያሜ ነው፡፡

**ቅዱስ ዮሐንስ ፡-** መጥምቁ ዮሐንስ የብሉይ ኪዳን መጀመሪያ የሐዲስ ኪዳን መጀመሪያ ነበር፡፡ የዓመቱ የመጀመሪያ ቀንም አሮጌው ዓመት አልፎ አዲሱ መተካቱን ለማብሰር ይህ ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡ በተጨማሪም ዮሐንስ መጥምቅ መስከረም ፪ ይታሰባል፡፡

የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር *ዐሥራ ሦስት ወራትን በመያዝና በመስከረም በመጀመሩ*

ከምዕራባዉያን (ጎርጎሮሳዉያን) የዘመን አቆጣጠር ይለያል፡፡

የኢትዮጵያ አንድ ዓመት ፲፫ ወራት አሉት፡፡ እነርሱም ፡- መስከረም ፣ ጥቅምት ፣ ኅዳር ፣ ታኅሣሥ ፣ ጥር ፣ የካቲት ፣ መጋቢት ፣ ሚያዝያ ፣ ግንቦት ፣ ሰኔ ፣ ሐምሌ ፣ ነሐሴ እና ጳጉሜን ይባላሉ፡፡

የአውሮፓውያን አንድ ዓመትም ፡- ጃንዋሪ ፣ ፌብሩዋሪ፣ ማርች፣ አፕሪል፣ ሜይ፣ ጁን፣ ጁላይ፣ ኦገስት፣ ሴፕቴምበር፣ ኦክቶበር፣ ኖቬንበር እና ዲሴምበር የሚባሉ ዐሥራ ሁለት ወራት አሉት፡፡

ከስያሜዎቹ እንደምንረዳዉ የእኛ ዘመን አቆጣጠር የተፈጥሮን ሂደት መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ለምሳሌ መስከረም ማለት  ከክረምት በኋላ (ክረምት አለፈ)የሚል ትርጉም አለው፡፡

የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በመስከረም ወር ሲጀምር የአውሮፓውያን በእኛ ታኅሣሥ ፳፫ በእነሱ ጃንዋሪ ፩ ይጀምራል፡፡

የኢትዮጵያ የዘመናት ስያሜና አቆጣጠር ከአምስት ሺሕ ዓመታት በላይ ዕድሜ ያስቆጠረ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የዓመቱን መጀመሪያ መስከረም ፩ እናከብራለን፡፡

## ለምን እናከብራለን?

**እግዚአብሔርን ለማመስገን፡-** የጊዜያት አስገኚና ባለቤት ልዑል እግዚአብሔር ዘመናትን እያፈራረቀ አዲሱን ዘመን ስለመረቀልን ለማመስገን እናከብራለን፡፡

**በአዲስ መንፈስ ቀጣዩን ጊዜ ለመጀመር፡-** በመጸለይ ፣ መልካም ለመመኘት ፣ ለማቀድና ለመዘጋጀትም የአዲሱን ዓመት መጀመሪያ ማክበር ይጠቅማል፡፡

**እንዴት ይከበራል?**

**በምሥጋና፡-** በየዓመቱ መስከረም ፩ ከዋዜማዉ ጀምሮ ዘመናትን ለሚያፈራርቀው ለእግዚአብሔር የምሥጋና መሥዋዕት ይቀርባል፡፡ ምእመናንም፡- በማስቀደስ ፣ በመዘመር እና ቃለ እግዚአብሔርንና አዋጁን በመስማት ይሳተፋሉ፡፡

www.zeorthodox.org

**ወንጌል ይነበባል፡-** እግዚአብሔር የዘመናት ባለቤት መሆኑን የሚያበስሩና የሚያስተምሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይነበባሉ፡፡ ለምሳሌ፡-መዝ.፷፬፥፲፩ ፤ ሉቃ.፬፥፲፰ . . .

**የዓመቱ በዓላትና አጽዋማት ይታወጃሉ፡፡** በዕለቱ በጠዋት በካህኑ አማካይነት ፤ በአዲሱ ዓመት የሚዉሉት በዓላት (ለምሳሌ ፋሲካ) ፤ አጽዋማትም መቼ እንደሚገቡ ይታወጃል፡፡ ለምሳሌ አቢይ ጾምና ጾመ ሐዋርያት መቼ እንደሚጀመሩ የሚታወጀው በመስከረም አንድ ነው ፡፡

**በባህላዊ መንገድም፡፡** ባህላዊ ልብስ በመልበስ ፣ ችቦ በማብራት፣ ስጦታ በመለዋወጥ ይከበራል፡፡ ሕፃናት መልካም ምኞታቸዉን መዝሙር በመዘመር እና ሥዕል ሥለው ለቤተሰብና

ለጎረቤታቸው ሲሠጡ ፤ አዋቂዎችም ለልጆች የሚገባ ስጦታ ይሠጣሉ፡፡

## ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር በምድራችን ካሉ ጥንታዊ የዘመን አቆጣጠሮች አንዱ ነው፡፡

ዐሥራ ሦስት ወራት ያሉት የዓመት አቆጣጠራችን፣ መስከረም አንድ ይጀመራል፤ ቀኑም ርእሰ ዐውደ ዓመት ተብሎ ይከበራል፡፡

የዘመን መለወጫ ቀናችን አዲስ ዓመት፣ እንቁጣጣሽ፣ ዐውደ ዓመት የሚባሉ ስያሜዎች አሉት፡፡

የምናከብረውም የዘመናት ባለቤትና ሰጭ የሆነውን እግዚአብሔርን ለማመሥገን፣ ለመጪው ዘመን በመዘጋጀት እና መልካም ምኞታችንን ለመግለጥ ነው፡፡

በሃይማኖታዊና በባህላዊ መንገዶችም ይከበራል፡፡

## ተግባር

ትምህርታችሁን ፣ የቤተሰቦቻችሁን እና የአገራችሁን ዕቅድ እግዚአብሔር እንዲባርክላችሁ ጸልዩ፡፡

የሚከተለዉን መዝሙር አጥንታችሁ ለወላጆቻችሁ ዘምሩ፡፡

***መዝሙር***

ዐውደ ዓመት ለባርኮ (2)

ንዒ ማርያም(3) ለምሕረት ወሳህል

www.zeorthodox.org

# ካህኑ ዘካርያስ

## ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ** ፡- ልጆች በእግዚአብሔር ማመን እና በመታመን መኖርን ከአባታችን ከካህኑ ዘካርያስ ሕይወት ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ**፡- *‹‹በጊዜው የሚፈጸመው ቃሌ››* ሉቃ.፩፥፳

**ተጨማሪ ምንባብ**፡- ሉቃ.፩፥፭-፳፭

**መግቢያ፡-** በሁለተኛው ሳምንት ትምህርታችን ስለ ርእሰ አውደ ዓመት ተምረናል ፤ በዓሉ ከሚጠራባቸው ስያሜዎች አንዱ ቅዱስ ዮሐንስ መሆኑንም አይተናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችን የመጥምቁ ዮሐንስን አባት የዘካርያስን ታሪክ እንማራለን፡፡

## የትምህርቱ ዋና ትኩረት

ልጆች በድሮ ዘመን የኦሪት ካህናት በቤተሰብ መጠሪያቸው ተከፋፍለው ያገለግሉ ነበር፡፡ ካህኑ ዘካርያስም ከአብያ ቤተሰብ የሚወለድ ነበር፡፡ እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት ዘመን (ከ2005 ዓመታት በፊት) በቤተ መቅደስ ያገለግል የነበረ ካህን ነው፡፡ ሚስቱ ኤልሳቤጥ ትባላለች ፣ ሁለቱም እግዚአብሔርን የሚፈሩና በጸሎት ተወስነው የሚኖሩ ባልና ሚስቶች ነበሩ፡፡ ልጅ ስላልነበራቸው እግዚአብሔር እንዲሰጣቸው ለመኑት፡፡ ጸሎታቸውን የሰማው እግዚአብሔር ጊዜው ስላልደረሰ አዘገየባቸው፡፡ ልጆች እግዚአብሔር የጠየቅነውን የሚያደርግልን ጊዜ አለው፡፡ ካህኑ ዘካርያስና ሚስቱ ኤልሳቤጥም ሁሉንም ለእግዚአብሔር ትተው በአገልግሎታቸው ጸኑ፡፡ እርስዋ በመካምነትዋ እርሱም በተሾመበት የክህነት አገልግሎት ጸና፡፡

ካህኑ ዘካርያስ አንድ ቀን በተለመደው አገልግሎቱ ተራው ደርሶ ለማገልገል ወደ ቤተመቅደስ ገባ፡፡ሕዝቡ በውጭ እየጸለዩ ፣ እርሱ በቤተ መቅደሱ እጣን መሰዊያ ፊት እያጠነ ነበር፡፡ በመሠውያው በስተቀኝ የእግዚአብሔር መልአክ ቆሞ ታየው ፣ መላእክት የእግዚአብሔር ጸጋ ከእነርሱ ጋር አለ፣ ካህኑ ዘካርያስም እግዚአብሔርን የሚፈራና የሚያከብር ሰው ነበር፡፡ እናም መልአኩን ሲያይ ደንግጦ ፈራ፡፡

***‹‹መልአኩም እንዲህ አለው፦ ዘካርያስ ሆይ፥ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አትፍራ፤ ሚስትህ ኤልሳቤጥም ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፥ ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ፡፡ ደስታና ተድላም ይሆንልሃል፥ በመወለዱም ብዙዎች ደስ ይላቸዋል፡፡ በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና፥ የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም፤ ገናም በእናቱ ማኅፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል፤ ከእስራኤልም ልጆች ብዙዎችን***

www.zeorthodox.org

*ወደ ጌታ ወደ አምላካቸው ይመልሳል። እርሱም የተዘጋጁትን ሕዝብ ለጌታ እንዲያሰናዱ፥ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ ይመልስ ዘንድ በኤልያስ መንፈስና ኃይል በፊቱ ይሄዳል። »* ሉቃ.፩፥፲፫-፲፯። *«ዘካርያስም መልአኩን። እኔ ሽማግሌ ነኝ ሚስቴም በዕድሜዋ አርጅታለችና ይህን በምን አውቃለሁ? አለው።»* ሉቃ.፩፥፲፰

*«መልአኩም መልሶ፦ እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ፥ እንድናገርህም ይህችንም የምሥራች እንድሰብክልህ ተልኬ ነበር፤ እነሆም፥ በጊዜው የሚፈጸመውን ቃሌን ስላላመንህ፥ ይህ ነገር እስከሚሆን ቀን ድረስ ዲዳ ትሆናለህ መናገርም አትችልም አለው»*

በውጭ በጸሎት የነበረው ሕዝብ በመዘግየቱ እየተደነቁ ጠበቁት፤ እርሱም ወጥቶ በምልክት ነገራቸው ራእይ እንዳየም አስተዋሉ። ካህኑ ዘካርያስም ለዘጠኝ ወራት ዲዳ ሆኖ ኖረ። ሚስቱ ኤልሳቤጥ ፀነሰች፤ ለስድስት ወራትም እግዚአብሔርን እያመሰገነች ራስዋን ደበቀች። በስድስተኛው ወር መልአኩ ወደ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ተልኮ ጌታችንን እንደምትወልድ አበሰራት። ጌታም ተፀነሰ፤ ማርያምም ወደ አክስትዋ ኤልሳቤጥ ሄደች ለሦስት ወራት ቆይታም ተመለሰች። ከዚህ በኋላ ኤልሳቤጥ ወለደች፤ ዘመዶችዋ ስሙ ማን ይባል ሲሉ ዮሐንስ አለች፤ እነርሱም ከዘመድሽ በዚህ ስም የተጠራ የለም ብለው በአባቱ ስም ዘካርያስ ሊሉት ፈለጉ አባቱም ብራና ለምኖ ዮሐንስ ይባል አለ። ወዲያዉም አንደበቱ ተከፈተለት። ሕዝቡም በሁሉም አደነቁ።

ከሁለት ዓመት በኋላ ሰብዓ ሰገል፤ «የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት አለ? ልንሰግድለት መጥተናልና፤» አሉ። ንጉሡ ሄሮድስ ሥልጣኑን የሚቀማው የመጣ መስሎት ፈራ። ኢየሩሳሌምም ታወከች። ሄሮድስ ሰብአ ሰገል ምልክቱን ያዩበትን ወራት አጣርቶ፤ ከሁለት ዓመት በታች የሆኑትን ሕፃናት ሁሉ ለመግደል ሰበሰበ። በዚህ ጊዜ እመቤታችንና ጌታችን ወደ ግብጽ ሲሰደዱ፤ ካህኑ ዘካርያስም ልጁን ከእናቱ ጋር ወደ ሲና በረሓ ልኮ በቤተ መቅደስ ቀረ። ይህን ያወቁ ሰዎች ለሄሮድስ የተወለደው ንጉሥ ዮሐንስ ሳይሆን አይቀርም አሉት። እርሱም ወታደሮችን ወደ ካህኑ ዘካርያስ ላከ። እነርሱም ዮሐንስን እንዲያመጣው ጠየቁት። እርሱም መልአኩ ያበሰረበትን ቦታ እያሳያቸው፤ ለሰጠው እግዚአብሔር ማስረከቡን ነገራቸው። ወታደሮቹም በዚያው በቤተ መቅደሱ ውስጥ በሰይፍ ገደሉት። ይህም መስከረም ስምንት ቀን ሆነ።

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ካህኑ ዘካርያስ እና ኤልሳቤጥ በቅድስና ኖረው ፤ እግዚአብሔርን ሲጠብቁት ልጅ ሰጣቸው።
ካህኑ ዘካርያስም መስከረም ስምንት በሰማዕትነት ዐርፎአል።

## ተግባር

እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን በጊዜው ይሰጠናል ብለን ማመንና መጠበቅ አለብን።

# ቅዱስ መስቀል

# ሦስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች የመስቀልን ታሪክና ኃይል ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው፡፡ እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል፡፡"* ቆላ.፪፥፲፬

**ተጨማሪ ምንባብ ፡-** ስንክሳር የመስከረም ፲፮ እና ፲፯፡፡

**መግቢያ፡-** ልጆች ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ እርሱ በተሰቀለበት መስቀል ብዙ ተአምራት ይደረግ ነበር ፡፡

በዛሬው ትምህርታችንም በመስቀሉ ምን እንደተፈጸመና ፤ ተደብቆ ከኖረበት እንዴት እንደተገኘ እንማራለን፡፡ በቤተ ክርስቲያን መስቀልን መቼና እንዴት እንደምናከብርም እናያለን፡፡

## የትምህርቱ ይዘት፡-

በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ዕሌኒ የተባለች ንግሥት የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል ለማግኘት ፈለገች ፣ ለሦስት መቶ ዓመታት ከተቀበረበት ፈልጋ አገኘችው፡፡ ለምን የፈለገችው ይመስላችኋል ? በክፍል ዉስጥ ተወያዩ፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ ከሞት አድኖናል፤ ፍቅሩንም በመስቀል ገልጾልናል፡፡ ይህ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል ብዙ ተአምራትን ሲፈጽም፤ ከጌታችን ትንሣኤ በኋላም ብዙ ሰዎች በመስቀሉ ማዳን እየተሳቡ በጌታችን እያመኑ ክርስቲያን ሆነዋል፡፡

ጌታችንን ለጲላጦስ አሳልፈው የሰጡትና ሞት የፈረዱበት አይሁድ ይህንን ዐይተው አልተመለሱም፡፡ እንዲያውም በቅናትና በእልህ መስቀሉን ለመደበቅ ፈለጉ፡፡ እናም ከከተማ ርቆ እንዲቀበርና ሥፍራዉም ቆሻሻ መጣያ እንዲሆን አደረጉ፡፡ ጌታችንን ግን ለሰዉ ልጅ በሙሉ ካለው ፍቅር የተነሣ ታገሳቸው፡፡

www.zeorthodox.org

በዚህ ዓይነት ሦስት መቶ ዓመታት ካለፉ በኋላ ፣ ንግሥት ዕሌኒ የጠፋውን መስቀል ለመፈለግ ተነሣች፡፡ የንግሥት ዕሌኒ ልጅ ቆስጠንጢኖስ የሮም ንጉሥ ነበር፡፡ የእናቱን መልካም ፍላጎት ተረድቶ ሊያሳካላት ፈለገ፡፡ ልጆች እናንተስ የወላጆቻችሁን ፍላጎት ታሟላላችሁ ? ምን ያህልስ ትታዘዛላችሁ? ቤተሰቡን የሚወድ ቤተሰቡን ያስደስታል፡፡ የወላጆቻችሁ ፍላጎት ኀበዝ

ተማሪዎች ሆናችሁ፤ ነገ ለሀገር፣ ለቤተክርስቲያን እና ለሕዝብ የሚጠቅም ታላቅ ሥራ የምትሠሩ እግዚአብሔር የሚወዳችሁ እንድትሆኑ ነው። ወላጆቻችሁ የሚያዙአችሁም ለዚህ ነው።

ንጉሡ ቆስጠንጢኖስ መስቀሉን ለመፈለግ ንግሥት ዕሌኒን የሚረዷት ወታደሮች አዘጋጀላት። ከዚያም ከሮም ተነሥተው ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዙ። እዚያ ሲደርሱ መስቀሉ ያለበት ቦታ አልታወቀም ነበር። በብዙ ድካም ኪርያኮስ የተባለ አረጋዊ ተገኘና መስቀሉ የተቀበረበትን አካባቢ አሳያት። ንግሥቲቷም እንዴት እንደምታወጣው በጸሎት እግዚአብሔርን ጠየቀች። ከዚያም ትልቅ ደመራ ደምራ ዕጣን አጨሰችበት። ልጆች ዕጣን ምንድነው ? ደመራስ ዐይታችሁ ታውቃላችሁ ?

ልጆች ይገርማችኋል በደመራው የጨሰዉ ዕጣን ወደ ሰማይ ወጥቶ እንደገና ተሰብስቦ አጎነበሰና ወደ ምድር በመውረድ መስቀሉ ያለበት ቦታ ላይ አመላከተ። ንግሥቲቱና አብረዋት ያሉት ሁሉ በታላቅ ደስታ ሥፍራዉን መቆፈር ጀመሩ። ለሦስት መቶ ዓመታት የኖረውን የቆሻሻና አፈር ክምር ተራራ በስድስት ወር ቆፍረው ሲጨርሱ፣ ሦስት መስቀሎች ተገኙ። እነኚህም አንደኛዉ ጌታችን የተሰቀለበት ሲሆን፤ ሁለቱ በጌታችን ቀኝና ግራ የተሰቀሉት ወንበዴዎች የተቀጡባቸው ነበሩ። ቀጣዩ ሥራ የጌታችንን መስቀል መለየት ነበር። እናም የታመመ ሰው እና ሙት አምጥተው መስቀሎቹ ላይ አደረጉ። ሁለቱ አላዳኑም አንዱ ብቻ አዳነ። በዚህ የጌታችን መስቀል መሆኑ ተለየ። በታላቅ ደስታም በዓል አድርገው አከበሩ ፤ ይህ ቀን መስከረም ፲፯ ነበር።

ቤተ ክርስቲያንም ይህንኑ ቀን በየዓመቱ ደመራ በመትከል ታስበዋለች ፣ በጸሎትና በዝማሬም ታከብረዋለች። የቅድስቲቷን ንግሥት የዕሌኒን መልካም ሥራም ታስተምራለች። የመስቀሉ ኃይልና በረከት ከእኛ ጋር ይሁን !!! አሜን!

## *የክለሳ ጥያቄዎች*

1. መስቀሉን ማን ቀበረው ? ለምን ?

_______________________________

2. መስቀሉን ያገኘችው ማናት ?

www.zeorthodox.org

_______________________________

3. የልጇ ስም ማን ይባላል ? ሥራው ምን ነበር ?

_______________________________

4. በቤተ ክርስቲያን የመስቀል ምልክት አይታችኋል ? የት ?

_______________________________

## ማጠቃለያ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል በክፉዎች ቅናት ለሦስት መቶ ዓመታት ተቀብሮ ነበር፡፡

በንግሥት ዕሌኒ አማካይነት ተገኝቶአል፡፡

በየዓመቱ መስከረም ፲፯ ቀን የምናከብረውም ይህንኑ ለማሰብ ነው፡፡

አከባበሩም ንግሥት ዕሌኒ መስቀሉን ለመፈለግ ደመራ እንደደመረችው ተደርጎ ነው፡፡

## ተግባር

በቤተ ክርስቲያን መስቀል ያለባቸውን ቦታዎች አስተውላችሁ ተመልከቱ፡፡

ለምን እንደተደረገም ጠይቁ

የሚከተለውን መዝሙር አጥኑ

### *መዝሙር*

መስቀል ኃይልነ መስቀል ጽንዕነ መስቀል ቤዛነ(2)

መድኃኒትነ ለእለ አመነ(4)

### *ትርጉም*

መስቀል ኃይላችን ነው፤ መስቀል መጽኛችን ነው፤ መስቀል ቤዛችን ነው፡፡

ላመንበትም መዳኛችን ነው፡፡

www.zeorthodox.org

# ሥነ ፍጥረት (፩)

## አራተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች ስለ ሥነ ፍጥረት ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***‹‹እግአብሔርም የፈጠረው ሁሉ መልካም እንደሆነ አየ››*** ዘፍ.፩፥፴፩

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ዘፍ.፩፥፩-፴

### ሥነ ፍጥረት ማለት ምን ማለት ነው ?

ሥነ ፍጥረት ማለት ያማረ የተዋበ ፍጥረት ማለት ነው፡፡ ***‹‹እግአብሔርም የፈጠረው ሁሉ መልካም እንደሆነ አየ››*** ዘፍ.፩፥፴፩፡፡ ሁሉን ቻይና አዋቂው እግዚአብሔር ፍጥረታትን፣ የፈጠረበትን ሥርዓት የምንማርበት ትምህርት ሥነ ፍጥረት ይባላል፡፡

### ለምን ስለ ሥነ ፍጥረት እንማራለን ?

ማንኛውም ባለሞያ የሠራውን ሲያደንቁለት ደስ ይለዋል፡፡ ***ለምሳሌ*** ሠዓሊ ሥዕሉን ፣ ሸክላ ሠሪ ድስቱን ወይም ስኒውን ፣ መሐንዲስ ሕንጻውን ሲያደንቁለት ይደሰታል - መልካም ነገርን ማድነቅም አለብን፡፡ እንዲሁም ማንኛውም ሥራ የሰሪውን ችሎታና ማንነት ያሳውቃል፡፡

ዓለማትን የፈጠረው እግዚአብሔርም ፍጥረቱን እና አፈጣጠሩን አውቀን እንድናመሰግነው እና እንድናምነው ፤ ሥነ ፍጥረትን እንማራለን፡፡ ዕብ.፲፩፥፫

### የሁሉም ፈጣሪ ፤ ሁሉን ቻይ፤ እግዚአብሔር ብቻ ነው !!!

በሚታየውና በማይታየው ዓለም ያሉት ሁሉ በእግዚአብሔር ተፈጥረዋል፡፡ ***‹‹በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ››*** ዘፍ.፩÷፩ ***‹‹አቤቱ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ ሰማያትም የእጆህ ሥራዎች ናቸው፡፡››*** መዝ.፻፩÷፳፭

www.zeorthodox.org

ሁሉንም የፈጠረው እግዚአብሔር መነሻ የሚሆን ምንም ነገር አላስፈለገውም ፤ የሚነሣበት ፣ የሚያገናኘው ፣ የሚያዋሕደው ምንም ነገር ሳይኖር ፍጥረትን አስገኘ፡፡ መዝ. ፴፪(፴፫)÷፱ ፣ ፪ኛ መቃ.፲፬÷፲

### ለምን ተፈጠርን ?

ልጆች እግዚአብሔር ፍጥረታትን የፈጠረበት ዓላማ በሁለት ይከፈላል ፡-

**ሰው እና መላእክት**፡- የእግዚአብሔርን ስም ለመቀደስ ፣ መንግሥቱንም ለመውረስ ሲፈጠሩ፤

**ሌሎቹ ፍጥረታት**፡- ለሰው ልጅ ምግብነት ፣ ለአንክሮ (እግዚአብሔርን እንድናደንቅባቸው) ፣ ለተዘክሮ (እግዚአብሔርን እንድናስታውስባቸው) የተፈጠሩ ናቸው፡፡ ኢሳ.፵፫÷፯-፰ ፣ መዝ.፻፵፰÷፩-፲፫፣ ሐዋ.፲፬÷፲፯ ፣ ሮሜ.፩÷፳

ከፍጥረታት የትኛውን ታደንቃላችሁ ርግብ፣በግ፣ዛፍ ወይስ ሌላ? ባያችሁት ፍጥረት አምላካችሁን ያደነቃችሁበትን አጋጣሚስ ታስታውሳላችሁ? በክፍል ውስጥ አስረዱ፡፡ ሁሉም የእግዚአብሔር ሥራዎች ናቸው፡፡

## ስንት ፍጥረታት አሉ ?

የፍጥረታት ብዛታቸው አይታወቅም፡፡ ነገር ግን ብዙዎቹ እንደ አንድ እየተቆጠሩ እግዚአብሔር ሃያ ሁለት ፍጥረታትን ፈጥሮአል እንላለን፡፡ ይህ ማለት በዓይነታቸው ተመድበው ነው ፤ **ለምሳሌ** በዓለማችን ብዙ ዓይነት ወፎች እና የአዕዋፍ ዝርያዎች አሉ፡፡ ንስር፣ ዶሮ፣ ወፍ፣ ርግብ፡፡ ነገር ግን ሁሉም በአንድነት የሰማይ ወፎች ተብለው ይቆጠራሉ፡፡

## እንዴት ተፈጠሩ ?

ፍጥረታት የተፈጠሩት በሦስት መንገድ ነው ፡፡

1. **በማሰብ**፡፡ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር እንዲፈጠሩ ስለ ፈቀደ ብቻ የተገኙ አሉ፡፡ ይህም በግእዝ - ***በኃልዮ*** ወይም ***በአርምሞ*** ይባላል፡፡ **ለምሳሌ**፡- መላእክት፣ አራቱ ባሕርያት እና እነዚህን የመሰሉ ሰባት ፍጥረታት በዚህ መንገድ ተፈጥረዋል፡፡
2. **በመናገር**፡፡ ልዑል እግዚአብሔር ፡- ይሁኑ ፣ ይፈጠሩ ፣ ይገኙ …. በማለቱ ብቻ የተፈጠሩ አሉ፡፡ ይህ አፈጣጠር በግእዝ ***በነቢብ*** ይባላል፡፡ በዚህ መንገድ ዐሥራ አራት ፍጥረታት ተገኝተዋል፡፡ **ለምሳሌ**፡- ብርሃን ፣ ወፎች ፣ ዕፅዋት፡፡
3. **በመሥራት**፡፡ እግዚአብሔር በእጆቹ የሠራው ሰውን ብቻ ነው፡፡ ይህም በግእዝ ***በገቢር*** ይባላል፡፡

## መቼ ተፈጠሩ ?

www.zeorthodox.org

እግዚአብሔር ሁሉንም የፈጠረው በስድስት ቀናት ብቻ ነው፡፡ እነዚህ ቀናትም ከእሑድ እስከ ዓርብ ያሉት ቀናት ናቸው፡፡

# የስድስቱ ቀን ፍጥረታት፡፡

**የዕለተ እሑድ ፍጥረት**፡- እግዚአብሔር በመጀመሪያው ቀን እሑድ ስምንት ፍጥረታትን አስገኘ፡፡ እነርሱም፡- ነፋስ፣ እሳት፣ መሬት፣ ውኃ፣ ጨለማ፣ ብርሃን፣ ሰማያትና መላእክት ናቸው፡፡ ሰማያት ሰባት ናቸው፤ እነርሱም ጽርሐ አርያም፣ መንበረ መንግሥት፣ ሰማይ ውዱድ፣ ኢየሩሳሌም

ሰማያዊት፣ ኢዮር፣ ራማ፣ ኤረር ይባላሉ።

***የሰኞ ፍጥረታት፦*** በሁለተኛው የፍጥረት ቀን እግዚአብሔር ጠፈርን ብቻ ነው የፈጠረው። እሑድ የተፈጠረው ውኃ ከምድር እስከ ሰማይ ነበር። ሰኞ ውኃን ወደታችና ወደላይ ከፈለ። በመካከሉም ጠፈርን አደረገ። ዘፍ.፩÷፮-፰ ፣ ኩፋሌ ፪÷፱ ከጠፈር በላይ የቀረው ውኃ ሐኖስ ሲባል ፤ ከጠፈር በታች የቀረው ውቅያኖስ ይባላል።

## ማጠቃለያ

***‹‹ ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ፥ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን።››*** ዕብ.፲፩÷፫ እምነት የፈጠረንን የምናሳተውልበት ነው፤ ለዚህም የሥነ ፍትረትን ታሪክ ተምረናል።

የተፈጠርንበት ዓላማ እግዚአብሔርን በማመስገን መንግሥቱን ለመውረስ ነው ።

ተመሳሳይ ፍጥረታትን እንደ አንድ በመቁጠር ሃያ ሁለት ፍጥረታት አሉ። እነዚህም በማሰብ ፣ በመናገር እና በመሥራት ተፈጥረዋል። ሁሉን ቻይ ጌታ እግዚአብሔር እነዚህን ሁሉ የፈጠረው በስድስት ቀናት ነው።

የፍጥረት መጀመሪያ ቀን እሑድ ነው። ሰኞ እና እሑድ ዘጠኝ ፍጥረታት ተገኝተዋል። እነኚህም፦ ነፋስ፣ እሳት፣ መሬት፣ ውኃ፣ ጨለማ፣ ብርሃን፣ ሰማያት፣ መላእክት እና ጠፈር ናቸው።

ሌሎችን ፍጥረታት እግዚአብሔር ቢፈቅድ ብንኖርም በሚቀጥለው ሳምንት ትምህርታችን እንመለከታለን።

## ተግባር

ፈጣሪያችንን በፍጥረቱ እያደነቅን እናመስግነው። በምታዩት በሚቀጥለው ሁሉ እንደ ዳዊት ‹‹***ሥራህ ድንቅ ነው***›› በሉ።

ሁሉንም የምትሠሩበት ጊዜ ይኑራችሁ። እግዚአብሔር በስድስት ቀናት የፈጠረውን በአንዲት ሰከንድ መጨረስ ይችል ነበር። ሆኖም ሁሉንም በጊዜው መሥራትን ሲያስተምረን ይህን አደረገ። እናንተም የምግብ፣ የትምህርት፣ የዕረፍት፣ የጥናት፣ የጨዋታም ጊዜ አላችሁ። እናም ቤተሰቦቻችሁ የሚያወጡላችሁን መርሐ ግብር በሚገባ ተጠቀሙ።

www.zeorthodox.org

### ***የክለሳ ጥያቄዎች***

1. የሥነ ፍጥረትን ታሪክ ለምን እንማራለን ?
2. ሥነ ፍጥረት በስንት ቀን ተፈጠሩ ?
3. እሑድና ሰኞ የተፈጠሩ ፍጥረታት ስንት ናቸው ? በየቀናቸው ለይታችሁ ዘርዝሩ።

# *ሥነ ፍጥረት (፪)*

# (ከማክሰኞ - ዓርብ የተፈጠሩ ፍጥረታት)

## አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ስለ *ሥነ* ፍጥረት የጀመርነውን ትምህርት በመቀጠል፤ ተማሪዎች/ልጆች/ ከማክሰኞ እስከ ዓርብ የተፈጠሩትን ፍጥረታት አውቀው፣ የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ተገንዝበው በሥራዎቹም እምነታቸውን አጠንክረው ምስጋናቸውን ከማቅረብ ጋር ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *‹‹ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት፡፡ ሥራህ ግሩም ነው……..፡፡››* መዝ.፻፬÷፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍጥ.፩÷፱-፳፫ ፣ ሉቃ.፪÷፲፩ - ፍጻሜው፣ *መጽሐፈ ሥነ ፍጥረት*(ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ)……

**መግቢያ፡-** በሥነ ፍጥረት የመጀመሪያ ትምህርታችን የቃሉን ትርጉም፣ ለምን እንደምንማር፣ የፍጥረታትን አፈጣጠርና ብዛት፣ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀናት የተፈጠሩትንም ተምረናል፡፡ የተማራችሁትን በማስታወስ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1. ሥነ ፍጥረት ማለት ምን ማለት ነው ?
2. ለምን ስለ ሥነ ፍጥረት እንማራለን ?
3. ሥነ ፍጥረታት በማን ? እንዴት? ተፈጠሩ?
4. እሑድ ስንት ፍጥረታት ተፈጠሩ ? ሰኞስ ?
5. ፍጥረታት የተፈጠሩት በስንት ቀናት ነው ? ቀናቱን ዘርዝሩ፡፡

ስንቱን ጥያቄዎች መለሳችሁ ? ጥሩ ነው፡፡ ዛሬም ቀሪዎችን ፍጥረታት እንማራለን፡፡ ከስድስቱ የፍጥረታት ቀን ከማክሰኞ እስከ አርብ ያሉት፡፡ ሦስተኛ ፣ አራተኛ ፣ አምስተኛ እና ስድስተኛ ቀናት ይባላሉ፡፡ በእነኚህ ቀናት ዐሥራ አራት ፍጥረታት ሲገኙ ፣ በዛሬው ትምህርታችን ዐሥራ ሦስቱን እንማራለን፡፡

www.zeorthodox.org

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

#### ማክሰኞ (ሠሉስ) - ሦስተኛው ቀን

በዚህ ቀን አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር ሦስት ፍጥረታትን አስገኝቷል፡፡ እነርሱም ዕፅዋት፣

አዝርእት እና አታክልት ናቸው። ( ልጆች ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን ሰኞ እግዚአብሔር ውኃን በሦስት ቦታ ሲሰበስብ አንደኛውን እጅ በምድር እንዳደረገው ታስታውሳላችሁ? አዎ ከሆነ መልሳችሁ የተማራችሁትን አስረዱ፣ ካላስታወሳችሁ መምህርን ጠይቁ፤)

ልጆች እግዚአብሔር ሁሉንም በጥበብ አደረገ። ማክሰኞ ከምድር የሚበቅሉትን ለመፍጠር ሲፈቅድ፤ በመጀመሪያ መብቀያውን ምድርን አዘጋጀ። ያዘጋጀውም እንዲህ ነበር፡- *« እግዚአብሔርም፦ ከሰማይ በታች ያለው ውኃ በአንድ ስፍራ ይሰብሰብ ፥ የብሱም ይገለጥ አለ እንዲሁም ሆነ።»* ዘፍ.፩፥፱ በዚህ ጊዜ ውኃው ተሰበሰበ፣ ምድርም ተገለጠች፣ ለማብቀል የምትችል ደረቅ መሬትም ሆነች። *‹‹እግዚአብሔርም የብሱን ምድር ብሎ ጠራው የውኃ መከማቻውንም ባሕር አለው።››* ዘፍ.፩፥፲ ከዚያም *‹‹እግዚአብሔር፦ ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል አለ...››* ዘፍጥ.፩፥፲፩-፲፪ በዚህ ጊዜም፡-

ዕፅዋት (ዛፎች)፣

አዝርዕት (የሚታጨዱና የሚለቀሙ)፣

አታክልት (ፍራ ፍሬዎች) ተገኙ።

## የረቡዕ - አራተኛ ቀን ፍጥረታት

በዚህም ቀን ***ሦስት ፍጥረታት ተፈጥረዋል***። እነርሱም ***ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት*** ናቸው። ልዑል እግዚአብሔር እነዚህን የፈጠረበት ምክንያት ፡- *« ቀንና ሌሊትን ይለዩ ዘንድ ... ለምልክቶች ለዘመኖች ለዕለታት ለዓመታትም ..... በምድርም ላይ ያበሩ ዘንድ ...»* ነው። ዘፍ.፩፥፲፬-፲፭ ልጆች ከዚህ እውነተኛ ቃል ***ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት*** የተፈጠሩት ፡-

***ቀንና ሌሊትን ለመለየት***። ማለትም ቀንን ልንሠራበት ሌሊትን ልናርፍበት ነው።

***ጊዜያትን የምንቆጥርበትና የምንለይበት ምልክት እንዲሆኑ ነው***። ለምሳሌ አሁን ባለው ዓመት ላይ የደረስነው ቀናት ተደምረው፣ ሳምንታት፤ ሳምንታት ተደምረው፣ ወራት፤ ወራት ተደምረው ፣ ዓመታት፤ ዓመታት ተደምረው፣ ዘመናትን ስለሰጡን ነው። እነዚህ ሁሉ የሚቆጠሩት በብርሃናቱ (በፀሐይ፣ በጨረቃና በከዋክብት) መፈራረቅ ነው።

www.zeorthodox.org

በዚህም መሠረት ረቡዕ ዕለት *‹‹እግዚአብሔር ሁለት ታላላቆች ብርሃናትን አደረገ፤ ትልቁ ብርሃን በቀን እንዲሠለጥን፥ ትንሹም ብርሃን በሌሊት እንዲሠለጥን ከዋክብትንም ደግሞ አደረገ። እግዚአብሔርም በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ በሰማይ ጠፈር አኖራቸው።››* ዘፍ.፩፥፲፮-፲፯ እግዚአብሔር ዓላማ ሳይኖረው የፈጠረው የለም።

ልጆች ሰኞ ጠፈርን ሲፈጥር ለምን እንዳዘጋጀው አስተዋላችሁ። በእያንዳንዳችን ሕይወትም አዋቂው እግዚአብሔር ይህንኑ ያደርጋል፣ ቤተሰባችንን፣ ቤተ ክርስቲያናችንን ወዘተ... ያዘጋጀልን በሕይወታችን ዓላማ ስላለው ነው።

## የሐሙስ - አምስተኛ ቀን ፍጥረታት

በዚህ ቀን እግዚአብሔር ከውኃ ሦስት ፍጥረታትን አስገኝቶአል ። እነርሱም ፡- አእዋፍ ዓሣት እና አናብርት ናቸው። ***‹‹እግዚአብሔርም አለ፡ ውኃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ ፥ ወፎችም ከምድር በላይ ከሰማይ ጠፈር በታች ይብረሩ››*** ዘፍ.፩፥፳ ብሎ ባዘዘው መሠረት፡-

በሰማይ የሚበሩ አእዋፍ፣

በባሕር የሚኖሩ ዓሦችና የውኃ ፍጥረታት በሙሉ፣

በምድር እና በባሕር እየወጡ እየገቡ የሚኖሩት ተገኙ።

## የዓርብ - ስድስተኛ ቀን ፍጥረታት

በዚህ ቀን ከምድር የተገኙ አራት ዓይነት ፍጥረታት ተፈጠሩ። እነርሱም ሰውና እንስሳት ሲሆኑ፤ በዚህ ቀን የተፈጠሩት እና እኛ በተለምዶ እንስሳት ብለን የምንጠራቸው ሦስት ዓይነት ናቸው ፡-

አራዊት፤ በጫካና በበረሓ የሚኖሩ።

እንስሳት፤ በቤትና ከሰው ጋር የሚኖሩ።

የመሬት ተንቀሳቃሾች፣ በሆዳቸው የሚሳቡ ናቸው።

**ማጠቃለያ፡-** አምላካችን ሁሉንም በጥበብ ሠርቶአል። ምክንያት ሳይኖረው የተፈጠረም የለም። አንዱ ለሌላው አስፈላጊ ነበር። ጠፈር የፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት መመላለሻ ነበር። ምድርን ገለጦ ዕፅዋት እና እንስሳትን አስገኘ።

## ተግባር

እያንዳንዱ ሰው ለሌላው አስፈላጊ ነው። እናም ለሰው ሁሉ ፍቅር ይኑራችሁ።

የሚከተለውን መዝሙር አጥኑ።

***መዝሙር***

ኵሎ ዘፈቀደ ገብረ እግዚአብሔር
www.zeorthodox.org
በሰማይኒ ወበምድርኒ ወበባሕርኒ ወበኵሉ ቀላያት

***ትርጉም***

እግዚአብሔር የወደደውን ሁሉ አደረገ

በሰማይ በምድርም በባሕርም ሆነ በወንዞች

# የአዳም እና ሔዋን አፈጣጠር

## ስድስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች የመጀመሪያውን የሰውን አፈጣጠር ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***‹‹እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው››*** ዘፍጥ.፩፥፳፯

**የትምህርቱ መግቢያ፡-** ባለፉት ተከታታይ ትምህርቶች የፍጥረታትን መገኘት ተምረናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም ከፍጥረታት ሁሉ የሚበልጠውን እና በመጨረሻ የተፈጠረውን የሰውን አፈጣጠር እና ክብር እናያለን፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች

***የሚስማማውን ቃል መርጣችሁ ሙሉ፡፡***

ሀ. ቀንን ለ. ምድር ሐ. ሌሊት መ. ከውኃ ሠ. ያበሩ

ዓሳዎች እና አዕዋፍ ከ-----------------ሲፈጠሩ፤ አራዊት እና እንስሳት ከ---------------ተፈጠሩ፡፡ ፀሐይ፣ ጨረቃ እና ከዋክብት የተፈጠሩት ----------- እና ----------- ይለዩ ዘንድ፤ ለምልክቶችና በምድር ላይ ------- ዘንድ ነው፡፡

ዓርብ ስንት ፍጥረታት ተፈጠሩ ?----------------፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት

እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያለውን ክብር እና ፍቅር ለመግለጽ ለሰው የሚያስፈልገውን ኹሉ አስቀድሞ ካዘጋጀለት በኋላ ፈጠረው፡፡ ዓርብ ጠዋት ልዑል እግዚአብሔር ***‹‹በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር አለ፡፡››*** ዘፍ.፩፥፳፮

www.zeorthodox.org

በተናገረው መሠረት ከምድር አፈር ወሰዶ አበጃጀው (ሠራው)፤ ከዚያም የሕይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት፡፡ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ፡፡ ዘፍ.፪፥፯ ልጆች እግዚአብሔር ገና ሲፈጥረን የሰውን ልጅ እንዴት እንዳከበረው አስተዋላችሁ፡፡ ሌሎቹን ፍጥረታት በማሰብ እና በመናገር ብቻ ሲፈጥር የሰውን ልጅ ግን አስቦ፣ እንፍጠር ብሎ ተናግሮ፣ በመጨረሻም በተቀደሱ እጆቹ ሠራው፡፡ በእስትንፋሱ እፍ ብሎ ለዘላለም የምትኖር፣ አዋቂና መናገር የምትችል ነፍስ ሰጠው፡፡ በነፍሳችን

መላእክትን በሥጋችን እንስሳትን እንመስላቸዋለን፡፡

**ሰው** የሚለው ቃል በአማርኛ ሲሆን በግእዝ **ሰብእ** ይባላል፡፡ ሰባት ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ሰው (ሰብእ) እንፍጠር ሲል ሰባት ነገሮች ያሉትን እንፍጠር ማለቱ ነበር፡፡ ሰው አራት ባሕርያተ ሥጋና ሦስት የነፍስ ሥራዎች አሉት፡፡ እነርሱም **አራቱ ባህርያተ ሥጋ ፡-** አፈር፣ ውኃ፣ ነፋስ እና እሳት ሲሆኑ፤ **ሦስቱ የነፍስ ሥራዎች** (ግብራተ ነፍስ) ደግሞ፡- **መናገር፣ ለዘላለም መኖር** እና **ማሰብ መቻል** ናቸው፡፡ እነኚህም በግእዝ ***ነባቢነት ፣ ሕያውነት እና ለባዊነት*** ይባላሉ፡፡

የሰው ልጅ የተፈጠረው በእግዚአብሔር መልክ እና ምሳሌ ነው፡፡ እግዚአብሔር እንደ ሰው የሚታይ እና የሚዳሰስ አካል ባይኖረውም ረቂቅ አካል አለው፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከቱ፡፡ መዝ.፹፪(፹፫)÷፲፰፣ ፻፲፰(፻፲፱)÷፸፫፣ ፻፴፩(፻፴፪)÷፯ ፣ ኢሳ.፳፯÷፩፣ መዝ.፹፫(፹፬)÷፲፮-፲፯ (መምህር ጥቅሶቹን አስነብበው፤ ከትምህርቱ አንጻር ያብራሩላቸው፡፡)

አምላካችን የፈጠረውን ሰው **አዳም** አለው፡፡ አዳም ማለትም ***ያማረ*** ማለት ነው፡፡ አዳምም ብቻውን ለአንድ ሳምንት ቆየ፡፡

በሳምንቱ ዓርብ እግዚአብሔር በአዳም ላይ ከባድ እንቅልፍ ጣለበት፡፡ ከዚያም ከጎኑ አጥንት ወሰደ፤ ሴት አድርጎም ፈጠራት፡፡ አዳም ከእንቅልፉ ነቃ፡፡ አጠገቡ ያለችውንም አየ፡፡ እግዚአብሔር እንዴት እንደፈጠረለትም አስተዋለ፡፡ ሴትዋም እጅግ ውብ ነበረች፡፡ በዚህ ጊዜ አዳም ‹‹ ***ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት ፥ ሥጋም ከሥጋዬ ናት እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል፡፡››*** አለ፡፡ ዘፍ.፪÷፳፫

አባታችን እግዚአብሔር በምሥራቅ አቅጣጫ ገነትን ተከለ፤ ልጆች ገነት ከምድር ከፍ ብላ ያለች መንፈሳዊት ሀገር ናት፤ ገነት እጅግ የምታምር ደስ የሚያሰኙና ለሰውነት የሚስማሙ ፍሬዎች አሉባት፡፡ ከብዙ ቀናት በኋላ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ከተፈጠሩባት ምድር (ከዚህች ምድር) ወደ ገነት አስገባቸው፤ ዛሬም የሚሞቱ ቅዱሳን ወደገነት ይገባሉ፡፡ እኛም በእግዚአብሔር መንገድ ከሄድን እንገባባታለን፡፡

**አዳም በገነት እያለ ፡-**

www.zeorthodox.org

**እግዚአብሔር የፈጠራቸውን እንስሳት አዳም ስም እንዲያወጣላቸው ፈቀደለት፡፡**

***‹‹እግዚአብሔር አምላክም የምድር አራዊትንና የሰማይ ወፎችን ሁሉ ከመሬት አደረገ፤ በምን ስም እንደሚጠራቸውም ያይ ዘንድ ወደ አዳም አመጣቸው አዳምም ሕያው ነፍስ ላለው ሁሉ በስሙ እንደ ጠራው ስሙ ያው ሆነ፡፡››*** ዘፍ.፩÷፲፱ አዳም ይናገርበት በነበረው ቋንቋ ለእንስሳቱ አንበሳ ፣ ንስር ፣ በግ ፣ ዓሣ እያለ ጠራቸው ስማቸውም እንደዚያው ሆነ፡፡

**ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን እንዲበዙና ሌሎችን ፍጥረታት እንዲገዙ ባረካቸው፡፡**

‹‹ ***እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው፦ ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም***

*የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው፡፡›› ዘፍ.፩፥፳፰*

## ማጠቃለያ

ፈጣሪያችን ሕያው እግዚአብሔር አዳምን በስድስተኛው፣ ሔዋንንም አዳም በተፈጠረ በሳምንቱ ፈጠረ፡፡ እግዚአብሔር አክብሮ በእጁ ሠራቸው የሕይወት እስትንፋስንም እፍ አለባቸው፡፡

አባታችን እግዚአብሔር በልግሥናው አዳምና ሔዋን በምድር ያሉትን እንዲገዙ፣ ከምድር ፍሬም እንዲበሉ ፈቀደላቸው፣ እንዲበዙም ባረካቸው፡፡

## ተግባር

**ሰው ክቡር እና ተወዳጅ ፍጡር ነው፡፡** ልጆች እናንተም እግዚአብሔርን በመምሰል እደጉ፤ ይህም በቅድስና መኖር ነው፡፡ ለምሳሌ፡- አትዋሹ፣ አትሳደቡ፣ ጎበዞችና ሁሉንም (ትምህርት፣ ጥናት፣ ዕረፍት…) በጊዜው የምትሠሩ ሁኑ፡፡ አስበንና አስተውለን ሁሉንም በጊዜው ስለምንሠራ እኛ ከእንስሳት እንለያለን፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች**፡- ተስማሚውን ቃል የያዘውን ፊደል መርጣችሁ በባዶ ቦታ ሙሉ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. በሳምንቱ | ሐ. አዳም |
| ለ. በስድስተኛው | መ.ገነት |

አዳም በ------ ቀን ሔዋንም በ------- ተፈጠሩ፡፡ ለእንሳሳት ስም ያወጣላቸው--------- ነው፡፡ ሰው በዚህ ምድር ተፈጥሮ በ------- ኖረ፡፡

***መዝሙር***

እናመስግነው(2)

አምላካችን ውለታው ብዙ ነው፡፡(2)

ከባርነት ቀንበር ከሞት ደጅ ጎትቶ መንግሥቱን ለሰጠን በሕይወት አኑሮ

ዘላለማዊ ቤት ታላቅ ሀብት ያደለን መቼም የማይተወን ታላቅ አባት አለን፡፡

www.zeorthodox.org

# የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ትእዛዝ

## ሰባተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች እግዚአብሔር ለሰው የሰጠውን የመጀመሪያውን ሕግ ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *‹‹ እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው ፡ ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፡፡ መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና ››* ዘፍ.፩፥፲፮-፲፯

**መግቢያ፡-** ልጆች ባሳለፍነው ሳምንት የአዳምና እና ሔዋንን አፈጣጠር ተምረናል፤ አባታችን እግዚአብሔር ስለሚወደን ሁሉንም አሟልቶ እንደፈጠረን፣ አዳምን እና ሔዋንንም በምድር ገዢ እንዲሆኑና እንዲባዙ እንደባረካቸውም አይተናል፡፡ የሚከተሉትን የክለሳ ጥያቄዎችና ትምህርቶች አስታውሱ፡-

1. አዳም መቼ ተፈጠረ ?
2. ለምን በመጨረሻው ቀን ፈጠረው ?
3. እግዚአብሔር ለአዳም የሰጠው ሥልጣን ምን ነበር ?

ልጆች እግዚአብሔር በጣም ስለሚወደን አክብሮ ፈጥሮናል፤ የሚያስፈልገንንም አዘጋጅቶልናል፤ ከፍጥረታት ሁሉ የበላይ አድርጎ ግዟቸው ብሎናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም ከሚጎዳን እንድንጠበቅና የተሰጠንን በረከት እየተጠቀምን እንድንኖር የተሰጠውን ትእዛዝ እንማራለን፡፡

የመጀመሪያዋ ትእዛዝ ምንድናት? እናንተስ አምላካችሁ የሚያዛችሁን እና ቤተሰቦቻችሁ ለሚሉአችሁ ትታዘዛላችሁ? ለመምህር አስረዱ፡፡

www.zeorthodox.org

## የሳምንቱ ትምህርት

### የሚበሉትን ሰጣቸው፡፡

ልዑል እግዚአብሔር ለእኛ የሚያስፈልገውን ሁሉ ያውቃል ፤ ከሚያስፈልገንም አንዳች አልከለከለንም ፤ እንዴውም ***ሰጠኋችሁ*** በማለት ፈቅዶልናል፡፡ ***‹‹እግዚአብሔርም አለ፦ እነሆ መብል ይሆናችሁ ዘንድ በምድር ፊት ሁሉ ላይ ዘሩ በእርሱ ያለውን ሐመልማል ሁሉ፥ የዛፍን ፍሬ የሚያፈራውንና ዘር ያለውንም ዛፍ ሁሉ ሰጠኋችሁ››*** ዘፍ.፩፥፳፱

ልጆች እግዚአብሔር የሚሰጠን የሚጠቅመንን ነው፤ የሚከለክለንም የሚጎዳንን ብቻ ነው። የሚከተለውን አስተውሉ።

## ትበላለህ እንዲሁም አትብላ፤ የሚል ትእዛዝ አዘዛቸው።

*‹‹እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፦ ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ። መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና ››* ዘፍ.፪፥፲፮-፲፯

*ሀ. ‹‹እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው……››* ልጆች እግዚአብሔር አምላካችን ነው፤ እኛም የእጁ *ሥራዎች* የሆንን ፍጡራኑ ነን። እርሱን መውደዳችንና ለእርሱ መገዛታችን የሚታወቀው የሚያዘንን በመስማት ነው። የእግዚአብሔር ትእዛዝ ለመልካም ነው።

*ለ. ‹‹ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ።››* ልጆች ስለ ገነት መፈጠር ከሁለት ሳምንት በፊት ከተማራችሁት ትምህርት ታሳታውሳላችሁ ? በክፍል ውስጥ አስረዱ።ልጆች መጽሐፍ ቅዱስ በገነት ሦስት ዓይነት ዛፎች እንደነበሩ ፤ ይነግረናል *‹‹ እግዚአብሔር አምላክም ለማየት ደስ የሚያሰኘውን፥ ለመብላትም መልካም የሆነውን ዛፍ ሁሉ ከምድር አበቀለ በገነትም መካከል የሕይወትን ዛፍ፥ መልካምንና ክፉን የሚያስታውቀውንም ዛፍ አበቀለ።››* ዘፍ.፪፥፱ እነርሱም፦

**የሕይወት ዛፍ።** ይህች በገነት መካከል ነበረች *‹‹በገነትም መካከል የሕይወትን ዛፍ፥……..አበቀለ››* ዘፍ.፪፥፱። ይህችን የሚበላበት (የሚያስፈልገው)ጊዜ ገና አልደረሰምና፤ በወቅቱ ብላም አትብላም አልተባለም፤

**ለመብላት የሚስማማ ለማየትም ደስ የሚያሰኝ ዛፍ** ።*‹‹ እግዚአብሔር አምላክም ለማየት ደስ የሚያሰኘውን፥ ለመብላትም መልካም የሆነውን ዛፍ ሁሉ ከምድር አበቀለ።››* ዘፍ.፪፥፱ እነዚህ በገነት የሞሉ ናቸው፤ ተቀጥፈው ሲበሉ ወዲያው ይተካሉ። ለሰውነት ተስማሚ፣ ሲበሉ ደስ የሚያሰኙና ሲታዩም የሚያምሩ ናቸው። ልጆች አዳም*ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ* የተባለው ከላይ በቁጥር ሁለት ያየናቸውን ዛፎች በሙሉ ነው።

www.zeorthodox.org

**የበለስ ዛፍ።** ይህች ዛፍ አንዲት ናት ‹‹ *መልካምንና ክፉን የሚያስታውቀው.. ዛፍ››* ዘፍ.፪፥፱ ትባላለች።

*ሐ.‹‹ መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና ››* ዘፍ.፪፥፲፮-፲፯

ይህችን ዛፍ አለመብላት መልካም ያሳውቃል። ልጆች ለምሳሌ መውደቅ ለስብራት፣ ለመፈንከት፣ ለሕመም ያጋልጣል። አለመውደቅ ደግሞ በተቃራኒው ለስብራትም ሆነ ለሕመም አያጋልጥም። ክፉና ደግን ከምታስታውቀው ዛፍ መብላት ለሞት ይዳርጋልና ‹‹አትብላ›› አለው።

የመጀመሪያዋን ትእዛዝ የሰጠው አምላካችን ነው፡፡ ሁሉንም ሰጥቶ አንዲት ፍሬ ብቻ ከለከላቸው፤ ይህንንም ያደረገው

ለአምላካችን ለእርሱ መታዘዝን ሊያስተምራቸው፤

የሚጎዳንን በመተው በጎውን መምረጥን ሊያሳያቸው ፤

የእርሱን አምላክነት የእነርሱን ፍጡርነት ሊያሳውቃቸውም ነበር፡፡

**ለሰባት ዓመታት ታዘዙ፡-** አዳም እና ሔዋን በገነት ጌቶች ሆነው፣ ለእግዚአብሔርም እየታዘዙ፣ አትብሉ የተባሉትን ሳይበሉ፣ የተፈቀደላቸውን እየተመገቡ ለሰባት ዓመታት ኖሩ፡፡

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ፈጥሮን የሚያስፈልገንን አዘጋጀልን፣ በለጋስነቱም በጎውን ሁሉ ሰጠን፡፡ ብሉ፣ ግዙ አለን፡፡ እንድንበዛም ባረከን፡፡

የሚጎዳንን ማለትም የሚገድለንን አትብሉ አለን፡፡ ባይጎዳን ሌሎችን እንደፈቀደ ይፈቅድልን ነበር፡፡

የእርሱን አምላክነት እና ጌትነት የሚያሳውቀውን ትእዛዝ ***አትብሉ*** ሲል ሰጣቸው፡፡ በዚህ ትእዛዝ ውስጥ፤ የእርሱን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተቀብሎና አክብሮ መከተልና በሕይወት መኖር ወይም ትእዛዙን አለመስማት፤አለማክበርና መሞት ነበሩበት፡፡

የሠራን እርሱ እግዚአብሔር የመምረጥ ነጻነታችንንም ሰጥቶን ጠብቆልናል፡፡

## ተግባር

**እግዚአብሔር የባረከልንን እና የሰጠንን እንጠቀም፡፡** ልጆች ቤተሰቦቻችሁ ፣ ትምህርት ቤታችሁ ፣ አእምሮአችሁና የምትበሉት የምትጠጡትም፤ ከእግዚአብሔር የተሰጣችሁ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያንን፣ መጽሐፍ ቅዱስን ሰጥቶናል፤ ቅዱስ ቁርባንንም ብሉ ብሎናል፡፡

**የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ብንጠብቅ ሁሉም ለእኛ የተሠራ ነው፡፡** በመሆኑም ነገ ትልቅ ቦታ ለመድረስና የደስታ ሥፍራ የሆነችውን ገነት ለመውረስ ለእግዚአብሔርና ለቤተሰቦቻችሁ የምትታዘዙ ሰዎችን አክባሪ ልጆች ሁኑ፡፡

www.zeorthodox.org

### *የክለሳ ጥያቄ*

1. እግዚአብሔር ሁሉንም ፈቅዶ አንድ ፍሬ ብቻ--------- አለ፡፡
2. እግዚአብሔር ለምን አትብሉ አለ ?
3. በገነት ስንት ዓይነት ዛፎች ነበሩ ? አዳምና ሔዋን ስንት ዓመት በገነት ኖሩ ?

# እግዚአብሔር ኖኅንና ቤተሰቡን በመርከብ አዳነ

## ስምንተኛ ሳምንት

ዓላማ፡- እግዚአብሔር ኖኅን በዓለም ከደረሰው ጥፋት ያዳነበትን መንገድ ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

ምንባብ ፡- ዘፍጥረት.፮÷፩ እስከ ፍጻሜ፡፡

### መግቢያ፡-

ልጆች ኖኅን ታውቁታላችሁ? ከአዳም ዐሥረኛው ትውልድ ነው፡፡ ኖኅ እግዚአብሔርን የሚወድና ትእዛዙን የሚያከብር መልካም ሰው ነበር፡፡ ምድር በውኃ ስትጠፋ አስቀድሞ እግዚአብሔር ለእርሱና ቤተሰቦቹ መርከብ እንዲሠራ አደረገው፡፡ በመርከብ ሆነው በእግዚአብሔር ፈቃድና ቸርነት ከጥፋት ውኃ ተረፉ፡፡

- ልጆች መርከብ አይታችሁ ታዉቃላችሁ? ለምን ይጠቅማል?
- በዛሬው ትምህርታችን ኖኅ ከጥፋት ውኃ እንዴት እንደዳነ እንማራለን፡፡

### የትምህርቱ ይዘት

ኖኅ የተባለ እግዚአብሔርን የሚወድና ትእዛዙን የሚጠብቅ ጻድቅ ሰው ነበር፡፡ ሴም ፣ ካም እና ያፌት የተባሉ ሦስት ልጆችም ነበሩት፤ የሚከባበሩና እግዚአብሔርን የሚፈሩ መልካም ቤተሰቦች ነበሩ፡፡ በዚያው ዘመን እግዚአብሔር ቃሉን በማይሰሙት እና ትእዛዙን በማያከብሩ ክፉ በሚሠሩት ብዙ ሰዎች አዝኖ ነበር፡፡ እነዚህ ሕዝቦች ብዙ መጥፎ ነገሮችን ያደርጉ ነበርና እግዘአብሔር በኖኅ በኩል አስመክራቸው፤ ነገር ግን አልሰሙትም፤ በመጨረሻም በውኃ ሊያጠፋቸው ወሰነ፡፡

www.zeorthodox.org

ኖኅ ግን ጻድቅ ስለነበር፣ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ አገኘ፡፡ እግዚአብሔርም እርሱንና ቤተሰቡን እንዲሁም ከእንስሳት ሁሉ ለዘር በማስቀረት ሊያድን ፈቀደ፡፡ ልጆች አባታችን እግዚአብሔር ፍጥረቱን ስለሚወድ በኃጢአት የበደለው ዓለም በሙሉ ጠፍቶ እንዲቀር አልፈለገምና ኖኅ መርከብ እንዲሠራ አዘዘው፡፡

መርከብዋ ከጎፈር እንጨት እንድትሠራ፣ በቅጥራንም እንድትለቀለቅ፣ ሦስት ደረጃ (ፎቅ)፣ መስኮቶች እና በር እንዲኖርዋትም እግዚአብሔር ለኖኅ ነገረው፤ የመርከቢቱን ርዝመት ሦስት መቶ ክንድ (135 ሜትር)፣ ጎንዋን ሃምሣ ክንድ (23 ሜትር)፣ ቁመትዋንም ሠላሳ ክንድ (14 ሜትር)

እንዲያደርገውም ለኖኅ ተነገረው፡፡ ኖኅም እንደታዘዘው አድርጎ መርከብ ሠራ፡፡ ኖኅ ለእግዚአብሔር እየታዘዘ መርከብ ሲሠራ ሕዝቡ ግን በኖኅ ላይ ይቀልዱ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ንስሐ በመግባት ወደ መልካምነት እንዲመለሱ ቢያስተምራቸውም አልሰሙም፡፡

ኖኅ መርከቡን ሠርቶ ፈጸመ፡፡ ከዚያም ቤተሰቡን፣ ከንጹሕ እንሰሳት አምስት ንጹሕ ካላሆኑትም ሁለት ሁለት ወንድና ሴት አድርጎ በሰባት ቀን ወደ መርከቡ እንዲያስገባ እግዚአብሔር አዘዘው፡፡ ልጆች ንጹሕ የሚባሉት ለመሥዋዕት የሚቀርቡና የሚበሉ ሲሆኑ ንጹሕ ያልሆኑ የማይበሉ ናቸው፡፡ ኖኅም የታዘዘውን ፈጽሞ ወደ መርከብዋ ገባ፡፡ እግዚአብሔርም መርከብዋን ከኋላው ዘጋበት፡፡

ከዚያም የሰማይ መስኮቶች ተከፈቱ የምድርም መሠረቶች ተነደሉ (ተከፈቱ)፡፡ ከባድ ዝናብ ከሰማይ ከመሬትም ታላቅ ጐርፍ ሆነ፡፡ በኖኅ ሲስቁ የነበሩትና እግዚአብሔር አንድ መቶ ሃያ ዓመት ሰጥቶ የጠበቃቸው ሕዝቦች ከጥፋት ውኃው ለማምለጥ ወደኖኅ መርከብ ለመግባት ሞከሩ፡፡ ነገር ግን በጣም የዘገየ ውሳኔ ነበር፡፡ ምክንያቱም የኖኅ መርከብ በሰው ሳይሆን በእግዚአብሔር ተዘግታ ነበር፡፡ አርባ ቀንና ሌሊት ዘነበ፣ በምድር ላይ ያሉ ታላላቅ ተራሮች ሁሉ በውኃ ተሸፈኑ፡፡ መርከብዋም በውኃ ላይ ተንሳፈፈች፡፡ በምድር የነበረው ተንቀሳቃሽ ሁሉ ጠፋ፡፡ ኖኅ ቤተሰቡ እና በመርከብ የነበሩት እንሰሳት ብቻ በመርከቧ ውስጥ ሆነው ዳኑ፡፡

ከአንድ መቶ ሃምሳ ቀናት በኋላ ውኃው መጉደል ጀመረ፡፡ ኖኅ በጠቅላላው በመርከብ ላይ ለአንድ ዓመት ቆይቶ ከመርከብ ወጣ፡፡ አብረውት የነበሩት ቤተሰቦቹና እንስሳትም ወጡ፡፡ በግፍ እና በክፉ ሥራ ተሞልታ የነበረችው ምድርም ጸዳች፡፡ በግፉ ያልተባበረው ብቸኛ ሰው ኖኅ እና ቤተሰቦቹም ስምንት ነፍሳት ሆነው፣ በጸዳችው ምድር እንደገና መኖር ጀመሩ፡፡

**ማጠቃለያ፡-** እግዚአብሔር በብዙ መንገድ ያድነናል፡፡ ከእነዚህም ኖኅንና ቤተሰቡን ያዳነበት መርከብ አንድዋ ናት፡፡ ዛሬም በቤተ ክርስቲያን በመኖርና በማደግ በዓለም ከሚመጣው ጥፋት እንድናለን፡፡

**ተግባር፡-** የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፡፡ ታዘዙም እርሱ ከጥፋት የምንድንበትን ያዘጋጅልናል፡፡

***የክለሳ ጥያቄ***

www.zeorthodox.org

1. በኖኅ ዘመን የነበሩት ሰዎች ምን አደረጉ ?
2. እግዚአብሔር ኖኅንና ቤተሰቡን እንዴት አዳነ ?
3. ከእንስሳት እየመረጠ ወደ መርከብ እንዲያገባ የታዘዘው ለምን ነበር ?
4. መርከብዋ ከተዘጋች በኋላ ምን ሆነ ?

***መዝሙር***

እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው(2)
የሚያስደነግጠኝ የሚያስፈራኝ ማነው? አምላኬ መመኪያዬ ነው፡፡

# ተወዳጁ የኖኅ መሥዋዕት

## ዘጠነኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች፤ በእግዚአብሔር ፊት የተወደደ ጸሎትና መሥዋዕት ስለሚያስገኘው መልካም መልስ ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *‹‹ እግዚአብሔርም መልካሙን መዓዛ አሸተተ ››* ዘፍ.፰፥፳፩

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ዘፍጥ.፰፥፩-ፍጻሜ

**መግቢያ፡-** ልጆች ከዚህ በፊት የተማራችሁትን ታስታውሳላችሁ? ኖኅና ቤተሰቡ ከታላቁ የጥፋት ውኃ እንዴት እንደዳኑ ተምረናል፡፡ ለሚከተሉት የክለሳ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1. እግዚአብሔር በታላቁ የጥፋት ውኃ ምድርን ለማጥፋት ለምን ወሰነ?
2. ኖኅ ከሌሎቹ ሰዎች ተለይቶ ለምን ተረፈ?
3. ኖኅ ራሱንና ዓለምን ለማትረፍ የቻለው ምን ሠርቶ ነው?
4. የኖኅን መርከብ መጠን ታስታውሳላችሁ?
5. ኖኅ ከእንስሳት ምን እና ስንት አስገባ?
6. ንጹሕ እንስሳት እና ንጹሕ ያልሆኑ እንሳሳት ሲባል ልዩነቱ ምንድነው ?

በዛሬው ትምህርታችንም ኖኅ ስላቀረበውና በእግዚአብሔር ፊት ስለተወደደለት ንጹሕ መሥዋዕት እንማራለን፡፡ ልጆች ለጸሎት ስትቆሙ፣ ቤተ ክርስቲያን ስትሄዱም ታጥባችሁ ንጽሕናችሁን በመጠበቅ መሆን አለበት፡፡ እግዚአብሔር ንጹሕ ነውና ንጽሕናን ይወዳል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

www.zeorthodox.org

በምድር ላይ የጥፋት ውኃ በተጀመረ በዓመት ከዐሥር ቀናት በኋላ ምድር ደረቀች፡፡ ኖኅና ቤተሰቡ የምድር እንስሳትም ሁሉ ከመርከብ ወጡ፣ እግዚአብሔርም ኖኅን ***‹‹አንተ ሚስትህንና ልጆችህን የልጆችህንም ሚስቶች ይዘህ ከመርከብ ውጣ፡፡አንተ ጋር ያሉትን አራዊት ሁሉ፥ ሥጋ ያላቸውን ሁሉ፥ ወፎችንና እንስሶችን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ከአንተ ጋር አውጣቸው በምድር ላይ ይርመስመሱ፥ ይዋለዱ፥ በምድርም ላይ ይብዙ፡፡››*** ዘፍ.፰፥፲፮-፲፯

እግዚአብሔር ለሚታገሡት ቸር ነው፡፡ እንደ እውነተኛ ፈራጅነቱ ታጋሽም ነውና ፈጽሞ አያጠፋንም፡፡ መሐሪና ሰውን ወዳጅም ነው፡፡ የተበላሸችውን ምድር በጥበቡና በቅጣትም ካጸዳ በኋላ ኑሮና መዋለድ እንዲቀጥል አዘዘ፡፡

ኖኅም ለእግዚአብሔር *መሠዊያን ሠራ*። ከንጹሕ እንስሳት እና ከንጹሕ *አዕዋፍ* ወሰደ። ለእግዚአብሔርም *መሥዋዕት* አቀረበ። ልጆች *መሥዋዕት* ለእግዚአብሔር ሲቀርብ፦

ለእርሱ በተዘጋጀ *መሠዊያ* ላይ ብቻ ነው። የሚቀርበውም *መሥዋዕት* ንጹሕ *መሆን* አለበት። ኖኅ ለእግዚአብሔር ብሎ *ያቀረበውን* ንጹሕ *መሥዋዕት* እግዚአብሔር ተቀበለለት፦ ***« እግዚአብሔርም መልካሙን መዓዛ አሸተተ»***

***«እግዚአብሔርም በልቡ አለ፦ ምድርን ዳግመኛ ስለ ሰው አልረግምም፥ ... ደግሞም ከዚህ ቀድሞ እንዳደረግሁት ሕያዋንን ሁሉ እንደ ገና አልመታም»*** ሲል ቃል ኪዳን ገባላቸው። ዳግመኛም ***በምድር ዘመን ሁሉ መዝራትና ማጨድ፥ ብርድና ሙቀት፥ በጋና ክረምት፥ ቀንና ሌሊት አያቋርጡም።*** አለ - ልዑል እግዚአብሔር።

ከዚያም እግዚአብሔር ኖኅንና ልጆቹን ባረካቸው፣ አዳምንና ሔዋንን ብዙ እንዳላቸው እነርሱንም ተባዙ አለ። *መብልና መጠጥን* ሁሉ የምድርንም ፍሬ ሰጣቸው። *ነገር* ግን ሰው ሰዉን እንዳይገድል አዘዘ።

*ዳግመኛም* ምድርን በንፍር ውኃ *እንደማያጠፋት ቃል* ኪዳን ገባለት፤ የ*ቃል* ኪዳንኑንም ምልክት በቀስተ ደመና ሰጠው። ለዚህም ነው ከዝናብ በኋላ ቀስተ ደመና የምናየው።

***« ቀስቲቱም በደመና ትሆናለች በእኔና በምድር ላይ በሚኖር ሥጋ ባለው በሕያው ነፍስ ሁሉ መካከል ያለውን የዘላለም ቃል ኪዳን ለማሰብ አያታለሁ።እግዚአብሔርም ኖኅን፦ በእኔና በምድር ላይ በሚኖር ሥጋ ባለው ሁሉ መካከል ያቆምሁት የቃል ኪዳን ምልክት ይህ ነው አለው»*** ዘፍ.፱፥፲፮-፲፯

## ማጠቃለያ

፩. ኖኅ ከጥፋት ውኃ በኋላ ለእግዚአብሔር *መሥዋዕት* አቀረበ፤ እግዚአብሔርም ተቀበለው።

፪. በምድር ፍጥረታት እንዲባዙ፣ ወቅቶች እንዲፈራረቁ እግዚአብሔር *ዳግመኛ* አዘዘ።

፫. የ*ቃል* ኪዳኑንም ምልክት በቀስተ ደመና አድርጎ *ዳግመኛ* ምድርን *እንደማያጠፋት ቃል* ገባለት።

www.zoorthodox.org

## ተግባር

ልጆች በንጽሕና ለእግዚአብሔር የምናቀርበው *መሥዋዕት* እንዲህ ዓይነት *መልካም መልስ* ያስገኛል። እናንም ስትጸልዩ በንጽሕና ይሁን።

***የክለሳ ጥቂዎች***

፩. ኖኅ ከመርከብ ሲወጣ ምን አደረገ ?

፪. ኖኅ መሥዋዕት ለማቅረብ ያዘጋጀው ምንድነው?

፫. እግዚአብሔር ምን መልስ ሰጠው ?

፬. ምድር ዳግመኛ በውኃ እንደማትጠፋ የተሰጠው ምልክት ምን ነበር ?

**መዝሙር**

እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው(2)

የሚያስደነግጠኝ የሚያስፈራኝ ማነው?

አምላኬ መመኪያዬ ነው።

www.zeorthodox.org

# በባሕር የተጣለው ሙሴ ባሕር አሻገረ

## ዐሥረኛ ሳምንት

**ዓላማ** ፦ ሙሴ እስራኤልን ከግብጽ ለማውጣት እንዴት እንደመራቸው ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**ምንባባት**፦ ዘጸ.፫፥፳፣፲፫ እና ፲፬፣

**መግቢያ፡-** በዛሬው ትምህርታችን ሙሴ በፈርዖን ቤት የነበረውን የክብር ኑሮ በመተው እስራኤልን ነፃ ለማውጣት በእግዚአብሔር መመረጡን እንማራለን፡፡

### *የመግቢያ ጥያቄዎች*

፩. ሙሴ የት አደገ?

፪. በፈርዖን ቤት መኖሩን እንዴት አቆመ?

## ትምህርት

ሙሴ እስራኤልን ከግብጽ ባርነት ወደ ተስፋይቱ ምድር ያወጣ ነው፡፡ የተወለደው ከእስራኤል የሚወለድ ወንድ ሁሉ እንዲሞት አዋጅ በተነገረበት ወቅት ነበር፡፡ እናቱ ግን እንደተወለደ ለሦስት ወራት ከደበቀችው በኋላ በሳጥን አድርጋ በወንዝ ዳር አስቀመጠችው፡፡ ወደወንዙ የሔደችው የፈርዖን ልጅ አግኝታው ወሰደችው፤ እንደ ልጇ አድርጋም አሳደገችው፡፡ እናቱ እንደሞግዚት ሆና ታሳድገውና ታስተምረው ስለነበረም ዕብራዊ መሆኑን አወቀ፡፡

ሕዝቡ በባርነት እንዴት እንደሚሠቃዩ ያይ ነበር፡፡ አንድ ቀንም አንድ ዕብራዊ እና ግብጻዊ ሲጣሉ አይቶ ዕብራዊውን እየደበደበ በግፍ ያሰቃየው የነበረውን ግብጻዊውን ገደለው፡፡ ይህ ዜና በግብጽ ተሠማ፤ ስለዚህም ሙሴ ከፈርዖን ቤት ሸሽቶ ምድያም በተባለች ምድር መኖር ጀመረ፡፡ በዚያም የዮቶርን ልጅ አግብቶ ሁለት ልጆች ወለደ፡፡

www.zeorthodox.org

የአማቹ የዮቶርን ከብቶች ሲያግድ ነበር በኮሬብ (የእግዚአብሔር ተራራ) በሚባለው ቦታ በቁጥቋጦው መሐል በሚነድ እሳት እግዚአብሔር የተገለጠለት፡፡ ሙሴ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የነበረውን ሕይወት ቀጥሎ እንማራለን፡፡ ይህም እግዚአብሔር ከተገለጠለት በኋላ ማለት ነው፡፡

ሙሴ ያደገው የፈርዖን የልጅ ልጅ ተብሎ በቤተ መንግሥት ነበር፡፡ እያደገም በእስራኤላውያን ላይ የሚፈጸመውን በደል እያየ በጣም ያዝን ነበር፡፡ ልጆች ሙሴ ያዘነው ለምን እንደሆነ

ታውቃላችሁ? ግብጻውያን እስራኤላውያንን ባሮች አድርገዋቸው በግፍ ያሰቃዩዋቸው ስለነበር ነው፡፡ ከዚያም አንድ ግብጻዊ ሌላ እስራኤላዊውን እያሰቃየ ሲደበድበው አይቶ እስራኤላዊውን ለማዳን ሲል የሠራው ሥራ ስለታወቀበት ሙሴ ከፈርዖን ቤት ከግብጽ ሸሽቶ ወደ ምድያም ምድር ሄደ፡፡

በዚያም ሚስት አግብቶ በአማቹ ቤት ከብት እየጠበቀ በእረኝነት ኖረ፡፡ አንድ ቀን ሙሴ ፡፡ *‹‹ቁጥቋጦው በእሳት ሲነድድ ቁጥቋጦውም ሳይቃጠል አየ፡፡››* በዚህ የተደነቀው ሙሴ ይሄን ለመመርመር ወደ ተራራው ሄደ፡፡ ወደ እሳቱ ሲቀርብ፤ *‹‹ ሙሴ ሙሴ የቆምክባት ምድር የተቀደሰች ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ፡... እኔ እግዚአብሔር ነኝ የአባቶችህ አምላክ ፤ የአብርሃም አምላክ ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቆብም አምላክ ነኝ››* የሚል ድምፅ በቁጥቋጦው መሐል ከሚነደው እሳት ውስጥ ሰማ፡፡

ልጆች፤ ወደ ቤተ ክርስቲያን ስትግቡ ጫማችሁን ታወልቃላችሁ? ለምን እንደሆነ አስረዱ፡፡

እግዚአብሔር የሕዝቡን ለቅሶ እንደሰማ ለሙሴ ነገረው፣ እስራኤልንም ነጻ ለማውጣት ላከው፡፡ ከእርሱ ጋር እንደሚሆንም ነገረው፡፡ ሙሴም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተቀብሎ ወደ ፈርዖን ሄደና፤ *‹‹የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሕዝቤን ልቀቅ ይልሃል፡፡››* አለው፡፡

ፈርዖን ግን እስራኤላውያንን ለቆ በነጻነት እንዲሄዱ አልፈለገም፡፡ እግዚአብሔርም ብዙ ቅጣቶችን በፈርዖንና በግብጻውያን ላይ አወረደ፡፡ ታላቅ ተአምራትም አሳያቸው፡፡ የፈርዖንን ልጅ ጨምሮ የግብጻውያን የመጀመሪያ ልጆች /በኩር ልጅ/ ሞቱ፡፡ ፈርዖን በመጨረሻ ሕዝቡ ነጻ እንዲወጡ ፈቀደ፡፡

እስራኤላውያንም በግብጽ የነበራቸውን ንብረት ሁሉ ሰብስበው እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው ወደማለላቸው ምድር ለመሔድ ጉዞ ጀመሩ፡፡ ቀይ ባሕር ሲደርሱ ግን ፈርዖን ሐሳቡን ቀየረ፡፡ እስራኤላውያንን እንዲመልሱ ሠራዊቱን በሙሉ ላከ፡፡ ሕዝበ እስራኤል ከኋላቸው የሚያሳድዷቸውን የፈርዖንን ሠራዊት፣ ከፊት ቀይ ባሕርን ሲያዩ መሄጃ ስላልነበራቸው በሙሴ ላይ ጮኹበት፡፡

ሙሴም ሕዝቡን *‹‹የእግዚአብሔርን ማዳን እዩ››* አላቸው፡፡ ባሕሩንም በበትር መታው፡፡ ልጆች ሙሴ ባሕሩን በበትሩ ሲመታው ምን እንደሆነ ገምቱ? ባሕሩ ወዲያውኑ ለሁለት ተከፈለና እንደ ግርግዳ ቆመ፡፡ የሚያልፉበት ደረቅ መሬትም ተገለጠ፡፡ ሕዝበ እስራኤል በደረቅ መሬት ተሻግረው ሲያበቁ፤ የፈርዖን ሠራዊትም ተከትሏቸው ገብቶ ከባሕሩ መሐል ደረሰ፡፡ ሕዝበ እስራኤል ከተሻገሩ በኋላ ሙሴ ዳግመኛ ባሕሩን ሲመታው ለሁለት የተከፈለው ውኃ በደረቀው መሬት ላይ ፈሰሰ፡፡ የፈርዖን ሠራዊት ከፈረሶቻቸውና ሠረገሎቹ ጋር በቀይ ባሕር ሰጠሙ፡፡ እስራኤልም እግዚአብሔርን በመዝሙር አመሰገኑ፡፡ ‹‹*በክብር ከፍ ከፍ ብሎአልና ለእግዚአብሔር እዘምራለሁ፤* ››

| **መዝሙር** | **ትርጉም** |
|---|---|
| ንሴብሖ (2) ለእግዚአብሔር | እናመስግነው (2) እግዚአብሔርን |
| ስቡሓ ዘተሰብሐ | ምስጉን ነው የተመሰገነ |

www.zeorthodox.org

# አብርሃም በጌራራ

## ዐሥራ አንደኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች፤ስሕተትን ቶሎ ማረምን ከአቤሜሌክ፤ በጥበብ መመላለስን ከአብርሃም ታሪክ ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***‹‹እኔም ደግሞ በፊቴ ኃጢአትን እንዳትሠራ ከለከልሁህ ስለዚህም….. አልተውሁም፡፡ ››*** ዘፍጥ.፳፥፮

**ተጨማሪ ምንባብ፡-**ዘፍጥ.፳፥፩-፲፰

**መግቢያ፡-** አባታችን አብርሃም እግዚአብሔርን የሚፈራና የሚከተል ደግ ሰው ነበር፡፡ በሚያርፍበት ቦታ ሁሉ ድንኳኑን እየተከለና እየነቀለ ሲጓዝ ኖረ፡፡ በዚህ ጉዞውም ጌራራ በምትባል ምድር ተቀመጠ፡፡ በዛሬው ትምህርታችን አብርሃም በጌራራ ያጋጠመውን እንማራለን፡፡

**የሳምንቱ ትምህርት፡-** ሰዶምና ገሞራ ከጠፉ በኂላ አብርሃም ወደ አዜብ ምድር ሄደ፡፡ በዚያም ወደ ጌራራ ምድር በእንግድነት ተቀመጠ፡፡ ጌራራ ንጉሥ ነበራት፡፡ የአገሩ ሰዎች ለሚስቱ ሲሉ እንዳይገድሉት አብርሃም ፈራ፡፡ ሚስቱ ሳራንም እኅቴ ናት አለ፡፡ የጌራራ ንጉሥ አቤሜሌክ ይባላል፤ እርሱም ወደ ሳራ መልእክተኞች ልኮ ወሰዳት፡፡

በሌሊት በሕልሙ እግዚአብሔር ለአቤሜሌክ ተገልጾ እንዲህ አለው፦ ‹‹***እነሆ፥ አንተ ስለ ወሰድሃት ሴት ምውት ነህ እርስዋ ባለ ባል ናትና ፡፡*** ዘፍጥ.፳፥፫ አቤሜሌክም ‹‹ ***እኅቴ ናት ያለኝ እርሱ አይደለምን ? እርስዋም ደግሞ ራስዋ፦ ወንድሜ ነው አለች በልቤ ቅንነትና በእጄ ንጹሕነት ይህንን አደረግሁ፡፡..››*** አለው፡፡ እግዚአብሔርም በሕልም አለው፦ ***‹‹ይህን በልብህ ቅንነት እንዳደረግህ እኔ አወቅሁ፥ እኔም ደግሞ በፊቴ ኃጢአትን እንዳትሠራ ከለከልሁህ ስለዚህም ትነካት ዘንድ አልተውሁም፡፡ ››***

www.zeorthodox.org

‹‹አሁንም የሰውን ሚስት መልስ፤ ነቢይ ነውና ስለ አንተ ይጸልያል፡፡ አንተም ትድናለህ ብትመልስም አንተና የአንተ የሆኑት ሁሉ ይሞታሉ›› አለው፡፡ ንጉሡም ለባርያዎቹ ነገራቸው፡፡ በእግዚአብሔር እጅ መውደቅ ያስፋራል፡፡ እናም ሁሉም ፈሩ፡፡ አብርሃምንም አስጠራው፡፡ እርሱም ሄደ፡፡ ንጉሡም ይህን ሁሉ ኃጢአት በመንግሥቴና በሕዝቤ ላይ ያመጣህብን ምን አደረግንህ ለምን እኅቴ ናት አልከኝ አለው፡፡ አባታችን አብርሃምም ሦስት ምክንያቶችን ነገረው፡-

1. በአገሩ እግዚአብሔርን መፍራት እንደሌለ ዐይቶ እንዳይገድሉት ለመጠንቀቅ ይህን ማድረጉን፡፡
2. በእናትዋ አትወለድ እንጂ በአባትዋ ሳራ እኅቱ እንደሆነች ለሚስትነት እንደታጨችለት፡፡
3. ከአባቱ ቤት ሲወጣ ጀምሮ እኅቱ ነኝ እንድትል ቃል መገባባታቸውን የዚህ ምክንያቱም ሳራ መልከ መልካም ሴት በመሆንዋ ለጥንቃቄ ብለው ቃል እንደተገባቡ አስረዳው፡፡

አቤሜሌክም ለአብርሃም እና ለሳራ ስጦታ በመስጠት አሰናበታቸው፡፡ አብርሃምም ጸለየ፤ በአቤሜሌክ ቤት የነበረው መቅሰፍት ቆመ፡፡

## ማጠቃለያ

1. የእኛ ያልሆነውን ሁሉ መንካት የለብንም፡፡ ይህን ካደረግን በራሳችን ላይ ፈተና እናመጣለን፡፡
2. ነቢያት እና ሌሎችም ቅዱሳን ሲጸልዩልን ከብዙ መከራ እንድናለን፡፡ ምልጃ ማለትም ይሄው ነው፡፡
3. እግዚአብሔር ሲመክረን እንደ አቤሜሌክ ወዲያው መመለስ አለብን፡፡
4. አደጋ ፊታችሁ ሲጋረድ እንዳትጎዱና ሕይወታችሁን እንዳታጡ እንደ አብርሃም እውነተኛና ዘዴኛ ሁኑ፡፡

## ተግባር

የእግዚአብሔርን ቃል አንብቡ፣ አቤሜሌክ ከስሕተት የተመለሰው የእግዚአብሔርን ቃል በመስማቱ እንደ ነበር ተገንዝባችሁ ከስህተቶቻችሁ ተመለሱ፡፡

www.zeorthodox.org

# እጆቼን ወደ እግዚአብሔር አንሥቼአለሁ

## ዐሥራ ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች፤ መልካም የሆነውን ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር ማድረግን ከአብርሃም ታሪክ ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***‹‹ሰማይንና ምድርን ወደሚገዛ ወደ ልዑል እግዚአብሔር እጄን ከፍ አድርጌአለሁ፡፡ ››*** ዘፍጥ.፲፬፥፳፪

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ዘፍጥ.፲፬፥፩-፳፬

**መግቢያ፡-** ሎጥ የአብርሃም ወንድም የሐራን ልጅ ነው፡፡ አብርሃም በእግዚአብሔር ጥሪ የቤተሰቦቹን ሀገር ትቶ ሲወጣ፤ ተከትሎት ወጥቶአል፡፡ ከአብርሃም ጋር እንግዳ እየተቀበለ ኖረ፡፡ ከብቶቻቸው በዝተው መንጋውን የሚጠብቁት እረኞች ተጣሉ፡፡ ‹‹***አብርሃምም ወንድማማቾች ነን በእኔና በአንተ በእረኞቼና በእረኞችህ ጠብ እንዳይሆን እለምንሃለሁ***›› አለ፡፡ ሎጥ ሰዶም የተባለውን ምድር መረጠ፤ አብርሃም በተቃራኒው ባለው ሃገር ብቻውን መኖር ጀመረ - ሁለቱም በርቀት በፍቅር ሊኖሩ ተለያዩ፡፡ ከዓመታት በኂላ ሎጥ በነበረበት አካባቢ ጦርነት ተነሥቶ ሎጥ ተማረከ፡፡ አብርሃምም ይህንን ሰምቶ ሎጥን ለማዳን ሄደ፡፡ በዛሬው ትምህርታችን በዚህ ታሪክ ላይ ተመርኩዘን ለፍቅር ስለ መኖርና ስለ መትጋት፣ እንዲሁም በነገር ሁሉ ታማኝ ስለመሆንና እግዚአብሔርን ስለማክበር እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

### የሲዲም ጦርነት

www.zeorthodox.org

ሎጥ የመረጠው ምድር ሰዶምን ነበር፡፡ የሰዶም ንጉሥና ሌሎች በአካባቢው የነበሩ ነገሥታት ለኤላም ንጉሥ ለኮሎዶጎምር እየገበሩ ይኖሩ ነበር፡፡ ዐሥራ ሁለት ዓመታት እየገበሩ ኖሩ፡፡ ሎጥም ከሰዶም ሕዝብ ጋር አብሮ ለኮሎዶጎምር ይገብር ነበር፡፡ በዐሥራ ሦስተኛው ዓመት በአካባቢው የነበሩ፡- የሰዶም፣ የገሞራ፣ የአዳማ፣ የሰቦይም እና የዞዓር ነገሥታት ዓመጹ፡፡ በአንድነትም በኮሎዶጎምር ላይ ተነሱበት፡፡ ነገር ግን ከኤላም ንጉሥ ከኮሎዶጎምር ጋር ፡- የሰናዖር፣ የእላሳር እና የአሕዛብ ነገሥታት አብረውት ነበሩ፡፡ እነዚህ ለሁለት (አምስት እና አራት ሆነው) የተከፈሉት በዐሥራ አራተኛው ዓመት ጦርነት አደረጉ፡፡ በኮሎዶጎምር የሚመሩት ብዙ ቦታዎችን አሸንፈው ተቆጣጠሩ፡፡

በመጨረሻ በሲዲም ሸለቆ ከሰዶምና አብረውት ካሉት አራት ነገሥታት ጋር ተጋጠሙ። ልጆች ይህ ቦታ ትላልቅ ጉድጓዶች አሉበት፣ ጉድጎዶቹም ዝፍት የተባለ የሚያጣብቅ የነዳጅ ፈሳሽ ያለበት ነው። የሰዶምና የገሞራ ነገሥታት በዚህ ጉድጓድና በኮሎዶጎምር በሚመራው ሠራዊት መካከል ገቡ። እናም ብዙ ወታደር በጉድጓድ ሲገባባቸው ነገሥታቱ ሸሹ። አሸናፊዎቹም ወደ ከተማው ገብተው ያለውን ሁሉ ማርከው ወጡ። ከተማረኩት ቦታዎች አንድዋ ሰዶም ናት። በሰዶም ሎጥ ይኖራል። ሰዶምን የማረኩት የኮሎዶጎምር ነገሥታት ሎጥን ፣ ቤተሰቡን ፣ ከብቱንና ያለውን ሁሉ ማርከው ወሰዱ። ከአብርሃም ጋር በነጻነት የነበረው ሎጥ ተማርኮ በባርነት ተወሰደ። ***« የሰዶምንና የገሞራን ከብት ሁሉ መብላቸውንም ሁሉ ወስደው ሄዱ። በሰዶም ይኖር የነበረውን የአብራምን የወንድም ልጅ ሎጥን ደግሞ ከብቱንም ወስደው ሄዱ።»*** ዘፍ.፲፬፥፲፩-፲፪

## አብርሃም ሰምቶ ወንደሙን ለማዳን ወጣ

ከምርኮ አንድ ሰው ሸሽቶ አመለጠ። ይህ ሰው ከአብርሃም ጋር ቃል ኪዳን የነበራቸው ሰዎች ባሉበት የነበረ ነው። ለአብርሃም የወንድሙን የሎጥን መማረክ ነገረው። ***«አብራምም ወንድሙ እንደ ተማረከ በሰማ ጊዜ በቤቱ የተወለዱትን ሦስት መቶ አሥራ ስምንት (318) ብላቴኖቹን አሰለፈ፥ፍለጋቸውንም ተከትሎ እስከ ዳን ድረስ ሄደ።»*** ዘፍጥ.፲፬፥፲፬

## ድልና ለእግዚአብሔር የቀረበ ስጦታ

አብርሃም ከእርሱ ጋር የነበሩትን « ***ብላቴኖቹንም ከፍሎ*** » ለማስመለስ ተዘጋጀ።ከዚያም ***በሌሊት እርሱ ከባሪያዎቹ ጋር*** የኮሎዶጎምር ሠራዊት እና የተማረኩት ባሉበት ደረሰ፤ ሠራዊቱም ላይ ***«ወረደባቸው ፥ መታቸውም፥ ..... ሖባ*** እስከተባለ ሥፍራ ድረስም ***አሳደዳቸው።..»*** ጦሩን አሸንፎ ሲመለስ « ***ከብቱንም ሁሉ አስመለሰ፥ ደግሞም ወንድሙን ሎጥንና ከብቶቹን ሴቶችንና ሕዝቡን... መለሰ።»*** ዘፍ.፲፬፥፲፫-፲፯

ከድል መልስ የሸሸው የሰዶም ንጉሥ ሊቀበለው መጣ። የእግዚአብሔር ካህን፣ የጽድቅና የሠላም ንጉሥ የነበረው መልከጸዴቅ ኅብስትና ወይን ይዞ ወጣ፤ አብርሃምን ***ባረከው*** እንዲህም አለ፦« ***አብራም ለሰማይንና ምድርን ለሚገዛ ለልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ነው። ጠላቶችህን በእጅህ የጣለልህ ልዑል እግዚአብሔርም የተባረከ ነው አለውም። አብራምም ከሁሉ ዐሥራትን ሰጠው።»*** ዘፍጥ.፲፬፥፲፰-፳

ልጆች ዐሥራት? ኅብስትና ወይን ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ቅዱስ ቁርባን የምትቀበሉት እንዴት እንደሆነስ ታስተውላላችሁ? ለካህኑ የምትሰጡትስ ክብር ምን ድረስ ነው?

www.zeorthodox.org

*ዐሥራት ማለት ከዐሥር አንድ ማለት ሲሆን ይህም የእግዚአብሔር ገንዘብ ነው፡፡ ክርስቲያኖች እንደ አብርሃም ዐሥራታቸውን በካህኑ አማካይነት ለቤተ ክርስቲያን ይሰጣሉ፡፡*

ካህናት በቤተ ክርቲያን የሚያቆርቡን የጌታችን ሥጋና ደም በኅብስትና በወይን ነው፡፡ የእግዚአብሔር አገልጋይ ለሆኑ ካህናት መንፈሳዊ ክብር መስጠትን ከአብርሃም እንማራለን፡፡

የሰዶም ንጉሥ ባላ ከተሸሸገበት ወደ አብርሃም መጥቶ ፡-‹‹***ሰዎቹን ስጠኝ፥ ከብቱን ግን ለአንተ ውሰድ አለው፡፡››***

አብርሃምም ‹‹***ሰማይንና ምድርን ወደሚገዛ ወደ ልዑል እግዚአብሔር እጄን ከፍ አድርጌአለሁ፡፡ አንተ፡ አብራምን ባለጠጋ አደረግሁት እንዳትል፥ ብላቴናኖቹ ከበሉት በቀር ከእኔ ጋር ከሄዱትም ድርሻ በቀር፥ ፈትልም ቢሆን የጫማ ማዘቢያም ቢሆን፥ ለአንተ ከሆነው ሁሉ እንዳልወስድ አውናን ኤስኮልም መምሬም እነርሱ ድርሻቸውን ይውሰዱ››*** ዘፍ.፲፬፥፳፪-፳፬

## ማጠቃለያ

ሎጥ የመረጠው ቦታ በጦርነት ተሸፍኖ ምርኮን ቢያተርፍለትም፣ አብርሃም ወንድምነቱን አስቦ ሊያድነው ወጣ፣ እግዚአብሔርም ድል ሰጠው፡፡

አብርሃም ከድል መልስ ለእግዚአብሔር ዐሥራትንና ምስጋናን ለካህኑም ክብርን ሰጠ፡፡ በጦርነት ያገኘውን አልነካም፡፡ *ያገኘ የመሰለው ንጉሥ* ***ውሰድ*** ሲለው ***ወደ ልዑል እግዚአብሔር እጄን ከፍ አድርጌአለሁ፡፡*** በማለት ፍጹም እምነቱን ገለጠ፡፡

## ተግባር

በሁሉም ነገር እግዚአብሔርን አመስግኑ፡፡

www.zeorthodox.org

# ሎጥ

## ዐሥራ ሦስተኛ ሳምንት

ዓላማ ፡- ልጆች የሎጥን ታሪክ ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

የሚጠና ጥቅስ፡- *"ሁለቱም መላእክት በመሸ ጊዜ ወደ ሰዶም ገቡ ሎጥም በሰዶም በር ተቀምጦ ነበር ፡፡ ሎጥም ባያቸው ጊዜ ሊቀበላቸው ተነሣ ፊቱንም ደፍቶ ወደ ምድር ሰገደ "* ዘፍጥ.፲፱÷፩

ተጨማሪ ምንባብ፡- ዘፍጥ.፲፱÷፩-ፍጻሜ

**መግቢያ፡-** ሎጥ የአብርሃም ወንድም ልጅ ነው፡፡ እግዚአብሔር አብርሃምን የቤተሰቦቹን ሀገር ትቶ እርሱ ወደሚመራው ቦታ እንዲሄድ ሲጠራው ሎጥም አብርሃምን ተከትሎ አገሩን ትቶ ወጥቶአል፡፡ አብርሃም እና ሎጥ በሄዱበት ሀገር ከብቶቻቸው በዝተው እረኞቻቸው ሲጣሉ ተለያዩ፡፡ ሎጥ ለምለምና ለመኖር ምቹ ሆኖ የታየውን ሰዶም እና ገሞራን መረጠ፡፡ የሰዶም ሰዎች ግን በእግዚአብሔር ያመጹና ኃጢአተኞች ነበሩ፡፡

በዚህ ትምህርታችንም በሰዶም ሰዎች ላይ ከደረሰው ጥፋት ሎጥ ከቤተሰቡ ጋር እንደተረፈ እንማራለን፡፡

## የትምህርቱ ይዘት፡-

የሰዶምና የገሞራ ሰዎች በጣም ኃጢአተኞች ስለሆኑና ፈጣሪያቸዉ ላይ ስላመጹ ፣ እግዚአብሔር ከተማይቱን ሊያቃጥል ወሰነ፡፡ እግዚአብሔር ይሄንን ከማድረጉ በፊት ለወዳጁ ለአብርሃም አሳወቀው፡፡

አብርሃም ጥቂት በከተማይቱ አመጽ ያልተባበሩ ጻድቃን ቢኖሩ እነርሱን አስቦ ከተማይቱን እንዳያጠፋ እግዚአብሔርን ለመነ፡፡ እግዚአብሔርም አብርሃም የጠየቀውን እንደሚያደርግለት ቃል ገባለት፡፡ ነገር ግን በሁለቱ ከተሞች (ሰዶም እና ገሞራ) የተገኘዉ ጻድቅ ሎጥ ብቻ ነበር፡፡ አብርሃምም ወደ ቤቱ ተመለሰ፡፡

www.zeorthodox.org

ልዑል እግዚአብሔርም ሁለት መላእክትን ወደ ሰዶምና ገሞራ ሰደደ፡፡ መላእክቱ ሁለት ወጣት ሰዎችን ተመስለዉም ወደ ከተማይቱ ገቡ፡፡ ሎጥም ከአብርሃም ጋር ያደርግ እንደነበረው በከተማይቱ መግቢያ ተቀምጦ እንግዶችን ይቀበልና ያስተናግድ ነበር፡፡

ሰው መስለው የገቡትን ሁለቱን መላእክት ሎጥ ወደ ቤቱ እንዲገቡ ለመናቸው። መላእክቱም ብዙ ከለመናቸው በኋላ ወደ ሎጥ ቤት ገቡ። ከተሞችን ለማጥፋት የገቡት መላእክት የመጀመሪያ ሥራም ሎጥን ማዳን ሆነ። እግዚአብሔርም አብርሃምን አስቦ ብቸኛውን ጻድቅ ሎጥን በመላእክቱ አዳነው።

ነገር ግን የከተማው ሰዎች በሰው አምሳል የገቡትን ሁለቱን መላእክት አሳልፎ እንዲሰጣቸው ፈለጉ። ሎጥም አይሆንም ብሎ ተሙዋገተ። ወደ ቤቱ የመጡት ሰዎች ብዙ ስለነበሩ ገፍተውት ወደ ቤቱ ሊገቡ ሲሉ፣ መላእክቱ ሎጥን ወደ ቤት አስገብተው፣ ወደ ሎጥ ቤት በዓመጽ በክፋት የመጡትን ሰዎች ዐይናቸውን አሳወሩአቸው።

ሎጥንና ቤተሰቡንም ከተማይቱ ከመጥፋትዋ በፊት እንዲወጡና፣ ዘመድ ካላቸውም አብረው እንዲያወጡአቸው ነገሩት። ሎጥም ወደ አማቾቹ ሄደና ***ዉጡ ከተማይቱ ልትጠፋ ነው*** አላቸው። አማቾቹ ግን ሳቁበት። (ልጆች አማች ማለት የባል ወይም የሚስት ቤተሰብ ማለት ነው።) ሎጥ ግን አማቾቹን፣ ንብረቱንና ሌሎች ነገሮችን ሲሰበስብ ዘገየ።

መላእክትም የሎጥና የቤተሰቡን እጆች ይዘው ከከተማይቱ አወጡት። በከተማይ ዳርቻ አድርሰውት፤ ከሩቅ ወዳለችው ተራራ እንዲሸሽና ወደ ኋላ እንዳያይም አዘዙት። እስከዚያም ከተማይቱን እንደማያጠፉ ነገሩት። ሎጥም ተራራዉ ሩቅ ስለሆነ ፊት ለፊት ወዳለችዉ ዞዓር ወደ ተባለች ቦታ እስኪደርስ ከተማይቱን እንዳያጠፉዋት ለመነ። መላእክቱም የለመነውን አደረጉለት ዞዓርም አልጠፋችም።

ሎጥና ቤተ ሰቦቹ ከወጡ በኋላ መላእክቱ ከተማይቱን እሳት እና ዲን አዘነቡባት፣ ከተማይቱም በእሳት ጠፋች። ነገር ግን መላእክቱ ወደ ኋላ እንዳያዩ ለሎጥ ያዘዙትን ትእዛዝ የሎጥ ሚስት ተላለፈችና ወደ ኋላ ዞራ ዐየች፤ ወዲያውም የጨው ሐውልት ሆና ቀረች። ሎጥና ሁለቱ ልጆቹም ከጥፋት ተርፈው ዞዓር ገቡ።

## ማጠቃለያ

ሎጥ ከአብርሃም የተማረዉን መልካም ነገር ይዞ በመገኘቱ ከጥፋት አድኖታል። እኛም ከቤተሰቦቻችን እና ከቤተ ክርስቲያን የሚሰጠንን መልካም ነገር አክብረን በአግባቡ እንያዝ።

www.zeorthodox.org

የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንፈጽም፣ የሎጥ ሚስት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መተላለፍዋ ጎድቶአታል።

## ተግባር

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ።

መዝሙሩን አጥኑ።

## *የክለሳ ጥያቄዎች*

1. በሎጥና በአብርሃም የነበረው ዝምድና ምን ነበር ?
2. ሰዶምና ገሞራ እንደሚጠፉ ሲያውቅ አብርሃም እግዚአብሔርን የለመነው ምን ነበር ?
3. ሎጥና ቤተሰቡ በሰዶምና ገሞራ ከደረሰዉ ጥፋት የዳኑት ለምንድነው ?
4. ሰዶምና ገሞራን ለማጥፋት የተላኩት እነማን ናቸው ?
5. ሎጥ ከከተማው እንዲወጣ ያዘዘው ማነው ?
6. የሎጥ ሚስት ምን ሆነች ? ለምን ?
7. መላእክት ሎጥን ሲያድኑት ያዘዙት ምንድን ነው ?

## *መዝሙር*

እግዚአብሔር እረኛዬ ነው ይጠብቀኛል(2)
በዕረፍት ውኃ፣ በለምለም መስክ (2) እኔን ይመራኛል፡፡

www.zeorthodox.org

# ይስሐቅ

## ዐሥራ አራተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ልጆች የተስፋ ልጆች ሆኖ ስለማደግ ከይስሐቅ ታሪክ ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ ፡-** ***‹‹ቃል ኪዳኔን ግን በሚመጣው ዓመት በዚሁ ጊዜ ሣራ ከምትወልድልህ ከይስሐቅ ጋር አቆማለሁ፡፡››ዘፍ.17፡21***

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ዘፍጥ.፲፯÷፲፭-፳፩፤፲፰÷፱-፲፭፤ ፳፩÷፩-፯፤፳፪፤፳፬፤፳፭÷፲፱-፳፯፤፳፯÷፴፬፤ ፴፭÷፳፰-፳፱

***መግቢያ፡-*** ልጆች አብርሃም እና ሣራ ልጅ አልነበራቸውም፤ በመጨረሻም የሣራ የመውለጃ ዕድሜ ካለፈ በኋላ በእግዚአብሔር ቸርነት ይስሐቅ ተወለደ፡፡ በተስፋ፣ በእግዚአብሔር ብሥራትና በተአምር የተገኘው ይስሐቅ በመልካም ኑሮ እና በእምነት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘ አባት ነበር፡፡ በዛሬው ትምህርታችን የይስሐቅን ታሪክ እንማራለን፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት

ይስሐቅ - ይስቃል ማለት ነው፡፡ የአብርሃም እና የሣራ ልጅ የያዕቆብና የኤሳው አባት ነው፡፡ አብርሃምና ሣራ እግዚአብሔርን ፈርተው እና በእምነታቸው ጸንተው ሲኖሩ ልጅ አልነበራቸውም፡፡ እግዚአብሔር ‹‹***የምድር አሕዛብ በዘርህ ይባረካሉ***፤›› በማለተ ቃል የገባለት አብርሃም ልጅ ስላልነበረው ያዝን ነበር፡፡ ሣራም የመውለጃዋ ዕድሜ አለፈ፡፡

አብርሃም በሞቶ ዓመቱ ሣራም ዘጠኛ ዓመት ሲሆናት እግዚአብሔር ለአብርሃም ተገልጦ በቤቱ የሚወለዱት ሁሉ እንዲገረዙ ነገረው፡፡ አብራም እና ሦራ የሚሉት ስሞችም - የብዙዎች እናት እና አባት ስለሚሆኑ አብርሃም ***የብዙዎች አባት*** ሣራ ***የብዙዎች እናት*** እንዲባሉ እግዚአብሔር ስማቸውን ቀየረው፡፡ ከሣራ ልጅ እንደሚሰጠውም ቃል ገባለት፡፡‹‹ ***አብርሃምም በግምባሩ ወደቀ፥ ሳቀም፥ በልቡም አለ፡፡ የመቶ ዓመት ሰው በውኑ ልጅ ይወልዳልን? ዘጠና ዓመት የሆናትም ሣራ ትወልዳለችን?*** ›› አብርሃም በልቡ በተናገረው በመሳቁም እግዚአብሔር እንዲህ አለው፡- ‹‹***በእውነት ሚስትህ ሣራ ወንድ ልጅን ትወልድልሃለች፥ ስሙንም ይስሐቅ ብለህ ትጠራዋለህ፤ ከእርሱ በኋላ ለዘሩ የዘላለም ቃል ኪዳን እንዲሆን ቃል ኪዳኔን ከእርሱ ጋር አቆማለሁ፡፡***››

ልጅ የሚወልድበትን ጊዜ እና የይስሐቅን መመረጥ ***‹‹ቃል ኪዳኔን ግን በሚመጣው ዓመት በዚሁ ጊዜ ሣራ ከምትወልድልህ ከይስሐቅ ጋር አቆማለሁ፡፡››*** ሲል አረጋገጠለት፡፡ ዘፍ.፲፯÷፳፩

በሌላ ቀን በቀትር ጊዜ አብርሃም በቤቱ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በሦስት ሰው



www.zeorthodox.org

ተመስሎ ተገለጠለት። አብርሃምም ***አትለፈኝ*** ብሎ ወደ ቤቱ አስገባው። ከሚስቱ ከሣራ ጋር የሚበላና የሚጠጣ አቅርበው እግዚአብሔርን አስተናገዱ። ሣራም ከውስጥ ሆና የሚበላውን እያቀረበች ከአብርሃም ጋር የሚነጋገሩትን ትሰማ ነበር። እግዚአብሔር ‹‹ሣራ ወዴት ናት?›› አለ። አብርሃምም ‹‹በድንኳን ውስጥ›› አለ። እግዚአብሔርም ***‹‹የዛሬ ዓመት እንደ ዛሬው ጊዜ ወደ አንተ በእውነት እመለሳለሁ ሚስትህ ሣራም ልጅን ታገኛለች አለ። ሣራም በድንኳን ደጃፍ በስተ ኋላው ሳለች ይህንን ሰማች።›› *** እርስዋና ባልዋ በጣም ስላረጁና ስለደከሙ ‹‹እንዴት ይሆናል?›› ስትል *ሳቀች።* እግዚአብሔርም ሣራ ለምን ሳቀች ***‹‹በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን? የዛሬ ዓመት እንደ ዛሬው ጊዜ ወደ አንተ እመለሳለሁ ሣራም ልጅን ታገኛለች።››*** ብሎት ሄደ። ዘፍ.፲፰፥፱-፲፭ እግዚአብሔር በተናገረው ቀን ሣራ ወለደች። ስሙንም ይስሐቅ አሉት። ይስሐቅም አደገ። አንድ ቀን እግዚአብሔር አብርሃምን፤ ‹‹አንድ ልጅህን ሰዋልኝ›› አለው። አብርሃምም እንደታዘዘው ይስሐቅን ለመሠዋት ወሰደ፤ እግዚአብሔርም ልጁን እንዳይነካው ነገረው። በመታዘዙም እግዚአብሔር ባርከው። የመሥዋዕቱንም በግ ሰጠው አብርሃምም በይስሐቅ ፋንታ ለመሥዋዕት ከእግዚአብሔር የተሰጠውን በግ ሠዋው።

***‹‹መንገዴን ዛሬ በፊቴ አቅናልኝ››*** ዘፍ.፳፬፥፲፪

ይስሐቅ ለቤተሰቡም ታዛዥ ልጅ ነበር። አብርሃም እግዚአብሔር እንድሠዋህ አዞኛል ሲለው እንኳ ታዛዥ ነበር። አብርሃም ሲያረጅ፣ ከመሞቱ በፊት አገልጋዩን ጠራና ወደ አባቶቹ አገር ሄዶ ለልጁ ለይስሐቅ ሚስት እንዲያመጣለት አዘዘው።

የአብርሃም ሠራተኛም ለመንገዱ አስፈላጊውን አዘጋጅቶ፣ ጉዞውን ቀጠለ። የአብርሃም አገልጋይም ***‹‹የጌታዬ የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር ሆይ መንገዴን በፊትህ አቅና ለጌታዬ ለአብርሃምም ምሕረት አድርግለት እግዚአብሔር ትክክለኛዋንና የእርሱ ፈቃድ የሆነውን የይስሐቅ ሚስት እንዲሠጠውም ለመነው ።››*** ሲጸልይም ጉድጓድ አጠገቡ ነበር እና ጸሎቱን ከመጨረሱ በፊት ርብቃ የምትባል ሴት እንሥራ ይዛ ከጉድጓዱ ውኃ ልትቀዳ መጣች።

www.zeorthodox.org

እንሥራዋን ከሞላች በኋላ የአብርሃም አገልጋይ ወደእርሷ ቀረቦ ውኃ እንድታጠጣው ጠየቃት። ለእርሱ እና ለግመሎቹም እንዲወስድ ነገረችው። ለራሱና ለግመሉ ከጠጡ በኋላም በቤታቸው በቂ ማረፊያ ቦታ ስላለ እንዲያርፉ ነገረችው። የአብርሃም አገልጋይ በመልካምነትዋ ተደንቆ፣ የእግዚአብሔር ምልክት መሆኑንም አስተዋለ። ርብቃ ለይስሐቅ የተመረጠች መሆንዋንም አወቀ። ወደ ርብቃ ቤትም ገብቶ ከየት እንደመጣ እና ምን እንደፈለገም ገለፀላቸው። እግዚአብሔርን እንዲመራው ጠይቆ እንዴት እንዳገዘውም ነገራቸው። በርብቃ ያየውን ፈቃደ እግዚአብሔርም ገልጦ ጠየቃቸው። የርብቃ ቤተሰቦች አብርሃምን ያውቁት ነበርና ርብቃ ለይስሐቅ ሚስት እንድትሆንም ፈቀዱ።

ርብቃም ተስማማች፡፡

የአብርሃም አገልጋይም ከርብቃ ጋር ወደ አብርሃም ተመልሶ እግዘአብሔር ያደረገለትን ነገረው ፤ እግዚአብሔርንም አመሠገነ፡፡ ርብቃና ይስሐቅም ተጋቡ፡፡ ርብቃ መካን ነበረችና ልጅ አልወለደችም፡፡ ***‹‹ይስሐቅም ስለሚስቱ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፥ መካን ነበረችና እግዚአብሔርም ተለመነው፥ ሚስቱ ርብቃም ፀነሰች፡፡››*** ያዕቆብ እና ዔሳው የተባሉ ልጆችም ተወለዱ፡፡ ሁለቱም መንትዮች ሲሆኑ ዔሳው መጀመሪያ ስለተወለደ ታላቅ ነበር፡፡ የበኩር ልጅ በመሆን ከአባቱ የሚያገኘው ልዩ በረከትም ነበር፡፡ ዔሳው አንድ ቀን አደን ቀይቶ በጣም ተርቦ ወደ ቤቱ ተመለሰ፡፡ ያዕቆብ ወጥ እየሠራም አገኘውና ከሚሠራው እንዲያበላው ጠየቀው፡፡ ያዕቆብም ብኩርናውን ስጠኝና አበላሃለው አለው፡፡ ዔሳውም ብኩርናውን ለያዕቆብ ሰጥቶ በላ፡፡ ይስሐቅ ሲያረጅም ያዕቆብ ከአባቱ የብኩርናውን በረከት ወሰደ፡፡ ዔሳው ግን በረከቱን ስለተዋት አላገኛትም፡፡ እግዚአብሔርም ይስሐቅን ባረከው፡፡ዘፍ.፳፯÷፫-፳፱፣፴፰፣፳፬፤፳፮÷፲፪-፲፬፣ ፳፰-፳፱፡፡ እርሱም ልጆቹን ባረካቸው፡፡ ይስሐቅም ያዕቆብን ባረከው፡፡ ዔሳውንም የምድር በረከትን ባረከው፡፡ ዘፍጥ.፳፯÷፩-ፍጻሜው፡፡

ይስሐቅ የተስፋው ልጅ እንደሆነ በእምነት የምንመስለውና በመንፈስ የምንወለድ ሁሉ እንደ ይስሐቅ የተስፋው ልጆች ነን፡፡ ሮሜ.፱÷፯-፱፤ገላ.፬÷፳፩-፴፩÷፯

ይስሐቅ በአንድ መቶ ሰማንያ ዓመቱ ዐረፈ ወደ አባቶችም ተከማቸ፡፡ ዘፍጥ.፴፭÷፳፰-፳፱

## ማጠቃለያ

ይስሐቅ በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል የተወለደ፤ የአብርሃም እና የሣራ ብቸኛ ልጅ ነው፡፡ ለቤተሰቡ እየታዘዘ አደገ፡፡ ከእግዚአብሔር የአብርሃምን በረከት ተቀብሎ፤ ለልጆቹም በረከት ያስተላለፈ አባት፡፡

## ተግባር

ልጆች ለቤተሰቦቻችሁ ታዘዙ፡፡ ከአባቶቻችሁ የወረሳችሁትን መልካም ኑሮ ተከተሉ፡፡ ለሁሉም ጊዜ አለው፡፡ እናንተ በወላጆቻችሁ ለመባረክም ሆነ አድጋችሁ ወልዳችሁ ልጆቻችሁን ለመባረክ ጊዜ አለው፡፡ እናንተም ለመባረክ ትጉ፡፡

www.zeorthodox.org

**ጥያቄዎች፡-**

1. ይስሐቅ ማለት ምን ማለት ነው ?
2. የይስሐቅ አባት ማነው? እናቱስ? መቼ ልጅ አገኙ?
3. ይስሐቅ ስንት ዓመት ኖረ?

# የምስራች መላእክት

## ዐሥራ አምስተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ልጆች የቅዱሳን መላእክትን ሥራ ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "መልአኩም መልሶ፦እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ፥ እንድናገርህም ይህችንም የምሥራች እንድሰብክልህ ተልኬ ነበር፤" ሉቃ. ፩፥፲፱

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ሉቃ.፩፥፳- ፍጻሜው፣ ሉቃ.፪፥፲-፲፩፣ ማቴ.፳፰፥፩-፯

**መግቢያ፡-** መላእክት የእግዚአብሔር መልእክተኞች ናቸው፡፡ ስለኛ ይጸልያሉ፣ በብዙ መንገድም ይረዱናል፡፡ ዛሬ ለኛ /ለሰው ልጆች በሙሉ/ መልካም ዜና ያበሰሩባቸውን ታሪኮች እንማራለን፡፡

## ትምህርቱ

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል የሰው ልጆች ድኅነት ሲታወጅ የተላከ መልአክ ነው፡፡

በዚህ መሠረትም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል መጀመሪያ የተላከው ወደ ካህኑ ዘካርያስ ነበር፡፡ አባታችን ዘካርያስ እና ሚስቱ ኤልሳቤጥ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ቅዱሳን ነበሩ፡፡ልጅ ሳይወልዱ ሳይኖራቸው ለረጅም ዘመናት ኖሩ፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ካህኑ ዘካርያስ በቤተመቅደስ እያጠነ ተገለጠለት፡፡ መንገድ የሚጠርግ ልጅ እንደሚወልድ እና ስሙንም ዮሐንስ እንደሚለው አበሠረው፡፡ በመልአኩ ብሥራት መሠረት ኤልሳቤጥ ልጅ ወለደች ስሙንም ዮሐንስ አሉት፡፡

መልአኩ ለዘካርያስ በተገለጠለት በስድስተኛው ወር ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ተገልጦ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደምትፀንስና እንደምትወልደው አበሠራት፡፡

www.zeorthodox.org

*"ደስ ይበልሽ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፡፡ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት፡፡"* እርስዋም *ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው ብላ አሰበች፡፡*

መልአኩም *‹‹ማርያም ሆይ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ፡፡ እነሆ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ፡፡ እርሱ ታላቅ ነው፤ የልዑል ልጅም ይባላል ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፡፡ በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም ይነግሣል ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም፡››አላት፡፡* ማርያምም *‹‹ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል?››*

*አለችው፡፡*

መልአኩም፤‹‹***መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል፡፡እነሆ.. ኤልሳቤጥ በእርጅናዋ ወራት ወንድ ልጅ ፀንሳለች ይህ ስድስተኛ ወር ነው፡፡ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና፡፡ እርስዋም እነሆኝ የጌታ ባርያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ አለች፡፡" ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከእርስዋ ተፀነሰ፡፡***

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት ሌሊትም መላእክት እረኞች ልደተ ክርስቶስን አብረዋቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ መልአኩ ተገልጦ እንዲህ ነበር ያላቸው፡፡ ***"ዛሬ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምስራች እነግራችኋለሁ፡፡ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት የሚሆን ጌታ ክርስቶስ ተወልዶላችኋልና አትፍሩ፡፡"*** እረኞች ጌታ በተወለደ ጊዜ፤ ***"በሰማይ ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን በምድር በጎ ፈቃድ ለሰው ልጆች ..."*** ሲሉ ዘምረዋል፡፡

በትንሣኤ ታሪክ መላእክት ምን እንደሠሩ ታስታውሳላችሁ? አዎን! መላእክት የክርስቶስን ትንሣኤ ለሴቶች አብሥረዋል፡፡ ጌታ በተቀበረበት ቦታ ጎሎጎታ እያዘኑ ለተገኙት እናቶች መላእክት፤ ***"አትፍሩ እናንተስ ክርስቶስን እንድትፈልጉ አውቃለሁና ከዚህ የለም ተነሥቷል፡፡"*** ነበር ያሉዋቸው፡፡

ሦስቱ ወጣቶች የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ላቆመው ጣዖት፤ ***አንሰግድም፤*** በማለታቸው ወደ ሚነደው እቶን ሲጣሉ፤ እሳቱን ሊያበርድላቸው የተላከው ***ቅዱስ ገብርኤል*** ነበር፡፡ ታሪኩ እንዲህ ነበር፡፡ ናቡከደነፆር ዱራ ሜዳ በተባለ ቦታ ትልቅ ጣዖት አቆመ፤ከዚያም ላቆመው ምስል ሁሉም እንዲሰግዱ አዋጅ አስነገረ፡፡ ሁሉም ለምስሉ ሲሰግዱ አንሰግድም ያሉትን ሦስቱን ወጣቶች ከለዳውያን ከሰው በንጉሡ ፊት አቆምዋቸው፡፡ ንጉሡም በታላቅ ቁጣ ሦስቱ ወጣቶች ላቆመው ጣዖት ካልሰገዱ በሚነድ እቶን ውስጥ እንደሚጣሉ አስጠነቀቃቸው፡፡ እነርሱም፤‹‹***ንጉሥ ሆይ እኛ በዚህ ነገር እንመልስልህ ዘንድ አስፈላጊያችን አይደለም፡፡ የምናመልከው አምላካችን ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይችላል፤ ከእጅህም ያድነናል፤ ንጉሥ ሆይ ነገር ግን እርሱ ባያድነን፤ አማልክትህን እንዳናመልክ ላቆምኸውም ለወርቁ ምስል እንዳንሰግድለት እወቅ›› አሉት፡፡*** ናቡከደነፆር ተቆጥቶ፤ ሲድራቅ ሚሳቅ እና አብደናጎም ታስረው በሚነድ የእሳት እቶን እንዲጣሉ አደረገ፡፡ የጣሉዋቸውንም ሰዎች የነበልባሉ ወላፈን ገደላቸው፡፡ በዚያን ጊዜ ንጉሡ ባየው ተደንቆ ሦስቱን ሰዎች አስረን በእሳቱ ውስጥ ጥለን አልነበረም፤ እነሆ እኔ የተፈቱ በእሳቱም መካከል የሚመላለሱ አራት ሰዎች አያለሁ፤ ምንም አላቆሰላቸውም የአራተኛውም መልክ የአማልክትን መልክ ይመስላል አለ፡፡ ወጣቶችንም ኑ ውጡ ብሎ ጠራቸው፤ የራሳቸው ጠጉር ሳይቃጠል ሰናፊላቸውም(ልብሳቸውም) የጢስ ሽታ ሳይኖረው ወጡ፤ ናቡከደነፆርም ‹‹***መልአኩን የላከ... በእርሱ የታመኑትን ባርያዎቹን ያዳነ የሲድራቅና የሚሳቅ የአብደናጎንም አምላክ ይባረክ››*** አለ፡፡ ያም መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ነበረ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ቅዱሳን መላእክት የእግዚአብሔር መልእክተኞች እንደመሆናቸው ከእግዚአብሔር መልካሙን የምስራች ለሰው አሰምተዋል፤ ዛሬም ያሰሙናል። ሦስቱ ወጣቶች በሃይማኖት ስለጸኑ እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ ረዳቸው፤ አዳናቸው።

## ተግባር

- የእግዚአብሔርን ፍቃድ እና ትእዛዝ ‹‹እንደቃልህ ይደረግልኝ›› ብለን ማመን ይገባናል።
- የማይገባ ነገር እንድንፈጽም ሲገፋፉን ከእኛ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ኃይል እንደሚበለጥ በማመን በእምነት ልናሸንፍ እና ልንጸና ይገባል፤

| *መዝሙር* | *ትርጉም* |
|---|---|
| ወእዘ ትፌትል(2) ወረቀ ወሜላተ | እያስማማች ስትፈትል(2) ሀር እና ወርቁን |
| አስተርኣያ ገብርኤል አስተርአያ ለማርያም | ታያት ገብርኤል ማርያምን ታያት |

www.zeorthodox.org

# ልደት

## ዐሥራ ስድስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ስለ ጌታችን ልደት ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ ፡-** ***“ ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ አሉ፡፡”***

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** *ማቴ.፩÷፩-መጨረሻው ፣ ሉቃ.፪÷፰-፲፬*

***መግቢያ፡-*** *መመህር* ስለ ብስራት የተማሩትን ትምህርት ይከልሱላቸው፡፡ የመግቢያ ጥያቄዎችን እንዲመልሱም ያበረታቱዋቸው፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የት ተወለደ? ከማን ተወለደ? እረኞችና መላእክት በጌታችን ልደት ምን አደረጉ?

## ትምህርቱ፡-

**ጌታችን የት ተወለደ?** ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ ልሔም እንደሚወለድ ነቢያት ቀድመው ተንብየው ነበር፡፡ ከእነርሱም ንጉሥ የነበረው ነቢይ ዳዊት መዝ.፻፴፩(፻፴፪)÷፮ እና ነብዩ ሚክያስ ይገኙበታል፡፡ ***‹‹አንቺም ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ ፥ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ ፥ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል፡፡››*** ሚክ.፭÷፪ በዚህ መሠረት ጌታችን በቤተልሔም ተወለደ፡፡

ቤተልሔም በኢየሩሳሌም አቅራቢያ የምትገኝ አነስተኛ ከተማ ናት፡፡ ከተማዋ ዓለቶች፣ ሸለቆዎችና ተራሮች ይከቡዋታል፡፡ እናቱ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ዘጠኝ ወር ሞልቶአት ልትወልድ ስትደርስ፤ የሮሙ ንጉሥ አውግስጦስ ሀገሩ ሁሉ እንዲቆጠር አዘዘ፡፡ የከተማና የገጠር ነዋሪዎች በየ አባቶቻቸው ቤት ሊቆጠሩ ተሰበሰቡ፡፡ ድንግል ማርያምም ከዳዊት ቤት ስለነበረች ወደ ዳዊት ከተማ ወደ ቤተልሔም ወጣች፡፡ በቤተልሔም የነበረው ሕዝብ ብዙ ስለነበር የእንግዶች ማደሪያ አልነበራቸውም፡፡ በመጨረሻም በከብቶች በረት እንዲተኙ ፈቀዱላቸው፡፡ በዚያም እመቤታችን ክርስቶስን ወለደችው፡፡

www.zoorthodox.org

**መቼ ተወለደ?** ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለም በተፈጠረች በ5500 ዓመት፤ ወይም ከዛሬ 2005 ዓመታት በፊት ተወለደ፡፡ ወቅቱ ክረምት ሲሆን ቀዝቃዛ አየር ነበረው፡፡ ይህም በኢትዮጵያ አቆጣጠር ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ነበር፡፡

እናቱ በጨርቅ ጠቅልላ በግርግም አስተኛችው፡፡ በዚያች ሌሊት ከብቶቻቸውን የሚጠብቁ እረኞች ነበሩ፡፡ ድንገትም የሰማይ መላእክት ተገለጡላቸውና፡፡ እንዲህ እያሉም አመሰገኑ *“ ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ አሉ፡፡”* ሉቃ.፪፥፲፬ እረኞቹ ባዩት ነገር እየተደነቁ ሳለ ፡- *‹‹መልአኩም እንዲህ አላቸው፦ እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ፡፡ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና፡፡››*

*ከመልአኩ ጋር የነበሩት እያመሰገኑ ተሰወሩአቸው፡፡ ‹‹መላእክትም ከእነርሱ ተለይተው ወደ ሰማይ በወጡ ጊዜ፥ እረኞቹ እርስ በርሳቸው፤ እንግዲህ እስከ ቤተ ልሔም ድረስ እንሂድ እግዚአብሔርም የገለጠልንን ይህን የሆነውን ነገር እንይ ተባባሉ፡፡››* ሄደውም እንደተባለው ሆኖ አገኙት ደስ አላቸው አምላካቸውንም አመሰገኑ፡፡

## ማጠቃለያ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በይሁዳ ቤተ ልሔም ተወለደ፡፡ እረኞችም ከመላእክት በተነገራቸው መሠረት ሄደው ጌታችንን አመሰገኑ፡፡

## ተግባር

የከብቶች በረት ለመሥራት የሚያስችል ቁሳቁስ ተዘጋጅቶ ልጆች በመምህሩ ርዳታ ይሥሩ፡፡ የሚከተለውን መዝሙር አጥኑ፡፡

| *መዝሙር* | *ትርጉም* |
|---|---|
| በጎል ሰከበ በአጽርቅት ተጠብለለ | በበረት ተኛ በጨርቅ ተጠቀለለ |
| ቤዛ ኩሉ ዓለም ዮም ተወልደ | የዓለም መድኃኒት ዛሬ ተወለደ፡፡ |

www.zeorthodox.org

# ጥምቀት - መገለጥ

## ዐሥራ ሰባተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን መጠመቅና መገለጥ፣ የጥምቀትንም አስፈላጊነት ልጆች ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም፡፡" ዮሐ.3፥5***

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ.፫፥፩-፲፯፣ ማር.፩፥፩-፲፩፣ ሉቃ.፫፥፩-፳፫፣ ዮሐ.፩፥፲፱-፴፯፣ ዘሌዋ. ፲፪፥፩-መጨረሻ

**መግቢያ፡-** ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሠላሳ ዓመት ሲሞላው በዮሐንስ እጅ ለመጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ ሄደ፡፡ በዚያም መንገድ ጠራጊውና መጥምቁ ዮሐንስ ያጠምቅ ነበር፡፡

**ልጆች፡-** ከልደት እስከ ጾመ ነነዌ ያለው ወራት ***ዘመነ አስተርእዮ-የመገለጥ ወራት*** ይባላል፡፡ ምክንያቱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን፣ ለማስተማር እና ጥምቀትን ሊሰጠን የተገለጠበት ወራት ስለሆነ ነው፡፡

## ትምህርቱ

ዮሐንስ የንስሐ ጥምቀትን እያጠመቀና የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣትዋን እያበሰረ በዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ ነበር፡፡

ሕዝቡም መሲሑ እርሱ መስሎአቸው ***"አንተ ነህን?"*** ሲሉት ***"የመሲህ (ክርስቶስን) መንገድ ጠራጊ እንደሆነና የጫማውን ጠፍር ሊፈታ እንኳን እንደማይገባው"*** ይነግራቸው ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሊጠመቅ ወደ ዮርዳኖስ ሲመጣም መጥምቁ ዮሐንስ ለሕዝቡ፤ ***"እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚያብሔር በግ፡፡ አንድ ሰው ከእኔ በኋላ ይመጣል፥ ከእኔም በፊት ነበርና ! ከእኔ ይልቅ የከበረ ሆኖአል ብዬ ስለ እርሱ ያልኩት ይህ ነው፡፡"*** ማር.፩፥፲፪ አላቸው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ተጠምቆ ከዮርዳኖስ ወንዝ ሲወጣ፡-

ሰማያት ተከፈቱ

መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳለ በራሱ ላይ ዐረፈ

አብ ከሰማይ *"በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ እርሱ ነው÷ እርሱን ስሙት"* አለ። በዚህ ጊዜ ፡-

ሀ. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ ተገለጠ።

ለ. የሥላሴ ሦስትነትም በገሃድ ተገለጠ ።

ሐ. መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ በመጠመቅ የትኅትናና የጥምቀታችን ምሳሌ ሆነን።

መ. እኛም የክርስቶስን ምሳሌ ተከትለን እንጠመቃለን።

## ጥምቀት ለምን አስፈለገ ?

***መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ።*** ካልተጠመቅን የእግዚአብሔርን *መንግሥት* አንወርስም። *"ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም"* ዮሐ.፫÷፭ ስለዚህም የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ መጠመቅ አለብን።

**የእግዚአብሔርን ልጅነት ለማግኘት።** **" ለተቀበሉት ሁሉ ግን ፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው ፤ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም።"** ዮሐ.፩÷፱ ስንጠመቅ የእግዚአብሔር ልጅነትን ሥልጣን እናገኛለን።

ወንዶች በአርባ ሴቶች በሰማንያ ቀናቸው ይጠመቃሉ። የክርስትና አባትና እናት ይኖረናል። እነርሱም ሃይማኖት ያስተምሩናል።

የክርስትና ስም ይሰጠናል። ልጆች ክርስትና ስማችሁን ታስታውሳላችሁ ?

## ማጠቃለያ፡-

ጌታችን ተጠምቆ ጥምቀትን ሰጥቶናል። ሲጠመቅም የእግዚአብሔር ልጅነቱ እና የእግዚአብሔር ሦስትነት ተገልጾአል።

እኛም በመጠመቃችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባትንና የእግዚአብሔርን ልጅነት እንቀበላለን።

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

በጥምቀት ምን እናዳገኛችሁ ለቤተሰባችሁ አስረዱ።

***የክለሳ ጥያቄዎች***

መጥምቁ ዮሐንስ ስለራሱ የተናገረው ምን ነበር? ምንስ አስተማረ?

ጌታችን ሲጠመቅ ዕድሜው ስንት ነበር? የት ተጠመቀ?

ጌታችን ለምን ተጠመቀ?

እኛስ ለምን እንጠመቃለን? ዕድሜአችን ምን ያህል ሲሆን እንጠመቃለን?

# ቅዱስ እስጢፋኖስ - ቀዳሜ ሰማዕት

## ዐሥራ ስምንተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ቅዱስ እስጢፋኖስ የጌታችንን ምሳሌ እንዴት እንደተከተለ እንዲሁም የጌታችንን ቃል መጠበቅና መንገዱን መከተል ጠቀሜታውን ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ጌታ ሆይ፣ ይህን ኃጢአት አትቁጠርባቸው ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፡፡"*** የሐዋ.ሥ.፯፥፷

**ምንባብ፡-** የሐዋ.ሥ.፯፥፩-፷

### መግቢያ

ሰማዕትነት የራስን ሕይወት ለሌላው አሳልፎ መስጠት ነው፡፡ ብዙ ክርስቲያኖች በክርስቶስ በማመናቸው በግፍ ተገድለዋል፡፡ በክርስቶስ ማመናቸውም ስላልተው እና ስለርሱ ስለመሰከሩ ሕይወታቸውን እንዲከፍሉ ተደርጓል፡፡ ለማንኛውም ጣዖት ስላልሰገዱና ስላልሠውም ብዙ ሰማዕትነትን ተቀብለዋል፡፡ ቅዱስ እስጢፋኖስ ስለ ክርስቶስ ሰማዕትነትን የተቀበለ የመጀመሪያው ሰማዕት ነው፡፡

ቅዱስ እስጢፋኖስ በእምነቱ ጸንቶ የክርስቶስን ምሳሌ እስከ ሞት ድረስ እንዴት እንደተከተለ እንማራለን፡፡

### ትምህርቱ

ቅዱስ እስጢፋኖስ ከሰባቱ ዲያቆናት አንዱና ከመጀመሪያዎቹ የቤተ ክርስቲያን አማኞች ወገን ነው፡፡ ታማኝ፣ በጥበብ የተሞላና መንፈስ ቅዱስ ያደረበትም ነበር፡፡ በሕዝቡ መካከልም ታላላቅ ምልክትና ተዓምራትን ያደርግ ነበር፡፡ ከአይሁድ ምኩራብ ብዙ አይሁድም ይከራከሩት ስለነበረ የሚናገርበትን መንፈስ መቋቋም ግን አልቻሉም ነበር፡፡ በሐሰት ከሰውት ምሥክር አቆሙበት፡፡ ወደ ፍርድ አደባባይም ተወሰደ ፣ የካህናት አለቆችም የተከሰሰበት ነገር እውነት መሆኑን ጠየቁት፡፡ ቅዱስ እስጢፋኖስም በእምነቱ ጸንቶ ያለምንም ፍርሐት ሦስት ነጥቦችን አንሥቶ በእውነት መሰከረ፡፡

1. ከአብርሃም ጀምሮ የነበረውን የአይሁድ ታሪክ አስረዳ
2. ስለክርስቶስ የተነገሩትን የነቢያትን ትንቢት አብራራ
3. ስለ ክርስቶስ የተተነበየው ትንቢት መፈጸሙንም መሰከረ፡፡

ከዚያም ***"እናንተም.....ሁልጊዜ መንፈስ ቅዱስን ትቃወማላችሁ"*** አላቸው፡፡ ከሳሾቹ ይህን

www.zoorthodox.org

ሲሰሙም ተቆጡ፡፡

አብ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን ሰማያት ተከፍተው ወልድን በአብ ቀኝ ቆሞ አየው፡፡ ይህን ሲነጋራቸው ***‹‹በታላቅ ድምፅም እየጮኹ ጆሮአቸውን ደፈኑ ፥ በአንድ ልብ ሆነውም ወደ እርሱ ሮጡ፡፡››*** ያዙትና እያንገላቱት ከከተማ ውጭ አውጥተው በድንጋይ ወገሩት፡፡ እርሱም ***"ጌታ ሆይ ነፍሴን ተቀበል… ይህን ኃጢአት አትቁጠርባቸው ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፡፡"*** ይሄን ብሎም አንቀላፋ በሰማዕትነትም ዐረፈ፡፡ ሳውል የተባለው ሰውም ቅዱስ እስጢፋኖስን የወገሩትን ሰዎች ልብስ ሰብስቦ በመያዝ ከገዳዮቹ ጋር ተባብሮ ነበር፡፡

## ማጠቃለያ

ቅዱስ እስጢፋኖስ በፍርድ አደባባይ ሲቆምና ሲከሰስ በእምነቱ ጸንቶ እውነቱን መናገሩ ሕይወቱን እንደሚያስከፍለው እያወቀ ነው፡፡ እስከ ሞት የሚያደርስ ስቃይና መከራ ቢደርስበትም እውነቱን መናገር አልፈራም፡፡ አያችሁ ቅዱስ እስጢፋኖስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ነበር ያስተዋለው፡፡ ውጤቱ ምንም ይሁን እግዚአብሔር በእውነት የተሞላን እንድንሆን ይፈልጋል፡፡ የክርስቶስ ምስክር ሆነው የተሰውት ቅዱሳን የክብር አክሊል የተቀዳጁት ለእውነት ስለሞቱ ነው፡፡ ነገር ግን በመንፈስ ሕያዋን ናቸው፡፡ በዘላለማዊ ደስታም ከእግዚአብሔር ጋር ይኖራሉ፡፡

ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ፣ ለሰቃዮቹ ጸልዮላቸዋል፡፡ ክርስቶስ ይሄን ያደረገው እኛም ለሚያሳድዱን ክፉ ለሚያደርጉብን እንድንጸልይ አርኣያ ሊሆነን ነው፡፡ ቅዱስ እስጢፋኖስም ከዚህ ተምሮ ነው በድንጋይ ለሚወግሩት የጸለየው፡፡ ስለዚህም የፍቅርን ምሳሌ ለሌሎች ሰጥቶኣል፡፡ የቅዱስ እስጢፋኖስ መልካም ሥራና ሰማዕትነት ልንከተለው የሚገባን መልካም አርአያ በመሆኑ እኛም ምሳሌ መሆን ይጠበቅብናል፡፡

ከላይ እንደተመለከትነው ቅዱስ እስጢፋኖስ ስለክርስቶስ ምሥክር በመሆን ሕይወቱን ሰጥቶአል፣ ወንጌልንም አስፋፍቶኣል፡፡ ሰማዕትነት የተቀበለውም ለእውነት ሲመሠክር ነው፡፡ ከጌታችን ዕርገት በኋላም የመጀመሪያው ሰማዕት ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያናችንም ቀዳሚ (የመጀመሪያው) ሰማዕት ይባላል፡፡

www.zoorthodox.org

## ተግባር

በተሰለፋችሁበት የእምነትም ሆነ የትምህርት ጉዞ የሚፈለገውን ነገር ሁሉ በሰማዕትነት ፈጽሙ፡፡

***የክለሳ ጥያቄዎች***

1. ቅዱስ እስጢፋኖስ ለምን የመጀመሪያው ሰማዕት ተባለ ?

_______________________________________________

2. ቅዱስ እስጢፋኖስ የተከሰሰበት ክስ ምን ነበር ?

_______________________________________________

3. የአይሁድ መሪዎች በሸንጎ ሲከሱት ምን አለ ?

_______________________________________________

4. አይሁድ በድንጋይ ሲወግሩት ቅዱስ እስጢፋኖስ ምን አደረገ? ያየውስ ምን ነበር ?

_______________________________________________

5. እስጢፋኖስ ክርስቶስ የተወልንን አርኣያ (ምሳሌ) እንዴት ፈጸመ ?

_______________________________________________

6. ምንም ቢሆን እንደ ቅዱስ እስጢፋኖስ እውነቱን ትናገራላችሁ ?

_______________________________________________

7. ሰማዕትነት ምንድነው ?

_______________________________________________

www.zeorthodox.org

# የሳውል መጠራት

## ዐሥራ ዘጠነኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** የሳውልን ወደ ቤተ ክርስቲያን መመለስ ታሪክ ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነው…"*** የሐዋ.ሥ ፱፥፲፭

**ምንባብ፡-** የሐዋ. ሥራ .፱÷፩-፴፩

**መግቢያ፡-** ሳውል የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ሆኖ ወደ ቤተክርስቲያን ከመመለሱ በፊት ክርስቲያኖችን የሚያሳድድ ነበር ፤ ወደ ክርስትና ተመልሶም በጾም በጸሎትና መጽሐፍ ቅዱስ በማንበብም ለታላቅ አገልግሎት ደርሶአል፡፡

### *የክለሳ ጥያቄዎች*

- ባለፈው ሳምንት የተማርነውን የቅዱስ እስጢፋኖስን ታሪክ ታስታውሳላችሁ? እስጢፋኖስ ለምን በድንጋይ ተወገረ፡፡
- እስጢፋኖስን ሲወግሩት የነበሩትን የነበሩትን ልብስ በመያዝ የተባበራቸውስ ማን ነበር ?
- ሳውል ማነው ?

ቅዱስ እስጢፋኖስ እውነትን በማስተማሩ በድንጋይ ተወግሮ በሰማዕትነት ሲያርፍ ፣ ‹‹***ይህን ኃጢአት አትቁጠርባቸው ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ*** ›› ፣ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ ታላቅ ኃይል ታደርጋለች እንደተባለው፤ የቅዱስ እስጢፋኖስ ጸሎት ዋና የቤተ ክርስቲያን አሳዳጅ የነበረውንና በእስጢፋኖስ ሞት የተስማማውን ሳውልን ወደ ክርስትና አመጣው፡፡

www.zeorthodox.org

ልጆች በዛሬው ትምህርታችንም ስለ ሳውል እንማራለን፡፡

## ትምህርቱ

የክርስቶስን ደቀ መዛሙርት የሚያሳድድ ሳውል የተባለ ቀናኢ አይሁድ ነበር፡፡ ይህ ሰው በክርስቶስ አያምንም ነበር፡፡ አንድ ቀን እንደልማዱ ክርስቲያኖችን አስሮ ለማምጣት የሚያስችለው ማዘዣ ከአይሁድ የካህናት አለቆች ተቀብሎ፡፡ ከዚያም ወደ ደማስቆ ተጓዘ፡፡ ወደ ደማስቆ ከተማ ሊደርስ ትንሽ ሲቀረው ኃይለኛ ብርሃን በዙሪያው ሆነ፤ እርሱም እጅግ ደንግጦ መሬት ላይ ወደቀ፡፡

***“ሳውል ሳውል ስለምን ታሳድደኛለህ?”*** የሚል ድምፅ ሰማ። ***“አንተ ማነህ?”*** አለ ሳውል። ጌታችንም ***“እኔ የምታሳድደኝ ኢየሱስ ነኝ”*** አለው። ሳውልም ደንግጦ ***“ጌታ ሆይ ምን ላደርግ ትፈልጋለህ?”*** አለው። ወደ ከተማ እንዲገባና ማድረግ የሚገባውንም እንደሚነግሩት ገለጠለት።

ሳውል ከተቀመጠበት ተነሣ ማየት ግን አልቻለም። አብረውት የነበሩት ሰዎችም እየመሩ ከተማ አደረሱት። ሳውልም ሳይበላና ሳይጠጣ ሦስት ቀን በጸሎት ቆየ። በዚያም ሐናንያ የሚባል ሰው መጥቶ ለማየት እንደሚያስችለውም በራእይ አወቀ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐናንያ ለተባለ ደቀ መዝሙር ተገልጦ ወደ አይሁድ ቤት ሄዶ ሳውል የሚሉት የጠርሴስ ሰው ፈልጎ እጁን ጭኖ እንዲጸልይለት ነገረው። ሐናንያ ሳውል ብዙ ክፋት እንዳደረገና ከካህናት አለቆች ክርስቲያኖችን ለማሰር ሥልጣን እንደተሰጠው ገለጠ። ጌታችንም ***“ስሜን የሚሸከም ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነውና ሂድ”*** አለው።

ሐናንያም ሳውል ወዳለበት ቤት ሄደ፤ ሳውልም ተገናኘው እጁን ጭኖበት ከጸለየ በኋላም እንዲህ አለው፤ ***“ወንድሜ ሳውል ሆይ፦ ጌታ እርሱም በመጣህበት መንገድ የታየህ ኢየሱስ ነው፣ ደግሞ ታይ ዘንድና መንፈስ ቅዱስ ይሞላብህ ዘንድ ላከኝ “*** አለ።

ወዲያውም ቅርፊት ከዓይኑ ወደቀ፣ አየም፣ ተጠመቀም፣ በልትቶም በረታ። ከጌታችን ደቀ መዛሙርት ጋር ተቆጥሮ ስለ ክርስቶስ ማስተማር ጀመረ።

## ማጠቃለያ

ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቲያኖችን ሲያሳድድ እግዚአብሔርን እንደሚያሳዝን አላወቀም።ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እውነቱን እንዲያይ ዓይኖቹን ከፈተለት። እናም አመነና እንደሌሎቹ ደቀ መዛሙርት የጌታ ምስክር ለመሆን በቃ። ብዙ መልእክቶችንም ጽፎአል። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መኖርንም ለብዙ ሰዎች አስተምሮአል። ከመልእክቱም እግዚአብሔርን እንዴት እንደምንከተለው እንማራለን።

www.zeorthodox.org

ሳውል ማየት ሲያቅተው ሦስት ቀንና ሌሊት እየጾመ ጸልዩአል። ጌታም ለሐናንያን ተገልጦ ወደ ሳውል ላከው፤ ዓይኑንም አበራለት። እኛም በመከራ ጊዜ ልንጾምና ልንጸልይ እንደሚገባንና እግዚአብሔር መፍትሔ እንደሚሰጠን እንማራለን።

## ተግባር

እንደ ቅዱስ እስጢፋኖስ ለተሳሳቱ ሰዎች ጸልዩላቸው።

አጥፍታችሁ ስትመከሩ ምክሩን ተቀብላችሁ ወዲያው ተግባራዊ አድርጉ።

## ጥያቄዎች

1. ሳውል ክርስቲያኖችን ያሳድድ የነበረው ለምንድነው ?

2. ሳውልን ጌታችን በደማስቆ በረሓ ሲያናግረው ወዴት እየሄደ ነበር ? ለምን ?

3. በመንገድ ላይ ሳውል ታላቅ ብርሃን ሲያንፀባርቅበት ምን ተፈጠረ ?

4. ጌታችንስ ምን አለው ?

5. ሳውልን ማን አጠመቀው ?

6. ሳውል ከተጠመቀ በኂላ ምን ሠራ ?

7. ሳውል ዓይኑ እስኪበራ ለስንት ቀን ጸሎትና ጾም ያዘ ?

www.zeorthodox.org

# ተተኪው ኢያሱ - ባሕር አሻገረ

## ሃያኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** በአባቶቻችን የጽድቅ መንገድ ከሄድን እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ያደረገውን ለእኛም እንደሚያደርግ ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *« እንደ አባቶቼ አድርጌ በንጹሕ ሕሊና የማመልከውን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ ፤»* ፪ኛ ጢሞቴ.፩፥፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘዳ.፴፩፥፩-፰፣ ፴፬፥፩-፱ ኢያ.፩፥፩-፱፣ ምዕ.፫፥፬

**መግቢያ፡-** ልጆች ሙሴን ታውቁታላችሁ? አዎ ሙሴ በእግዚአብሔር ኃይል እስራኤልን ከግብጽ ባርነት ነፃ ያወጣ ነው። የኤርትራን ባሕር በበትሩ ሲመታትም ባሕር ተከፍሎ ሕዝበ እስራኤል ተሻግረዋል። በሲና በረሓ ሲጓዙ ከድንጋይ ውኃ እያፈለቀ፣ ከሰማይም መና እያወረደ እንዲመራቸው እግዚአብሔር ኃይልና ሥልጣን ሰጥቶት ነበር። ለአርባ ዓመታት ሕዝቡን መርቶ የሚያርፍበት ጊዜ ሲደርስ ፣ ተተኪውን ኢያሱን በእግዚአብሔር ፍቃድ አዘጋጀ።

በዛሬው ትምህርታችን ተተኪው ኢያሱ እንደ አባቱ እንደ ሙሴ ታላቅ ድንቅ ማድረጉን እንማራለን።

## የሳምንቱ ትምህርት

ሙሴ ለአርባ ዓመታት እስራኤልን በበረሓ መርቶ፤ አንድ መቶ ሃያ ዓመት ሲሆነው፤ እግዚአብሔር የዮርዳኖስን ወንዝ አትሻገርም እንዳለው ፣ ለመውጣትና ለመግባት እንደማይችልና ኢያሱ እግዚአብሔር ወደ ማለላቸው ምድር እንደሚያገባቸው ለሕዝቡ ተናግሮ በናባው ተራራ ሞቶ ተቀበረ። እስራኤልም ለሠላሳ ቀናት አለቀሱለት። ከዚያም እግዚአብሔር ኢያሱን፤ ‹‹ዮርዳኖስን ተሻገሩ። ከሙሴ ጋር እንደነበርኩ ከአንተ ጋር እሆናለሁ። አልጥልህም አልተውህምም። ጽና ፣ አይዞህ ፣ በርታ አለው። ኢያሱም ማልዶ ተነሣ የእግዚአብሔርን ቃል አምኖ ተዘጋጀ።

ሕዝበ እስራኤል በኢያሱ መሪነት ከሰጢም ተነሥተው ወደ ዮርዳኖስ ዳር መጡ። ሳይሻገሩም በዚያው አደሩ። ወቅቱ ወንዝ የሚሞላበት ነውና ዮርዳኖስ ወንዝም ሞልቶአል። በዮርዳኖስ ዳርቻ ሦስት ቀን ተቀመጡ። ከሦስት ቀናት በኋላ ኢያሱ ያዘጋጃቸውና የእግዚአብሔርን ቃል የነገራቸው አለቆች በሕዝቡ መሐል አለፉ።*‹‹ሕዝቡንም ፦ የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ታቦት ሌዋውያን ካህናት ተሸክመውት ባያችሁ ጊዜ ፥ ከሰፈራችሁ ተነሥታችሁ ተከተሉት።››* አሉ።

www.zoorthodox.org

ከታቦቱ በሁለት ሺሕ ክንድ እንዲርቁም አዘዙ።

ልጆች የበላዮቻችን የሚሉንን መልካም ነገር መስማትና ማክበር አለብን። ታቦት ሲወጣም መከተል የሚገባው በርቀት ነው። ይህ የሚደረገውም ለእግዚአብሔር ያለንን ክብር ለመግለጥ ነው። ምክንያቱም ታቦት የእግዚአብሔር ማደሪያ ነው።

***‹‹ኢያሱም ሕዝቡን፦ ነገ እግዚአብሔር በመካከላችሁ ድንቅ ነገር ያደርጋልና ተቀደሱ አለ።››*** የእግዚአሔርን ድንቅ ነገር የሚቀበሉ አግዚአብሔር የሚፈልገውን ቅድስና ሊይዙ ይገባልና። ልጆች እናንተም ልትቆርቡ ወደ ቤተክርስቲያን ስትመጡ ታጥባችሁ፣ ከክፉ ንግግር፣ ከስድብ፣ የራሳችሁ ያልሆነውና ቤተሰብ ያልፈቀደላችሁን ነገር ሁሉ ከመውሰድ ተቆጥባችሁ በንጽሕና መሆን አለበት።

***‹‹ኢያሱም ካህናቱን፦ የቃል ኪዳኑን ታቦት ተሸክማችሁ በሕዝቡ ፊት እለፉ ብሎ ተናገራቸው፤ የቃል ኪዳኑንም ታቦት ተሸክመው በሕዝቡ ፊት አለፉ።››*** ሕዝቡም ከድንኳኖቻቸው ተነሥተው ተከተሉት። የቃል ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙት ካህናት የዮርዳኖስን ወንዝ ሲረግጡ። ወንዙ ቆመ፤ ሕዝቡም ተሻገሩ። በመጨረሻ ታቦቱን የተሸከሙት ተሻገሩ። የዮርዳኖስ ወንዝም እንደቀድሞው መፍሰስ ቀጠለ።

ከሕዝቡ የተመረጡ አንድ አንድ ድንጋይ ተሸክመው እንዲሻገሩ ታዘዙ። የተባሉትንም ፈጸሙ። ያንንም ድንጋይ እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ለማስታወስ እና ለልጆቻቸው ለማሳየት ክምር ድንጋይ አድርገው አቆሙት።***‹‹በዚያም ቀን እግዚአብሔር ኢያሱን በእስራኤል ሁሉ ፊት ከፍ አደረገው ሙሴንም እንደ ፈሩ በዕድሜው ሁሉ ፈሩት።››***

ልጆች እግዚአብሔር የፈቀደልን ሁሉ አይቀርም። ከእኛ የሚጠበቀው ለእርሱ መታዘዝ ነው። ትልቅ ስትሆኑ በወላጆቻችሁና በታላላቆቻችሁ ተተክታችሁ ታላቅ ሥራን ለመሥራት ዛሬ መታዘዝን መልመድ አለባችሁ። ኢያሱ ሙሴን ይታዘዘው ነበር። እግዚአብሔር የሚለውንም ሁሉ ይፈጽም ነበር። እናንተም የነገ ታላቅ ሥራችሁን ዛሬ በመማር ፣ በመታዘዝና እግዚአብሔርን በመፍራት ጀምሩት።

## ማጠቃለያ

www.zeorthodox.org

ኢያሱ ሙሴን ተክቶ እስራኤልን መርቶአል። እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ኃይል ያደረገለትና ሕዝቡን ለመምራት መመረጡን ያሳየውም የዮርዳኖስን ወንዝ በታቦቱ ኃይል በማስቆምና ሕዝቡ እንዲሻገሩ በማድረግ ነው።

ዮርዳኖስን መሻገራቸው ***ድንቅ ነገር*** ነበር። ለዚህም በመቀደስ ተዘጋጁ። ከተሻገሩ በኋላም የመታሰቢያ ድንጋይ አቆሙ። እናንተም እግዚአብሔር ለሚያደርግላችሁ ተዘጋጁ። ውለታውንም ሁል ጊዜ አስቡ።

## ተግባር

- የእግዚአብሔርን ቃል ሁል ጊዜ ስሙ።
- ለታላላቆቻችሁ ታዘዙ።

### *የክለሳ ጥያቄዎች*

1. ሙሴ በስንት ዓመቱ ሞተ ?
2. ሙሴን የተካው ማን ነው ?
3. የዮርዳኖስ ወንዝ እንዴት ቆመ ?
4. ሕዝቡና ካህናቱ ከተሻገሩ በኋላ የቆመው የድንጋይ ሐውልት ለምን አስፈለገ ?

www.zeorthodox.org

# ብኵርና

## ሃያ አንደኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የተሰጠንን ስለመጠበቅ ልጆች ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *‹‹ ለፍጥረቱ የበኵራት ዓይነት እንድንሆን በእውነት ቃል አስቦ ወለደን፡፡››* ያዕ.፩፥፲፰

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ዘፍጥ.፳፫፥፳፫-፴፬

## መግቢያ

- ብኵርና ምንድነው ?
- ከያዕቆብና ከዔሳው በኵር ማን ነበር ?
- በኵር መሆን ለምን ይጠቅማል ?

የዛሬው ትምህርታችን ስለ ብኵርና ነው፤ ለዚህም የሁለቱን ወንድማማቾች ታሪክ መሠረት በማድረግ እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ልጆች ከሰው ወይም ከእንስሳ መጀመሪያ የሚወለደው ሁሉ በኵር ይባላል፡፡ ዘዳ.፳፩፥፲፯ ከሰው ወይም ከእንስሳ መጀመሪያ የሚወለደው በኵር ለእግዚአብሔር ይሰጣል፤ ያም ባይሆን ይዋጃል፡፡ (ይዋጃል ማለትም በበኵሩ ፋንታ የሚቀርብ ስጦታ ይቀርባል ማለት ነው፡፡) ሰው እግዚአብሔርን ለማገልገል ፣ እንስሳትም ለመሥዋዕት ፤ ለእግዚአብሔር ቤት ይሰጣሉ፡፡ (ዘጸ.፲፫፥፲፪-፲፫፤፳፪፥፳፱)

በኵር ከአባት ቀጥሎ በቤቱ የተከበረ ነው፡፡ አባቱ በሌለበትም እንደ አባት ነው፡፡ በድሮ ዘመን ከሌሎች ልጆች ዕጥፍ ውርስም ያገኝ ነበር፡፡ዘዳ.፳፩፥፲፯ የአባቶቻቸውን በረከት የሚወርሱትም በኵሮች ነበሩ፡፡ ዘፍ.፳፯፥፩-፬

www.zeorthodox.org

የይስሐቅ ሚስት ርብቃ ቆይታ ስትፀንስ በማኅፀንዋ ያሉት መንትያዎች ነበሩ፡፡ መጀመሪያ የተወለደው ቀይ ነበር፡፡ ሁለንተናውም ፀጉራም ነበር፤ እርሱንም ዔሳው አሉት፡፡ ወንድሙም በእጁ የዔሳውን ተረከዝ ይዞ ወጣ ፣ ስሙንም ያዕቆብ አሉት፡፡ ዘፍ.፳፭፥፳፭-፳፮ መንትያዎቹ ዔሳው እና ያዕቆብ ሲወለዱ፣ ዔሳው መጀመሪያ ስለተወለደ በኵር ነበር፡፡ ያዕቆብም ታናሽ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ያዕቆብ ብኵርናውን በጣም ይፈልግ ነበር፡፡

አንድ ቀን ዔሳው አደን ውሎ መጣ ፤ በጣም ርቦት ነበር፡፡ ያዕቆብም ቀይ ወጥ ሠርቶ ነበረ፤

ዔሳው ‹‹እጅግ ደክሜአለሁ ከቀዩ ወጥ አብላኝ›› አለው፡፡ ያዕቆብም በመጀመሪያ ብኵርናህን ሽጥልኝ አለው፡፡ ዔሳውም እነሆ፥ እኔ ልሞት ነኝ ይህች ብኵርና ለምኔ ናት? አለ፡፡ ያዕቆብም በመጀመሪያ ማልልኝ አለው፡፡ ዔሳውም ማለለት ብኵርናውንም ለያዕቆብ ሸጠ፡፡ ዘፍ.፳፭፥፳፱-፴፬

ለብዙ ዓመታት ቆይቶ ዔሳው በብኵርናው የሚያገኘውን በረከት ሊቀበል ሲል ወንድሙ ያዕቆብ ወሰደበት፡፡ ምክንያቱም ዔሳው ብኵርናውን ስለ አቃለላት እና በመሀላ ስለሸጣት ነው፡፡ (በረከቱ ምን እንደነበር በሚቀጥለው ሳምንት እናያለን፡፡)

ልጆች እግዚአብሔር የሰጠንን ሁሉ ማክበር አለበን፡፡ **ለምሳሌ**፡- ቤተሰባችንን፣ ጤንነታችንን፣ ክርስትና እምነታችንን፣ ካህናት አባቶቻችንን፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ቤተ ክርስቲያንን እግዚአብሔር የሰጠንና እኛም ማክበር ያለብን ነገሮች ናቸው፡፡

ዔሳው ያቃለላትን ብኵርና አልቅሶ ቢፈልጋትም ማግኘት አልቻለም፡፡ እናንተም እግዚአብሔር የሰጣችሁን አክብራችሁ ያዙ፡፡

ክርስቲያኖች የፍጥረታት በኵር ናቸው፡፡‹‹ ***ለፍጥረቱ የበኵራት ዓይነት እንድንሆን በእውነት ቃል አስበ ወለደን፡፡››*** ያዕ.፩፥፲፰

## ማጠቃለያ

- ❖ ብኵርና በመጀመሪያ በመወለድ የሚገኝ ሲሆን በሥጋ እና በነፍስ የሚታይና የማይታይ በረከትና ዋጋ ያስገኝ ነበር፡፡
- ❖ ያዕቆብ የተመኛትና ዔሳው ያቃለላት ብኩርና ዋጋዋ ታላቅ ነበር፡፡ በመጨረሻ ዔሳው ጸጸትን ያዕቆብም በረከትን አግኝተውበታል፡፡
- ❖ የእኛ ብኵርና ክርስትናችን ነው፡፡ በመማር ከቤተሰብም ምክር በመውሰድ ልንጠብቀው ይገባል፡፡

## ተግባር

www.zeorthodox.org

ብኵርናችሁን መጠበቅ የምትችሉት በመማር ነውና ቤተሰብ ወደ ቤተክርስቲያን እንድትማሩ ሲያመጣችሁ በሚገባ ተማሩ፡፡

***የክለሳ ጥያቄዎች***

1. በኵር ማለት ምን ማለት ነው ?
2. በኵር የሚባሉት እነማን ናቸው ?
3. ዔሳው የያዕቆብ መንትያ ሆኖ እንዴት በኵር ሆነ?
4. ያዕቆብ ብኩርናውን ያገኘው እንዴት ነበር ? የእኛ ብኵርናስ ምንድነው?

# በወላጆቻችሁ ትባረኩ ዘንድ ታዘዙ

## ሃያ ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች፤ ስለ በረከት እና መታዘዝ ጥቅም ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *‹‹የአባትህ በረከቶች ጽኑዓን ከሆኑ ከተራሮች በረከቶች ይልቅ ኃያላን ናቸው፤ ዘላለማውያን ከሆኑ ከኮረፍቶችም በረከቶች ይልቅ ኃያላን ናቸው››* ዘፍ.፵፱፥፳፮

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ዘፍ.፳፭፥፳፯-ፍጻሜው፤፳፮፥፴፪-፵፫፤ ፳፯፥፩-፳፱፤፴፪፥፳፬-፴፪

**መግቢያ፡-** ይስሐቅ ስልሣ ዓመት ሲሞላው ሚስቱ ርብቃ ሁለት ልጆችን ወለደችለት፤ ስማቸውም ዔሳው እና ያዕቆብ ነበር፡፡ ዔሳው የበኵር (መጀመሪያ የተወለደ ) ልጅ ሲሆን ፤ ያዕቆብ ሁለተኛ ነበር፡፡ በዛሬው ትምህርታችን ያዕቆብ ለቤተሰቡ የሚታዘዝ ልጅ ስለነበር በረከት መቀበሉን እንማራለን፡፡

### *የክለሳ ጥያቄዎች*

ልጆች ስለ ይስሐቅ የተማራችሁትን ታስታውሳላችሁ ? ----------------------------------

ይስሐቅ ስንት ልጆች ነበሩት ? ----------------------------------------------------------------

ስማቸውስ ማን ነው ? ----------------------------------------------------------------------

## የሳምንቱ ትምህርት

www.zoorthodox.org

ያዕቆብ ጭምት እናቱን እየታዘዘና እየተላላከ የሚኖር ልጅ ነበር፡፡ ዘፍ.፳፭፥፳፯ እናቱም በጣም ትወደው ነበር፡፡ ዔሳው አዳኝ እና በአባቱም የተወደደ ነበር፡፡ ዔሳው በምስር ወጥ ብኵርናውን ሸጠ፡፡

በሌላ ጊዜ አባቱ ይስሐቅ ኤሳውን ሊባርከው እንደሆነ እናቱ ርብቃ ሰማች፡፡ በመታዘዙ የምትወደው ልጅዋ ያዕቆብ እንዲባረክ፣ የጣፈጠ ምግብ አዘጋጀችና ወደ ይስሐቅ ገብቶ እንዲባረክ አደረገችው፡፡ ይስሐቅም *‹‹እግዚአብሔርም ከሰማይ ጠል ከምድርም ስብ የእህልንም የወይንንም ብዛት ይስጥህ፡፡ አሕዛብ ይገዙልህ ሕዝብም ይስገዱልህ ለወንድሞችህ ጌታ ሁን፥ የእናትህም ልጆች ይስገዱልህ የሚረግምህ እርሱ ርጉም ይሁን የሚባርክህም ቡሩክ ይሁን፡፡››* ሲል ባረከው፡፡

ዔሳው ሲመጣ ወንድሙ በረከቱን እንደወሰደበት አወቀ፡፡ ሊገድለውም ፈለገ፡፡ *‹‹ለርብቃም ይህ*

*የታላቁ ልጅዋ የዔሳው ቃል ደረሰላት ታናሹን ልጅዋን ያዕቆብንም አስጠርታ አስመጣችው፥ አለችውም። እነሆ፥ ወንድምህ ዔሳው ሊገድልህ ይፈቅዳል። አሁንም ልጄ ሆይ ቃሌን ስማ ተነሣና ወደ ካራን ምድር ወደ ወንድሜ ወደ ላባ ሂድ›* አለችው። ይስሐቅንም በዔሳው ሚስቶች ምክንያት አሳመነችው። ዔሳው ከቤተሰቡ ጋር ሳይማከር ሁለት በእግዚአብሔር የማያምኑ ሴቶችን አግብቶ ነበር ፣ እነርሱም የይስሐቅንና የርብቃን ልብ ያሳዝኑ ነበር። ለዚህም ነው *ርብቃ ይስሐቅን ፦ ከኬጢ ሴቶች ልጆች የተነሣ ሕይወቴን ጠላሁት ያዕቆብ ከዚህ አገር ሴቶች ልጆች ሚስትን የሚያገባ ከሆነ በሕይወት መኖር ለምኔ ነው ?* ያለችው። ይስሐቅም ተስማማ ያዕቆብም ምንም እንኳዋን ከቤተሰቦቹ መለየት ባይፈልግም፤ ለቤተሰቦቹ ታዛዥ ነበረና የእናቱን ትእዛዝ እና ምክር ሰምቶ ለመሄድ ተዘጋጀ። *‹‹ይስሐቅም ያዕቆብን ጠራው፥ ባረከውም፥ እንዲህም ብሎ አዘዘው፦ ከከነዓናውያን ሴቶች ልጆች ሚስትን አታግባ.....ሁሉን የሚችል አምላክም ለብዙ ሕዝብ ጉባኤ እንድትሆን ይባርክህ፥ ያፍራህ፥ ያብዛህ ስደተኛ ሆነህ የተቀመጥህባትን እግዚአብሔርም ለአብርሃም የሰጣትን ምድር ትወርስ ዘንድ የአብርሃምን በረከት ለአንተ ይስጥህ፥ ለዘርህም እንዲሁ እንደ አንተ›› አለው።*

ልጆች አሁንም ለእናቱ የታዘዘው ያዕቆብ ያገኘውን በረከት አስተውሉ።

*‹‹ይስሐቅም ያዕቆብን ሰደደው፥ እርሱም ... የርብቃ ወንድም የሚሆን .... ላባ ወዳለበት ወደ ሁለቱ ወንዞች መካከል ሄደ።››* መንገድ ላይ ሌሊት ተኝቶ በሕልሙ ከምድር እስከ ሰማይ በተዘረጋ መሰላል ላይ መላእክት ሲወጡ ሲወርዱ አየ። ከመሰላሉ ጫፍም እግዚአብሔር ቆሞበት ነበር። አሁንም ቤተሰቡን ታዞ የወጣው ያዕቆብ እግዚአብሔር ባረከው፡- *እንዲህም አለው፦ ‹‹የአባትህ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ እኔ እግዚአብሔር ነኝ ይህችን አንተ የተኛህባትን ምድር ለአንተም ለዘርህም እሰጣለሁ። ዘርህም እንደ ምድር አሸዋ ይሆናል እስከ ምዕራብና እስከ ምሥራቅ እስከ ሰሜንና እስከ ደቡብ ትስፋፋለህ የምድርም አሕዛብ ሁሉ በአንተ በዘርህም ይባረካሉ።እነሆም እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፥ በምትሄድባትም መንገድ ሁሉ እጠብቅሃለሁ፥ ወደዚችም ምድር እመልስሃለሁ የነገርሁህን ሁሉ እስካደርግልህ ድረስ አልተውህምና። ያዕቆብም ከእንቅልፉ ተነሥቶ። በእውነት እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ ነው እኔ አላወቅሁም ነበር አለ።››* ያንንም ስፍራ ቤቴል አለው።

www.zeorthodox.org

ብዙ ዓመታት ቆይቶ ያዕቆብ እግዚአብሔር የገባለትን ቃል ሁሉ አድርጎለት ተመለሰ። በመንገድም ሌሊት እግዚአብሔር እንደ ሰው መስሎ ተገለጠለት። ሲታገለውም አደረ። ሲነጋ ልሒድ አለው። ያዕቆብም ካልባረከኝ አልቅህም አለው። እርሱም ባረከው ስሙም ከያዕቆብ (ተረከዝ ያዥ ማለት ነው።) ወደ እስራኤል(የእግዚአብሔር ሕዝብ ማለት ነው።) ተቀየረለት። *‹‹ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ እስራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ አይባል ከእግዚአብሔር ከሰውም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና››*

ልጆች መታዘዝ በሰውም በእግዚአብሔርም እንዲህ ያስባርካል።

## ማጠቃለያ

ያዕቆብ ከልጅነቱ ጀምሮ ለቤተሰቦቹ ታዛዥ እና በረከትን የሚናፍቅ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም በረከትን ሰጠው፡፡

## ተግባር

- ለታላላቆቻችሁና ለቤተሰብ ታዘዙ፡፡
- ሰውን ሁሉ የምታከብሩና እግዚአብሔርን የምትፈሩ ሁኑ፡፡
- ቤተሰቦቻችሁ የሚመክሩአችሁ የሚጠቅማችሁን ነው፡፡ ያዕቆብ የርብቃን ቃል እንደሰማ እናንተም ምክር የምትቀበሉ ሁኑ፡፡

www.zeorthodox.org

# ታማኙ ያዕቆብን እግዚአብሔር ረዳው

## ሃያ ሦስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች ስለ ታማኝነት ግንዛቤ አግኝተው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *« እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል፡፡ »* ሮሜ.፰፥፴፩

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ዘፍጥ.፳፱፥፩-፴፩

***መግቢያ፡-*** ልጆች እንደምን ሰነበታችሁ፤ ባለፈው ሳምንት ያዕቆብ በመታዘዙ እንደተባረከ ተምረናል፤ ለሚከተሉት የማስታወሻ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

ያዕቆብ ምን ይሠራ ነበር? እናቱ እንዴት እንዲባረክ አደረገች?

ርብቃ ያዕቆብ ወደ ሌላ ቦታ እንዲሸሽ ያደረገችው ለምን ነበር?

ይስሐቅ ያዕቆብን ወዴት እንዲሄድ መከረው?

ያዕቆብ በአባቱና በእናቱ ምክር ወደ ሶርያ ሄደ፡፡ በዚያም የእናቱን ወንድም ላባንና ልጆቹን አገኘ፡፡ ተቃቅፈው ከተሳሳሙ በኋላ በአንድነት መኖር ጀመሩ፡፡ ያዕቆብ የላባን ከብቶች ይጠብቅለት ነበር፡፡ በዛሬው ትምህርታችን ያዕቆብ ለሃያ ዓመታት በኖረበት በላባ ቤት የነበረውን ታማኝነት እና ከእግዚአብሔር ያገኘውን በረከት እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ያዕቆብ በቤተሰቦቹ ምክር በአምላኩ ረድኤት ከረጅም ጉዞ በኋላ በምሥራቅ አቅጣጫ በሁለት ወንዞች መካከል ካለው ቦታ ደረሰ፡፡ አንድ ታላቅ የውኃ ጉድጓድ ካለበት ሲደርስም፣ ከጉድጓዱ አጠገብ መንጎቻቸውን የሚጠብቁ ሰዎች አገኘ፡፡ ስለ ላባ ጠየቃቸው እነርሱም ልጁ መምጣትዋን ነገሩት፡፡ ወዲያውም ራሔል መጣች፡፡ እርሱም የርብቃ ልጅ መሆኑን ነገራት፡፡ እርስዋም ለአባትዋ ነገረችው፤ ላባም በደስታ ተቀበለውና ወደ ቤት ወሰዱት፡፡

www.zoorthodox.org

ያዕቆብ ላባን ማገልገል ጀመረ፡፡ ከብቶቹን ይጠብቅለትም ነበር፡፡ ላባ ያዕቆብን ደሞዝህን ንገረኝ አለው፡፡ እርሱም ነገረው፤ ያዕቆብም ስለ ደሞዙ ሰባት ዓመት አገለገለው፡፡ ነገር ግን ላባ ያዕቆብ ያገለገበትን የሰባት ዓመት ደመወዝ ላለመክፈል ፈልጎ አታለለው፣ ተጨማሪ ሰባት ዓመት አገልግሎ ያዕቆብ ደመወዙን እንዲወስድ ነገረው፡፡ ያዕቆብም እንዲሁ አደረገ፡፡ ሰባት ዓመት ቆይቶም ያዕቆብ

ደመወዙን ከላባ ተቀበለ፡፡

ያዕቆብ ከላባ ጋር በተነጋገሩት ቃል መሠረት ታማኝ ሆኖ አገለገለው፡፡ ላባ ቃላቸውን አፍርሶ ቢያታልለውም ያዕቆብ አልጠላውም ነበር፡፡ እንደውም ተጨማሪ ዓመታትን አገለገለው፡፡ የላባን ልጆች አግብቶ ዐሥራ አንድ ወንዶች እና አንዲት ሴት ልጅ ተወለዱለት፡፡ ብዙ ዓመታት ቆይቶ ያዕቆብ ላባን ወደ ስፍራዬ ወደ አገሬም እመለስ ዘንድ አሰናብተኝ አለው፡፡ ***‹‹ላባም፡፡ በዓይንህ ፊት ሞገስን የማገኝ ብሆንስ ከዚሁ ተቀመጥ እግዚአብሔር በአንተ ምክንያት እንደ ባረከኝ ተመልክቼአለሁና አለው፡፡ ደመወዝህን ንገረኝ፥ እርሱንም እሰጥሃለሁ አለ፡፡››***

ያዕቆብም የላባን ከብቶች እንዴት እንደጠበቀለት ፣ እግዚአብሔርም እንዳበዛው ፤ ገልጦ ለቤቴ የምሠራው መቼ ነው? አለ፡፡ ላባም መልሱ ምን ልስጥህ አለው፡፡ ያዕቆብም በጎቹንና ፍየሎቹን በመልካቸው ለይቶ ደመወዝ እንዲሰጠው እንዲህ ሲል ጠየቀው ***‹‹ከበጎችህ መካከል ዝንጕርጕርና ነቍጣ ያለበቱን ጥቁሩንም በግ ሁሉ፥ ከፍየሎቹም ነቍጣና ዝንጕርጕር ያለበቱን እነርሱም ደመወዜ ይሆናሉ፡፡››*** ላባም ***ይሁን*** አለ፡፡

ያዕቆብ ዥንጉርጉሮችን ለየ፡፡ ነጭና ጥቁሮችንም ለየ፡፡ የሦስት ቀን መንገድ ርቀት አስቀመጣቸው፡፡ ከዚያም በእግዚአብሔር ጥበብ ዥንጉርጉሮቹ እንዲበዙለት አደረገ፡፡ ልጆች ያዕቆብ የእርሱን በጎችና ፍየሎች እንዲበዙለት ለማድረግ ምን የተጠቀመ ይመስላችሁዋል?

ያዕቆብ በመጀመሪያ የተለያዩ እንጨቶችን ከዛፎች ወሰደ፡፡ እንጨቶችንም ዝንጉርጉር አድርጎ ላጣቸው፡፡ ከዚያ በውኃ ገንዳ ውስጥ ከተተው፡፡ በጎቹ ውኃ ለመጠጣት ሲመጡ በውኃው ውስጥ ያለውን ዝንጉርጉር ሽመል/እንጨት/ እያዩ ይጎመጁ ጀመር፡፡ በጎቹም ጎምጅተው ሽምልምሌ ነቁጣም መሳይ ወለዱ፡፡ ከዚያም የበረቱትን ከደከሙት ለይቶ ሽምልምሌውን አሳያቸው፡፡ የበረቱትም በዙ፡፡ ***ያዕቆብ እጅግ ባለ ጠጋ ሆነ፤ ብዙም ከብት ሴቶችም ወንዶችም ባሪያዎች ግመሎችም አህዮችም ሆኑለት፡፡***

የላባ ልጆችም ያዕቆብን፤ በአባታችን ሀብት ከበረ፤ ሲሉ ሰማ፡፡ ላባም በተነጋገሩት መሠረት ይሁን ያለውን ትቶ በያዕቆብ ላይ ፊቱን አጠቆረበት፡፡ ያዕቆብም የላባ ፊት እንደዱሮው አልዳልሆነ አየ፣ አዘነም፡፡ እግዚአብሔርም ያዕቆብን ፦ ***ወደ አባትህ ምድር ወደ ዘመዶችህም ተመለስ ከአንተም ጋር እሆናለሁ አለው፡፡*** ያዕቆብም ሚስቶቹን ልያንና ራሔልን ጠርቶ ፦ የአባታችሁ ፊት እንደዱሮው አይደለም፡፡ ነገር ግን ***የአባቴ አምላክ ከእኔ ጋር ነው፡፡*** እኔ ባለኝ ጉልበት አባታችሁን አገልግያለሁ፡፡ ***‹‹ አባታችሁ ግን አታለለኝ ፥ ደመወዜንም አሥር ጊዜ ለወጠ እግዚአብሔር ግን ክፉ ያደርግብኝ ዘንድ አልፈቀደለትም፡፡››*** የእግዚአብሔር መልአክም በሕልም እንዲህ አለኝ፦ ***‹‹ ላባ በአንተ ላይ የሚያደርገውን ሁሉ አይቼአለሁና፡፡ ሐውልት የቀባህበት በዚያም ለእኔ ስእለት የተሳልህበት የቤቴል***

www.zeorthodox.org

*አምላክ እኔ ነኝ አሁንም ተነሥተህ ከዚህ አገር ውጣ፥ ወደ ተወለድህበትም ምድር ተመለስ፡፡››*

ልያና ራሔልም *እግዚአብሔር ያለህን ሁሉ አድርግ አሉት፡፡* እርሱም ያለውን ሁሉ ይዞ በሌሊት ወደ አባቱ አገር ሄደ፡፡ የያዕቆብን መሄድ ዘግይቶ የሰማው ላባ ተከተለው፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሔር መልአክ በሕልም *ያዕቆብን በክፉ ነገር እንዳናገረው ተጠንቀቅ አለው፡፡* ሁለቱም ተገኛኙተው ተነጋገሩና ተማምለው ተለያዩ፡፡ ያዕቆብም ወደ መንገዱን ሄደ፡፡

## ማጠቃለያ

ያዕቆብ በሥራው ታማኝ ትጉህ እና ጥበበኛ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ሆኖ ያግዘው ነበር፡፡ ብዙ በረከትንም ለራሱና ለላባ ቤት አገኘ፡፡

ላባ በተቃራኒው ነው፡፡ በተከታታይ ያታልላል፤ ለገንዘብ እንጂ ለቤተሰቡ ፍቅር ትኩረት አልነበረውም፡፡ ይህም ድርጊቱ በረከት ያገኘበት ከነበረው ከያዕቆብ ጋር አለያየው፡፡

## ተግባር

- ❖ ሁሌም ታማኞች ሁኑ፡፡ እግዚአብሔር የእናንተ የሆነውን ይሰጣችኋል፡፡
- ❖ እንደ ያዕቆብም በእግዚአብሔር ፍቃድ የምተኖሩ ሁኑ፡፡

www.zeorthodox.org

# ዮሴፍ ክፉውን በበጎ አሸነፈ

## ሃያ አራተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ልጆች የይቅር ባይነትን ጥቅም ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *‹‹ ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ፡፡›› ሮሜ.፲፪፥፳፩*

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ዘፍጥ.፵፪፥፵፯

**መግቢያ፡-** ዮሴፍ ከዐሥራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች አንዱ ሲሆን፤ ወንድሞቹ ቀንተውበት ለግብጽ ነጋዴዎች አሳልፈው ሸጡት፡፡ በአንድ መኮንን ቤት በታማኝነት እየሠራ ቆይቶ ያለጥፋቱ ተከስሶ ታሰረ፡፡ በታሰረበት ወህኒ ቤት እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለሆነ ተወዳጅና ተደማጭ ነበር፡፡ አብረውት በወህኒ የነበሩ እስረኞች ሕልም ሲያዩ እየነገሩት ይፈታላቸው ነበር፡፡ ሕልም የፈታላቸው ሰዎች ስለ ዮሴፍ ለፈርዖን ስለነገሩት፤ ፈርዖንም ያያውን ሕልም እንዲፈታለት ዮሴፍን አስጠራው ፤ ዮሴፍም ሕልሙን ፈታለት፡፡ ሰባት የራብና እና ሰባት የጥጋብ ዓመታት እንደሚመጡም ተረጎመለት፡፡ ፈርዖንም ምን ማድረግ እንዳለበት ጠየቀው፡፡ እርሱም በጥጋቡ ዘመን የነበረውን ብዙ የእህል ምርት አከማችቶ በራቡ ዘመን ከተከማቸው እህል እየተጠቀመበት ክፉን ዘመን እንዲያልፍ መከረው፡፡ ፈርዖንም ይህንኑ እንዲሠራለት ዮሴፍን በግብጽ ሁሉ ላይ ሾመው፡፡

በዛሬው ትምህርታችን ዮሴፍ ከሸጡት ወንድሞቹና ከአባቱ ጋር እንደተገናኘና ለባዕድ ሀገር አሳልፈው የሸጡትን ወንድሞቹን ይቅርታ እንዳደረገላቸውም እንማራለን፡፡

## የመግቢያ ጥያቄዎች

1. በዮሴፍ ላይ ወንድሞቹ ያደረጉበትን ታስታውሳላችሁ ? ለምን ይህን አደረጉ ?
2. የፈርዖን ሕልም እና ትርጉሙስ ምን ነበር ?
3. የፈርዖን ሕልም ከተተረጐመ በኋላ ዮሴፍ ምን ሆነ ?

*መምህር በልጆች መልስ ላይ ተመርኩዘው ታሪኮችን በአጭሩ ያብራሩላቸው፡፡*

www.zeorthodox.org

## ትምህርቱ

ዮሴፍ ግብጽን በሙሉ እንዲያስተዳድር በፈርዖን ተመረጠ፡፡ በሰባቱ የጥጋብ እና የምርት ዓመታትም ዮሴፍ በግብጽ ምድር ሁሉ ዞሮ እህል ሰበሰበ በጐተራ አከማቸ፡፡ ከሰባት ዓመታት በኋላ

በግብጽ እና በዓለም ታላቅ ረኃብ ተከሠተ፡፡ በዓለም ያሉ ሰዎችም በግብጽ ሀገር እህል መኖሩን ሰምተው ከረኃብና ከችግራቸው ለመዳን ወደ ዮሴፍ እየመጡ እህል ይገዙ ነበር፡፡

የዮሴፍ ቤተሰቦችም በሚኖሩበት በምድረ ከነዓን ከፍተኛ ረኃብ ነበር፡፡ በግብጽ እህል እንዳለ ሰሙ፡፡ ያዕቆብም ልጆቹ ወደ ግብጽ ሄደው ምግብ እንዲገዙ ላካቸው፡፡ የያዕቆብ ልጆቹ እህል ሊገዙ ወደ ግብጽ ሀገር መጡ፡፡ በዚያ የንጉሡ እንደራሴ ሆኖ ከፍተኛ ሥልጣን የነበረው ወንድማቸው ዮሴፍ ነው፡፡ ወደ እርሱ ዘንድ ቀርበው ሰገዱለት፡፡ ዮሴፍም አወቃቸው፡፡ ወንድሞቹ ግን ለባርነት አሳልፈው የሸጡት ታናሽ ወንድማቸው ዮሴፍ መሆኑን አላወቁትም:: ዮሴፍ ግን የነገራቸውንም ሕልም አስታወሰ፡፡ ልጆች ዮሴፍ ወንድሞቹ ለባርነት ሳይሸጡት ያየውን ሕልም ታስታውሳላችሁ፡፡

ዮሴፍ ወንድሞቹን ከየት እንደ መጡ ጠየቃቸው፡፡ ከምድረ ከነዓን እንደመጡ ዐሥራ ሁለት ወንድማማቾች እንደሆኑና አንዱ ወንድማቸው መሞቱንም ነገሩት፡፡ አባታቸው ሽማግሌ በመሆኑ ትንሹ ወንድማቸው ከአባቱ ጋር እንደቀረም ነገሩት፡፡ ዮሴፍም በሚገባ አስተናግዶ ወደ ግብጽ የመጡበት ጉዳይ እህል እንዲጫንላቸው አደረገ፡፡ ከዚያም ከታናሽ ወንድማቸው ከብንያም ጋር እንዲመለሱ አዘዛቸው፡፡ ወደ አባታቸው ወደ ያዕቆብ ተመልሰው ፤ አይበቶቻቸውን (ጆንያዎቻቸውን) ሲከፍቱ የእያንዳንዳቸውን ገንዘብ በጆንያዎቻቸው ውስጥ አገኙ፡፡

እህሉ ሲያልቅም ያዕቆብ ሄዳችሁ እህል አምጡ ብሎ ልጆቹን አዘዘ፤ ልጆቹ ግን ብንያምን ይዛችሁ ኑ ብሎናል አሉት፡፡ እስራኤልም በሚወደው ልጁ በዮሴፍ ኃዘን ስለ ተጎዳና ብንያምንም የዮሴፍ ምትክ አድርጎ ይወደው ነበር፡፡ መጽናኛው የነበረው ትንሹ ልጁ ብንያምም በሔደበት ይቀራል ወይ ይሞታል ብሎ አዘነ፡፡ ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ ይሁዳ ዋስ ሆኖት እንዲሄዱ ፈቀደ፡፡

ወደ ግብጽ ሲደርሱም ዮሴፍ ተቀብሎ አስተናገዳቸው አለቀሰም ፣ በመጨረሻም ወንድማቸው መሆኑን ገለጸላቸው፡፡ ወንድሞቹ ግን ራሱን ሲገልጽላቸው ሊበቀለን ነው ብለው ፈሩ፡፡ ዮሴፍ ግን እግዚአብሔርን ምክንያት አድርጎ ራሱን ቤተሰቡንና ሕዝቡን ለማዳን ወደ ግብጽ እንደላከው እንጂ ክፉ ያደረጉበትን እንደማያስብ ነገራቸው፡፡ ተመልሰውም አባታቸውንና ያለውን ሁሉ ይዘው ወደ ግብጽ እንዲመጡና አብረውት እንዲኖሩ ነገራቸው፡፡ ለያዕቆብም ስጦታ ላከለት፡፡ ወንድሞቹ ዮሴፍ በሕይወት መኖሩን ለአባታቸው ተመልሰው ነገሩት፤ እርሱ ግን አላመነም፡፡ ስጦታውንም አይቶ አመናቸው፤ እጅግም ተደሰተ፡፡ ወደ ግብጽ ሄዶ ዮሴፍን ለማየት እንደሚፈልግ ነግሯቸው ቤተሰቡን ሁሉ ይዞ ሄዱ፡፡ ግብጽ እንደደረሱ ዮሴፍ አባቱን በአክብሮት ተቀበለ፡፡ ተቃቅፈውም ተሳሳሙ ወደ ፈርዖን ቤተ መንግሥትም አስገባቸው፡፡ ፈርዖንም ሲያያቸው ተደሰተ፡፡ ለቤተሰቡና ለመንጋቸው የተመረጠ ቦታ እንዲሠጣቸውም አዘዘ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

1. ዮሴፍ በአባቱ ቤት ፣ በጲጥፋራ ቤት እና በእስር ቤት ታማኝ ነበር። እግዚአብሔርም በሚበልጠው የግብፅ ቤተ መንግሥት እንዲሾም አደረገው።
2. ዮሴፍ ሥልጣንና ኃይል ቢያገኝም ክፉ ያደረጉበትን ወንድሞችን አልተበቀላቸውም። ይቅርታ አደረገላቸው። ይህን በማድረጉም ከአባቱ በረከትን ተቀበለ።

## ተግባር

ክፉውን በመልካም አሸንፉ እንጂ በክፉ አትሸነፉ

***ጥያቄዎች፣***

1. ዮሴፍ በግብጽ ሀገር በሰባቱ የጥጋብ ዓመታት ምን አደረገ ?

______________________________________________________________

2. የዮሴፍ ወንድሞችና የዓለም ሕዝቦች ወደ ግብጽ ዮሴፍ ዘንድ የሚመጡት ለምን ነበር ?

______________________________________________________________

3. ዮሴፍ ለወንድሞቹ ራሱን ሲገልጥላቸው ወንድሞቹ ምን አሉ ? ለምን ?

______________________________________________________________

4. ______________የዮሴፍ ታናሽ ወንድም ነው።
5. ዮሴፍ ***ሕይወትን ለማዳን የላከኝ*** ______________ነው። አለ።
6. ፈርዖን፤ ዮሴፍን ለቤተሰቡ______________እንዲሰጣቸው ነገረው።

www.zeorthodox.org

# ጌታችን በሰይጣን ተፈተነ

## ሃያ አምስተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ስለ ጌታችን ጾም እና በሰይጣን ስለ መፈተኑ ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**ምንባብ፡-** ማቴ. ፬÷፩-፲፩

**መግቢያ፡-** ጌታችን ለማስተማር ከመውጣቱ በፊት አርባ ቀንና ሌሊት ጾሟል፡፡ በዚህ ትምህርታችንም ጌታችን እንዴት እንደ ጾመ እና እንደ ተፈተነ ማን እንደፈተነውም እንማራለን፡፡

***የክለሳ ጥያቄዎች***

1. ጌታችንን ማን አጠመቀው ? የት ተጠመቀ ? ሲጠመቅ ስንት ዓመቱ ነበር ? ጌታችን ተጠምቆ ሲወጣ ምን ተፈጸመ ?

## ትምህርቱ

ጌታችን ከተጠመቀ በኋላ ወዲያውኑ ወደ በረሓ ለመጾም ሄደ፡፡ በዚያም አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ጾመ፡፡ ጌታችንም ከመወለዱ ከብዙ ዓመታት በፊት እንደሚወለድ ከተነበዩት ነብያት መካከል አርባ ቀንና ሌሊት የጾሙ ሦስት ነቢያት ነበሩ፡፡ እነርሱም ፡- ሙሴ በሲና /ዘጸ.፳፬÷፲፪-፲፰/፤ ኤልያስ በኮሬብ /፩ኛነገ.፲፱÷፰/ እዝራ በኢየሩሳሌም/ ሱቱኤል ፲፫÷፴፮-፵፫/ ተራራዎች ነበር፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከጾመ በኋላ ፈታኙ ሰይጣን መጥቶ ሦስት ፈተናዎች አቀረበለት፡፡

1ኛ. ድንጋዩን አንሥቶ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ ዳቦ አድርገው አለው፡፡ ጌታችንና መድኃኒታችንም ‹‹ ***ሰው በእግዚአብሔር ቃል እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም"*** አለው፡፡

2ኛ. ሰይጣን አሁንም ተመልሶ መጥቶ ስላንተ መላእክትን ያዝልሀል ተብሎአልና ራስህን ከቤተ መቅደስ ጫፍ ወደ መሬት ጣል አለው፡፡ ጌታም ‹‹***ጌታ አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ ተጽፎአል››*** አለው፡፡

3ኛ. የዓለምን ነገሥታት ክብር ያላቸውንም ሁሉ አሳይቶ ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይሄን ሁሉ አሰጥሃለሁ አለው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ***"ሂድ አንተ ሰይጣን ለጌታ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምላክ ተብሎ ተጽፎአልና"*** አለው፡፡ ያን ጊዜም ዲያብሎስ

www.zoorthodox.org

ሊያሸንፈው አልቻለምና ተወው፡፡ ቅዱሳን መላእክትም ቀርበው ያገለግሉት ነበር፡፡

## ማጠቃለያ

ነቢያት ይጾሙ ነበር፡፡ ጌታችንም ጾሞአል፡፡ በጾሙም ተፈትኖ ድል አድርጎአል፡፡

## ተግባር

በዚህ ጾም ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ቤተ ክርስቲያን እየሄዳችሁ ሥርዓቱን አስተውሉ፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. ከጌታችን በፊት አርባ ቀንና ሌሊት የጾሙ ነቢያት ስንት ናቸው? ስማቸውን ጥቀስ
2. መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጾመበት ቦታ ማን ይባላል?
3. ዲያብሎስ ጌታችንን ስንት ፈተናዎች ፈተነው?
4. "ራስህን ጣል" ያለውን ለምን ነበር?
5. ጌታችን ክፉ ሰይጣንን ካሸነፈ በኋላ ወደ እርሱ የመጡት እነማን ናቸው? ለምን?

www.zeorthodox.org

# መጻጉዕ ተፈወሰ

## ሃያ ስድስተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ልጆች የመጻጉዕን ታሪክ ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *‹‹እነሆ ድነሃል ከዚህ የሚብስ እንዳይደርስብህ ወደፊት ኃጢአት አትሥራ››* ዮሐ.፭፥፲፬

**ተጨማሪ ምንባብ** ፡- ዮሐ. ፭፥፩-፲፮

**መግቢያ፡-** መጻጉዕ ማለት ሕመምተኛ ማለት ነው፡፡ ልጆች በዐቢይ ጾም ካሉት እሑዶች አራተኛው ሰንበት መጻጉዕ ይባላል፡፡ በዚህ ቀን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕሙማንን ማዳኑ ይታሰብበታል፡፡ በተለይም መጻጉዕን የፈወሰበት ቀን ነው፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም የመጻጉዕን ታሪክ እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ጊዜ ሕመምተኞችን ይፈውስ ነበር፡፡ ብዙ ዕውራን ዐይተዋል፣ አንካሳዎች ድነው ሄደዋል፣ ለምጻሞችምንም አንጽቶአቸዋል፡፡ ሙታንን በማስነሣትም ተአምር ሠርቶአል፡፡ ጌታችን ካዳናቸው ሕሙማን ብዙዎቹ ንስሐ ገብተው ከእግዚአብሔር ጋር ኖረዋል፡፡

ጌታችን በዚህ ምድር የኖረው ሠላሳ ሦስት ዓመት ሲሆን ከሠላሳ ዓመቱ ጀምሮ ሦስት ዓመት ተዘዋውሮ አስተምሮአል፡፡ በዚህ ጊዜ ብዙዎችን ከነበረባቸው ሕመም አድኖአቸዋል፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን የአይሁድ በዓል ስለነበር ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ፡፡ በኢየሩሳሌም ቤተ ሳይዳ የምትባል አምስት በሮች የነበሩዋት መጠመቂያ ነበረች፡፡

www.zeorthodox.org

ልጆች መጠመቂያ ምንድነው? ጠበል ተጠምቃችሁስ ታውቃላችሁ? መምህር ስለጠበል ቦታና ሥርዓቱ ይንገርዋቸው፡፡

የመጠመቂያውን ውኃ የጌታ መልአክ መጥቶ ያናውጠው ነበር፤ መጀመሪያ የገባም ይፈወሳል፡፡ በዚያም መናወጡን የሚጠባበቁ በሽተኞች፣ ዕውሮች፣ አንካሶችም፣ ሰውነታቸውም የሰለለ ብዙ ሰዎች ነበሩ፡፡ ከእነዚህ በሽተኞችም ውኃው ሲናወጥ ወስዶ የሚከተው ሰው ያልነበረው አንድ በሽተኛ ነበር፡፡ እርሱም ፴፰ ዓመት በአልጋው ላይ ሆኖ እየታመመ ኖረ፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፤ *መጻጉዕ* እንዲህ እንደኖረ ማንም ሳይነግረው አውቆ፣ ልትድን ትወዳለህ? አለው፡፡ ልጆች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሕይወታችን የሚያደርግልን ሁሉ ፈቃዳችንን ጠይቆ ነው፡፡ አሁንም ይህን ሕመምተኛ ጠየቀውያም ሰው አንስቶ ወደ ተናወጠው ውኃ የሚያስገባው ይፈልግ ስለነበር፡-***‹‹ጌታ ሆይ፥ ውኃው በተናወጠ ጊዜ በመጠመቂያይቱ ውስጥ የሚያኖረኝ ሰው የለኝም ነገር ግን እኔ ስመጣ ሳለሁ ሌላው ቀድሞኝ ይወርዳል ብሎ መለሰለት፡፡››***

ኢየሱስም፦ ***ተነሣና አልጋህን ተሸከመህ ሂድ*** አለው፡፡ ወዲያውም ሰውየው ዳነ አልጋውንም ተሸክሞ ሄደ፡፡ ያም ቀን ሰንበት ነበር፡፡ ልጆች አይሁድ ተቀምጦ መዋል ብቻ፤ ሰንበትን ማክበር ይመስላቸው ነበር፡፡ ሰንበትን ማክበር ማለት ግን ማስቀደስ፣ በሽተኛ እና የታሰረ መጎብኘት፣ ያዘነንን ማጽናናትም ነው፡፡ አይሁድም ግን *መጻጉዕን*፤ ***አልጋህን ተሸክመህ ልትሄድ አልተፈቀደልህም ሰንበት ነው*** አሉት፡፡ ይህን ያሉትም የሰንበትን ትርጉም ስላልተረዱ ነው፡፡ ***እርሱ ግን፦ ያዳነኝ ያ ሰው፡፡ አልጋህን ተሸክመህ ሂድ አለኝ ብሎ መለሰላቸው፡፡*** እነርሱም ***ማነው ?*** ብለው ጠየቁት፡፡ እርሱም ብዙ ሕዝብ ስለነበር እና ክርስቶስም ወዲያው ወደ ቤተ መቅደስ ሄዶ ስለነበር፤ ማን እንዳዳነው አላወቀም፡፡

ከዚህ በኂላ ኢየሱስ በቤተ መቅደስ አገኘውና፡- ***እነሆ ድነሃል ከዚህ የሚብስ እንዳይደርስብህ ወደፊት ኃጢአት አትሥራ*** አለው፡፡ ሰውየውም ሄዶ ያዳነው ኢየሱስ እንደሆነም ለአይሁድ ነገረ፡፡

**ማጠቃለያ፡-** ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙዎችን አድኖአል፡፡ *መጻጉዕም* ከዳኑት መካከል አንዱ ነው፡፡ *መጻጉዕ* ያዳነውን አለማወቁ ያሳዝናል፡፡ ሆኖም ክርስቶስ እርሱን የሚያውቅበት እድል ሰጥቶት ነበር፡፡ በኃጢአት ከሚመጣበት ደዌ እንዳይያዝም መክሮታል፡፡ ሰውየው ግን ሲያመሰግን አልታየም፤ እንዲያውም ጌታን ለመክሰስ ፈልገው ወደጠየቁት አይሁድ ሄዶ አወራላቸው፡፡ ልጆች የእግዚአብሔርን ቸርነትና ስጦታ መዘንጋት የለብንም፡፡ በተሰጠንም አመስጋኞች መሆን ይገባናል፡፡

## ተግባር

www.zeorthodox.org

እግዚአብሔር ስለሰጣችሁ ሁሉ አመስግኑት፡፡ ልጆች ለቤተሰብ፣ ለውጭ ሰው እና ለካህናት ተለይቶ የሚነገር አለ፡፡ እንደ መጻጉዕ ጥንቃቄ የጎደለው ወሬ ማውራት የለባችሁም፡፡ ቤተሰብ አይወራም ያለንን መጠበቅ አለብን፡፡

***የክለሳ ጥያቄዎች***

1. *መጻጉዕ ማለት ምን ማለት ነው ?*

_______________

2. በቤተ ሳይዳ ምን ነበር ?

_______________

3. በቤተ ሳይዳ የነበሩት በሽተኞች ይጠባበቁ የነበረው ምንድነው?

_______________

4. ጌታችን መጻጉዕን ሲያድነው ምን ብሎ ጠየቀው ? ለምን ?

_______________

5. አይሁድ ድውዩን ***አልጋህን ተሸክመህ መሄድ አልተፈቀደልህም*** ለምን አሉት ?

_______________

6. ክርስቶስ በቤተ መቅደስ ድውዩን ሲያገኘው ምን አለው ?

_______________

www.zeorthodox.org

# ሕፃናት ጌታችንን ተቀበሉ

## ሃያ ሰባተኛ ሳምንት

***ዓላማ:-*** ክርስቶስ በክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱን ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

***ምንባብ:-*** *‹‹ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው ፤ ሆሣዕና በአርያም፡፡››* ማቴ.፳፩፥፱

***ተጨማሪ ምንባባት:-*** ማቴ.፳፩፥፩-፲፫፣ ማር.፲፩፥፩-፲፣ ሉቃ.፲፱፥፳፰-፵፰፣ መዝ.፰፥፪፣ ዘካ.፱፥፱

**መግቢያ:-** ነቢያት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአህያ ላይ ተጭኖ እንደሚመጣ እና ሕፃናት እንደሚቀበሉትም ተንብየዋል፡፡ ዛሬ የዚህን ትንቢት ፍጻሜ እንማራለን፡፡

### ትምህርቱ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ብዙ ተዓምራት ፈጽሞዋል፡፡ አዎን እርሱ ሽባው እንዲራመድ፣ ዕውራኑ እንዲያዩ፣ የማይሰሙት እንዲሰሙ አድርጓል፡፡ አንድ ቀን ÷ አይሁድ በኢየሩሳሌም በዓል የሚያከብሩበት ቀን ነበርና ብዙ ሕዝብ ለበዐሉ ተሰባስበው ነበር ፤ ክርስቶስም በአህያ ተጭኖ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ፡፡

ብዙ ተዓምራት ሲያደርግ ይሰሙ ስለነበር አልዓዛርን ከሞት ማስነሳቱም ስለተሰማ፡፡/ ዮሐ. ፲፩÷፩-ፍጻሜ / ለበዐል የተሰበሰቡት ሕዝብ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም መምጣቱን ሲሠሙ ሊቀበሉት ፣ ሊያዩትም ወጡ፡፡

ጌታችን በአህያይቱ ላይ ተጭኖ ሲገባ፡፡ የዘንባባ ዝንጠፊ ፣ የዛፍ ቅጠል ጫፍ ፣ ልብሳቸውንም እያነጠፉ በክብር ተቀበሉት፡፡ በዚህ ዕለት ልጆች ፤ በእናታቸው እቅፍ የተያዙ ሕፃናትም ሊያዩት መጡ፡፡ እንዲህ ሲሉም ዘመሩ፡፡ *‹‹ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፤ ሆሣዕና በአርያም፡፡››* ማቴ ፳፩፥፱

ደቀ መዛሙርቱ እንዲሆኑ ጌታችንና መድኃኒታችን የመረጣቸው ሐዋርያት በመጀመሪያ ምን እንደተደረገ አላስተዋሉም ነበር፡፡ በኋላ ግን ነቢያት ቀድመው የተነበዩት መፈጸሙን አስተዋሉ፡፡ መዝሙረኛው ንጉሥ ዳዊት *‹‹ከሕፃናትና ከሚጠቡ አፍ ምሥጋናን ለራስን አዘጋጀህ››* መዝ.፰÷፪ ሲል ቀድሞ ተንብዮ ነበር፡፡

ነቢዩ ዘካርያስም *‹‹ ለጽዮን ልጅ፡- እነሆ ÷ ንጉሥሽ የዋህ ሆኖ በአህያ ላይና በአህያይቱ*

www.zeorthodox.org

***ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል በሉኣት›*** ዘካር. ፱÷፱ ብሎ ነበር፡፡

ልጆች የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የማዳንና ጠፍቅር ሥራዎች በሙሉ ቀድመው በነቢያት የተነገሩ ናቸው፡፡ ዛሬም ያየነው ከእነዚህ ትንቢቶች የአንዱን ፍጻሜ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም የገባው በአህያ ላይ ሆኖ ነበር፡፡ አህያ በሰዎች የተናቀች ብትሆንም ክርስቶስ ግን ሊመሰገንባት መረጣት፤ እኛም እግዚአብሔር ከመፍጠር ያልተጸየፈውን ፍጡር መናቅ አይገባንም፡፡

ሕፃናት ***ሆሳዕና በአርያም*** እያሉ መድኃኒችንን እንዳመሰገኑት እኛም አብረን ማመስገንን ተምረናል፡፡ ለእርሱ መመስገን የባሕርዩ ነው፤ ይገባዋል፤ እኛም እርሱን በሁሉም ማመስገን የተፈጠርንበት ነው፡፡

የትንቢቱን ፍጻሜ ሐዋርያት ያስተዋሉት ዘግይተው ነው፡፡ ከተረዱ በኂላ ግን ምስክሮች ሆነዋል፡፡ ልጆች ከዕድሜያችንና ከዕውቀታችን አንጻር ቶሎ የማንረዳቸው ነገሮች ይኖራሉ፡፡ እኛ አልተረዳነውም ማለት ስሕተት ነው ማለት አይደለም፡፡ ተረጋግተን መጠየቅና ከሚያውቁት ለመረዳት መጣር አለብን፡፡ አንዳንድ ነገሮችን ያልተረዳናቸው የምናውቅበት ጊዜ ስላልደረሰም ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ሲሆን ትክክለኛውን ጊዜ በትዕግሥት መጠበቅ መልካም ነው፡፡

## ተግባር

- የሚከተለውን መዝሙር አጥኑ፡፡ የተሰጢችሁን ጥቅሶች ማታ ማታ ከመኝታችሁ በፊት አስነብቡ ወይም አንብቡ፡፡
- በቤተ ክርስቲያን የሚፈጸመውን የሆሳዕና በዓል ሥርዓት አይታችሁ እና ጠይቃችሁ፣ ለቤተሰብ አስረዱ፡፡

***መዝሙር***

www.zeorthodox.org

ሆሳዕና በአርያም እያሉ ዘመሩ ሕፃናት በኢየሩሳሌም፡፡

***ጥያቄዎች***

1. ጌታችን ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጣ ሕዝቡ እንዴት ተቀበሉት ?
2. ጌታ ወደ ኢየሩሳሌም የገባው በምንድነው ? ሕዝቡና ሕፃናት ምን ብለው ዘመሩ ?
3. ስለ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም መምጣትና ልጆች እንደሚዘምሩለት የተነበዩት እነማን ናቸው ?

# የኤማሁስ መንገደኞች

## ሃያ ስምንተኛ ሳምንት

***ዓላማ፡-*** ልጆች ስለ ክርስቶስ ትንሣኤና ለኤማሁስ መንገደኞች እንዴት እንደተገለጠ ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

***የሚጠና ጥቅስ፡-*** **"ሕያውን ከሙታን መካከል ስለምን ትፈልጋችሁ? ተነስቶአል እንጂ በዚህ የለም፡፡" ሉቃ.፳፬፥፭-፮**

***ምንባብ፡-*** ሉቃ. ፳፬፥፲፫-፲፰

***መግቢያ፡-*** ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከሞተ በኋላ በሦስተኛው ቀን ተነሣ፡፡ መጀመሪያ ለቅዱሳት አንስት ከዚያም ለሌሎች ደቀ መዛሙርቱ ተገለጠ፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም በኤማሁስ መንገድ የሆነውን መገለጥ እንማራለን፡፡

## ትምህርቱ

በጌታ መቃብር ትንሣኤውን የሚያበስር መልአክ መገለጡን፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ለመግደላዊት ማርያም እንደተገለጠ፣ የሰሙ ሁለት ደቀ መዛሙርት ከኢየሩሳሌም ወደ ኤማሁስ ሄዱ፡፡ በመንገዳቸውም ክርስቶስ ሲሰቀል ስለነበረው ሁኔታና ስለተፈጸሙት ተአምራት ይነጋገሩ ነበር፡፡ በዚህ መካከል ጌታችን ከጎናቸው ሆኖ መንገደኞቹን ስለሚነጋገሩት ነገር ጠየቃቸው፡፡ እነርሱ ግን አላወቁትም ***ስለምን እያወራችሁ ነው*** ሲላቸውም ***"በኢየሩሳሌም ብቻህን ትኖራለህ ? ወይስ በነዚህ ቀናት የሆነውንስ እንዴት አታውቅም?"*** ጌታችን ኢየሱስም መልሶ ***"ምንድን ነው?"*** አላቸው፡፡

ኢየሱስ የተባለ ነቢይ እንደተነሣና ብዙ ድንቆችን እንደፈጸመ፣ የካህናት አለቆችና መኳንቶቻቸው ግን ለሞት አሳልፈው እንደሠጡት፣ እስራኤልን ይዋጃል ብለው ይጠብቁት የነበረው ግን እርሱን እንደነበር ነገሩት፣ ከሞተ ሦስት ቀን እንደሆነውና፣ ሴቶች ግን በመቃብሩ ሥፍራ ሥጋው እንደሌለና መነሣቱንም እንዳረጋገጡ ነገሩን አሉት፡፡

ጌታችንም ***ልባቸው ከማመን የዘገየ*** መሆኑን ወቅሶ ክርስቶስ ይሄን ሁሉ መከራ ይቀበል ዘንድ አስቀድሞ በነቢያት እንደተናገረ አስረዳቸው፡፡ በክብር እንደሚነሳም አበሰራቸው፡፡ ወደ መንደሩ ሲደርሱም ስለመሸ ከነርሱ ጋር እንዲቆይ የግድ ብለው ለመኑት፡፡ ወደ ቤት ከገቡና በማዕድ ከተቀመጡ በኋላ ባርኮ የሚበሉትን ሰጣቸው ዓይኖቻቸው ተከፈቱና እርሱ ***ኢየሱስ ክርስቶስ*** መሆኑን አወቁ፡፡ ከዚያም ተሰወራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

ሲያስተምራቸው ልባቸው ይቃጠልባቸው እንደነበርና መጻሕፍትንም እንደገለጠላቸው አስተዋሉ፡፡ ወደ እየሩሳሌምም ተመልሰው በኤማሁስ መንገድ የሆነውን ተናገሩ፡፡

## ማጠቃለያ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መነሳቱን የሰሙት የኤማሁስ መንገደኞች ይህን አላመኑም ነበር፡፡ በተስፋ መቁረጥ ሲጓዙ ተስፋችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቃን እየተረጎመ፣ ተስፋቸውንም እያደሰ አጠገባቸው ነበር፡፡ ልጆች አምላካችን ሁሌም ከእኛ ጋር ነው፤ በተለያዩ መንገዶች ሲያጽናንና ሲመክረን ልንሰማው ይገባናል፡፡

የጌታችንን እውነተኛነት ሲነጋገሩ የነበሩት መንገደኞች የተበሰረላቸውን ትንሳኤና የመጻሕፍትን ትንቢት አለማመናቸው፣ ከዚህም በላይ ስለክርስቶስ ሊያምኑ የሚገባቸውን ከማመን መዘግየታቸው በጌታችን አስወቅሶቸዋል፡፡ እኛም ከዚህ ተምረን ለማመን መዘግየት የለብንም፡፡

የኤማሆስ መንገደኞች ክርስቶስን እርሱ መሆኑን ሳያውቁ ወደቤታቸው ገብተው እንዲስተናገድ የግድ ብለውታል ይህም እንግዳ ተቀባይነታቸውን ያሳያል፡፡ እኛም እንግዶችን ማስተናገድን ችላ ማለት የለብንም፡፡ ***‹‹እንግዶችን መቀበል አትርሱ፤ በዚህ አንዳንዶች ሳያውቁ መላእክትን እንግድነት ተቀብለዋልና፡፡››*** ዕብ.፲፫፥፩

በቤት አስተናግደውት ክእርሱ ጋር ሲበሉና ሲጠጡ ባርኮ ሲሰጣቸው ዐይኖቻቸው ተከፈቱ፡፡ እኛም ስንበላ ና ስንጠጣ አምላካችን እንዲባርክልን በጸሎት አንጠይቅ፣ የክርስቶስን ምሥጢር ለመረዳትም ከእርሱ ጋር በመዓድ እንቀመጥ፡፡ ይኸውም ቅዱስ ስጋውንና ክቡር ደሙን መብላትና መጠጣት ነው፡፡ ***‹‹ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ፡፡››*** ዮሐ.፮፥፶፮

## ተግባር

- ❖ ከጎደኞቻችሁ ጋር ከትምህርት ውጪ የእግዚአብሔርን ቃል መነጋገር ልመዱ፡፡
- ❖ የምትሰሙትን የእግዚአብሔርን ቃል አስተውሉ፡፡
- ❖ ስትመገቡ ጸልዩ፡፡
- ❖ ሁሌም ከቅዱስ ቁርባን አትራቁ፡፡

www.zeorthodox.org

| ***መዝሙር*** | ***ትርጉም*** |
|---|---|
| ወምድርኒ ትገብር ፋሲካ | ምድርም በክርስቶስ ደም ታጥባ |
| ተኃጺባ በደመ ክርስቶስ | ፋሲካን (ደስታ) ታደርጋለች፡፡ |

***ጥያቄዎች***

1. ጌታችን ከተነሣ በኋላ በመጀመሪያ የተገለጠው ለማን ነው ?

___

2. በኤማሁስ መንገደኞቹ ስለምን ነበር የሚያወሩት? ጌታችን ለኤማሁስ መንገደኞች የነገራቸው ምንድነው?

___

3. የኤማሁስ መንገደኞች የሚያናግራቸው ክርስቶስ መሆኑን ያወቁት መቼ ነው ?

___

www.zeorthodox.org

# ጴጥሮስ እና ዮሐንስ በቤተ መቅደስ

## ሃያ ዘጠነኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ልጆች ቅዱስ ጴጥሮስ እና ቅዱስ ዮሐንስ ***"መልካም በሚልዋት መመላለሻ"*** ያደረጉትን ተአምራት ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ‹‹ ***ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ፤ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ አለ፡፡››*** የሐዋ. ፫፥፮

**ምንባብ፡-** የሐዋ.ሥ ፫፥፩- ፍጻሜው

***መግቢያ፡-*** ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ባረገ በዐሥረኛው ቀን፣ ደቀ መዛሙርቱ ከእመቤታችን ጋር በተሰበሰቡበት ቤት መንፈስ ቅዱስ ወረደ ቤቱንም ሞላው፡፡ ደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፤ በብዙ ቋንቋዎች መናገርም ቻሉ፡፡ እንደታዘዙትም ወጥተው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማስተማር ጀመሩ፡፡ በስሙም ብዙ ተአምራት መፈጸም ቻሉ፡፡

ዛሬም ቅዱስ ጴጥሮስ እና ቅዱስ ዮሐንስ መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ያደረጉትን ተአምር እንማራለን፡፡

## ትምህርቱ

አንድ ቀን ቅዱስ ጴጥሮስ እና ቅዱስ ዮሐንስ ለጸሎት ወደ ቤተ መቅደስ ይሄዱ ነበር፡፡ የቤተ መቅደሱም መግቢያ ***"መልካሚቱ መመላለሻ"*** ትባል ነበር፡፡ በዚህች መግቢያ ከተወለደ ጀምሮ መራመድ የማይችል ሰው ነበር፡፡ ይህ ሰው በመልካሚቱ መግቢያ ተኝቶ ገንዘብ፣ ምግብ፣ ብር፣ ወርቅ፣ ልብስና ሌሎችም ስጦታዎችን በልመና እየጠበቀ ይኖር ነበር፡፡ ጴጥሮስና ዮሐንስም ወደ መቅደስ ሲመጡ ተመልክቶ ምጽዋትን ለመናቸው፡፡

www.zeorthodox.org

ጴጥሮስ ከዮሐንስ ጋር ቆሞ በትኩረት ተመለከተው እና ***" ብርና ወርቅ የለኝም፤ ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ አለው፡፡"*** በቀኝ እጁም ይዞ አስነሣው፡፡ ወዲያውም ተነሣና መራመድ ቻለ፡፡

ይህ ሰው መራመድ በመቻሉ በጣም ተደሰተ፡፡ እየዘለለና እግዚአብሔርንም እያመሰገነ ከእነርሱ ጋር ወደ መቅደስ ገባ፡፡ ሕዝቡም እያመሰገነ ሲራመድ ሲያዩት ያውቁት ስለነበረ እግዚአብሔርን አመሰገኑ፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያምኑት ብዙ ምልክቶች እና ተአምራት እንደሚከተሉአቸው ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ ነግሮአቸው ነበር። እንደነገራቸውም ደቀ መዛሙርቱ ብዙ ተአምራትን መፈጸም ችለዋል። አጋንንትን አውጥተዋል። በሽተኞችንም ፈውሰዋል።

**ማጠቃለያ፦** ጴጥሮስና ዮሐንስ ባላቸው ሁሉ መልካምን ነገር ይሠሩ ነበር። ለዘመናት በደዌ የኖረው ሰውም ሁሌም ሳያቋርጥ ወደ ቤተ መቅደስ በመመላለሱ ተፈወሰ። ቅዱስ ጴጥሮስ ያለውን ሰጥቶ ያን ሰው በእግዚአብሔር ፈቃድና ቸርነት አዳነው።

## ተግባር

- ቤተ ክርስቲያን መሄድ አታቋርጡ። የተቸገረ ስታዩ የምትችሉትን ሁሉ አድርጉ። በተደረገላችሁ እግዚአብሔርን አመስግኑ።

### *ጥያቄዎች*

1. የቤተ መቅደሱ መግቢያ ምን ይባል ነበር ?

_______________________________________________

2. በዚያ ይለምን የነበረውን ሰው ቅዱስ ጴጥሮስ ምን አደረገለት ?

_______________________________________________

*መዝሙር*

ተናገሩ ድንቅ ሥራውን መስክሩ(2)

ተአምሩን ለዓለም ንገሩ(2) ድንቅ ሥራውን መስክሩ(2)

www.zeorthodox.org

# መልአኩ ቅዱስ ጴጥሮስን ከእስር አወጣው

## ሠላሳኛ ሳምንት

**ዓላማ**:- ልጆች፤ ስለ ቅዱሳን መላእክት ተራዳኢነትና ጥበቃ ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ።

**የሚጠና ጥቅስ**:- « የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙርያ ይሰፍራል ያድናቸውማል።» መዝ.፴፫(፴፬)፥፯

**ምንባብ**:- የሐዋ. ሥራ. ፲፪፥፫-፲፱

**መግቢያ**:- ቅዱሳን ሐዋርያት ስለ ክርስቶስ እየሰበኩ ስለእርሱ ሲመሠክሩ በአይሁድና በሌሎች ኢአማንያን ብዙ መከራ ደርሶባቸዋል። በዛሬው ትምህርታችን ቅዱስ ጴጥሮስ በእስር እንደተጣለና በመልአኩ ርዳታ እንዴት እንደተፈታ እንማራለን።

### *የክለሳ ጥያቄዎች*

1. የቅዱስ ጴጥሮስ የመጀመሪያው ተአምር ምን ነበር ?
2. ደቀ መዛሙርቱ ስለ ክርስቶስ መስበክ የጀመሩት መቼ ነው ?

## ትምህርቱ

ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ መጀመሪያ ማስተማር የጀመሩት በኢየሩሳሌም ነበር። የአይሁድ መሪዎች የክርስቶስን ደቀ መዛሙርት በማሰርና በመግረፍ ዝም ለማሰኘት ሞክረዋል ። ለነገሥታቱ ይከሱዋቸውም ነበር። ከእነዚህ አንዱ ሄሮድስ የተባለው ሀገረ ገዥ ያዕቆብ የተባለውን ሐዋርያ ጥፋቱን ሳያጣራ አንገቱን አሰይፎ አስገደለው።

ሄሮድስ በዚህ አይሁድ ደስ እንደተሰኙ ሲያይ ጴጥሮስን አሰረው። ሌሎቹ ሐዋርያት እና ደቀ መዛሙርትም ይሄን ሲሰሙ ጴጥሮስ ከእስር ቤት እንዲፈታ እንዲፈታ ጸሎት ያዙ። ቅዱስ ጴጥሮስ በሰንሠለት ታስሮ ከሁለት ጠባቂዎች መካከል ተኝቶ ነበር። በውጪ ያለውን በር የሚጠብቁ ሰዎችም ነበሩ።

www.zoorthodox.org

ሁሉም ተኝተው በእንቅልፍ ላይ ሳሉ በመንፈቀ ሌሊት የእግዚአብሔር መልአክ በድንገት ተገለጠ ፤ እስር ቤቱም በብርሃን ተሞላ። ከዚያም መልአኩ ቅዱስ ጴጥሮስን ቀሰቀሰው፤ ጫማውን አድርጎ እንዲከተለውም አዘዘው። ጴጥሮስም መልአኩ እንደነገረው አደረገ። ወዲያውም ሰንሠለቶቹ ከእጁ ወደቁ። ጴጥሮስ በሕልሙ ራእይ የሚያይ ይመስለው ነበር። የእስር ቤቱን በሮች አልፈው

ወደ ዋናው የእስር ቤቱ የብረት በር ሲደርሱም ማንም ሳይነካው በሩ ተከፍቶላቸው ወጡ፡፡

በመንገድ አደባባይ ሲደርሱ መልአኩ ተሠወረው፡፡ ጴጥሮስም ጌታ መልአኩን ልኮ እንዳዳነው ተረዳና የማርቆስ እናት ወደ ማርያም ቤትም ሄደ፣ በዚያም ስለ እርሱ ጸሎት ተይዞ ነበር፡፡ እንደደረሰ በሩን አንኳኳ፡፡ ሮዴ የተባለች አገልጋይ ‹‹ማነው?›› ብላ ወደ በሩ ስትቀርብ የጴጥሮስ ድምፅ መሆኑን አወቀች፡፡ ደንግጣ በሩን ሳትከፍት በቤት ላሉት ነገረቻቸው፤ እነርሱም መጀመሪያ አላመኑዋትም ነበር፤ እርሱ መሆኑን ሲያረጋግጡ በጣም ተደሰቱ፤ ጴጥሮስም ጌታ መልአኩን ልኮ እንዴት እንዳዳነው ተረከላቸው፡፡

## ማጠቃለያ

አይሁድ በቅናት በክርስቶስና በቅዱሳን ሐዋርያት ላይ ተነሥተው ነበር፡፡ ሐዋርያት ግን በእውነት ጸንተው በፍቅር ለማሸነፍ ይጥሩ ነበር፡፡ እኛም በእምነታችንና በፍቅራችን መጽናትን እንማራለን፡፡

እንደ ሓዋርያት ለእውነት እየሠሩና በእውነት እያመኑ መከራን መታገስ ከእግዚአብሔር ዋጋ ያሰጣል፡፡ እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ ቅዱስ ጴጥሮስን ከእስር እንዳወጣው ለእኛም መላእክትን እንዲራዱን ይልክልናል፡፡

ጸሎት ታላቅ ኃይል ታደርጋለች፡፡ የሚያምን ድል ማድረግ የሚችለውም በጸሎት ነው፡፡ እኛም ለቤተሰቦቻችንም ሆነ ለራሳችን ጸሎት ብናደርግ እግዚአብሔር ከማንኛውም መከራና ኃይል ይበልጣልና ይረዳናል፡፡

ቅዱሳን መላእክት ***ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት፤*** ዕብራ.፩፥፲፬ ስለሆኑ በሚያስፈልገን ይራዱናል፡፡ ከእኛ የሚጠበቀው አምነን መጸለይ ብቻ ነው፡፡

## ተግባር

- ይህን ታሪክ ለሌሎች ንገሩ፡፡
- ሌሎቹ ስለ ቅዱስ ጴጥሮስ እንደጸለዩ እናንተም ለሌሎች ጸልዩ፡፡

www.zeorthodox.org

***መዝሙር***

**ይበራል በክንፉ ምልጃውም ፈጣን ነው**
**የአምላክ ስም አለበት ስሙም ሚካኤል ነው**
**ያሳደገኝ መልአክ ዛሬም ከእኔ ጋር ነው (2)**

## ጥያቄዎች

1. ጴጥሮስን ያሰረው ንጉሥ ማነው?

___

2. ቅዱስ ጴጥሮስ ከእስር እንዲፈታ የተጸለየው የት ነው?

___

3. ጴጥሮስን ከእስር ያወጣው ማነው?

___

4. ጴጥሮስ ከእስር እንደ ወጣ ወዴት ሄደ?

___

5. ጴጥሮስ ለምን ታሰረ?

___

www.zeorthodox.org

# ከዓሣ አጥማጅነት የተጠሩት ሐዋርያት

## ሠላሳ አንደኛ ሳምንት

**ዓላማ**:- ስለ መጀመሪያዎቹ ሐዋርያት ጥሪ ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ።

**የሚጠና ጥቅስ**:- ***"እነሆ የእግዚኣብሔር በግ አለ።... ደቀ መዛሙርቱም ሲናገር ሰምተው ኢየሱስን ተከተሉት"*** ዮሐ. ፩÷፴፮-፴፯

**ምንባባት**:- ማቴ.፬÷፲፰-፳፪፣ ማር.፩÷፲፮-፳፣ ሉቃ.፭÷፩-፲፩፣ ዮሐ.፩÷፴፭-፵፫

### መግቢያ:-

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ሆነው የተጠሩት አባቶቻችን ሐዋርያት ዐሥራ ሁለት ናቸው። ከእነዚህም በዛሬው ትምህርታችን ከዓሣ አጥማጅነት የተጠሩትን ሐዋርያት እንዴት? እና ለምን? እንደተጠሩ እንማራለን።

### ትምህርቱ:-

መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ ከእርሱ በኋላ ስለሚመጣውና ከእርሱ ስለሚልቀው ያስተምር ነበር። ብዙ ሕዝብም ይሰማው ነበር። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደርሱ ሲመጣ ባየው ጊዜ፣ አስቀድሞ ያስተማራቸው ስለእርሱ እንደነበር መሰከረ።

በቀጣዩ ቀንም መጥምቁ ዮሐንስ ከሁለት ደቀ መዛሙርቱ ጋር ነበር። ጌታችንን አይቶ ***እነሆ የእግዚአብሔር በግ*** አለ። ከዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ሁለቱም ይሄንኑ ምስክርነት ሰምተው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ተከተሉት። ጌታም ሲከተሉት አይቶ ***ምን ትፈልጋላችሁ?*** አላቸው። እነርሱም ***ወዴት ትኖራለህ*** ? አሉት። ***መጥታችሁ እዩ*** አላቸው። እነርሱም ተከተሉት፣ ከርሱም ጋር ዋሉ ። እነኚህ ሁለት ደቀ መዛሙርት እንድርያስና ዮሐንስ ነበሩ። እንድርያስም መሲሕን አግኝተናል ብሎ ጴጥሮስ የተባለውን ስምዖንን ጠራው። ዮሐ.፩÷፴፭-፵፫

በሚቀጥለውም ቀን እንድርያስ እና ስምዖን ዓሣ ሲያጠምዱ አደሩ። ያዕቆብ እና ዮሐንስም እልፍ ብለው ከአባታቸው ጋር እንዲሁ ዓሣ ለማጥመድ ይጥሩ ነበር። ነገር ግን ዓሣ አላገኙምና ተስፋ ቆርጠው መረባቸውን ማጠፍ ጀመሩ።

ጌታችንም እያስተማረ ወደ ጴጥሮስ ታንኳ ገባ። ታንኳውን ወደ መሐል ፈቀቅ እንዲያደርገውም

www.zeorthodox.org

ጴጥሮስን አዘዘው። በጴጥሮስም ታንኳ ላይ ሆኖ አስተማረ። ጌታችን አስተምሮ ሲጨርስ፣ ወደ መካከል ገብተው መረባቸውን በባሕሩ እንዲጥሉ አዘዘ። ሌሊቱን ሞክረው ባይሳካላቸውም ለጌታ በመታዘዝ መረባቸውን ጣሉ። ብዙ ዓሣም ያዙ፣ መረባቸው እስኪቀደድና የያዕቆብንና የዮሐንስን ርዳታ እስኪፈልጉም ብዙ ዓሣ አጠመዱ። ሁለቱም ታንኳዎችም በዓሣ ተሞሉ። ጴጥሮስም ከጌታ እግር ሥር ወድቆ እኔ ኃጢአተኛ ነኝና ከእኔ ራቅ አለው። ጌታችንም ***አትፍራ ከእንግዲህ ወዲህ ሰውን የምታጠምድ ትሆናለህ።*** አለው። ሁሉም እጅግ ተደነቁ። ሉቃ.፭፥፪-፲፩

ጌታችንም በመጀመሪያ እንድርያስንና ጴጥሮስ ***በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ*** አላቸው። ከዚያም ያዕቆብንና ዮሐንስን ጠራቸው። ማቴ.፬፥፲፰-፳፪ እነርሱም ***ታንኳዎችን ወደ ምድር አድርሰው ሁሉን ትተው ተከተሉት።***

*የመጀመሪያዎቹ ደቀመዛሙርት ወንድማማቾቹ ዓሣ አጥማጆች እንድርያስና ጴጥሮስ እንዲሁም ዮሐንስና ያዕቆብ ናቸው።*

## ማጠቃለያ፡-

መጥምቁ ዮሐንስ የእውነት መምህር ነው። የተጠራበትን ዓላማ ብቻ ፈጽሞአል። ዮሐንስ ሲፀነስ አስቀድሞ በመልአኩ እንደተነገረለት ኖረ። የሚያሰክር አልጠጣም፤ በጾምና በጸሎት ተወሰነ፤ የሰዎችን ልብ ለክርስቶስ ማዘጋጀትንም በሚገባው ፈጸመ። ክርስቶስም ***እውነት እላችኋለሁ፥ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ አልተነሣም፤*** ማቴ.፲፩፥፲፩ ብሎ መሰከረለት። እኛም የተጠራንበትን ከፈጸምን ጌታችን ሲመጣ ***እናንተ የአባቴ ብሩካን ኑ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ።*** ማቴ.፳፭፥፴፬ ብሎ በፍጥረት ሁሉ ፊት ይመሰክርልናል።

ዮሐንስ በትምህርት ካዘጋጃቸውና የንስሐ ጥምቀት ካጠመቃቸው ተማሪዎቹ መካከል የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት የሆኑ አሉ። እነርሱም የመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት፡- ጴጥሮስ፣ እንድርያስ፣ ያዕቆብ እና ዮሐንስ ናቸው። አራቱም ዓሣ አጥማጆች ነበሩ። የዮሐንስን ምስክርነትና የጌታችንን ጥሪ ሰምተው ሁሉን ትተው ተከተሉት። እርሱም ሾማቸው። የክርስትና ግብም ይህ ነው።

www.zeorthodox.org

የጌታችንን ቃል በመፈጸማቸው ብዙ ዓሦች አገኙ። ልጆች እኛም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ብንፈጽም አምላካችን በሥራችንና በሕይወታችን ሁሉ በረከትን ይሰጠናል። ***የአምላክህንም የእግዚአብሔርን ቃል ብትሰማ ..በረከቶች ሁሉ ይመጡልሃል ያገኙህማል።*** ዘጸ.፳፰፥፪

## ተግባር፡-

- ዮሐንስ ስለ ክርስቶስ እንደ መሰከረ እናንተም ከቤተሰባችሁ ጋር ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተነጋገሩ፡፡
- አራቱን ዓሣ አጥማጆች ፣ ሁለቱን ታንኳዎች እና ጌታችን ሲያስተምር በወረቀት ላይ ሳሉ፡፡
- ክርስቲያን ማለት የክርስቶስ ተከታይ ነው፡፡ እናንተም ለጌታችን የምትታዘዙ ሁኑ፡፡

## ጥያቄዎች

1. የዮሐንስ ደቀመዛሙርት የነበሩት ሐዋርያት ማንና ማን ናቸው ?

   ______________________________

2. በዚህ ትምህርት ጌታችንን የተከተሉት ዓሣ አጥማጆች ስንት ናቸው ?

   ______________________________

3. መጥምቁ ዮሐንስ ጌታችንን ሲያየው ምን አለ ?

   ______________________________

4. ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት የነበሩና ስለ ክርስቶስ የጻፉት እነማን ናቸው ?

   ______________________________

www.zeorthodox.org

# የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ (እግዚአብሔርን መፍራት)

## ሠላሳ ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች፤ እግዚአብሔርን ስለ መፍራት ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *‹‹የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፡፡ ››* ምሳ.፩፥፯

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ዘፍ.፴፱፥፩-፱፣ ዳን.፫፥፩-፴

### መግቢያ፡-

ልጆች በምድራችን ብዙ ዓይነት ጥበብ አለ፡፡ ሰዎች ጥበብን በተለያዩ መንገዶች ያገኛሉ፡፡ የመጀመሪያው እግዚአብሔር በሰጠን አእምሮ ስንጠቀም ነው፡፡ ሌላው ከአካባቢና ከቤተሰብ ነው፡፡ ከትምህርት ቤት የምናገኘው ጥብበም አለ፡፡ በሕይወት ልምድም ጥበብ ይገኛል፡፡

ሆኖም ሰው የቱን ያህል ጥበበኛ ቢሆን እግዚአብሔርን የማይፈራ ከሆነ የራሱ ጥበብ ራሱንና ሌሎችን ለማጥፋት ምክንያት ይሆናል፡፡ መጨረሻው የሚያምረው ጥበብ እግዚአብሔርን በመፍራት የተያዘ ሲሆን ነው፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ስለሆነው እግዚአብሔርን ስለመፍራት እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ፈጣሪ አምላካችን እግዚአብሔር እጅግ የሚወደንና የሚንከባከበን አምላክ ነው፡፡ እርሱ ስለፈቀደ ተፈጥረናል፡፡ ሲጠራንም ወደ እርሱ እንሄዳለን፡፡ ለእኛ ካለው ፍቅር የተነሣ ስንሳሳትና የዘላለም ሞትን ስናመጣ እስከሞት ወዶናል፡፡ የምንወዳቸውን ቤተሰቦች ፣ ሕይወታችንንና በጎዎችን ነገሮች ሁሉ የሰጠን እርሱ ነው፡፡ ለወደፊቱም ያሰበልንና ያዘጋጀልን መልካም ነገሮች አሉ፡፡ ይህንን አምላክ ማምለካችን ደስ ያሰኛል ፤ እርሱን መውደድ እና ማመንም ታላቅ በረከት ነው፡፡

www.zeorthodox.org

እግዚአብሔር አምላካችን የማይወዳቸው ነገሮችም አሉ፡፡ እነዚህም ክፉ ነገሮች ናቸው፡፡ ክፉ ማድረግ ራሳችንን ይጎዳናል፡፡ የተማርነውንና ያገኘነውን ጥበብ ያጠፋብናል፡፡ ለምሳሌ ተምረው አጥፊ በመሆናቸው ብቻ ሰው የማያምናቸው አሉ፡፡ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ክፉ ከማድረግ ይጠነቀቃል፡፡

**እግዚአብሔርን መፍራት ማለት እርሱ ከማይወዳቸው ነገሮች መለየት ማለት ነው፡፡ ስድብ፣**

ትእቢት፣ ስንፍና፣ ስርቆት፣ አለመታዘዝ ወዘተ እግዚአብሔር የማይወዳቸው የኃጢአት ተግባራት ናቸው፡፡ በተቃራኒው እግዚአብሔር የሚወዳቸው ትኅትና፣ መዝሙር፣ ትጉህ ተማሪ መሆን፣ ለታላላቆች መታዘዝ ወዘተ ዋጋ ያስገኝልናል፡፡ ታላላቆቹ አባቶቻችንና እናቶቻችን አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ፣ ዮሴፍ፣ ዳዊት የመሳሰሉት እግዚአብሔር አምላካችንን በመፍራት ስለኖሩ ታላቅ በረከት ተቀብለዋል፡፡

**እግዚአብሔርን መፍራት ማለት ለራሳችንና ለሌላው የሚጠቅም ነገር ማድረግ፣ ከሚጎዳም፤ ከክፉ ነገር፤ መከልከል ነው፡፡** ልጆች ይህ ማለትም እግዚአብሔር አታድርጉ የሚለን የሚጎዳንን ነው ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- መስረቅ የተወሰደበትን ሰው ስሜት እና አእምሮ ይጎዳል፡፡ ለእኛም የጥፋት ስሜት ያመጣብናል፡፡ ስንፍና የትምህርታችንን ውጤት ያበላሻል፡፡ ትዕቢት በሌሎች እንድንጠላ ያደርጋል፡፡ እነኚህ ሁሉ እኛን ይጎዳሉ፤ እግዚአብሔርን በመፍራት ከእነኚህ ስንርቅ እንጠቀማለን፡፡

እግዚአብሔርን የምንፈራው አባቶቻችንም እርሱን በመፍራት የኖሩት ለምን? ይመስላችኋል ተወያዩ ፡-

ሀ. **እግዚአብሔርን የምንፈራው ስለምንወደው ነው፡፡** *የምንወዳቸውን የሚያሳዝን ነገር መሥራት አንፈልግም፡፡ እግዚአብሔርንም ከወደድነው እናከብረዋለን እንፈራዋለንም፡፡*

ለ. **እግዚአብሔርን የምንፈራው እውነተኛ ዳኛ ስለሆነ ነው፡፡** እግዚአብሔር ሁሉንም ያውቃል ፤ ለሁሉም እውነተኛ ፍርድ ይሰጣል፡፡ ይህንን ስለምናምን በሰው ፊትም ሆነ ተደብቀን ክፉ ነገር አንሠራም፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔርን አምነን እና አክብረን ስለምንፈራው ነው፡፡

ሐ. **እግዚአብሔርን መፍራት ከክፉ ነገር ስለሚያድን እንፈራዋለን፡፡** ጠቢቡ ንጉሥ ሰሎሞን እንዲህ ሲል ይመክረናል፡፡ ***እጅግ ክፉ አትሁን፥ እልከኛም አትሁን፥ ጊዜህ ሳይደርስ እንዳትሞት፡፡ እግዚአብሔርን የሚፈራ ከሁሉ ይወጣልና ይህን ብትይዝ ከዚያም ደግሞ እጅህን ባታርቅ መልካም ነው፡፡*** መክ.፯፥፲፰ አያችሁ ልጆች እጅግ ክፉ የሆነና እልከኛ የሆነ ሰው ሌሎችንም ይጎዳል ራሱም ይጎዳል፡፡ እግዚአብሔርን የሚፈራ ግን ከክፉ ነገር ሁሉ ይወጣል፡፡

www.zeorthodox.org

መ. **እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ነው፡፡** ጠቢቡ ንጉሥ ሰሎሞን ***‹‹የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፡፡ ››*** ምሳ.፩፥፯ እንዳለን ፤ ማንኛውንም ጥበብ እግዚአብሔርን ከፈራን እናገኛለን፡፡

ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን ሁልጊዜም ይፈሩታል፤ ያከብሩታል፡፡ ልጆች እግዚአብሔርን አንዳንዴ እየፈራን ሌላ ጊዜ የምንንቀው አምላክ አይደለም፡፡ ክርስቲያን ስንሆን ሁልጊዜም እርሱን እየፈራን እያከበርን እንኖራለን፡፡ ***‹‹ ቀኑን ሙሉ እግዚአብሔርን በመፍራት ኑር፡፡››*** ምሳ.፳፫፥፲፯

***ምሳሌዎቻችን***

**ዮሴፍ፡-** አባታችን ዮሴፍ እግዚአብሔርን ይፈራ ነበር፡፡ አንድ ቀን አንዲት ሴት ክፉ ነገር እንዲሠራ አስጨነቀችው፡፡ እርሱም ***በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ*** አላት፡፡ ልጆች እናንተም እንዲሁ ጓደኞቻችሁ ሰው መሳደብ ወይም ሌላ ክፉ ነገር እንድታደርጉ ሲያስጨንቁአችሁ እንደ ዮሴፍ እግዚአብሔርን መፍራታችሁን መግለጥ አለባችሁ፡፡ ዘፍጥ.፴፱፥፩-፱

**ሦስቱ ልጆች፡-**ባቢሎን በሚባል ሀገር የነበሩ ናቸው፡፡ አንድ ጊዜ ንጉሡ ናቡከደነጾር ሰው ሁሉ እርሱ ላቆመው ምስል/ጣዖት/ እንዲሰግድ አዘዘ፡፡ እነኚህ ሦስት ሕፃናትም እግዚአብሔርን በጣም የሚፈሩ ልጆች ነበሩና ከእግዚአብሔር በስተቀር አንሰግድም አሉ፡፡ እግዚአብሔርም ከሚነድ እሳት አዳናቸው፡፡ ዳን.፫፥፩-፴

**ማጠቃለያ፡-** ልጆች እግዚአብሔርን መፍራት የጥበባትና የበረከት ምንጭ ነው፤ እግዚአብሔርን በመፍራት የኖሩ ተጠቅመውበታል፡፡ እናንተም የምትወዱትን እግዚአብሔርን ፍሩ፡፡

## ተግባር

እግዚአብሔርን ስለ መፍራት ተነጋገሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# ልደታ ለማርያም

## ሠላሳ ሦስተኛ ሳምንት

**ዓላማ**:- ልጆች፤ ስለ ድንግል ማርያም የልደት ታሪክ ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ**:- *"ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ"* ሉቃስ.፩፥፳፰

**ተጨማሪ ምንባብ** :- የግንቦት ፩ ስንክሣር ፤ ነገረ ማርያም፡፡

**መግቢያ**:- የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ቅድስት ድንግል ማርያም ፤ እግዚአብሔር በቅድስናና በንጽሕናዋ እናቱ እንድትሆን የመረጣት ናት፡፡ በዛሬው ትምህርታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እናት ስለ ድንግል ማርያም የልደት ታሪክ እንማራለን፡፡

## ትምህርቱ

በኢየሩሳሌም ባዕለ ጸጋ የሆኑ ነገር ግን ንብረታቸውን የሚወርስ ልጅ ያልነበራቸው ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ነበሩና ልጅ እንዲሰጣቸው ዘወትር ይጸልዩ ነበር፡፡ አንድ ቀን ላም ልጅ ስትወልድ የተወለደችዋም ሌላ እየወለደች ስድስት ትውልድ ከደረሰ በኋላ፤ ስድስተኛዋ ጨረቃ ስትወልድ ፤ ጨረቃዋም ፀሐይ ስትወልድ በሕልማቸው አዩ፡፡

እንደ ዮሴፍ ሕልም ወደሚተርጉም ሰው ሄደው ያዩትን ሕልም ነገሩት፡፡ ሕልሙ ልጅ እንደሚያገኙ መሆኑን፤ ላሞቹም እስከ ስድስት ትውልድ የሚወልዱ ሴቶች ልጆቻቸው እንደሆኑ፤ ጨረቃዋም በስድስተኛው ትውልዳቸው የምትወለድ ታላቅ ሴት ልጅ እንደምትሆን ከተረጎመላቸው በኋላ ፀሐይ ምን እንደሆነ መተርጎም እንዳልቻለ ነገራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

ጥንዶቹም ሕልም ተርጓሚው እንደነገራቸው እስከ ስድስት ትውልድ ልጆችና ቤተሰቦች ተወለዱላቸው፡፡ የስድስተኛው ትውልድም ሐና ትባላለች፡፡ ቤተሰቦቿም ኢያቄም ለተባለ መልካም ሰው አጋቡዋት፡፡ ኢያቄም እና ሐና አብረው ለረጅም ጊዜ ኖሩ፡፡ ልጅ ሳይወልዱም አረጁ፡፡ ሐና እና ኢያቄም ድሆችን የሚረዱና ለእግዚአብሔር ትእዛዝም ታማኞች ነበሩ፡፡ ተስፋ ሳይቆርጡ በመጸለያቸው እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ሰምቶ መልአኩን ወደ ኢየቄም ላከ፡፡

የእግዚአብሔር መልአክ ለኢያቄም ተገልጾ የተወደደች ልጅ እንደሚሰጣቸው አበሠረው፡፡

ኢያቄም ለሐና ነገራት ሐናም በእምነት ተቀብላ እና አምና ጠበቀች፡፡ ሁለቱም በሕልም ተረድተው ሐና ፀነሰች፡፡ የመውለጃ ጊዜዋ አልፎ ስለፀነሰችም ዘመዶቿ ተደነቁ፡፡ ሐና አንድ ዓይና አክስት ነበረቻት፡፡ አንድ ቀን ሐና መፀነስዋን ሰምታ ሆዷን በእጅዋ ደስሳ ካረጋገጠች በኋላ ዓይኗን በዚያው እጅዋ ስትነካው የታወረው አንድ ዓይኗ በራላት፡፡

ሌሎች ሰዎች ይሄን ተአምር ሰምተው በመምጣት በተአምር ተፈወሱ፡፡ ነገር ግን አይሁድ ቀንተው ሐና እና ኢያቄም እንዲሰደዱ አደረጉ፡፡ ወደ ሊባኖስ ተራራም ተሰደዱ፡፡ በዚያም ግንቦት ፩ ቀን ሐና ቆንጆዋንና ተወዳጅዋን ልጅ ወለደች፤ ስሟንም ማርያም አለቻት፡፡ እንደስለታቸውም ድንግል ማርያም እስከ ዐሥራ አምስት ዓመቷ በቤተ መቅደስ እያገለገለች ኖረች፡፡ እግዚአብሔርም በቅድስና ኖረው በንጽሕና ከወለድዋት ልጃቸው ከድንግል ማርያም ተወልዶ ዓለምን ለማዳን ፍቃዱ ሆኖ መረጣት፡፡

## ማጠቃለያ

እመቤታችን የተወለደችው በቅድስና ከኖሩ ቤተሰቦች ነው፡፡ ይህም ነቢዩ ዳዊት ***መሠረቶችዋ በተቀደሱ ተራሮች ነው፡፡*** ያለውን ያስታውሰናል፡፡ መዝ.፹፮(፹፯)፥፩፡፡ እኛም በቅድስና ብንኖር ቤተሰቦችዋ ነን፡፡

ኢያቄምና ሐና በእምነት እየኖሩ የፈለጉትን ባያገኙም፣ የሰማይ አባታቸውን እግዚአብሔርን በተስፋ ይጠባበቁ ነበር፡፡ እርሱም መልካም ልጅ ታላቅ ስጦታ ሰጣቸው፡፡ እኛም እግዚአብሔርን ፈቅዶ የሚሰጠንን በእምነትና በተስፋ መጠባበቅን እንማራለን፡፡

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ግንቦት ፩ ቀን የተወለደችው፤ በሊባኖስ ተራራ ነበር፡፡ ዛሬም ያንን ለማሰብ ከቤት ተወጥቶ በቤተ ክርስቲያን ወይም በሰፈር ይከበራል፡፡ ይህም ከሰፈር አድባር  እየተባለ አንዳንድ ሰዎች ከሚያደርጉት የተሳሳተ ድርጊት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር

- የእመቤታችንን ልደት በመንፈሳዊው ክብር ተሳተፉ፡፡

***መዝሙር***

*ምሥራቀ ምሥራቃት ሙፃዓ ፀሐይ*

እግዝእትነ ዘመና ሙዳይ

ዘመና ሙዳይ (4) ማርያም ዘመና ሙዳይ

***ጥያቄዎች፦***

1. የእመቤታችን ቅደመ አያቶች ሕልም ምን ነበር ?

2. ሐና እመቤታችንን ስትፀንስ ምን ዓይነት ተአምር ተከሠተ

3. ድንግል ማርያም የተወለደችው የት ነው? ለምንስ ወላጆቿ ወደዚያ ሄዱ ?

4. በስተእርጅናው ልጅ እንዲሚወልድ ኢያቄምን የነገረው ማነው ?

5. በታሪኩ በጨረቃና በፀሐይ የተመሰሉት ማንና ማን ናቸው ?

www.zeorthodox.org

# ዘመነ ጰራቅሊጦስ እና ለሐዋርያነት የተመረጠው ማትያስ

## ሠላሳ አራተኛ ሳምንት

**ዓላማ**:- ማትያስ ለሐዋርያነት ስለ መመረጡና ስለ በዓለ ጰራቅሊጦስ ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ**:- *‹‹በዚህች አገልግሎትና ሐዋርያነት ስፍራን እንዲቀበል የመረጥኸውን ከእነዚህ ከሁለቱ አንዱን ሹመው አሉ››*

ሲጸልዩም፡፡ ‹‹የሁሉን ልብ የምታውቅ አንተ ጌታ ሆይ፥ ይሁዳ ወደ ገዛ ራሱ ሥፍራ ይሄድ ዘንድ በተዋት በዚህች አገልግሎት ሐዋርያነት ሥፍራን እንዲቀበል የመረጥኸውን ከእነዚህ ከሁለቱ አንዱን ሹመው አሉ፡፡ ዕጣም ተጣጣሉላቸው፣ዕጣውም ለማትያስ ወደቀና ከዐሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋር ተቆጠረ፡፡››

**ምንባብ**:- የሐዋ.፩÷፲፭-፳፮

**መግቢያ**:- ክርስቶስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ፣ አንድ መቶ ሃያው የክርስቶስ ቤተሰቦች በቤት ተሰብስበው ይጸልዩ ነበር፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዐሥራ ሁለት ደቀመዛሙርት ነበሩት ከእነርሱ አንዱ የአስቆሮቱ ይሁዳ ነው፡፡ እርሱም ጌታችንን ካደ፤ በእርሱ ምትክም ማትያስ ተተካ፡፡ በዛሬው ትምህርታችን በይሁዳ ምትክ ሐዋርያ እንዲሆን ስለተመረጠው አባት ስለማትያስ አመራረጥ እንማራለን፡፡

## ትምህርቱ

www.zeorthodox.org

ጌታችን ከሞት ከተነሣ ከአርባ ቀናት በኋላ፣ ደቀ ዛሙርቱን በደብረዘይት ሰበሰባቸው፡፡ መንፈስ ቅዱስን እስኪቀበሉ በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ አዘዛቸው፡፡ ኃይልና ጽናት እንደሚቀበሉም ነገራቸው፡፡ መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላም ለአሕዛብ ሁሉ ስለእርሱ እንዲያስተምሩ አዘዛቸው፡፡ እየባረካቸውም ዐረገ፤ ደመናም ሰወረችው፡፡ ደቀ መዛሙርቱ ክርስቶስ ካረገ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው በአንድነት እየጸለዩ ቆዩ፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እና ሌሎቹ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑም አብረው ነበሩ፡፡ ብዛታቸውም አንድ መቶ ሃያ ነበር፡፡

በዚያው ወራት ቅዱስ ጴጥሮስ ተነሥቶ ቆመ፡፡ ክርስቶስን በካደው በይሁዳ ምትክ

ስለሚመረጠው ተናገረ። ይሁዳ ክርስቶስን እንደካደውና ኃጢአቱ ወደ ሞት እንደመራውም አስረዳ።" ***ስለዚህ ከእነዚህ አንዱ ከእኛ ጋር የትንሣኤው ምስክር ይሆን ዘንድ ይገባል።"*** አለ። ሁሉም በሐሳቡ ተስማሙ፤ ከዚያም ጌታችን ሲያስተምር በደንብ የሚያውቁት፤ በመውጣት በመግባት አብረው የነበሩ ሁለት ደቀ መዛሙርት ዮሴፍና ማትያስ ተመረጡ። በሁለቱም ላይ በአንድነት ጸለዩ፤ እንዲህም አሉ፡ ***"የሁሉን ልብ የምታውቅ አንተ ጌታ ሆይ.... የመረጥኸውን ከእነዚህ ከሁለቱ አንዱን ሹመው"*** ብለው ጸለዩ። እጣም ተጣጥለው ለማትያስ ወጣ ፤ ማትያስም ከዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ጋር ዐሥራ ሁለተኛ ሆኖ ተቆጠረ።

ደቀ መዛሙርቱም ጌታችን እንዳዘዛቸው በኢየሩሳሌም ቆዩ። ጌታችን ወደሰማይ ከዐረገ ከዐሥር ቀናት በኋላም ፣ ሁሉም ተሰብስበው ሳሉ መንፈስ ቅዱስ በእሳት አምሳል ወረደ። የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ኃይልና እና በብዙ ልሳን መናገርን ተቀበሉ። የተለያየ ቋንቋ የሚናገሩና ከተለያዩ አካባቢዎች ወደ ኢየሩሳሌም ለበዓል የተሰበሰቡ ብዙ ሕዝቦች ነበሩ። ነገር ግን ሁሉም የደቀ መዛሙርቱን ንግግር በራሳቸው ቋንቋ ይሰሙ ነበር።

ቅዱስ ጴጥሮስ ከሌሎች ሐዋርያት ጋር ሆኖ ስለ ክርስቶስ አስተማረ ፣ 3000/ሦስት ሺሕ/ ያህል ሰዎችም በዚያችው ቀን በትምህርቱ አምነው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ። ለክርስቶስ ቤተሰቦች (ለደቀ መዛሙርቱ) መንፈስ ቅዱስ የተላከበትና ደቀ መዛሙርቱ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ የተቀበሉበት ዕለት ጰንጠቆስጤ ይባላል። ሃምሳኛ ቀን ማለት ነው። ክርስቶስ በተነሣ በሃምሳኛው ቀን ይህ ተፈጽሞልና ሃምሳኛ ተብሏል።

## ማጠቃለያ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካረገ በኋላ አንድ መቶ ሃያው ቤተሰብ ማትያስን በይሁዳ ምትክ መርጠዋል። መንፈስ ቅዱስን ተቀብለውም በዓለም በሙሉ አስተምረዋል።

## ተግባር

ለመወሰን ስትቸገሩ ጸልዩ።

www.zeorthodox.org

### *የሙከራ ጥያቄዎች*

(1.) ጌታችንን የከዳው ደቀ መዝሙር ____________ ይባላል።

(2.) በይሁዳ ምትክ የተተካው ሐዋርያ ________________ ይባላል።

(3.) በይሁዳ መተካት እንዳለበት የተናገረው ሐዋርያ ____________ ነው።

(4.) የሚተካውን ሐዋርያ ለመምረጥ መጀመሪያ__________አድርገው። ከዚያ በ____ ለዩ።

(5.) ሐዋርያት ጌታችን በተነሣ በ__________ቀን መንፈስሠቅዱስን ተቀበሉ።

# ትጋት

## ሠላሳ አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች ትጉህ ስለመሆን ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"ለሰው የከበረ ሀብት ትጋት ነው፡፡"* ምሳ.፲፪፥፳፯

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ማቴ.፳፭፥፩-፴

**መግቢያ፡-** ልጆች ለጥናት፣ ለትምህርት፣ ለጸሎት፣ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ምን ያህል ቀድማችሁ ትዘጋጃላችሁ? በሚገባው ሰዓትና ጊዜስ መሥራት ያለባችሁን ትፈጽማላችሁ? ትጋት ማለት ምን ማለት ነው? አንድ ልጅ ትጉህ ልጅ ነው የሚባለው ምን ሲያሞላ ነው ? ሰነፍ ልጅስ ምን ዓይነት ልጅ ይመስላችኋል ? መምህር ከትምህርቱ ዓላማ አንጻር ተማሪዎች ጥያቄዎቹ ላይ ትኩረት ሰጥተው እንዲመልሱ ይርዱዋቸው፡፡

ክርስቲያን ትጉህ ነው፡፡ መጽሐፍ ***‹‹ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፤ ››*** ፪ኛ ጴጥ.፩፥፭ እንዳለን፤ የእምነት ሕይወታችን በትጋት የሚታይ ነው፡፡ ስንፍናን እግዚአብሔር አይወድም፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም ስለ ትጋት እንማራለን፡፡

## ትምህርቱ

### ፩. ትጋት

ልጆች ትጋት ማለት በብርታት እና በጊዜው መሥራት ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ልጅ የትምህርት ሰዓቱን አክብሮ ለመገኘት፤ አስቀድሞ በጠዋት ከመኝታው መነሣት፣ ንጽሕናውን ጠብቆ አስፈላጊውን ዝግጅት ሁሉ ካደረገ በኋላ በሰዓቱ ትምህርት ቤት ከሄደ ትምህርቱን በአግባቡ ከተከታተለ፣ የሚሰጠውን ጥያቄም ሆነ የቤት ሥራ በወቅቱ ከሠራ፣ ለፈተና ተዘጋጅቶ ጥናቱን በየጊዘው በፕሮግራም አጥንቶ ውጤታማ ተማሪ ከሆነ፤ ለትምህርት ያለውን ትጋት ያሳየናል፡፡

www.zeorthodox.org

ትጉህ ክርስቲያን ደግሞ ጠዋትና ማታ ለመጸለይ፣ ቤተ ክርስቲያን ለመሳለም ለማስቀደስ፣ ለመቁረብ፣መልካም ሥራ ለመሥራት፣ ሁል ጊዜም አይሰንፍም፡፡ ወንጌል ለመማር ወደ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ሲመጣም ቀድሞ ነው፡፡ ይህንንም ሁሉ ሲያደርግ ***‹‹ ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉ፥ የምታደርጉትን ሁሉ በትጋት አድርጉት››*** ቆላስ.፫፥፳፫ የተባለውን የእግዚአብሔርን

ቃል እያሰበ ነው፡፡

ልጆች የአንድ ትጉህ አረጋዊ ታሪክ እንነግራችኋለን፡፡ ይህ አባት በጣም ሸምግሎ ለመራመድ ቢያቅተውም ጠዋት፣ ጠዋት ወደ ቤተ መቅደስ ይሄዳል፤ ይጸልያልም፡፡ ይህ ትጋቱ ታላቁ መጽሐፍ ላይ ተጽፎለታል፡፡ *« እነሆም፥ በኢየሩሳሌም ስምዖን የሚባል ሰው ነበረ፥ ይህም ሰው የእስራኤልን መጽናናት ይጠባበቅ ነበር፤ ጻድቅና ትጉህም ነበረ፥ መንፈስ ቅዱስም በእርሱ ላይ ነበረ፡፡»* ሉቃ.፪፥፳፭ ተብሎ ተጽፎአል፡፡ ትጉህ ተማሪ በትምህርቱ ጥሩ ውጤት ያመጣል፡፡ የነገ ብሩህ ተስፋ ይኖረዋል፡፡ ትጉህ ክርስቲያንም ከእግዚአብሔር ዋጋ ያገኛል፡፡ *"ለሰው የከበረ ሀብትም ትጋት ነው፡፡"* ምሳ.፲፪፥፳፯

**፪. ስንፍና ፣ ልግመት እና ቸልተኛነት**

በትጋት የምናገኘውን ዋጋ የሚያስቀሩብን ነገሮች አሉ፡፡ እነርሱም ፦ ስንፍና፣ መለገም እና ቸልተኛነት ናቸው፡፡ ከእነዚህ መራቅ አለብን፡፡

ስንፍና ይጎዳል፤ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጡት አምስቱ ደናግል ሰነፎች ነበሩ፡፡ በወቅቱ ተዘጋጅተው ዘይት አልያዙም፤ ሥራቸውን ዘግተው በቸልተኛነት ስንፍና ይዟቸው ተኝተው ነበር፡፡ ልባሞቹም ዘይታቸውን አዘጋጅተው ነበር፡፡ ንጉሡ ሲመጣ፣ ተነሡ ተቀበሉት ተባለ፡፡ ሁሉም መብራታቸውን አበሩ፡፡ የሰነፎቹ ዘይት ትንሽ ስለነበር መብራታቸው ሊጠፋባቸው ደረሰ፡፡ ልባሞች የሆኑት ተዘጋጅተው የጌታን መምጣት ይጠባበቁ የነበሩትን ጎበዞች ደናግላን፤ ‹‹***መብራታችን ሊጠፋብን ስለሆነ ከዘይታችሁ ስጡን***› አሉዋቸው፡፡ ልባሞቹም ለሁላችንም ሳይሆን እንዳይጠፋብን ፣ ከሚሸጡት ግዙ አሉዋቸው፡፡ ሰነፎቹ ዘይት ሊገዙ ወጥተው ሲመለሱ በሩ የሚዘጋበት ሰዓት ደረሰና ተዘጋ፡፡ መግባት ሳይችሉ ከንጉሡ ድገስና ሰርግ ቀሩ፡፡ ማቴ.፳፭፥፩-፲፫ ልጆች ሰነፎቹ ደናግል እንዴት እንደተጎዱ አያችሁ፡፡ እናንተም *« **የትጉህ አሳብ ወደ ጥጋብ ያደርሳል** ...፡፡»* ምሳ.፳፩፥፭ እንደተባለው ሁኑ፡፡

ልግመት፦ መሥራት እየቻለ በእንቢተኛነትና በቸልታ የሚዘናጋ አለ፡፡ ይህ ሰው ትምህርቱን የሚያጠናው፣ የሚጸልየው፣ ቤተ ክርስቲያን የሚመጣው ለሌላ ሰው ስለሚመስለው፤ በሁሉም ይለግማል፡፡ ማለትም ቀስ ብሎ፣ ወይም ሰው ፊቱ ሥላለ ብቻ የሚያጠናና የሚጸልይ ይመስላል፡፡ ነገር ግን የሚለግመው ልጅ ትምህርቱን በየጊዜው ሳይሰለች እና ሳያቋርጥ ስለማያጠና፤ በሥራው ሁሉ ልግምተኛ እና ሰነፍ ስለሆነ በትምህርቱም በፈተና ይወድቃል፤ በሕይወቱም ይጎዳል፡፡ ሳይሰለቹ በትጋት መማርና መሥራት እንዲሁም ታማኝ ሆኖ መገኘት ሁሉ ጥቅሙ ለራሳችን ነው፡፡

www.zeorthodox.org

አንድ ጌታ ሦስት ባሮቹን ጠርቶ ለአንዱ አምስት፣ ለአንዱ ሁለት፣ ለሦስተኛውም አንድ መክሊት ሰጠው፡፡ ሁለቱ ወጥተው ወርደው ተግተው በመሥራት ብዙ ትርፍ አተረፉበት፡፡ ባለ አምስቱ ዐሥር፣ ባለ ሁለቱም አራት አደረጉ፡፡ አንድ የተሰጠው ግን ልግመኛ ስለነበር የተሰጠውን ቀበረው፡፡ ጌታቸው መጥቶ የሰጣቸውን ምን እንዳደረጉበት ሲጠይቃቸው፤ ሁለቱ ጎበዞች ትርፋቸውን አሳዩ፡፡ ጌታቸውም በትጋታቸውና በሠሩት ሥራ እያንዳንዳቸውን እጅግ ተደስቶባቸው

በጥቂት ታምነህል በብዙ እሾምሃለሁ፡፡ አላቸው፡፡ ልጆች በትጋት መሥራት ለጊዜው አድካሚ ቢመስልም ለዘለቄታው ግን ታላቅ ዋጋ ያስገኛል፡፡ በመጨረሻ አንድ መክሊት የተቀበለው ቀርቦ፡፡ ጌታ ሆይ፥ ካልዘራህበት የምታጭድ ካልበተንህባትም የምትሰበስብ ጨካኝ ሰው መሆንህን አውቃለሁ፡፡ ፈራሁም ሄጄም መክሊትህን በምድር ቀበርሁት፤ እነሆ፥ መክሊትህ አለህ፤ አለ፡፡

ይህ ሰው ልግመቱ ሳያንሰው የመለሰው መልስ አሳዛኝ ነበር፡፡ ንጉሡም እጅግ ተቆጥቶ እንዲህ አለው፡- ***አንተ ክፉና ሃኬተኛ ባሪያ፥ ካልዘራሁባት እንዳጭድ ካልበተንሁባትም እንድሰበስብ ታውቃለህን ? ስለዚህ ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ልትሰጠው በተገባህ ነበር፥ እኔም መጥቼ ያለኝን ከትርፉ ጋር እወስደው ነበር፡፡ ስለዚህ መክሊቱን ውሰዱበት ዐሥር መክሊትም ላለው ስጡት፤*** ማቴ. ፳፭፥፲፭-፴፡፡ ልጆች እናንተም በቤተ ሰባችሁ፣ በትምህርት ቤትም ሆነ፣ በቤተ ክርስቲያን፣ ስትጸልዩም ሆን ስትላኩ « ***ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ፤*** » ሮሜ.፲፪፥፲፩

አንዳንድ ልጆች ደግሞ ቸልተኞች ናቸው፡፡ ሁሉንም በግድየለሽነት ያደርጋሉ፡፡ ልብሳቸው ቆሽሾ አይቀይሩም፣ ጫማቸው ተፈቶ እየጠለፋቸው አያስሩትም፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጡም ቸልተኞች ስለሆኑ አይሳለሙም፤ ከጸሎት ከትምህርት ይልቅ በጨዋታና በሳቅ ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ፡፡ ሌሎቹን ኅበዞች ይረብሻሉ፡፡ ቸልተኛነት ግን ያስቀጣል፡፡ ጫማ አለማሰር ጠልፎ እንደሚጥል ሁሉ፤ በቸልተኛነት መኖርም ከላይ እንዳየነው ባርያ ያስቀጣል፡፡

በመሆኑም ልጆች እናንተ ትጉሃን መሆን አለባችሁ፡፡ የእግዚአብሔር ልጆች ትጉሃን ናቸው፡፡ እናንተም፡- ጠዋት በሰዓታችሁ ተነሥታችሁ ለትምህርት በመዘጋጀት፣ ትምህርት ቤት በሰዓቱ በመድረስ፣ በክፍል ውስጥ እንደኅበዝ ተማሪ በመሳተፍ፣ የጥናት ሰዓታችሁን በአግባቡ በመጠቀም ፣ በጸሎት ሰዓታችሁ እና በቤተ ክርስቲያን ተሳትፎኣችሁ በትጋት በመሳተፍ ከእግዚአብሔር ዋጋ ለማግኘት ትጉ፡፡ " ***ለሰው የከበረ ሀብት ትጋት ነውና፡፡*** " ምሳ.፲፪፥፳፯

## ማጠቃለያ

www.zeorthodox.org

- በዛሬው ትምህርታችን ስለ ትጋት ተምረናል፡፡ ትጉህ ልጆች በሰውና በእግዚአብሔር ፊት ትጉህ ይሆናሉ፡፡
- ስንፍና ፣ ልግመት እና ቸልተኛነት፤ ትጉህ በመሆን የምናገኛቸውን መልካም ውጤትና በረከት እንዳያሳጡን እንጠንቀቅ፡፡

## ተግባር

- በተማራችሁት መሠረት ትጉህ ሁኑ፡፡

# የቤተ ክርስቲያን ግቢ አቀማማጥ

## ሠላሳ ስድስተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ልጆች ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"ፊተኛይቱም ደግሞ የአገልግሎት ሥርዓትና የዚህ ዓለም የሆነው መቅደስ ነበራት፡፡"* ዕብራ.፱፥፩

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ፩ኛ ቆሮን.፲፩፥፴፣ ፩ኛተሰሎ.፭፥፲፱

**መግቢያ፡-** ልጆች ቤተ ክርስቲያን ሁሉንም በአግባብ የምትፈጽምበት ሥርዓት አላት፡፡ ይህም ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ይባላል፡፡ በዚህ ሥርዓት መሠረትም የቤተ ክርስቲያን ግቢ እንደየአገልግሎቷ ጠባይና ሁኔታ እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡

**ልጆች፡-** ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገባ ወንዶች በየትኛው በር ይገባሉ? ሴቶችስ ? ቤተ ልሔም የሚባለውን የቤተ ክርስቲያን ቦታስ ታውቁታላችሁ? መቅደስ፣ ቅድስት እና ማሕሌት ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ደጀ ሰላም የሚባል ቦታም አለ፡፡ በዚያ ምን የሚደረግ ይመስላችኋል? ሁላችሁም የተጠመቃችሁበት/ክርስትና የተነሣችሁበት/ ቤት አለ፡፡ በየትኛው አቅጣጫ ይገኛል፡፡ ስሙስ? ማን ይባላል? ትምህርት የሚሰጥበት ቦታም አለ፡፡ ዓውደ ምሕረት ይባላል፡፡ ለምን በዚህ ስም የተጠራ ይመስላችኋል?

በዛሬው ትምህርታችን በቤተ ክርስቲያን የሚገኙትን ቦታዎች እና አገልግሎታቸውን እንማራለን፡፡

## ትምህርቱ

www.zeorthodox.org

**፩. ቤተ መቅደስ፡-** ልጆች ቤተ መቅደስ የምንለው ዋናውን ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን/በቤተ ክርስቲያን ግቢ/ መካከል እና ጉልህ ቦታ ላይ ይተከላል፡፡ ይህም ሦስት ዓይነት ሲሆን ፡- ዋሻ ፣ ሰቀልማ እና ክብ ይባላሉ፡፡

**ዋሻ፡-** አንድ በር ብቻ ያለውና በመጋረጃ የሚከፋፈል ነው፡፡

ለምሳሌ፡- ዋሻ ተክለ ሃይማኖት/አዲስ አበባ/፡፡

**ሰቀልማ፡-** ብዙ በር እና ጉልላት አለው፡፡ ለምሳሌ ቦሌ መድኃኒዓለም፡፡

**ክብ፡-** የሚባለውም ቅርጹ ክብ ሆኖ አንድ ጉልላት ብቻ አለው፡፡ የበሩ ብዛትም ሦስት ነው፡፡

*ሦስቱም አብያተ መቃድስ(መቅደሶች)፡-* ቅኔ ማሕሌት ፣ ቅድስት እና መቅደስ የሚባሉ ክፍሎች ከውስጥ አሉዋቸው፡፡

**ቅኔ ማሕሌት፡-** ቅኔና ምሥጋና ማለት ነው፡፡ በዚህ ክፍል በቅኔና በዜማ ለእግዚአብሔር ምሥጋና ይቀርባል፡፡

**ቅድስት፡-** ልጆች ቅድስት የምትቆርቡበት ቦታ ነው፡፡

***መቅደስ፡-*** ካህናት ብቻ የሚገቡበትና ቅዳሴ የሚቀድሱበት ክፍል ነው፡፡

፪. **ቤተ ልሔም፡-** የእንጀራ ቤት ማለት ነው፡፡ ከቤተ መቅደሱ በስተ ምሥራቅ (በፀሐይ መውጫ) በኩል ይገኛል፡፡ በዚህም መሥዋዕቱ /ቅዱስ ቁርባን/ ይዘጋጃል፡፡

፫. **ክርስትና ቤት፡-** አዳዲስ ክርስቲያኖች የሚጠመቁበት ቤት ነው፡፡

፬. ***ዓውደ ምሕረት፡-*** ከሕንጻው ቤተ ክርስቲያን በምዕራብ በኩል ያለው በረንዳ ዓውደ ምሕረት/የምሕረት አደባባይ/ ይባላል፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚነበቡበት፣ ትምህርተ ወንጌል የሚሰጥበት፣ በንግሥ በዓል ቀን ታቦት ወጥቶ የሚቆምበት፣ ካህናትና የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ፣ የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች ያሬዳዊ ዜማ፣ ወረብ የሚያቀርቡበት ቦታ ነው፡፡

፭. ***ዕቃ ቤት፡-*** ይህ ቤት የቤተ ክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳት የሚቀመጡበት ነው፡፡

፮. **ደጀ ሰላም፡-**ካህናትና ምእመናን ከቅዳሴ መልስ/በኋላ/ እህል ውኃ የሚቀምሱበት ቦታ ነው፡፡ ከቤተ መቅደስ ርቆ ይሠራል፡፡

፯. **አዳራሽ እና ቢሮዎች፡-** በእነዚህ ደግሞ የሰንበት ትምህርት ቤቶች እና ሌሎች ጉባዔያት ይካሄዳሉ፡፡ የቢሮ ሥራዎችም ይሰራሉ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

- በዛሬው ትምህርታችን ***ክብ ፣ ለቀልማ እና ዋሻ*** የሚባሉ ሦስት ዓይነት የሕንጻ ቤተ ክርስቲያን አሠራር እንዳለ፤ እያንዳንዱ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያንም ፡- ***ቅኔ ማሕሌት፣ ቅድስት እና መቅደስ*** ተብለው እንደሚከፈሉ ተምረናል፡፡
- ቤተ ልሔም፣ ዓውደ ምሕረት እና ክርስትና ቤት መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጥባቸው ክፍሎች ሲሆኑ፡፡ ዕቃ ቤት ፣ ደጀ ሰላም እና ቢሮዎችም ተጨማሪ የአገልግሎት ክፍሎች ናቸው፡፡

## ተግባር

ልጆች የአብያተ ክርስቲያናቱን ዓይነት ግቢያቸውን፣ አከፋፈላቸውን እና የአገልግሎታቸውን ሁኔታ እንዲጎበኙ ይደረግ።

### *የክለሳ ጥያቄዎች*

1. የቤተ ክርስቲያን ሥሪት ዓይነቶች ስንት ናቸው ? ምን ምን ይባላሉ ?

_______________________________________________

2. ቅኔ ማሕሌት ማለት ምን ማለት ነው ?

_______________________________________________

3. የምንቆርብበት ቦታ ምን ይባላል ?

_______________________________________________

4. በዓውደ ምሕረት ምን ይደረጋል ?

_______________________________________________

5. አንድ በር ያለው የቤተ ክርስቲያን ዓይነት ምን ይባላል ?

_______________________________________________

www.zeorthodox.org

# ለሌሎች ያለን ፍቅር

## ሠላሳ ሰባተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች፤ ለሌሎች ስለሚኖረን ፍቅር በቂ ግንዛቤ አግኝተው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***‹‹ ፍቅር ለዘላለም አይወድቅም፡፡››*** ፩ኛ ቆሮ.፲፫ ÷ ፰

**ተጨማሪ ምንባብ፡-**

**መግቢያ፡-** እንደምን ሰነበታችሁ የተወደዳችሁ የእግዚአብሔር ልጆች፤ በዛሬው ትምህርታችን ለሌሎች ሊኖረን ስለሚገባው ፍቅር እንማራለን፡፡ ሌሎችን ስትወዱ ለሌሎች ያላችሁ ፍቅር በምን መንገድ ይገለጣል፡፡ ክርስትና ተግባራዊ ኑሮ ነው፡፡ ፍቅር ደግሞ ከሁሉም ይበልጣል፡፡ ታዲያ ይህንን ከሁሉም የሚበልጥ አገልግሎት እንዴት እንፈጽማለን፡፡

በዛሬው ትምህርታችን እነዚህን ነጥቦች እንዳስሳለን፡፡

## ትምህርቱ

ፍቅር ተፈጥሮአዊ ነው፡፡ እያንዳንዱ ፍጥረት በፍቅር እንዲኖር ሆኖ ተፈጥሮአል፡፡ ፀሐይ፤ ብርሃንና ሙቀት ለሁሉም ትሰጣለች፤ ላምም ወተትዋን ትሰጠናለች፡፡ በአካባቢ ሳይንስ እንደተማ ራችሁት ወይም በአካባቢያችሁ እንደምታዩት ሁሉም ፍጥረት ለልጆቹ ፍቅር አለው፡፡ ይህም ፍቅር በተፈጥሮ እግዚአብሔር ለሁላችንም የሰጠን ጸጋ መሆኑን ያስረዳናል፡፡

እኛም ለሌሎቹ የምናከፍለው እና ከሌሎች ጋር የሚኖረን ፍቅር በሚከተለው መንገድ ይገለጣል፡፡

**፩. ለሌሎች ያለን ፍቅር በሐሳብና በቃላት ይገለጣል፡፡**

www.zoorthodox.org

ለሌላው መልካም ማሰብ፤ መጸለይ፤ ጥሩ ጥሩውን መመኘት ሌሎችን የመውደዳችን ማሳያ ነው፡፡ ለእኛ የምንፈልገውን ሌሎች ወንድምና እኅቶቻችን እንደሚያስፈልጋቸው አውቀን ፤ ማድረግ ባንችል እንዲያገኙ መጸለይ ይገባል፡፡

ለሌሎች ያለንን ፍቅር በቃላችን መግለጽም ይገባል፡፡ ይህም ወዳጃችንን ደስ ያሰኘዋል፡፡ ወዳጅነታችንንም ያጠነክራል፡፡ በዕድሜ ከፍ ያሉ አረጋውያን ወይም በአልጋ የተኙ ሕሙማንን እግዚአብሔር ይማራችሁ ማለት በቃላችንም እንደምንወዳቸው መግለጽ ከመድኃኒቱ እኩል

ይጠቅማቸዋል፡፡ በመንፈስ እንዲጠነክሩ፣ እንዲጽናኑ ያደርጋቸዋል፡፡

**፪. እውነተኛ ፍቅር በተግባር የሚገለጥ ነው፡፡**

በሐሳብና በቃላት የገለጥነው ፍቅር እውነተኛ ከሆነ በተግባርም መታየት አለበት፡፡ « ***ልጆች ሆይ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ፡፡***» ፩ኛ ዮሐ.፫፥፲፰ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ያለውን ፍቅር የገለጠልን እስከሞት በታየ እውነተኛ ተግባር ነው፡፡ እኛም ለሌሎች ያለንን ፍቅር በተግባር ማሳየት አለብን፡፡

በአንድ ወቅት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አንድ ሰው ቀርቦ ለሌሎች መልካም ስለማድረግ ጠየቀው፡፡ ጌታችንም እንዲህ አለው፡- አንድ ሰው ወንበዴዎች ደብድበውት በመንገድ ወደቀ፤ ሁለት ሰዎች አይተውት ፊታቸውን አዙረው እንዳላዩት ሆነው አለፉ፡፡ ሦስተኛም አንድ ሳምራዊ መጣ፤ እርሱም የወደቀውን ሰው አነሣው፣ ቁስሉን የሚያድን ዘይት አደረገለት፣ በአህያ ጭኖ ወደ ሚረዳበት ቦታ አደረሰው፡፡ የሚያስፈልገውንም አወጣለትና አደራ ብሎ ሄደ፡፡ ሉቃ.፲፥፴-፴፯

ልጆች የእኛም ፍቅር እንደ ሳምራዊው በተግባር የሚገለጥ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ከቤተሰብ ጀምሮ ለሰው ሁሉ ያለን ፍቅር በተግባር መታየት አለበት፡፡

**፫. ለሌሎች ያለንን ፍቅር ከስሕተት በማረማችንም ይታወቃል፡፡**

አንዳንድ ልጆች እና የምንወዳቸው ሰዎች ሊሳሳቱ ይችላሉ፡፡ ክፉ ነገር እንድናደርግ ሊገፋፉን፣ ሊጋብዙንም ይችላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ አብረን መሳሳት ፍቅራችንን አይገልጽም፤ ስሕተታቸውን በማረም እንዳይጎዱ ብናደርግ ግን መውደዳችን ይታወቃል፡፡ **ለምሳሌ፡-** በአንድ ወቅት ልጆች ተሰባስበው አንድ ሽማግሌ ላይ፤ ***አንተ መላጣ ውጣ ፣ አንተ መላጣ ውጣ፡፡*** እያሉ አፌዙበት፡፡ ከመካከላቸው ተዉ የሚልና ስሕተታቸውን የሚያርም ልጅ አልነበረም፡፡ ያ ሰው በጣም አዘነ፡፡ የትልቅ ሰው ሐዘን በጣም ይጎዳል፡፡ በዚህ ጊዜ ድብ የሚባል አውሬ ከጫካ ወጥቶ በአረጋዊው ሰው ላይ ያላገጡትን አርባ ሁለቱን ልጆች ሰባበራቸው፡፡ ፪ኛ ነገሥ.፪፥፳፫-፳፭ ልጆች ከመካከላቸው ሆኖ ጥፋታቸውን የሚያርም መልካም ልጅ ቢኖር እነዚህ ልጆች ባልተጎዱ ነበር፡፡

www.zoorthodox.org

እናንተም በቤተ ክስቲያን እንደመማራችሁ ሌሎችን ስትወዱ ከሚጎዱበት ስሕተት እያረማችሁ መሆን አለበት፡፡ በሚጎዳ ነገር እና ስሕተት በሆነ ነገር መተባበር ፍቅር አይደለም፡፡

**፬. ለሌሎች ያለን ፍቅር የሚገለጠው በመከራ ጊዜም ነው፡፡**

እውነተኛ ፍቅር ሰዎች በተጎዱ ቀን በምናደርገው ነገር ይታወቃል፡፡ ሰዎች በከፋቸው ቀን አቅማችሁ የሚፈቅደውን አድርጉ፡፡ ዮናታን የንጉሡ ሳዖል ልጅ ሲሆን ፤ ዳዊት እረኛ ነው፡፡ ዳዊት ጎልያድን ድል በማድረጉ ሰዎች ያደንቁት ነበር፡፡ ንጉሡም ቀንቶ ሊገድለው ፈለገ፡፡ ዳዊትም

እግዚአብሔር የቀባውን ንጉሥ አክብሮ ሸሸ፡፡

የንጉሡ የሳዖል ልጅ ዮናታን ከወዳጁ ከዳዊት በችግሩ ጊዜ አልተለየም፡፡ ዳዊትና ዮናታን የልብ ወዳጆች ነበሩ፡፡ (፩ኛ ሳሙ.፲፰፥፩-፬) ሳዖል ዳዊት ሊገድለው ሲያስጠራው አሁንም ወደ ነብዩ ሳሙኤል ሸሸ፡፡ ሳዖል መልእክተኞችን ልኮ እንዲሁም ራሱ ሄዶ ሊገድለው ሲል ዳዊትን እግዚአብሔር ረድቶት አመለጠ፡፡ (፩ኛ ሳሙ.፲፱፥፩-፳፬) ዳዊት ተደብቆ ዮናታንን አገኘው እርሱም በድብቅ ምልክት ሰጥቶ እንዳይሞት ረዳው፡፡ (፩ኛ ሳሙ.፳፥፩-፵፪) እናንተም ለወዳጆቻችሁ ያላችሁ ፍቅር በመከራም ቀን ይሁን፡፡

## ማጠቃለያ

፩. ለሌሎች ያለን ፍቅር በቃላት ፣ በተግባርና በክፉ ቀናቸውም ከጎናቸው በመሆን በማጽናናት የሚገለጥ ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሌሎች ሊኖረን የሚገባውን ፍቅር በተግባር አሳይቶናል፡፡

፪. ሌሎችን መውደድ በሕህተታቸው በመተባበር አይደለም፤ በፍቅር እና በትኅትና በመተራረም ነው፡፡

## ተግባር

❖ ፍቅራችሁን ያላችሁን በማካፈል ግለጡት፡፡ ለምሳሌ ትርፍ አሻንጉሊት ያለው ለሌለው ልጅ ይሰጣል፡፡ በትምህርቱ ጎበዝ የሆነው ልጅ የደከመውን ጓደኛውን ያስጠናል፡፡

❖ የተሳሳቱ ወዳጆቻችሁን ከጥፋታቸው ከስሕተታቸው እንዲመለሱ በትኅትና አርሙዋቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ጸሎት

## ሠላሳ ስምንተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ልጆች፣ የጸሎትን አስፈላጊነት እና ሥርዓት ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***‹‹በስፍራ ሁሉ አለ ቍጣና አለ ክፉ አሳብ የተቀደሱትን እጆች እያነሡ እንዲጸልዩ እፈቅዳለሁ፡፡››*** ፩ኛጢሞ.፪፥፰

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ፩ኛ ነገሥ.፫፥፩-፲፬፣ ሉቃ.፲፯፥፲-፲፱

**መግቢያ፡-** ሁል ጊዜም እንድንጸልይ ያስተማረን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ***« ሳይታክቱም ዘወትር ሊጸልዩ እንዲገባቸው የሚል ምሳሌን ነገራቸው፤››*** ሉቃ.፲፰፥፩፣ ስለዚህ ክርስቲያን ዘወትር መጸለይ አለበት፡፡ በዛሬው ትምህርታችን የጸሎትን ጥቅም እና ሥርዓት እንማራለን፡፡ ልጆች እንዴት ትጸልያላችሁ ? ጸሎት ለምን ያስፈልጋል? በቀን ስንት ጊዜ ትጸልያላችሁ?

## ትምህርቱ

### ፩. የጸሎት አስፈላጊነት

**ሀ. ለምስጋና፡-** የምንጸልየው ለምሥጋና ነው፡፡ አምላካችን ልዑል እግዚአብሔርን ዘወትር ማመሥገን ስለሚገባን ለጸሎት እንቆማለን፡፡ እግዚአብሔር ምሥጋና ይባዋል፡፡ ምክንያቱም እርሱ የፈጠረን ነው፣ የሚያኖረንም እርሱ ነው፡፡ በሕይወታችን ስላደረገልንና ስለሚያደርግልንም ምሥጋና ማቅረብ አለብን፡፡ ማንም ቢሆን ለእግዚአብሔር የሚያቀርበው የተለየ ስጦታ አይኖረውም፤ እግዚአብሔርም ከእኛ የሚፈልገው ምሥጋና ብቻ ነው፡፡ መምህር ሉቃ.፲፯፥፲-፲፱ ተርከው ፣ ከትምህርቱ አንጻር ያብራሩላቸው፡፡

www.zeorthodox.org

**ለ. ለልመና (የሚያስፈልገንን ለመጠየቅ)፡-** አባታችን ልዑል እግዚአብሔር በሕይወታችን የምንፈልጋቸውን ሁሉ ይሰጠናል፡፡ የምንፈልገውን የምንጠይቀውና የምንቀበለውም በጸሎት ነው፡፡‹‹ ***አምናችሁም በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ አላቸው፡፡››*** ማቴ.፳፩፥፳፪፡፡ አባታችን ያዕቆብም እንዲህ ሲል ይመክረናል፡፡ ***‹‹ከእናንተ ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል››*** ያዕ.፩፥፭ ጸሎት የምንፈልገውን

በተለይም ለእኛ መልካም የሆነውን ከእግዚአብሔር የምንቀበልበት ነው። ንጉሥ ሰሎሞን በልጅነቱ ሲነግሥ *‹‹አቤቱ አምላኬ ሆይ፥ እኔን ባሪያህን በአባቴ በዳዊት ፋንታ አንግሠኸኛል እኔም መውጫንና መግቢያን የማላውቅ ታናሽ ብላቴና ነኝ።..........መልካሙንና ክፋውንም እለይ ዘንድ ለባሪያህ አስተዋይ ልቡና ስጠኝ።››* ብሎ ጸለየ። እግዚአብሔርም *‹‹ እኔ እንደ ቃል አድርጌልሃለሁ እነሆ ፥ ማንም የሚመስልህ ከአንተ በፊት እንደሌለ ከአንተም በኋላ እንዳይነሣ አድርጌ ጥበበኛና አስተዋይ ልቡና ሰጥቼሃለሁ።››* ፩ኛ ነገሥ.፫፥፯-፲፬ አለው።

ዓይነ ሥውሩ በርጤሜዎስ በሙሉ ልቡ አምኖ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን የዓይን ብርሃኑ እንዲመልስለት ማየት ይችል ዘንድ ለመነው፤ ጌታችንም ዓይኑን አበራለት። ማር.፲፥፵፮-፶፪ እኛም የምንፈልገውን በጸሎት እንቀበላለን።

**፪. እንዴት እንጸልያለን?**

ልጆች ሁሉም ሰው በተለያየ መንገድ ይጸልያል። በቤተ ክርስቲያን በማኅበር ሆነን በምንጸልየው ጸሎት በአንድነት እግዚአብሔርን ለማምለክ ስንቆም የሚከተሉትን እንድንፈጽም መጽሐፍ ቅዱስና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ያስተምሩናል።

***ሀ. ቀጥ ብሎ በእግር መቆም።*** ማንኛውም ክርስቲያን ካልታመመ ወይም ከእቅሙ በላይ ካልደከመው በስተቀር፤ በሁለት እግሩ ቀጥ ብሎ በመቆም መጸለይ አለበት። ይህም ለአምላኩ ያለውን ክብር ለመግለጥ ነው።

**ለ. እጆችን በመዘርጋት ይጸለያል።** ይህም ሁሉን ማድረግ የሚቻለው ቸር እና ይቅር ባይ አምላክ መሆኑን በማመን፤ ከእግዚአብሔር ለመቀበል መጠበቅንና የመስቀል ምልክት በመሥራት ሰይጣንን ለማሸነፍ ነው። ሙሴ እጁን ዘርግቶ ሲጸልይ ሕዝበ እስራኤል ድል ያደርጉ ነበር። ዘጸ.፲፯፥፰-፲፯ ቅዱስ ጳውሎስም *‹‹በስፍራ ሁሉ አለ ቍጣና አለ ክፉ አሳብ የተቀደሱትን እጆች እያነሡ እንዲጸልዩ እፈቅዳለሁ።››* ፩ኛ ጢሞ.፪፥፰ ብሎአል።

ሐ. ዓይኖቻችንን ወደ ሰማይ በማንሣት እንጸልያለን። እንዲህ እንድንጸልይ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፤ በተግባር ሲያሳየን *‹‹ ወደ ሰማይ ዓይኖቹን አነሣና እንዲህ አለ፦ አባት ሆይ፥ ሰዓቱ ደርሶአል፤ ልጅህ ያከብርህ ዘንድ፥ በሥጋም ሁሉ ላይ ሥልጣን እንደ ሰጠኸው፥ ለሰጠኸው ሁሉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸው ዘንድ ልጅህን አክብረው።››* ዮሐ.፲፯፥፩

**መ. ፊታችንን እና መላ ሰውነታችንን በመስቀል ምልክት በማማተብ እንጀምራለን።** ጣታችንን በመስቀል ምልክት እናዘጋጃለን፦ ማለትም ጠቋሚ ጣታችንን ወደ ላይ ቀጥ አድርገን ሦስቱን ጣቶች በእኩል በማጠፍ ፤ አውራ ጣታችንንም በጠቆሚ ጣታችን ስር በማጠፍ ወይም በማዘነበል በመስቀል

www.zeorthodox.org

ምልክት አድርገን እናዘጋጃለን። ከዚያም ከራስ ወደ ደረት፣ ከግራ ትከሻ ወደ ቀኝ ትከሻ እጃችንን በማመላለስ የመስቀል ምልክት እየሠራን ሦስት ጊዜ እናማትባለን። ይህም ለምናምንበት በመስቀል የተገለጠውን ኃይል ከአምላካችን ለመለመንና ጠላታችንንም በመስቀል በተገለጠው የክርስቶስ ኃይል ለማሸነፍ ነው። ስናማትብ የእግዚአብሔርን ስም ***በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ***፡ እንላለን።

### ፫. መቼ እንጸልይ?

ልጆች የተለያየ የጸሎት ጊዜያት አሉ። ለምሳሌ በቤተ ክርስቲያን በዘወትር ቀናት ጠዋትና ማታ ይጸለያል። ይህም የሰርክና የነግህ ጸሎት ይባላል። በጾም እና በበዓላትም ወቅት የሚጸለዩ ጸሎቶች አሉ። እነርሱም ቅዳሴ ፣ ሰዓታትና ማሕሌት ይባላሉ። በገዳም ያሉ አባቶችም በቀን ሰባት ጊዜ ይጸልያሉ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ዳዊት በቀን ሰባት ጊዜ፣ ነቢዩ ዳንኤልም በቀን ሦስት ጊዜ ይጸልዩ ነበር። *መዝ.፻፲፰(፻፲፱)፥፻፷፬፣ ዳን.፮፥፲*

እኛም ከትምህርት እና ከሥራ ጠባያችን አንጻር እንደገዳማውያንና እንደ ቅዱሳኑ መጸለይ ስለማንችል ጠዋትና ማታ መጸለይ አለብን። ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንገባ፣ የአምላካችን ርዳታ በሚያስፈልገን ጊዜም ጸሎት ማድረግ ይጠቅመናል።

## ማጠቃለያ

ጸሎት ለሕይወታችን አስፈላጊ ነው። ክርስቲያን ዘወትር መጸለይ አለበት። በሥርዓቱ መሠረት ጸሎት ማድረግ በረከትን ያስገኝልናል።

## ተግባር

ልጆች በጸሎት በርቱ። ያልገባችሁን ከቤተሰብ እና ከመምህራችሁ በመጠየቅ በተማራችሁት መሠረት በተግባር አውሉ።

www.zeorthodox.org

# አባታችን ሆይ እና እመቤታችን

## ሠላሳ ዘጠነኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ልጆች፤ በየዕለቱ ማድረግ ስለሚገባቸው ጸሎት ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠኑ ጥቅሶች፡-**

- ❖ ‹‹ *በጸሎት ትጉ* ›› ሮሜ.፲፪፡
- ❖ ‹‹ ***እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብጽዕት ይሉኛል፡፡*** ›› ሉቃ. ፩፥፵፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃ.፲፩፥፩-፲፫፡፡

**መግቢያ፡-** ***"አባታችን ሆይ"*** ብለን የምንጸልየውን የጌታ ጸሎት ታውቃላችሁ ? ይህ ጸሎት ማን እንደሀጠንስ አውቃችኋል? እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ፣ የምንለውንስ ጸሎት ታውቃላችሁ?

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ያስተማራቸውን ጸሎት ***"አባታችን ሆይ"***ን እና ለጌታችን እናት ለቅድስት ድንግል ማርያም የሚገባትን ክብር የምናቀርብበትን ጸሎት እንማራለን፡፡

## ትምህርቱ፡-

### ሀ. የጌታ ጸሎት

አንድ ቀን ሐዋርያት ጸሎት እንዲያስተምራቸው ጌታችንን ጠየቁት፡፡ ሉቃ.፲፩፥፩-፫ እርሱም ስትጸልዩ እንዲህ በሉ አላቸው፡፡

www.zeorthodox.org

***"አባታችን ሆይ"*** ብለን የምንጸልየው ጸሎት ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው ስለሆነ ***"የጌታ ጸሎት "*** ተብሎ ይጠራል፡፡ በዚህ ጸሎት ጌታችን የሚከተሉትን አስተምሮናል፡፡

- ❖ እግዚአብሔርን ማመስገን፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወታችን እንዲፈጸም መጋበዝ
- ❖ የዕለት ምግባችንን መጠየቅ
- ❖ ይቅር እንድንባል ሌሎችን ይቅር በማለት ንስሐ መግባትን

- ከፈተና እንዲያወጣን መለመንና ከክፉ እንዲጠብቀን መጸለይ፡፡
- እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ነን እርሱም አባታችን ነው፡፡ ስለዚህ አባታችን ሆይ ብሎ አስተምሮናል፡፡

እኛም እንደ እግዚአብሔር ልጆች መኖርና ትእዛዙን መጠበቅን ሌሎችን በመውደድ ማሳየት አለብን፡፡

**ለ. በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል**

ልጆች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፡- የጌታችን እናት ነች፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመስቀል ላይ እነኋት እናትህ ብሎ ሰጥቶናል፡፡ ***ትውልድ ሁሉ ብጽእት*** እንዲላት እና ***የምድር አሕዛብ በፊትዋ እንዲማለሉ*** ሉቃ.፩፥፵፰፤ መዝ.፵፬(፵፭)፥፲፮-፲፯ ጸጋ ተሰጥቶአታል፡፡

በዚህ መሠረትም ለእመቤታችን የሚገባውን ምስጋና የምናቀርብ በምልጃዋ የምንማጸንበት ጸሎት ***በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል*** ይባላል፡፡ ይህን ጸሎት በግእዝና በአማርኛ እናጠናለን፡፡

**ማጠቃለያ፡-** ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ብለን መጸለይ እንዳለብን አስተምሮናል? እኛም እንዲሁ ዘወትር እንጸልያለን፡፡

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፤ በትውልዱ ሁሉ እንደምትመሰገን ከመንፈስ ቅዱስ የተነገረላትን ትንቢት ለመፈጸም በመቻላችን እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን፡፡

## ተግባር

የተማራችሁትን ጸሎት በቃል አጥኑ፡፡

www.zeorthodox.org

| | |
|---|---|
| አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር ስምህ ይቀደስ<br>መንግሥትህ ትምጣ፣<br>ፈቃድህ በሰማያት እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን፣<br>የዕለት እንጀራችንን ስጠን ለዛሬ፣<br>በደላችንን ይቅር በለን፤ እኛም የበደለሉን ይቅር እንደምንል፣<br>አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን፣<br>ከክፉ ሁሉ አድነን እንጂ፣<br>መንግሥት ያንተ ናትና<br>ኃይል ክብር ምስጋና ለዘለዓለሙ አሜን፡፡ | አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ<br>ትምጻእ መንግሥትከ<br>ወይኩን ፈቃድከ፣በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር፣<br>ሲሣየነ ዘለለ ዕለትነ ኃበነ ዮም፣<br>ኅድግ ለነ አበሳነ ወጌጋየነ ከመ ንኅነኒ ንኅድግ ለዘ አበሰለነ<br>ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት፣<br>አላ አድኅነነ መባልሐነ እምኲሉ እኩይ<br>እስመ ዚአከ ይዕቲ መንግሥት<br>ኃይል ወስብሐት ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡ |

| አማርኛ | ግእዝ |
|---|---|
| እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ፤ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እንልሻለን፤ በሐሳብሽ ድንግል ነሽ በሥጋሽም ድንግል ነሽ፡፡ የአሸናፊው የእግዚአብሔር እናት ሆይ ሰላምታ ላንቺ ይገባሻል፡፡ ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ የማኅፀንሽም ፍሬ ቡሩክ ነው፤ ጸጋን የተሞላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ፤ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነውና ከተወደደው ልጅሽ ከጌታችንና ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ይቅርታንና ምሕረትን ለምኚልን፤ ኃጢአታችንን ያስተሰርይልን ዘንድ ለዘለዓለሙ አሜን፡፡ | በሰላም ቅዱስ ገብርኤል መልአክ ኦ እግዝእትየ ማርያም ሰላም ለኪ ድንግል በሕሊናኪ ወድንግል በሥጋኪ እመ እግዚአብሔር ጸባዖት ሰላም ለኪ ቡሩክት አንቲ እም አንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርስኪ፡፡ ተፈሥሒ ፍሥሕት ኦ ምልእተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ፡፡ ጸልዩ ወሰአሊ ምሕረተ ኀበ ፍቁር ወልድኪ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ ይስረይ ለነ ኃጣውኢነ አሜን ፡፡ |

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ዮሐንስ ሐዊር

## አርባኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች፤ የቅዱስ ዮሐንስ ሐዊርን ታሪክ ተገንዝበው፣ ጽኑ በሆነ እምነት የሚፈጽመውን መታዘዝም ተረድተው የመታዘዝን ፍሬ በማድረግ ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *‹‹ የሁላችሁን መታዘዝ እያሰበ ፍቅሩ በእናንተ ላይ እጅግ በዝቶአል፡፡›› ፪ኛ* ቆሮ.፯÷፲፭

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** የጥቅምት ፳ ቀን ‹‹መጽሐፈ ስንክሳር›› እና ‹‹በበረሓው ጉያ ውስጥ›› በዲ/ን ዳንኤል ክብረት

**መግቢያ፡-** ልጆች ስለ መታዘዝ የተማራችሁትን ታስታውሳላችሁ፡፡ መታዘዝ የሚያስገኘው ጥቅም ምንድነው? እናንተስ ለወላጆቻችሁ፣ ለታላላቆቻችሁ፣ ትታዘዛላችሁ? ከሆነ ጎበዞች የማትታዘዙ ከሆናችሁም ልጆች የእግዚአብሔርን ዘለዓለማዊ ፍቅርና በረከት ለማግኘት ከዛሬ ጀምሮ መታዘዝ አለባችሁ፡፡

በዛሬው ትምህርታችን የታዛዡን አባት የቅዱስ ዮሐንስ ሐዊርን ታሪክ እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

### እድገቱና ጥሪው

ቅዱስ ዮሐንስ ሐዊር በላይኛው ግብጽ ቴባን በምትባል መንደር ተወለደ፡፡ ቤተሰቦቹ በኑሮአቸው ድሆች ነበሩ፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ግን በእምነት እና በመልካም ሥራ የበለጸጉ ነበሩ፡፡ ዮሐንስ ሐዊር በ፲፰ ዓመቱ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ወደ ገዳመ አስቄጥስ ሄደ፡፡ በዚያም አባ ባሞይ የተባሉ አባት አገኘ፡፡ በትኅትና እግራቸው ላይ ወድቆ በምንኩስና መኖር እንደሚፈልግ ነገራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

አባ ባሞይም፤‹‹ምንኩስና ከባድ ነው፡፡ በበረሐ በብቸኝነት መኖር፣ የራስህንና የሌሎችንም ምግብ በድካም ማዘጋጀት፣ ሌሊትና ቀን መጸለይ፣ አብዝቶ መጾምም ይኖርብሃል፡፡ ይህን ለማድረግ አትችልምና ወደ ዓለም ሄደህ ኑር›› አሉት፡፡ ዮሐንስም የመጣሁት በእግዚአብሔር ፍቃድ ነው፡፡ እርሱም ያስችለኛል፡፡ አባቴ በአንተ ጸሎት ፈተናዎችን የምቋቋምበት ኃይል አገኛለሁ፡፡ በገዳማዊ ሕይወት አብሬህ እንድኖር ፍቀድልኝ አለው፡፡

አባ ባሞይም የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ፍቃድ በጸሎት ጠየቀ፡፡ የእግዚአብሔር መልአክ ተገልጦ *እግዚአብሔር እንደ እኛ (እንደ መላእክት) እንዲኖር መርጨዋለሁና ተቀበለው ፤* ብሎሃል

አለው፡፡ እርሱም ለሦስት ቀን ሱባዔ ይዞ ከቆየ በኋላ የምንኩስና ልብስና ቆብ አልብሶ ዮሐንስን አመነኰሰው፡፡ ከዚያች ቀን ጀምሮም ዮሐንስ ሐዊር በታላቅ ብሕትውናና በቅድስና ሥራዎች ተጠምዶ ኖረ፡፡

## ለአባቶች እየተላላከ ማገልገሉ

ከዕለታት አንድ ቀን አባ ባሞይ አባ ዮሐንስን ትዕግሥት ሊያስተምረው ፈለገና ፣ ከበኣቱ (ከቤቱ እንዲወጣ) አዘዘው፤ ተቆጣውም፡፡ ዮሐንስም ለሰባት ቀን ይህንኑ ታግሶ ዝም አለ፡፡ በሰባተኛው ቀን አባ ባሞይ ትዕግሥትን ተፈትኖ ያለፈው አባ ዮሐንስ ሐዊር አክሊል ሲቀበል በራእይ አየ፡፡ ከዚያን ቀን ጀምሮም አባ ዮሐንስ በአባቶች ክብር ተቀመጠ፡፡

በሌላ ቀን አባ ባሞይ ደረቅ እንጨት ለአባ ዮሐንስ ሰጠውና ተክለህ ውኃ እያጠጣህ እንዲለመልም አድርግ አለው፡፡ አባ ዮሐንስም ያላንዳች ማንገራገር የታዘዘውን ፈጸመ፡፡ ለሦስት ዓመት ደረቁን እንጨት ከሩቅ ቦታ ውኃ እያመጣ ሳይታክት ያለማቋረጥ ያጠጣ እና እየኮተኮተ ይንከባከብ ነበር፡፡ በሦስተኛው ዓመት ደረቁ እንጨት ለምልሞ ፍሬ ሰጠ፡፡ ቅዱስ ዮሐንስም የለመለመውን ተክል ፍሬ ለመንፈስ አባቱ ወስዶ ሰጠ፡፡ አባቱም እጅግ ተደስቶ መረቀውና የገዳሙን አባቶች ሁሉ ጠርቶ ***እንካችሁ ብሉ ይህ የመታዘዝ ፍሬ ነው*** አላቸው፡፡ ሁሉም ታሪኩን ሲሰሙ ተደንቀው በቅዱሳኑ አድሮ ድንቅ ሥራ የሚሠራውን እግዚአብሔርን አመሰገኑ፡፡

## ከሲመቱ እስከ ዕረፍቱ

አባ ባሞይ ለዐሥራ ሁለት ዓመታት ታመመ፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ ሐዊርም ሳይሰለች እየተላላከ አስታመመው፡፡ የሚያርፍበት ቀን ሲደርስም የገዳሙን አባቶች ሁሉ አስጠርቶ ተሰናበታቸው፡፡ በመጨረሻም የአባ ዮሐንስን እጅ ይዞ ይህ መልአክ ነው፣ ታዘዙት አላቸውና ዐረፈ፡፡ ከዚያም የገዳሙ አባቶች ቅዱስ ዮሐንስ አበምኔት ሆኖ እንዲሾም መረጡት፡፡ ፓትርያርኩ መጥተው እጃቸውን በመጫን ሲሾሙት ፣ ከሰማይ፡- ***ይገባዋል!ይገባዋል!ይገባዋል!*** የሚል ድምፅ ተሰማ፡፡

ከተሾመ በኋላም አባቶችን እየታዘዘ ኖረ፡፡ በአንድ ወቅት ጥሩ ክርስቲያን የነበረች ሴት ፣ መሳሳትዋ ተሰማ፡፡ አባቶችም ቅዱስ ዮሐንስ ሐዊር ሄዶ ከስሕተቷ እንዲመልሳት ነገሩት፡፡ እርሱም ጸሎት አድርጎ ወደ ሴትዮዋ በመሄድ መከራት፤ ያችም ሴት ንስሓ ገብታ ለመሞት በቃች፡፡

www.zeorthodox.org

ከዚያም በዘመኑ የነበረው ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ አባ ዮሐንስ ላከው፡፡ ባቢሎን ወደ ተባለች ሀገር ሄዶ የቅዱሳንን አጽም እንዲያመጣ አዘዘው፤ እርሱም ከባድ ቢሆንም ይህንን ተልዕኮ ለመፈጸም ሄደ፡፡ ሲመለስም እግዚአብሔር በደመና እንዲጓዝ አድርጎ መንገዱን አቀለለለት፡፡

በዚህ ዓይነት እየታዘዘና በትኅትና እያገለገለ ኖሮ ቅዱስ ዮሐንስ ሐዊር በዕድሜው ሸመገለ፡፡ በቤቱ ተኝቶም መላእክት ክንፋቸውን ሲጋርዱለት ይታይ ነበር፡፡ በሕይወቱ መጨረሻም በገዳሙ

እያለ የአከባቢው ሽፍቶች ሊገድሉት መጡ። እርሱም መነኮሳቱን ይዞ ወደ ሌላ ቦታ ሸሸ። ይህን ያደረገበትን ምክንያት ሲገልጽ፡- *‹‹አሁን በርበራውያን እኔን ሊገድሉኝ ይመጣሉ ፣ በዚህ ምክንያትም እኔ ወደ ገነት ገዳዮችም ወደ ሲዖል እንገባለን ፣ ነገር ግን በእኔ ምክንያት ማንም እንዲቀጣ አልሻም ፤ ምክንያቱም ገዳዩ በሃይማኖት ባይመስለኝም በሰውነቱ ወንድሜ ነው።››* አለ።

በመጨረሻ ቅዱሳንና መላእክት ከበውት በክብር ዐረፈ።

**ማጠቃለያ፡-** ቅዱስ ዮሐንስ ሐፂር በእምነት እና በመታዘዝ ኖሮ ሞተ። እኛንም ለእግዚአብሔር እና ለአባቶች የመታዘዝን ሕይወት አስተምሮናል። እምነት እና መታዘዝ አይነጣጠሉም። በክርስቲያን ሕይወት ውስጥም ሁለቱም ሊኖሩ ይገባል።

## ተግባር

- ከዚህ በፊት በሠላሳ አራተኛው ሳምንት ስለ መታዘዝ የተማራችሁትን ከልሱ። በቤት ውስጥም እንዲነበብላችሁ አድርጉ።
- የምትታዘዙትን በተግባር ፈጽሙ።

## *የክለሳ ጥያቄዎች*

1. የቅዱስ ዮሐንስ ቤተሰቦች የማያምኑ አረማውያን ነበሩ።

   ሀ. እውነት ለ. ሐሰት

2. ቅዱስ ዮሐንስን ያመነኮሰው ፡- ሀ. አባ ባሞይ ለ. ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ
3. ቅዱስ ዮሐንስን ሽፍቶች ሊገድሉት ሲመጡ ያደረገው ምን ነበር?

   ሀ. አንገቱን ለሰይፍ ሰጠ። ለ. ፈርቶ ሸሸ

   ሐ. እርሱን በመግደላቸው እንዳይኮነኑ ወደ ሌላ ቦታ ሄደ።

4. ቅዱስ ዮሐንስ ሐፂር ያረፈበትና የሚታሰብበት ቀን መቼ ነው?

   ሀ. ጥቅምት ፳ ለ. ኅዳር ፲ ሐ. መስከረም ፩

5. ቅዱስ ዮሐንስ ለሰባት ቀናት ትዕግሥቱ ሲፈተን ምን አደረገ?

   ________________________________________

6. አባ ባሞይ የሰጠውን ደረቅ እንጨት ቅዱስ ዮሐንስ ምን አደረጋት?

   ________________________________________

www.zeorthodox.org

# ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ ምን ማድረግ አለብን?

## አርባ አንደኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** **ልጆች፤** ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ ማድረግ ያለብንን ዝግጅትና ሥርዓት አምልኮ ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***‹‹ ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች።››*** *ማቴ.፳፩፥፲፫*

**ምንባብ፡-** *ማቴ.፳፩፥፲፪-፲፯*

***መግቢያ፡-*** ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤት ስለሆነች ልዩ የክብር ቦታ ናት። ወደ እግዚአብሔር ቤት ለመምጣት ዝግጅቱ ከቤት ይጀምራል። ሰዓት አክብሮ መነሣት፣ ንጽሕናችንን መጠበቅ፣ ንጹሕ ልብስ መልበስ።

በዛሬው ትምህርታችንም ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ ማድረግ ያለብንን እንማራለን።

## ትምህርቱ

አንድ ቀን ጌታችን በኢየሩሳሌም ወደነበረው ቤተ መቅደስ ሄደ፤ በዚያም ሰዎች በሬ፣ በግ፣ ርግብ ሲሸጡ እና ገንዘብ ሲለዋወጡ አገኛቸው። ታዲያ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የቤተ መቅደሱን ገበያ ሲያይ አዘነ ተቆጣም። ጌታችን ለምን የተቆጣ ይመስላችኋል? አዎን ሰዎች ቤተ መቅደሱን እንዲያከብሩት ይፈልጋል። ስለዚህ ***"ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ ተጽፎአል፤ እናንተ ግን የወንበዶች ዋሻ አደረግኋት አላቸው።"*** ከቤተ መቅደሱም አውጥቶ መሸጫቸውንና ሸቀጣቸውን ጣለው።

ልጆች እናንተም እግዚአብሔር እንዲያዝንባችሁ አትፈልጉም አይደል? ስለዚህ በቤተ መቅደስ እንዴት መመላለስ አለብን ? ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤት ነውና የጸሎት ቤት ነው። እኛም ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ ፡-

www.zeorthodox.org

**፩. የግል ንጽሕናችንን መጠበቅና ንጹሕ ልብስ መልበስ ይገባናል።**

ጎበዝ ልጅ ንጽሕናውን ይጠብቃል። ወደ እግዚአብሔርም ቤት ስትመጡ ንጹሕ መሆን አለባችሁ። እግዚአብሔር ንጹሕ ስለሆነ ንጽሕናን ይወዳል። አቤል ንጹሕ መሥዋዕት ስላቀረበ እግዚአብሔር ተቀብሎለታል። ዘፍ.፬። እኛም ንጽሕናችንን በሚገባ መጠበቅ አለብን። ንጹሕ ልብስ ፣ ለብሰን መምጣት አለብን።

## ፪. ነጠላ በመስቀል ምልክት አጣፍቶ ይለበሳል፡፡

በተለይም ለቅዳሴና ለቅዱስ ቁርባን ስንመጣ፣ ነጠላችንን በመስቀል ምልክት እናደርጋለን፡፡ ይህም ነጩን ልብስ ለብሰው ጌታቸውን የሚከተሉት የጻድቃንን መንገድ እና እምነት ያመለክታል፡፡ መምህር በራእ.፯፥፱-፲፯ የተጠቀሰውን ያብራሩላቸው፡፡

## ፫. ማማተብ፡፡

ወደ ቤተክርስቲያን ስንገባ፣ ጸሎት ስንጀመርና ስንፈጽም በመስቀል ምልክት ማማተብ አለብን፡፡ የመስቀል ምልክት እንዴት እንደሚሠራና ለምን እንደምናማትብ የተማራችሁትን አስታውሱ፡፡

## ፬. የእግዚአብሔርን ስም መጥራት እና ሰላምታ መስጠት፡፡

ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንገባ በስመ ***አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ*** አሐዱ አምላክ ፤ ብለን ካማተብን በኋላ ***ሰላም ለኪ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን - ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሆይ ሰላም እልሻለሁ*** እንላለን፡፡

## ፭. ወደ ቤተ መቅደስ ስንገባም ጫማችንን እናወልቃለን፡፡

እግዚአብሔር ሙሴን ‹‹***የቆምህባት ስፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና፤ ጫማህን ከእግርህ አውጣ*** ›› አለው፡፡ ሙሴም አወለቀ፡፡ ኢያሱም መልአኩ ሲገለጥለት በተቀደሰው ስፍራ ጫማውን እንዲያወልቅ ተነግሮት ነበር፡፡ ዘጸ.፫፥፭፣ ኢያ.፭፥፲፭ እኛም ወደ ቤተ መቅደስ ስንገባ የተቀደሰ ስፋራ ስለሆነ ጫማችንን ከእግራችን አውልቀን ወደ ቤተ መቅደስ እንገባለን፡፡

፮. ከዚያም መጸለይ፣ ትምህርት ማዳመጥ እና በምንሳተፍባቸው አገልግሎቶች ብቻ መሳተፍ፤ ለምሳሌ፤ በጸጥታ ቆሞ ማስቀደስ፣ መቁረብ፣ ሲዘመር ማጨብጨብ፣ በቅዳሴው የምናውቀውን በዜማ መመለስ፤ ይገባል፡፡

www.zeorthodox.org

## ፯. መረጋጋትና ትኩረት፡፡

አንዴ ወደ ቤተክርስቲያን ከገባን በኋላ አገልግሎት እስኪፈጸም በጸጥታ ሆነን በአንድ ቦታ ልንቆም ወይም ልንቀመጥ ያስፈልጋል፡፡

እነዚህን ካደረግን ጌታችን ይደሰትብናል ይባርከናልም፡፡

## ማጠቃለያ

ቤተ ክርስቲያን የተከበረች የእግዚአብሔር ቤት ናት፡፡ እኛም በቤተክርስቲያን በሥርዓትና በክብር ልንወጣና ልንገባ ይገባል፡፡ ካህናትን ማክበር አለብን፡፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔር አገልጋይ ናቸው፡፡

እግዚአብሔር ከነሠራዊቱ በቤተ መቅደሱ አለ፡፡ በቅዳሴ ሰዓት ቅዱሳንና መላእክት ከእኛ ጋር ይሆናሉ፡፡

## ተግባር

- የተማራችሁትን በተግባር ፈጽሙ፡፡

*መዝሙር*

እግዚአብሔር ኀበነ ልሳነ ጥበብ (2)
ከመ ናዕምር ሕጋ (2) ለቤተ ክርስቲያን

www.zeorthodox.org

# የእግዚአብሔር ስሞች

## አርባ ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ያሉትን የእግዚብሔር ስሞች፤ የአምላካችን ስም ያለውን ኃይል እና የስሞቹን ትርጉም አውቀው፤ በቅዱስ ቃሉ ቢያድጉ በእግዚአብሔር ስም ድል እንደሚያደርጉ ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***‹‹የእግዚአብሔር ስም የጸና ግምብ ነው ጻድቅ ወደ እርሱ ሮጦ ከፍ ከፍ ይላል፡፡››*** ምሳ.፲፰፥፲፩

**መግቢያ፡-** ልጆች የዛሬውን ትምህርታችንን ከመጀመራችን በፊት ስለ እግዚአብሔር ስሞች የምታውቁትን አብራሩ፡፡ የምታውቁዋቸውን የእግዚአብሔር ስሞች ተናገሩ፡፡ የጠራችሁትን ስም ትርጉምስ ታውቁታላችሁ፡፡

የተወደዳችሁ ልጆች የእግዚአብሔር ስም ለእኛ አስፈላጊያችን ነው፡፡ የሚቀድሰን፣ የሚረዳንና የሚያድነን የአምላካችን ስም ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ስለ እግዚአብሔር ስም እና ትርጉሞቹን በዛሬው ትምህርታችን እናያለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

የእግዚአብሔርን ስም፣ ኃይል እና አስፈላጊነት የተረዱ ቅዱሳን ተጠቅመውበታል፡፡ ልጆች እናንተም በስሙ ሕይወት እንዲሆንልን በቅድሚያ የስሙን ክብር እንይ፡፡

**የአምላካችን ስም ቅዱስ ነው፡፡** እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በወንጌል በተጻፈልን ጸሎቷ ፡- ***ስሙም ቅዱስ ነው፡፡*** ሉቃ.፩፥፵፱ ብላናለች፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሔርን ስም በእምነትና በእውነት ስንጠራው ይቀድሰናል ማለት ነው፡፡

www.zeorthodox.org

**የእግዚአብሔር ስም ያድናል፡፡** በዚህ ምድር ከሰይጣንና ከክፉ ሥራዎቹ ሁሉ፤ ከክፉዎች ወጥመድ፣ ከሞት በኋላም ከሚመጣ የዘላለም ሞት ሰዎች መዳን እንችል ዘንድ አምላካችን አዳኝ ስሙን ሰጥቶናል፡፡ ***‹‹የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል፡፡››*** ኢዩ.፪፥፴፪

**የእግዚአብሔር ስም ድል ይሰጣል፡፡** አባታችን ዳዊት ከጎልያድ ጋር ሲጋጠም ሲሄድ፤ ጎልያድ በአምላኮቹ ስም ረገመው፡፡ በንቀትም ‹‹***በትርና ወንጭፍ ይዘህ የምትመጣብኝ እኔ ውሻ ነኝ ፣ ወዲህ ና ሥጋህን ለሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት እሰጣለሁ***›› አለው፡፡ ዳዊት ግን፤ ‹‹እኔ

***በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ፡፡›.*** አለው፡፡ በወንጭፉም ታላቁን ጠላቱን የጣለው የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ ነበር፡፡ እኛም ጠላታችን ሰይጣንና እርሱ የሚያመጣቸው ክፉ ሐሳቦች ሁሉ የአምላካችንን የእግዚአብሔርን ስም ጠርተን በመስቀል ምላሴ ስናማትብ ይርቃሉ፡፡ ሰይጣን ሲያስደነግጠን የእግዚአብሔርን ቅዱስ ስም ጠርተን እንጽናናለን፡፡ ክፉ ነገሮችን በሙሉ በእግዚአብሔር ስም እናሸንፋለን፡፡ ከቅዱስ ዳዊትም ጋር፤ ‹‹***በእግዚአብሔር ስም አሸነፍኋቸው*** ፤›› መዝ.፻፲፯(፻፲፰)፥፲-፲፪ ብለን ለመዘመር እንችላለን፡፡

የእግዚአብሔር ስም በከንቱ አይጠራም፡፡ በከንቱ መጥራት ማለት በሐሰት ፣ በቀልድ የእግዚአብሔርን ስም አንጠራውም ማለት ነው፤ ምክንያቱም ‹‹***የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ››*** ተብለን ታዘናል፡፡ ዘጸ.፳፥፯

**የእግዚአብሔር ስሞችና ትርጉማቸው፡፡**

የሰማዩ አባታችን አዶናይ፣ ኤልሻዳይ፣ ያህዌ በሚሉ ስሞች በድሮ ዘመን በብሉይ ኪዳን ይታወቅ ነበር፡፡ በዘመነ ሐዲስም አማኑኤል፣ ኢየሱስ፣ አብ፣ ጰራቅሊጦስ የሚሉ ስሞችን አውቀናል፡፡ ሁሉም ስሞች ትርጉም እና ምክንያት አላቸው፡፡ የኃያሉ እግዚአብሔር ስሞች በመሆናቸውም ድልንና ኃይልን ይሰጡናል፡፡

እግዚአብሔር ፡- የዓለም ጌታ ማለት ነው፡፡

አዶናይ፡- አሸናፊ ማለት ነው፡፡

ኤልሻዳይ፡- ሁሉን ቻይ ማለት ነው፡፡

ያህዌ፡- የነበረ ፣ ያለና የሚኖር ማለት ነው፡፡

ከእግዚአብሔር ስሞች የሚከተሉት ይገኛሉ፡-

**አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፡-** ልጆች ሁል ጊዜም ለጸሎት ስትቆሙ አስቀድማችሁ የእግዚአሔርን ስም በመጥራት ነው፡፡ ጸሎት የምትጀምሩትም በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ በማለት ነው፡፡ ‹‹በአብ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም ማለታችሁ ነው፡፡ እነዚህም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረን ስሞች ናቸው፡፡ ***እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ ደቀ መዛሙርቴ እድርጉዋቸው፡፡››*** ማቴ.፳፰፥፲፱ አብ ማለት አባት፤ ወልድ ማለት ልጅ፤ መንፈስ ቅዱስ ማለትም ቅዱስ የሆነ መንፈስ ማለት ነው፡፡ ይህም ታላቁን የእግዚአብሔር ምስጢር ይገልጻል፡፡ በቤተ ክርስቲያንም የቅድስት ሥላሴ የግብር ስም ይባላል፡፡

www.zeorthodox.org

**አማኑኤል፡-** እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሆነ ማለት ነው። ይህንን መጀመሪያ የነገረን ነቢዩ አሳይያስ ነበር። ኢሳ.፯፥፲፬ በኋላም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲወለድ እና ከእኛ ጋር ሲሆን ተጠራበት። ማቴ.፩፥፳፫

**ኢየሱስ፡-** አዳኝ (መድኃኒት) ማለት ነው። ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን ሲያበስራት ልጅዋን ኢየሱስ እንድትለው ነገራት። እርስዋም ኢየሱስ አለችው። ሉቃ.፩፥፴፩። ይህ ስም ከስሞች ሁሉ ይበልጣል፣ እንድንበትም ዘንድ የተሰጠን ስም ነው።

## ማጠቃለያ

- የእግዚአብሔር ስም ቅዱስና ኃያል ነው። በከንቱ ልንጠራው አይገባም። በስሙ ኃይል እና ድል ይገኛል።
- የእግዚአብሔርን ስሞች ትርጉም ማወቅ ጠቃሚ ነው።

## ተግባር

- ልጆች፤ የተማራችሁትን የእግዚአብሔርን ስሞችና ትርጉማቸውን በቃል አጥኑ።

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ገብርኤል፣ ቂርቆስና ኢየሉጣን አዳነ

## አርባ ሦስተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ልጆች፣ ቂርቆስና ኢየሉጣን ታላቅ እምነትና በዚህም እግዚአብሔር ከቶን እሳት እንዳዳናቸው ተገንዝበው አርአያነታቸውን በማስተዋል ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"በሞት ጥላ መካከል እንኳን ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህ ክፉን አልፈራም፡፡"*** *መዝ.፳፪(፳፫)÷፬*

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** *መጽሐፈ ስንክሳር*

**መግቢያ፡-** ከዚህ በፊት ክርስቲያኖች እንዴት መከራ ይደርስባቸው እንደነበር ተምረናል፡፡ ይኸው ችግርና መከራቸው ለብዙ ዓመታት ቢቀጥልም በእምነታቸው ጸንተው እግዚአብሔርን መመኪያና ተስፋ በማድረግ ኖረዋል፡፡ ይህ በእምነታቸው የተሰደዱና ታላላቅ መከራዎችን በእምነት ስላሸነፉ እናትና ልጅ የምንማረው ታሪክ ነው፡፡

### ትምህርቱ፡-

የቂርቆስ እናት ኢየሉጣ የተባለች ወጣት ሴት ናት፡፡ ባሏ ቂርቆስ እንደተወለደ ብዙም ሳይቆይ ሞተ፡፡ በክርስቲያኖች ላይ የሚፈጸመውን ግፍ ሽሽታ የሦስት ዓመት ልጅዋን ሕፃኑ ቂርቆስን ይዛ ከትውልድ ቦታዋ ተሰደደች፡፡

በተሰደደችበትም ቦታ ክርስቲያን በመሆንዋ ተከሰሰች፡፡ አገረ ገዢውም አድካሚ ሥራ እንድትሠራ ፈረደባት፡፡ በዚህ ሳያበቃ ጣዖት እንድታመልክ፣ ለምስል እንድትሰግድም አዘዛት፡፡ ቅድስት ኢየሉጣ ግን ከእግዚአብሔር በስተቀር ለተዘጋጀው ጣዖት አልሰገደችም፡፡ ነገር ግን ኢየሉጣ ለተዘጋጀው ምስል/ጣዖት/ ካልሰገደች ከልጅዋ ጋር በእሳት እንደሚያቃጥላት ንጉሡ አስጠነቀቀ፡፡ እርስዋም ስለምትወደው ልጅዋ ስትል በውስጧ ፍርሃት ተሰማት፡፡

ሕፃኑ ቅዱስ ቂርቆስ ግን በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ብርቱ መንፈሳዊ ነበርና ሀገረ ገዢውን፣ ***"ያንተ አማልክት ከድንጋይና ከእንጨት የተሠሩ የሰው እጅ ውጤቶች ናቸው፡፡ ከጌታዬ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ሌላ አምላክ የለም"*** አለው፡፡ እናቱንም ‹‹***አትፍሪ እግዚአብሔር ያድነናል***፡፡›› አላት፡፡

አገረ ገዢው እናትና ልጁ በእግዚአብሔር ባላቸው እምነት ጸንተው ላዘጋጀው ጣዖት አንሰግድም በማለታቸው ተናደደ፣ ተቆጣ፡፡ ከዚያም ቂርቆስ እና ኢየሉጣን ወደ እሳት አስጣላቸው፡፡

www.zoorthodox.org

ሆኖም እግዚአብሔር መልአኩን ቅዱስ ገብርኤልን ልኮ እናትና ልጁን በእሳት ከመቃጠል አዳናቸው፡፡ ይህን ተአምር ያዩ ብዙ ሰዎች በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ፡፡ ነገር ግን አገረ ገዢው ከዚህ የእግዚአብሔር ሥራ ሳይማር ብዙ ጊዜ አሰቃያቸው፡፡ ጌታ እግዚአብሔር እናትና ልጁ ከሚደርስባቸው ታላቅ መከራና ስቃይ ሁሉ ሲያድናቸው የሚመለከቱ ብዙ ሰዎች በጌችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያምኑ ነበር፡፡

በመጨረሻም ሕፃኑ ቅዱስ ቂርቆስ እና እናቱ ቅድስት ኢየሉጣ የሰማዕትነት ዘውድ ተቀዳጅተው ሐምሌ ፲፱ ዐረፉ፡፡ ጸሎትና በረከታቸው ከእኛ ጋር ትሁን አሜን!!

## ማጠቃለያ

ጣዖት አምላኪው አገረ ገዢ ሕፃኑን ለማባበል ልዩ እንክብካቤ ቢያደርግለትም ቂርቆስ ፈርቶ ወይመ ተደልሎ በገዢው ፊት ሃይማኖቱን  አልተወም፡፡ እኛም ለትናንሽ ምቾትና ደስታ ብለን እምነታችንን መተው የለብንም፡፡ ከመተኛታችን በፊትና ጠዋት ስንነቃም መጸለይ አለብን፡፡ እሑድ በጠዋት ነቅተን ተነሥተን ቅዳሴ ለማስቀደስ ቅዳሜ በጊዜ መተኛት አለብን፡፡

የቅዱሳንን ታሪክ መማር በእምነታችን ጠንካራ ያደርገናል፡፡ ሕፃኑ ቂርቆስ የአናንያ የአዛርያና የሚሳኤልን ታሪክ ያውቅ ነበር፡፡ ጽናታቸውን አስታውሶ እርሱም ጸና ፣ እምነታቸውን ተገንዝቦ እርሱም በእምነቱ ጸና፤ ለንጉሡ በተግሣጽ እናቱንም በማጽናት ያስተማራቸውም ይህንኑ የእግዚአብሔርን አምላክነት፣ አዳኝነት እና የቅዱስ ስሙን ኃይል ነው፡፡ የቅዱሳን ሕይወት የቅድስናና የጽናት ትምህርት ቤት መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

## ተግባር

- ❖ በተሰጣችሁ የጥናት ሰዓት ጊዜያችሁን በአግባቡ በመጠቀም ስለጽናት ተለማመዱ፡፡
- ❖ ቤተ ሰቦቻችሁንና ወዳጆቻችሁን በመልካም ቃላት አጽናኑ፡፡

www.zeorthodox.org

***ጥያቄዎች***

1. ቂርቆስና ኢየሉጣ የትውልድ ቦታቸውን ለምን ትተው ሄዱ ? በዚያ ጊዜ ቂርቆስ ስንት ዓመቱ ነበር ?

______________________________________________________________

2. አገረ ገዢው ቂርቆስና ኢየሉጣ ምን እንዲያደርጉ አዘዘ ?

______________________________________________________________

3. ቅድስት ኢየሉጣ ለምን ፈራች ?

________________________________________________________

4. የቅዱሳንን ታሪክ ማወቅ ለምን ይጠቅማል?

____________________________________________________

***መዝሙር፡***

ቂርቆስ ኢየሉጣን ያወጣህ ከእሳት (2)
እኛንም አድነን (2) ገብርኤል መልአክ

www.zeorthodox.org

# ነቢይት ዲቦራ

## አርባ አራተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች፤ የዲቦራን ታሪክ በማጥናት ከነቢይት ዲቦራ የአመራር ጥበብን ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *« እግዚአብሔርም ስለ እኔ በኃያላን ላይ ወረደ፡፡ »* መሳፍ.፭፥፲፫

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** መሳፍ. ፬ እና ፭

### መግቢያ፡-

፩. መስፍን ማለት ምን ማለት ነው? ሥራው፣ ሓላፊነቱ ምንድነው?

፪. ነቢይ ማለት ምን ማለት ነው? ትንቢትስ ምንድነው?

(መምህር ልጆች እነዚህን ጥያቄዎች ከሞከሩ በኋላ ወደ ዋናው ክፍለ ትምህርት ከመግባትዎ በፊት ያብራሩላቸው፡፡)

ልጆች በድሮ ዘመን/በብሉይ ኪዳን/ መሳፍንት የሚባሉ አስተዳዳሪዎች ነበሩ፡፡ እነዚህም ሕዝቡን የሚያስተዳድሩ ፣ ጦርነት ቢነሣ የሚመሩ እና ፍርድ የሚሰጡ ዳኞችም ነበሩ፡፡ ነቢያት ደግሞ ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዲያመልክ የሚያስተምሩ፤ ወደፊት የሚሆነውን የሚናገሩ ናቸው፡፡

ሕዝበ እስራኤል መሳፍንት በሚባሉ መሪዎች ይተዳደሩ ነበር፡፡ እነዚህ በብሉይ ኪዳን መሳፍንት ተብለው የሚሰየሙት ደግሞ ሕዝቡን በባርነት ከመገዛት ያድኑ ነበር፡፡ ከእነዚህ መሳፍንት አንድዋ ነቢይት ዲቦራ ናት፡፡ ዲቦራ በመስፍንነት ለሕዝቡ የምትፈርድ በነቢዩነትዋም ትንቢት ትናገር ነበር፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም ስለ ዲቦራ እንማራለን፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

www.zeorthodox.org

**ዲቦራ ማለት ንብ ማለት ነው፡፡** ዲቦራ እንደ ስምዋ ትጉህ ነበረች፣ በቤቷ ትተጋለች፤ ሥራዋንም በሚገባ አከናውና ትወጣለች፡፡ ባልዋንና ልጆቿን ትመግባለች፡፡ ሌሎችም የእርስዋ ድርሻ የሆኑትን ሥራዎች በየጊዜው ታከናውናለች፡፡

**የእስራኤል ፈራጅም ነበረች፡፡**

ዲቦራ ዳኛ ናት፤ ሕዝበ እስራኤል በሙሉ እርሷም ጋር እየመጡ ፍርድ ይጠይቁ ነበር፡፡ እርሷም ከዘንባባው ዛፍ በታች ተቀምጣ በአደባባይ ፍርድ ስትሰጥ ትውላለች፡፡ ሰዎችም በዳኝነቷ

ትክክለኛነት ይደሰቱ ነበር፡፡

### ነቢይቱ ዲቦራ

ዲቦራ በጸሎት የበረታች ነበረች ፤ የእግዚአብሔርን ድምፅ ትሰማለች፡፡ እግዚአብሔርም ነቢይት እንድትሆን ትንቢት የመናገር ጸጋ ስለሰጣት ትንቢት ትናገር ነበር፡፡

እግዚአብሔር ሕዝቡን ስለሚወድ በዘመኑ ይህችን የመሰለች ቅድስት እናት አስነሥቶላቸው ነበር፡፡ ሕዝበ እስራኤል ግን በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ ሠሩ፡፡ ለሃያ ዓመታትም በከነዓን ንጉሥ በኢያቢስ ተማረኩ፡፡ የንጉሡ የጦር መሪ ሲሣራ ይባል ነበር፡፡ እርሱም ዘጠኝ መቶ የብረት ሰረገሎች ነበሩት፤ በዚህም እስራኤልን ወግቶ ሕዝቡን በጣም አስጨነቀ፡፡

ሕዝበ እስራኤል መከራቸው ሲበረታ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ ፤ እግዚአብሔርም ሰማቸው፡፡ በነብይት በዲቦራም መልስ ሰጣቸው፡፡ እርስዋም እግዚአብሔር እንደነገራት አደረገች፡፡ ባርቅ የተባለውን ሰው ጠርታ ሕዝቡን ነጻ እንዲያወጣ እግዚአብሔር እንደላከው ነገረችው፡፡ እርሱም እግዚአብሔር ከዲቦራ ጋር እንደሆነ ስላወቀ፤ ‹‹***አንቺ ከእኔ ጋር ብትሄጂ እኔ እሄዳለሁ አንቺ ከእኔ ጋር ባትሄጂ አልሄድም***›› አላት፡፡ ልጆች እግዚአብሔር ከቅዱሳን ጋር ስለሆነ ከእነርሱ ጋር መሄድ መልካም ነው፡፡ ድል እንቀዳጅበታለን፡፡ ዲቦራም ***እሄዳለሁ*** አለችው፡፡ ባርቅ እንደተነገረለት እግዚአብሔር የሰበሰበለትን አስር ሺሕ ሠራዊት ይዞ ወደ ታቦር ተራራ ወጣ፡፡

የአሕዛብ የጦር መሪ የነበረው ሲሣራም የብረት ሰረገሎችን ይዞ ወጣ፡፡ ከጥቂት ቀናት ቆይታ በኋላ ዲቦራ፡- ‹‹***እግዚአብሔር ድልን የሚሰጥህ ዛሬ ነው፡፡ ከፊትህ እየሄደ ነውና ተነሣ***›› አለችው፡፡ እርሱም ከአስር ሺሕ ሰዎች ጋር ወጣ፡፡ በእግዚአብሔር ኃይል ድል አድርጎም ተመለሰ፡፡ የእውነተኛ ነቢያት ቃል እንዲህ ይፈጸማል፡፡ ነቢዩት ዲቦራም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመታደግ የተሰለፉትን መርታ፤እንደተናገረችው ተፈጸመ፡፡

### ዲቦራ ባለቅኔና ዘማሪ ነበረች፡፡

www.zeorthodox.org

ዲቦራ ሕዝበ እስራኤልን መርታ ድል ከተገኘ በኋላ እግዚአብሔርን አመሰገነች፡፡ ከባርቅ ጋር በቅኔ አመሰገኑ እንዲህም አሉ፡-

***ነገሥታት ሆይ ስሙ ፤***
***መኳንንት ሆይ አድምጡ ፤***
***እኔ ለእግዚአብሔር እቀኛለሁ፤***
***ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር እዘምራለሁ፡፡***
***በዚያ ጊዜ የቀሩት ወደ ኃያላኑና ወደ ሕዝቡ ወረዱ ፤***

*እግዚአብሔርም ስለ እኔ በኃያላን ላይ ወረደ።*

በመጽሐፍ ቅዱስ « ***ከእናንተ መከራን የሚቀበል ማንም ቢኖር እርሱ ይጸልይ፤ ደስ የሚለውም ማንም ቢኖር እርሱ ይዘምር።*** » ያዕ.፭፥፲፫ እንደተባለ የእግዚአብሔር ሰዎች ደስ ሲላቸው፣ ድል ሲያደርጉም እግዚአብሔርን በመዝሙር ያመሰግናሉ። መከራና ችግር ሲደርስባቸውም እግዚአብሔርን በጸሎት ይጠይቃሉ። ዲቦራና ባርቅም ድል ስለአደረጉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ።

ሕዝበ እስራኤል በኃጢአታቸው ከመጣባቸው ባርነት እግዚአብሔር በዲቦራ አማካኝነት ነጻ አውጥቶአቸው ለአርባ ዓመታት ዐረፉ።

## ማጠቃለያ

ዲቦራ ንብ ማለት ሲሆን እንደ ስሟ ትጉህ ሴት ነበረች። በነቢይነት፣ በመስፍንነትና በመዝሙር እግዚአብሔርንና ሕዝቡን አገልግላለች። እኛም በተሰጠን ጸጋ ከተጋን እግዚአብሔር ውጤታማ ያድርገናል።

## ተግባር

- ልጆች ለወደፊቱ ምን መሆን እንደምትፈልጉ ተወያዩ።
- የምታስቡትን መልካም ነገር እንዴት ማሳካት እንደምትችሉም ቤተሰብንና መምህርን ጠይቁ።

### *መዝሙር*

እናመስግነው (2) አምላካችን ውለታው ብዙ ነው።
ከባርነት ቀንበር ከሞት ደጅ አውጥቶ
መንግሥቱን ለሰጠን ከሲዖል አውጥቶ
ዘላለማዊ ቤት ታላቅ ሀብት ያደለን
መቼም የማይተወን ታላቅ አባት አለን።

www.zeorthodox.org

# ጌታችን ሕፃናትን ይወዳል

## አርባ አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ በተማረችውና በታዘዘችው መሠረተ ልጆችን እንደምትወድ ተንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***‹‹ሕፃናት ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተዉአቸው አትከልክሉአቸውም፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ እነዚህ ላሉት ናት››*** *ሉቃ.፲፰፥፲፮*

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** *ማር.፲፥፲፫-፲፮*

**መግቢያ፡-** እግዚአብሔር ፍጥረታት በሙሉ ይወዳል፤ በተለይም ለልጆች ፍቅር አለው፡፡ ይህንንም ሰዎችን እንደ ሕፃናት ካልሆናችሁ በማለቱ ለሕፃናት ያለው ፍቅር ይታወቃል፡፡ በዛሬው ትምህርታችን ጌታችን ሕፃናትን እንደሚፈልግና እንደሚወድ እንማራለን፡፡

## ትምህርቱ

ሐዋርያት በመንገድ እየሄዱ ማን እንደሚበልጥ በመካከላቸው ክርክር ሆነ፡፡ ይህንን ሲከራከሩ ጌታችን በአካል ከእነርሱ ጋር አልነበረም፡፡ ጌታ ወዳለበት ሲደርሱ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት ጌታችን እያስተማረ ነበር፡፡ በሕዝቡ መካከልም ሕፃናት ነበሩ፡፡ ሕዝቡን አስተምሮ ወደ ቤት ሲገባ ፤ ‹‹በመንገድ እርስ በእርሳችሁ ምን ተነጋገራችሁ?›› አላቸው፡፡ ጌታችን ትኅትናን ጌታችን ያስተምራቸው ስለነበር፤ እኔ እበልጣለሁ በሚል በመከራከራቸው አፍረው ዝም አሉ፡፡ እርሱም ተቀምጦ ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ወደ እርሱ ጠራ፡፡ ***‹‹ ከሁሉ ከፍተኛ ሊሆን የሚወድ የሁሉ አገልጋይ ይሁን››*** አላቸው፡፡ ከዚያም ሊማሩ ከመጡት ሕፃናት አንዱን በመካከላቸው አቆመውና ከዚያም አንስቶ አቀፈው፡፡ የሚከተሉትንም አላቸው፡-

www.zeorthodox.org

***፩. ካልተመለሳችሁ እንደ ሕፃናትም ካልሆናችሁ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም፡፡*** ማቴ.፲፰፥፫

ልጆች አስተዋላችሁ? ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገቡት እግዚአብሔርን የወደዱትና እርሱም እምነታቸውንና ሥራቸውን የወደደላቸው ናቸው፡፡ ጌታችን በጣም የሚወዳቸውን ቅዱሳንን በጣም በሚወዳቸው በሕፃናት መሰላቸው፡፡ ስለሚወደንም ‹‹መንግሥተ ሰማያት የሚገቡ እንደ ሕፃናት የሆኑ ብቻ ናቸው›› አለ፡፡ እናም ልጆች ከጌታችን ከእግዚአብሔር አትራቁ እርሱ እጅግ የሚወዳችሁ የሰማዩ አባታችሁ ነው፡፡

**፪. እንደዚህ ሕፃን ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ሁሉ በመንግሥተ ሰማያት የሚበልጥ እርሱ ነው።** ማቴ.፲፰፥፬

እግዚአብሔር ከልጆች በጣም የሚወደው ትኅትናን ነው። ትኑት ልጆች ‹‹ሲጠሩ አቤት ሲላኩ ወዴት›› ብለው በትኅትና ያገለግላሉ። እናንተም በልባችሁ ባለው ትኅትና ጌታችን አብዝቶ ይወዳችኋል።

ትኑት ልጅ አጥፍቶ ይቅርታ ይጠይቃል። ይህም በጌታችን በጣም የተወደደ ጠባይ ነው። አንድ ልጅ ለይቅርታ ራሱን ዝቅ በማድረጉም ከእግዚአብሔር ጸጋ ያገኛል። ***‹‹ እግዚአብሔር ትእቢተኞችን ይቃወማል ፤ ለትሑታን ግን ጸጋን አብዝቶ ይሰጣል ።*** *ያዕ.፬፥፮*

ልጆች እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ያለውን መልካም ጸባይ ምን ያህል እንደሚወደው አስተውሉ።

**፫. እንደዚህ ያለውን አንድ ሕፃን በስሜ የሚቀበል ሁሉ እኔን ይቀበላል።** ማቴ.፲፰፥፬

ይህኛው የጌታችን ቃል ደግሞ ከሁሉም ይልቅ ለልጆች ያለውን ፍቅር ያመለክታል። ሕፃናትን በጌታችን ስም መቀበል ጌታችንን ከመቀበል ጋር እኩል ነው። ይህም አስደናቂ መውደድ ነው። ሐዋርያትም ይህንን ከጌታችን ተምረው ሕፃናትን ሲቀበሉ ኖሩ። ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ ልጆችን ትወዳለች ትቀበላለችም። ለዚህም ነው ተቀብላ ያጠመቀቻችሁ። አሁንም ሰብስባ የምታስተምራችሁ፤ በእግዚአብሔር ቃል ኮትኩታ፣ በቅዱስ ቁርባን አጽንታ እየተከባከበች የምታሳድጋችሁ የጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ቃል መሠረት በማድረግ ነው። እናንተም እንደ ተወደዱ ልጆች ሆናችሁ ቃሉን ስሙ።

***፬. ‹‹ ሕፃናት ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተዉአቸው አትከልክሉአቸውም፤...››*** *ሉቃ.፲፰፥፲፮*

በሌላ ጊዜ ወላጆች ልጆቻቸውን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲባርክላቸው ሕፃናትን ወደ ጌታችን አመጡ። ደቀ መዛሙርቱም ከለከሉዋቸው። ጌታችንም ***‹‹ ሕፃናት ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተዉአቸው አትከልክሉአቸውም፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ እነዚህ ላሉት ናት››*** ሉቃ. ፲፰፥፲፮ አላቸው።

www.zeorthodox.org

እኛም ጌታችን ይህንን ያህል ከወደደን ለመባረክ እና በጸጋ ለማደግ ሁሌም በተቀደሰው ቤቱ በቤተ ክርስቲያን መገኘት አለብን። ቅዱስ ቃሉን እየሰማን፤ ቅዱስ ቁርባን እየተቀበልን፣ በትኅትና እየታዘዝን፣ መልካም ነገርን በማድረግ በቤቱ ተጠብቀን ማደግ አለብን።

## ማጠቃለያ

ጌታችን ሕፃናትን ይወዳል፤ ይህንንም በቃሉ አስተምሮ በተግባር አሳይቶናል። እናንተም የሚወዳችሁ እና የሚያስብላችሁን ሰማያዊ አባት ቅዱስ ቃሉን ስሙ።

## ተግባር

- ❖ ልጆች በትምህርት ቤት እና በሰፈር ለምታውቁዋቸው ልጆች ይንን የጌታችንን መልእክት አስተላልፉላቸው።

### *መዝሙር*

ኢየሱስ ክርስቶስ ይወደናል ይጠብቀናል
እርሱ ለእኛ ደሙን ክሶልናል።

www.zeorthodox.org

# ዕርገታ ለማርያም

## አርባ ስድስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች ስለ እመቤታችን ትንሣኤና ዕርገት ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡- «በወርቅ ልብስ ተጎናጽፋና ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች፡፡»**
መዝ.፵፬(፵፭)፥፱

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ስንክሳር ፣ ነገረማርያም

**መግቢያ፡-** ፍልሰታ ማርያም ብለን በተማርነው ትምህርት ፣ መላእክት የእመቤታችንን ሥጋ በገነት ከዕፀ - ሕይወት ሥር እንዳሳረፉት ተምረናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም የዚህን ታሪክ ቀጣይ ክፍል እንማራለን፡፡

## ትምህርቱ

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ካረፈች በኋላ መላእክት የእመቤታችንን ሥጋ በገነት አሳረፉት፡፡ ከሐዋርያት መካከል ይህንን ያወቀው ቅዱስ ዮሐንስ ብቻ ነበር፡፡ ሌሎቹ የእመቤታችን ሥጋ የት እንዳለ አላወቁምና አዘኑ፡፡ ከዚያም ከነሐሴ አንድ ቀን ጀምሮ ለሁለት ሳምንታት በጾምና በጸሎት ሆነው ስለ እመቤታችን ሥጋ እግዚአብሔርን ጠየቁት ፡፡ በዐሥራ አራተኛው ቀን ማለትም ነሐሴ ፲፬ ቀን ጌታ የእመቤታችንን ሥጋ ሰጣቸው፡፡ እነርሱም በጸሎት እግዚአብሔርን አመስግነው ቀበሩት፡፡

ቶማስም በዚያ ቀን ከሐዋርያት ጋር አልነበረም፡፡ ነገር ግን በሦስተኛው ቀን ነሐሴ ፲፮ ቀን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወደ ሰማይ ስታርግ ተመለከተ፡፡ ለማረጋገጫም የመግነዝ ጨርቋን ሰጠችው፡፡ ቶማስ እንደደረሰ ስለ እመቤታችን ሐዋርያትን ጠየቃቸው፤ እነርሱም የሆነውን ነገሩት፡፡ ሐዋርያው ቶማስም የመግነዝ ጨርቁንም ሳያሳያቸው፤ ‹‹***መቃብሩን ካላየሁ አላምንም***›› አላቸው፡፡

ሲሄዱም በመቃብሩ የእመቤታችንን ሥጋ አላገኙም፡፡ ቶማስም እርገትዋን ነገራቸው፤ ሰበኑንም (የመግነዝ ጨርቁን) አሳየቸው፡፡ ልጆች ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ካህናት በመስቀል ዉስጥ የሚያደርጉት ጨርቅ፡-የዚህ ሰበን እና የእመቤታችን እርገት ምሳሌም ነው፡፡

www.zeorthodox.org

ሐዋርያት ቶማስ ያየውን ለማየት በድጋሚ ሱባዔ ያዙ፤ ከዚያም የእመቤታችን እርገት ተገለጸላቸው።

## ማጠቃለያ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በንጹሕ ልቦና እና በእምነት ለምንጸልየው ጸሎት መልስ ይሰጠናል። ሐዋርያት እመቤታችንን ለማየት ሲጾሙና ሲጸልዩ ለጸሎታቸው መልስ ሰጥቷቸዋል። ጾመ ፍልሰታ የልጆች ጾም ትባላለች፤ በዚህ ሰሞን ልጆች ከወላጆቻቸው ወይም ከታላላቆቻቸው ጋር በብዛት ሆነው በየዕለቱ ወደ ቤተክርስቲያን በመሔድ ቅዳሴ ያስቀድሳሉ፤ ይቆርባሉ።

## ተግባር

**ልጆች** በፍልሰታ ጾም ወቅት አስቀድሳችሁ ለመቁረብ ወደ ቤተክርስቲያን ስትሄዱ ንጽሕናችሁን ጠብቃችሁ፣ በጸጥታ እና በእርጋታ ሁኑ።

### *ጥያቄዎች*

1. የእመቤታችንን ዕረፍት በመጀመሪያ ያወቀው ሐዋርያ ማን ነበር ?

_______________________________________________

2. ሐዋርያት የእመቤታችንን ሥጋ ሲቀብሩ በመካከላቸው ያልነበረው ሐዋርያ ማን ነው ?

_______________________________________________

3. በቤተ ክርስቲያን መስቀል ላይ የምናየው ጨርቅ የምን ምሳሌ ነው ?

_______________________________________________

www.zeorthodox.org

# ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት

## አርባ ሰባተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ልጆች፤ ስለ አቡነ ተክለሃይማኖት አውቀው፤ እግዚአብሔር ላከበራቸው ቅዱሳን መታሰቢያ የማድረግን ጥቅም ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ"*** ማቴ.፭÷፲፮

***"ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ዉኃ ብቻ በደቀመዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም።"*** ማቴ. ፲÷፵፪

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** መጽሐፈ ስንክሳር እና ገድለ ተክለሃይማኖት

### *የክለሳ ጥያቄዎች*

1. እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ካረፈች በኋላ ሥጋዋ ምን ሆነ?
2. ሐዋርያት የእመቤታችንን ሥጋ ለማግኘት ስንት ቀን ጾሙ?
3. የእመቤታችንን ትንሣኤና እርገት መጀመሪያ ያየው ሐዋርያ ማነው? ትንሣኤዋን በምን አረጋገጠላቸው ?

## መግቢያ

ከዚህ በፊት በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የተፈጸመውን የሐዋርያትን መንፈሳዊ ሥራና በክርስቶስ ስም የፈጸሙትን ተጋድሎ ተምረናል። በዛሬው ትምህርታችንም በኢትዮጵያ ከተነሡት ቅዱሳን አንዱ ስለሆኑት ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እንማራለን።

www.zeorthodox.org

## ትምህርቱ

ጻድቁ ተክለ ሃይማኖት እግዚአብሔርን ከሚወዱ ቤተሰቦች ጸጋ ዘአብ(የአብ ጸጋ) እና ከእናታቸው እግዚእ ሐረያ(በጌታ የተመረጠች) ታኅሣሥ ፳፬ ተወለዱ። የጻድቁ ቤተሰቦች እግዚአብሔርን የሚወዱ፣ በሽተኞችንና የተቸገሩትን የሚረዱ ደጋግ ሰዎች ነበሩ። ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል እንዲጸልይላቸው እየለመኑ እና በየወሩ በ፲፪ኛው ቀን የመልአኩን በዓል እያከበሩ ድሆችን ይመግቡ ነበር።

ቅዱስ ሚካኤል በሕልማቸው ተገልጾላቸው፤ እንደ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ዓይነት የተባረከ

ልጅ እንደሚወልዱ አበሠራቸው፡፡ እንደ ሕልማቸውም ልጅ ወለዱ፤ ስሙንም ፍስሐ ጽዮን አሉት፡፡ ይህም የጽዮን ደስታ ማለት ነው፡፡ ሕፃኑ መንፈስ ቅዱስ ሞልቶበት በተወለደ በሦስተኛው ቀን አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ብሎ አመሰገነ፡፡

የፍስሐ ጽዮን ቤተሰቦች የቅዱስ ሚካኤልን ዝክር ያደርጉ ነበር፡፡ አንድ ወቅትም የሚዘክሩበት እህል አጡ፡፡ በዚህ ጊዜ ፍሥሐ ጽዮን በአምላኩ በእግዚአብሔር ስም ጥቂቱን ዱቄትና ዘይት አበዛላቸው፡፡ ቤተሰቦቹም ዝክሩን አደረጉ፡፡ ልጆች ዝክር በቅዱሳንና በመላእክት ወይም በእግዚአብሔር ስም በቤተክርስቲያን እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ ካህናትን፣ ምእመናንን፣ የተቸገሩ ሰዎችን በመጋበዝ፣ መልካም ነገርን በማድረግ ሁሉ የሚደረግ መታሰቢያ ነው፡፡

ፍስሐ ጽዮን እግዚአብሔርን በመውደድና በማገልገል አደገ፡፡ በ፲፭ ዓመቱ ከአቡነ ቄርሎስ ፪ኛ እጅ ዲቁና ተቀብሎ፤ ወደቤቱ ሲመለስ ቤተሰቦቹ በትዳር እንዲወሰን አንዲት ሴት አጩለት፡፡ ፍስሐ ጽዮን ግን አልተቀበለውም፡፡ አንድ ቀን ከጓደኞቹ ጋር ለአደን እንደወጣ መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ተገልጦ ከዚህ በኋላ ያለውን ቀሪ ዘመኑን የሰዎችን ነፍስ በማዳን እንዲያሳልፍ መመረጡን አበሠረው፤ ስሙንም ተክለ ሃይማኖት የሃይማኖት ዛፍ (ተክል) አለው፡፡

ተክለ ሃይማኖት ወደቤቱ ሲመለስ ገንዘቡን ለቤተ ክርስቲያን እና ለድሆች ሰጥቶ ወደ ገዳም ሄደ፡፡ በኋላም ቅስና ተቀበለ፡፡ በቅስና ማዕረግ ሆኖ ወንጌልን በማስተማሩ ብዙ ሰዎች ወደ ክርስትና ተመለሱ፡፡ ከዚያም በደብረ ዳሞ ገዳም ለዓመታት በአገልግሎት ቆዩ፡፡ የደብረ ዳሞ ገዳም ተራራማ በሆነ ከፍተኛ ቦታ የገደል ጫፍ ላይ የሚገኝ ገዳም ነው፡፡ ወደ ገዳሙ የሚገባው በገደሉ ላይ በጠንካራ ገመድ እየተሳቡ ነው፡፡ ጻድቁ አቡነ ተክለሃይማኖት በገዳሙ በጸሎትና በአገልግሎት ቆይተው ወደታች በገመድ ሲወርዱ፣ ጠላት ገመዱን በጠሰባቸው በእምነታቸው ጽናት፣ በአገልግሎታቸው እና፣ በጸሎትቸውም ክንፍ ተሰጣቸው፡፡

ጻድቁ ተክለ ሃይማኖት ከተታ ወደ ተባለ ቦታ ሄዱ፡፡ በዚያም ያሉት ሰዎች ዛፍ ያመልኩ ነበር፡፡ በዛፉም ላይ ርኩስ መንፈስ አዩና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እርኩሱን መንፈስ አሠሩት፡፡ በአካባቢው የነበሩት በባዕድ አምልኮ ተይዘው የነበሩትንም ሰዎች በእግዚአብሔር ቃልና በተአምራት አስተምረው አጠመቁአቸው፡፡

www.zoorthodox.org

ጻድቁ አባታችን ሃያ ዘጠኝ ዓመታትን ያሳለፉት ደብረ አስቦ በተባለ ቦታ ቆመው በመጸለይ ነበር፡፡ በጸሎት ተግተው ብዙ በመቆም እግራቸው ተቆርጧል፡፡ ይህም ቢሆን ትጋታቸውን አላቋረጠውም፡፡ በአንድ እግራቸው ቆመው ለሰባት ዓመታት ጸልየዋል፡፡ በዚህ ተጋድሎአቸው የተማረኩ የመንፈስ ልጆቻቸቸው በዙ፣ በዚያም ገዳማዊ የአንድነት ኑሮ ተመሠረተ፡፡

በዚህ ሁኔታ አገልግለው ጻድቁ አባታችን ዘጠና ዘጠኝ (፺፱) ዓመት ሲሞላቸው ታመሙ፡፡ መነኮሳቱን ሰብስበው የጸሎትና የፍቅር አገልግሎታቸውን እንዲቀጥሉ መክረው፡፡ ነሐሴ ፳፬ ቀን

በክብር ዐረፉ። ጸሎታቸውና የአምላካቸው በረከት ከሁላችንም ጋር ይሁን አሜን።

**ማጠቃለያ፡-** የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተሰቦች እግዚአብሔርን በትዕግሥት በመጠበቃቸው የተባረከ ልጅ አገኙ። ቅዱስ ሚካኤልን ይዘክሩ፣ ችግረኞችንም ይረዱ ነበር። የቅዱሳን መታሰቢያ ቀናት የተቸገሩትን የምንረዳበት መልካም ነገርን የምናደርግበት ነው። ይህም በማድረግ በረከትን እንቀበልበታለን። *"የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነውና።"* ምሳ. ፲÷፯

ቅዱስ ሚካኤል የጻድቁ ተክለሃይማኖት ጠባቂ መልአክ ነበር። አባታችንም ከቤተሰቦቻቸው በተማሩት መሠረት ያከብሩት ነበር። እኛም ከቤተሰቦቻችን የተቀበልነውን መልካም ነገር መልቀቅ የለብንም። በመጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ ተብሏል። ***"ልጄ ሆይ የአባትህን ምክር ስማ÷የእናትህንም ሕግ አትተው፤ለራስህ የሞገስ ዘውድ ለአንገትህም ድሪ ይሆንልሃልና።"*** ምሳ ፩÷፰-፱ ቅዱስ ጳውሎስም ***"እንደ አባቶቼ አድርጌ በንጹሕ ሕሊና የማመልከውን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።"*** ፪ኛ ጢሞ. ፩÷፫ ብሏል።

አቡነ ተክለ ሃይማኖት በሐዋርያዊ ተልዕኮ፣ በምንኩስና፣ በጸሎት በመትጋት እግዚአብሔርን በማገልገል፣ ወንጌልን እየሰበኩ ክርስትናን በማስፋፋት ተጠምደው ኖሩ። በመጨረሻም የእግዚአብሔርን ጥሪ በሚገባ ፈጽመው የጽድቅ አክሊል ተቀብለዋል።

## ተግባር

❖ ልጆች ቤተሰቦቻችሁ የሚዘክሩትን ታቦት ጠይቁ፤ ለምን እንደመረጡም ጠይቁ።

### *ጥያቄዎች*

1. የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ወላጆች እነማን ናቸው?

___________________________________________

2. ተክለ ሃይማኖት ማለት ምን ማለት ነው ?

www.zeorthodox.org

___________________________________________

3. ፍስሐ ጽዮን ለመጀመሪያ ጊዜ እግዚኣብሔርን ሲያመሰግን ዕድሜው ስንት ነበር? ምን አለ ?

___________________________________________

4. የጻድቁ ቤተሰቦች ያከብሩ የነበረው በዓል ምንድንነው ?

___________________________________________

5. ተክለ ሃይማኖት ከተራራ ሲወርዱ ካጋጠማቸው አደጋ እንዴት ተረፉ ?

___________________________________________

# ኢትዮጵያዊው አቢሜሌክ

## አርባ ስምንተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች፤ እግዚአብሔር ከጥፋት መካከል እንደሚያድን ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *‹‹በዚያ ቀን አድንሃለሁ ፤ ይላል እግዚአብሔር ፤ በምትፈራቸው ሰዎች እጅ አልሰጥህም።››* ኤር.፴፱፥፲፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ኤር.፴፰፥፩-፲፫፣ ፴፱፥፲፯-፲፰፣ ተረፈ ባሮክ.፪፥፰፤፬፥፴፪

**መግቢያ፡-** የዛሬው ትምህርታችን እግዚአብሔር በአገሩ ሁሉ ከመጣ ጥፋት ስላዳነው የእግዚአብሔር ሰው ነው። ኢየሩሳሌም ናቡከደነጾር በተባለ ንጉሥ ተማርካ ተቃጠለች። ሕዝቡ ሲማረኩና ከተማይቱ ስትጠፋ እግዚአብሔር አቤሜሌክን አዳነው።

## የሳምንቱ ትምህርት

ልጆች ከብዙ ዓመታት በፊት በእስራኤል ሀገር ኢየሩሳለም በምትባል ከተማ የሚኖሩ ሕዝቦች ኃጢአት ሠርተው እግዚአብሔርን አሳዘኑ። እግዚአብሔርም በኃጢአታቸው እንዳይጠፉ ኤርምያስን ልኮ ንስሐ እንዲገቡ አስመከራቸው። እነርሱ ግን አልሰሙም።

እግዚአብሔርም ኤርምያስን ዳግመኛ ላከው፤ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር መጥቶ በጦር ይማርካችሁዋልና፤ ከተማይቱ ከዚህ በላይ እንዳትጠፋ ንስሓ ግቡ። ከኃጢአታችሁ ከበደላችሁ ብትመለሱ ግን እግዚአብሔር ያድናችኋል፤ አላቸው።

ነገር ግን ይህንን ሲናገር የሰሙ ሰዎች ሊያዳክመን ነው፤ ብለው ኤርምያስን ጭቃ ካለበት ጉድጓድ ውስጥ ጣሉት። በዚያ ምግብ የለም ውኃም የለም። ኤርምያስም በጣም አዝኖ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ።

www.zeorthodox.org

በዘመኑ በኢየሩሳሌም ቤተ መንግሥት ንጉሥ የነበረው ሴዴቅያስ ይባላል። የንጉሡ የቅርብ ወዳጅና አገልጋይ የሆነ አቤሜሌክ የተባለ ሰውም ነበር። አቤሜሌክ ኢትዮጵያዊ ነው። ነቢዩ ኤርምያስንም የሚወድና የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰማ ነበር። እርሱም ኤርምያስ በግዞት (እስር) ቤት ጉድጓድ መጣሉን ሰማ። ወዲያውም ለንጉሡ ነቢዩ ኤርምያስ በጉድጎድ መጣሉን ነገረው። ምግብ ስለሌለው እንዳይሞት ላውጣው ብሎም ጠየቀ። ንጉሡም ሠላሳ ሰዎች ይዘህ ሂድ አለው።

ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክም ሠላሳ ሰዎችን፣ ከንጉሡ መዝገብ ቤት አሮጌ ልብሶች ፣ ገመድም ይዞ እየሮጠ ወደ ኤርምያስ ሄደ። እንደደረሰም የተጠለፈ የገመድ ጫፍና ጨርቆቹን ወደ ጉድጓዱ ወረወራቸው። የገመዱንም ሌላ ጫፍ ሠላሳዎቹ ሰዎች እንዲይዙት አደረገ። ኤርምያስንም ጨርቆቹን በብብትህ ከገመዱ በታች አድርጋቸው አለው። ኤርምያስ ከጉድጓዱ ከወጣ በኋላ እንዲሁ አደረገ። ጎትተውም አወጡት። ኤርምያስም በአደባባዩ ተቀመጠ።

ነቢዩ ኤርምያስ በአደባባይ እያለ እግዚአብሔር ወደ እርሱ መጣ። ኤርምያስንም ወደ ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ ሄዶ በኢየሩሳሌም ከሚደርሰው ጥፋት እንደሚያድነው ንገር አለው። ኤርምያስም ሄዶ፡- *‹‹ የሠራዊት ጌታ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ... በዚያ ቀን አድንሃለሁ ይላል እግዚአብሔር፤ በምትፈራቸው ሰዎች እጅ አልሰጥህም። ፈጽሜ አድንሃለሁ ነፍስህም እንደ ምርኮ ትሆንልሃለች እንጂ በሰይፍ አትወድቅም፣ በእኔ ታምነሃልና ፣ይላል እግዚአብሔር።››* አለው። አቤሜሌክም አምላኩን አመሰገነ። ኤር.፴፱፥፲፮-፲፰

ኤርምያስ እንደተናገረው የባቢሎን ንጉሥ ኢየሩሳሌምን ለማጥፋ መጣ።  ኤርምያስም ከባሮክ ጋር በሌሊት ወደ ቤተ መቅደሱ ገብቶ መጸለይ ጀመረ። እግዚአብሔርም ከተማዋ ጠዋት እንደምትጠፋ ነገራቸው። እነርሱም በጣም አለቀሱ። ከዚያም ኤርምያስ ‹‹አቤሜሌክ እንዴት ይሆናል?›› አለ።

እግዚአብሔርም አቤሜሌክን በተራራው በኩል ወዳለው የወይን ቦታ ላከው። ባሮክ በኢየሩሳሌም ይቆይ አንተም (ኤርምያስ) ከሕዝቡ ጋር ተማርከህ አስተምራቸው አለው። ነቢዩ ኤርምያስም አቤሜሌክን ‹‹በተራራው በኩል ወደ አግሪጳ የወይን ቦታ ሂድ ለሕሙማንም በለስ ይዘህ ና›› አለው።

አቤሜሌክም የተባለውን ለመፈጸም ሮጠ። በቦታው ደርሶ በለሶችን ሰበሰበ፤ ረጅም መንገድ ስለተጓዘም ጥቂት ልረፍ ብሎ ጋደም እንዳለ እንቅልፍ ወሰደው። በዚያው እያለ ኢየሩሳሌምና ሕዝቦቿ በባቢሎን ተማረኩ። እግዚአብሔርም አቤሜሌክን የኢየሩሳሌምን ምርኮና ጥፋት እንዳያይ ለስድሳ ስድስት (፷፮) ዓመታት አስተኛው። ሲነቃ ራሱን ከብዶታል። ነቢዩ ኤርምያስ የላከኝን ሳላደርስ አረፈድኩ፤ እንዳይቆጣኝ በማለት እየሮጠ ሄደ። ኢየሩሳሌም ሲደርስ ተቀይራበታለች፤ አቤሜሌክ ደነገጠ። በሕልሙ መሰለው። ከዚያም ሊረጋጋ ወደ ተራራ ተመልሶ ወጥቶ ተቀመጠ።

በመንገድም ነቢዩ አንድ ሽማግሌ አገኘ። ‹‹የኢየሩሳሌም መንገድ ወዴት ነው? ነቢዩ ኤርምያስን የት አገኘዋለሁ?›› አለው። ሽማግላም ኤርምያስ ከተማረከ ፷፮ ዓመት እንደሆነው። ኢየሩሳሌምም መጥፋትዋን ነገረው። አቤሜሌክ ሽማግሌው ያሾፈበት መስሎት ተቆጣ። ‹‹በለሱን ለሽማግሌው አሳይቶ ኤርምያስ ልኮኝ የቆረጥኩት በለስ አልደረቀም። አንተ እንዴት ፷፮ ዓመት ሆነ ትለኛህ?›› አለው። ሽማግሌውም እግዚአብሔር ከጥፋት እንዳዳነው ነግሮት ተለየው።

አቤሜሌክም እግዚአብሔር የነገረው ቃል መፈጸሙን አስተውሎ። ጸሎት አደረገና ባሮክ



www.zeorthodox.org

ያለበትን ስፍራ አውቆ ደረሰ፡፡ ሁለቱም ስድሳ ስድስት ዓመታት ቆይተው ተገናኙ፡፡ በሆነው ነገር ሁሉ አለቀሱ፡፡ ከዚያም ደብዳቤ ጽፈው ለነቢዩ ለኤርምያስ ላኩ፡፡ በለሱንም ላኩለት፡፡ ከአራት ዓመታት በኋላ ነቢዩ ኤርምያስን አገኙት፡፡

## ማጠቃለያ

ልጆች የእግዚአብሔር ቃል እውነት ነው፡፡ ይፈጸማል፡፡ በዘመኑ የነበሩት ሰዎች ባይሰሙትም ነቢዩ ኤርምያስ የተናገረው ትንቢት ተፈጽሞ አይሁድ በባቢሎን ንጉሥ ተማረኩ፡፡

የእግዚአብሔርን ቃል የሰሙት ባሮክና አቤሜሌክ ተረፉ፡፡ እኛም የእግዚአብሔርን ቃል ብንሰማ ከክፉ ነገር እንጠበቃለን፡፡

## ተግባር

- ልጆች የእግዚአብሔርን ቃል ሰምታችሁ ፈጽሙ፡፡
- እንደ አቤሜሌክ አሮጌ ልብሶችን ለተቸገሩ ስጡ፡፡

### *የክለሳ ጥያቄዎች*

1. አቤሜሌክ የምን ሀገር ሰው ነበር ? በኢየሩሳሌምስ ምን ያደርግ በር ?
2. ለነቢዩ ኤርምያስ የዋለለት በጎ ነገር ምን ነበር ?
3. እግዚአብሔር ለበጎነቱ ምን አደረገለት ?

www.zeorthodox.org

# መታዘዝ

## አርባ ዘጠነኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች፤ የመታዘዝን መንፈሳዊነት ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *« ልጆች ሆይ፥ ይህ ለጌታ ደስ የሚያሰኝ ነውና በሁሉ ለወላጆቻችሁ ታዘዙ፡፡»* ቆላስ. 3፡20

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ዘፍ.፴፯፥፲፪-፲፯፣ ፩ኛ.ሳሙ.፲፯፥፲፪-፴፣ ዘጸ.፳፥፩-፲፯

**መግቢያ፡-** ልጆች በክፍል ውስጥ ከመምህሩ እና በቤት ውስጥ ከቤተሰብ ጋር በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡

1. መታዘዝ ማለት ምን ማለት ነው ?
2. ልጆች፤ ቤተሰቦቻችሁ አድርጉ የሚሉዋችሁን ታደርጋላችሁ ?
3. ለእግዚአብሔርስ ትታዘዛላችሁ ? ለእግዚአብሔር መታዘዝስ እንዴት ነው ?
4. በቤት ውስጥ በዕድሜ የሚበልጣችሁ ሲልካችሁ ፈጥናችሁ ትሄዳላችሁ ?
5. በዕድሜ ትልቅ የሆናችሁት ታናናሾቻችሁን የምትልኩዋቸው እንዳይሰለቹ በመጠንቀቅ ነው ?

ጎበዝ ልጆች ታዛዦች ናቸው፡፡ ቤተሰቦቻቸው የሚያዙዋቸውን ይፈጽማሉ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስና በታሪክ የምናገኛቸው ጎበዝ ልጆች እና ታላላቅ ሰዎች ታዛዦች ነበሩ፡፡ በዛሬው ትምህርታችን የዮሴፍ እና የዳዊትን የመታዘዝ ታሪክ እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ቤተሰቦቹ ሲጠሩት አቤት ሲልኩት ወዴት ብሎ ለቤተሰቡ የሚላክ፣ የሚመክሩት የሚሰማ ታዛዥ ልጅ ይባላል፡፡ መታዘዝ ማለት የተላኩበትን ጉዳይ እሺ ብሎ መፈጸም ነው፡፡ ልጆች እናንተም ለቤተሰብ እና ለእግዚአብሔር የምትታዘዙ ሁኑ፡፡

www.zeorthodox.org

### ፩. ለቤተሰብ መታዘዝ

በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፈው የምናገኛቸው ታላላቅ ቅዱሳን ታዛዦች ነበሩ፡፡ ለምሳሌ ያህልም የሚከተሉን ሁለት ታሪኮች አስተውሉ፡፡

#### ፩.፩. የዮሴፍ መታዘዝ

ልጆች ከዚህ በፊት ስለ ዮሴፍ የተማራችሁትን ታስታውሳላችሁ ? ዮሴፍ ታዛዥ እና ቅን ልጅ

ነበር። በድሮ ዘመን እረኞች ውኃ ከአለበት ሥፍራ እየፈለጉ በጣም ርቀው ይጓዙ ነበር። የዮሴፍ ታላላቅ ወንድሞችም *የአባታቸውን በጎች ይጠብቁ ዘንድ ሴኬም ወደ ተባለ ቦታ ሄዱ።* አባታቸው እስራኤልም ታዘዥ ልጁን ዮሴፍን *‹‹ወንድሞችህ በሴኬም በጎችን ይጠብቃሉና...... ወደ እነርሱ እልክህ ዘንድ ና አለው።* እርሱም፦ *እነሆኝ* አለው።›› አባቱም *ሄደህ ወንድሞችህና በጎቹ ደኅና እንደ ሆኑ እይ፥ ወሬአቸውንም አምጣልኝ አለው። እርሱም ኬብሮን ከተባለ ቆላማ ሀገር ፥* ወደ ተላከበት ወደ ሴኬም ሄደ። በዚያም ወንድሞቹን አጣቸው፤ በምድረ በዳም እየተቅበዘበዘ ፈለጋቸው። በመንገድ ላይም አንድ ሰው አገኘውና፣ ምን ትፈልጋለህ ብሎ ጠየቀው *እርሱም ወንድሞቼን እፈልጋለሁ በጎቹን የሚጠብቁበት ወዴት እንደ ሆነ እባክህ ንገረኝ አለ።* ሰውዬው፦ *ከዚህ ተነሥተዋል ወደ ዶታይን እንሂድ ሲሉም ሰምቼአቸዋለሁ* አለው። ዮሴፍም ወንድሞቹን ተከታትሎ ሄደ፥ በዶታይንም አገኛቸው።

ልጆች ለታዘዛችሁት ጉዳይ ምን ያህል ትተጋላችሁ? ዮሴፍ መጀመሪያ ወንድሞቹን ስላላገኛቸው ተስፋ ቆርጦ አልተመለሰም። አባቱ ያዘዘውን ለመፈጸም ብዙ ጥረት እድርጎአል። በመጨረሻም የታዘዘውን በሚገባ ለመፈጸም ቻለ።

### ፩.፪. የዳዊት ታዛዥነት

ዳዊት በቤተሰቡ ውስጥ የመጨረሻውና ትንሽ ልጅ ነበር። ታላላቆቹ የሀገራቸውን ድንበር ሊጠብቁ ከንጉሡ ከሳዖል ጋር በሜዳ ነበሩ። አባቱ እሴይ በሰልፍ ሜዳ ለነበሩት ሦስት ልጆቹ (ኤልያብ፣ አሚናዳብ እና ሳማ) ምግብ እንዲያደርስ ዳዊትን ላከው። እንዲህም አለው። *‹‹እሴይም ልጁን ዳዊትን እንዲህ አለው፦ ከዚህ ከተጠበሰው እሸት አንድ የኢፍ መስፈሪያ እነዚህንም አሥር እንጀራዎች ለወንድሞችህ ውሰድ፥ ወደ ሰፈሩም ወደ ወንድሞችህ ፈጥነህ አድርሳቸው፤ ይህንም አሥሩን አይብ ወደ ሻለቃው ውሰደው የወንድሞችህንም ደኅንነት ጠይቅ፥ ወሬአቸውንም አምጣልኝ።››* ዳዊትም፦*ማልዶ ተነሣ፥ በጎቹንም ለጠባቂ ተወ፥ እሴይም ያዘዘውን ይዞ ሄደ፤ ጭፍራውም ተሰልፎ ሲወጣ ለሰልፍም ሲጮኽ በሰረገሎች ወደ ተከበበው ሰፈር መጣ።* አባቱ ያዘዘውንም ፈጸመ። ልጆች የዳዊትን መታዘዝ፣ ፍጥነቱንም አስተዋላችሁ። እናንተም ወላጆቻችሁ ሲልኳችሁ እንዲሁ አድርጉ። ቅዱስ ጳውሎስም *ልጆች ሆይ፥ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ፥ ይህ የሚገባ ነውና።* ሲል ይመክረናል። ኤፌ.፮፥፩

www.zeorthodox.org

ዳዊት ወደ ተላከበት ቦታ ሲደርስ ጎልያድ የእግዚአብሔርን ሕዝብ እየተሳደበ ነበር። በዚህ ያዘነው ዳዊት የተላከውን አድርሶ ስለጎልያድ ሲጠይቅ፤ ተልኮ መምጣቱን ያላጣራው *ታላቅ ወንድሙ ኤልያብ ደግሞ ታናሽ ወንድሙ ከሰዎች ጋር ሲነጋገር ሰምቶ በዳዊት ላይ ተቆጣ። ለምን ወደዚህ ወረድህ ? እነዚያንስ ጥቂቶች በጎች በምድረ በዳ ለማን ተውሃቸው ? እኔ ኵራትህንና የልብህን ክፋት አውቃለሁና ሰልፉን ለማየት መጥተሃል አለው።*

*ዳዊትም እኔ ምን አደረግሁ አለ ?...ከታላቅ ወንድሙም ዘወር አለ፡፡*

በዕድሜ ታላላቅ ወንድሞቻችን አንዳንዴ ሳይረዱን ሊቆጡ ይችላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ እንደዳዊት በእርጋታ መመለስና ቁጣቸው እስኪበርድም ዘወር ማለት መልካም ጥበብ ነው፡፡ ታላላቆችም ከማይገባ ቁጣ መጠበቅ አለባችሁ፡፡

**፪. ለእግዚአብሔር መታዘዝ**

ልጆች እግዚአብሔር የፈጠረንና የሚያኖረን የሰማይ አባታችን ነው፡፡ እርሱ የሚለንን መታዘዝ አለብን፡፡ የሚያዘንም ለእኛ ጥቅም ነው፡፡ ለዚህም ነው ነብዩ፤ ‹‹***የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ደስ እንደሚለው እግዚአብሔር በሚቃጠልና በሚታረድ መሥዋዕት ደስ አይለውም፤ እነሆ፥ መታዘዝ ከመሥዋዕት ፥ ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል፡፡***›› ያለው ፩ኛ ሳሙ.፲፭፥፳፪

ልጆች እግዚአብሔርን የምንታዘዘው እንደ ወላጆቻችን ይህን አድርስ፣ ያንን አምጣ እያለን አይደለም፡፡ ቃሉን ስናዳምጥ፣ ሕግጋቱን ስናከብር፣ የተባልነውን ስንፈጽም ለእግዚአብሔር መታዘዛችን ነው፡፡ ለምሳሌ እግዚአብሔር አትስረቅ፣ በሐሰት አትማል፣ አባትህንና እናትህን አክብር ፣ የባልጀራህን ሃብት፣ ንብረት፣ ወዘተ.... አትመኝ ብሎናል፡፡ እርሱ ያለንን ስንፈጽም ለእርሱ እየታዘዝን ነው፡፡ ይህም ለጌታ ደስ የሚያሰኝ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

- በመጽሐፍ ቅዱስ የነበሩ አባቶች በሙሉ ለሚያዩዋቸው ቤተሰቦቻቸውና በዓይን ለማያዩት ለእግዚአብሔርም ይታዘዙ ነበር፡፡ እኛም በቅን ልቦና ስንታዘዝ እግዚአብሔር ይባርከናል፡፡

## ተግባር

- ልጆች ወላጆቻችሁ የሚያዙአችሁን ፈጽሙ፡፡

www.zeorthodox.org

***የክለሳ ጥያቄዎች***

1. ዮሴፍ አባቱ በላው ሥፍራ ወንድሞችን ሲያጣቸው ተመለሰ፡፡

ሀ. እውነት ለ. ሐሰት

2. ከንጉሡ ሳዖል ጋር ወደ ሰልፍ የሄዱት የዳዊት ወንድሞች ስም ማን ነበር፡፡

______________________________

3. ለእግዚአብሔር መታዘዝ ከመሥዋዕት እንደሚበልጥ ያስተማረው ማነው ?

ሀ. ጳውሎስ ለ. ሳሙኤል ሐ. ዮሴፍ

# ኤልሳዕ ክፉውንና መራሩን ውኃ አጣፈጠ

## ሃምሳኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር በኤልሳዕ ስለፈወሰው ውኃ ልጆች ተገንዝበው ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *‹‹እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ይህን ውኃ ፈውሼዋለሁ ከዚህም በኋላ ሞትናጭንገፉአይሆንበትም..›› ፪ኛ ነገሥ.፪፥፳፩*

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ፪ኛ ነገሥ.፪፥፩-፳፪

**መግቢያ፡-** ልጆች ባለፈው ሳምንት ስለመጻጉእ /ሕመምተኛው/ መፈወስ ተምረናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም ሌላ የፈውስ ታሪክ እንማራለን፡፡ አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር ሁሉንም ማድረግ የሚችል ድንቅ አምላክ ነው፡፡ ድንቃ ድንቅ ተአምራትንም በተለያየ መንገዶች ይሠራል፡፡ ከእነዚህም በቅዱሳኑ አድሮ የሚሠራው አንዱ እና ዋነኛው ነው፡፡ ለዚህም ነው ንጉሥ ዳዊት ***‹‹እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ላይ ድንቅ ነው የእስራኤል አምላክ እርሱ ኃይልን ብርታትንም ለሕዝቡ ይሰጣል እግዚአብሔርም ይመስገን፡፡››*** ያለው፡፡ መዝ.፷፯(፷፱)፥፴፭ እኛም ከንጉሡ ጋር እግዚአብሔርን እያመሰገንን ከቅዱሳኑ መካከል በአንዱ በኤልሳዕ የሠራውን ድንቅ ሥራ በዛሬው ክፍለ ትምህርታችን እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ነብዩ ኤልያስ እግዚአብሔርን የሚፈራ ቅዱስ ነበር፡፡ ለእግዚአብሔር እና ለሰዎች እውነተኛ ፍቅር ስለነበረውም ሰዎች እግዚአብሔርን ትተው አምላክ ጣዖቶች ያልሆኑትን ሲያመልኩ ከልቡ እያዘነ ይጸልይ፣ ያስተምርና በእግዚአብሔር ኃይል ብዙ ድንቆችን ይፈጽም ነበር፡፡

ከዕለታት በአንድ ቀን እግዚአብሔር ነቢዩ ኤልያስን፤ በእርሻ መሬቱ ላይ በሬ ጠምዶ እያረሰ ወደ ነበረው ወደ ኤልሳዕ ላከው፡፡ ኤልያስም ከኤልሳዕ ዘንድ ሄዶ መጎናጸፊያውን ጣለ፡፡ ይህም እግዚአብሔር መርጦሃልና ተከተለኝ ለማለት መሆኑን ኤልሳዕ በመንፈስ ተረድቶ፤ ኤልያስን ትንሽ ጊዜ እንዲሰጠው ለመነ፡፡ ከዚያም በሬዎቹን አርዶ ለድሆች አበላና ተከተለው፡፡ ከኤልያስ ጋር እየተማረ ኖረ፡፡

www.zeorthodox.org

እግዚአብሔር ኤልያስን የሚወስድበት ጊዜ ሲደርስም ኤልሳዕ ተከትሎት ሄደ፡፡ ኤልያስ ተመለስ ቢለውም አልለይህም ብሎ አብሮት ተጓዘ፡፡ በመጨረሻም ኤልያስ በእግዚአብሔር ሰረገላ ወደ ሰማይ ሲወሰድ መጎናጸፊያውን ጣለለት፡፡ ኤልሳዕም አባቴ አባቴ እያለ ተከተለው፤ መንፈሱም በዕጥፍ አደረበት፡፡ በዚህ መሠረትም ኤልሳዕ ብዙ ድንቅ ተአምራትን ፈጸመ፡፡

ከእነዚህም የመጀመሪያው በመንፈስ አባቱ በኤልያስ መጎናጸፊያ የዮርዳኖስን ወንዝ ከፍሎ መሻገሩ ነው፡፡ ይህን ያዩ ሰዎችም ***የኤልያስ መንፈስ በኤልሳዕ ላይ ዐርፎአል አሉ፡፡*** ወደ እርሱ መጥተው የአክብሮት ስግደት ሰገዱለት፡፡

ከዚያም ወደ ኢያሪኮ ከተማ ገባ፡፡ የኢያሪኮ ውኃ ክፉ ነበር፡፡ ማለትም ለመጠጥ አይሆንም፤ በምድር ሲደፉት አፈሩን ይጎዳዋል፡፡ በምድሪቱ የተተከሉትን ዕፅዋት ፍሬ ሳያፈሩ ያስጨነግፋቸዋል፡፡ በዚህ ምክንያትም የኢያሪኮ ሰዎች ተቸግረው ነበር፡፡

የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረበት ኤልሳዕ ወደ ከተማቸው መምጣቱን የሰሙት የኢያሪኮ ሰዎች ወደ ነቢዩ መጡና ***‹‹ እነሆ፥ ጌታችን እንደምታይ የዚች ከተማ ኑሮ መልካም ነው፤ ውኃው ግን ክፉ ነው፥ ምድሪቱም ፍሬዋን ትጨነግፋለች አሉት፡፡››*** እርሱም ማድረግ ያለበትን ከእግዚአብሔር በተሰጠው የትንቢት መንፈስ አውቆ ***‹‹አዲስ ማሰሮ አምጡልኝ፥ ጨውም ጨምሩበት››*** አለ፡፡ እነርሱም ***አመጡለት፡፡***

***ኤልሳዕም*** እግዚአብሔር ያዘዘውን ለመፈጸም ወደ ምንጭ ሄደ፤ ***ጨው ጣለበትና፤ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ይህን ውኃ ፈውሼዋለሁ ከዚህም በኋላ ሞትና ጭንገፋ አይሆንበትም*** አለ፡፡ **ኤልሳዕም እንደ ተናገረው ነገር ውኃው እስከ ዛሬ ድረስ ተፈውሶአል፡፡** እግዚአብሔር የፈወሰው ሁሉ ይፈወሳል፡፡

የኢያሪኮም ሰዎች በተፈወሰላቸው ውኃ ጠጥተው መርካት፣ ዘርተው ማጨድ፣ ተክለው ፍሬ መሰብሰብ ቻሉ፡፡ ይህንን ሁሉ ያደረገው በቅዱሳኑ አድሮ ድንቅን የሚሠራው የሠራዊት ጌታ ልዑል እግዚአብሔር ነው፡፡

## ማጠቃለያ

ኤልሳዕ ከመንፈስ አባቱ ከኤልያስ መንፈሳዊ ትምህርት የተማረና ታላቅ ደረጃ ላይ የደረሰ ነቢይ ነው፡፡ እኛም ከመንፈሳዊ፣ ከሥጋና ከቀለም አባቶቻችንን የምንማረውን በሚገባ ከሰማንና ከተገበርን ነገ ትልቅ እንሆናለን፡፡

የኢያሪኮ ሰዎች የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ ወደ ከተማቸው ሲመጣ በክብር ተቀብለው ለችግራቸው መፍትሔ አገኙ፤ እናንተም የሚባራኩዋቸሁን ካህናትና አባቶች አክብራችሁ በመቀበል በአግባቡ መጠቀም ያለባችሁን ጊዜ አታሳልፉ፡፡

www.zeorthodox.org

ክፋው እና መራራው የኢያሪኮ ውኃ የጣፈጠው በእግዚአብሔር ኃይል ነው፡፡ ምንም ዓይነት የሚያማርር ነገር ቢያጋጥማችሁ እግዚአብሔር ሁሉንም መቀየር እንደሚችል አምናችሁ ጸልዩ፡፡

## ተግባር

❖ እግዚአብሔር ሁሉንም ማድረግ ይችላል፡፡ እናንተም በእርሱ ታምናችሁ ተሰማሩ፡፡

# ዋቢ መጻሕፍት


- ሃብተማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት)፣ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ ማተሚያ ቤት፣ 1963 ዓ.ም
- ሃይማኖተ አበው፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1986 ዓ.ም
- አባ መልከ ጼደቅ (ሊቀ ጳጳስ)፣ ትምህርተ ክርስትና፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፣ 1984 ዓ.ም።
- አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1974 ዓ.ም።
- ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓት አምልኮና የውጭ ግኙኑነት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም.
- ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንትና ዛሬ፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1990 ዓ.ም.
- ሉሌ መልአኩ (መምህር)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1997 ዓ.ም።
- መሐሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት)፣ መጽሐፈ ሐዲሳት ሠለስቱ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1989 ዓ.ም።
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም።
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም
- ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1988 ዓ.ም
- ዳኛቸው ካሳሁን (መልአከ ሰላም)፣ ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር፣ አዲስ አበባ፣ ማኅበረ ቅዱሳን፣ 2003 ዓ.ም
- ደረጀ ጅማ (መጋቤ አእላፍ)፣ ምን ያስጨንቃችኋል ክፍል ፪፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 2002 ዓ.ም።


www.zoorthodox.org

- መጽሐፍ ቅዱስ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980 ዓ.ም
- ሐረገ ወይን ቸርነት፣ ሴትና አህያ፣ አዲስ አበባ፣ 2005 ዓ.ም፡፡
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ዶ/ር)፣ ጠቅላላ የቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2000 ዓ.ም
- ኀሩይ ኤርምያስ (መምህር)፣ መዝገበ ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም
- የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ 1996 ዓ.ም፡፡
- ቸርነት አበበ (መምህሩ)፣ የመጽሐፍ ቅድስ ጥናት፣ አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም
- H.G. Bishop Moussa@ The Characteristics of Orthodox Teaching@ Bishopric of Youth@ Harmony Press, 2007.
- H.G. Bishop Mouusa, An Introduction to the New Testament, Bishopric of youth, Dar EL Geel Press, 2001.
- H.G. Bishop Raphail, The Meaning of Miracles, Bishopirc of Youth, 2010.
- Sunday School Curriculum, Grade 1 to Grade 12. The Coptic Orthodox Diocese of The Southern USA.
- Sunday School Lessons, Class 1 to Class 10, E.O.T.C Latin America Diocese.


www.zeorthodox.org